የስርቻው መጣጥፍ



ትርጉም ፋሲል ይትባረክ

ምሥጋና

ይህን መጽሐፍ እንዳሳትም ያስቻሉኝ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚከተሉት ናቸው። እንባቢ እነዚህን ሰዎችና ተቋማት በበጎ እንዲያስብልኝ ምኞቱ ነው።

- የኢትዮ ኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሰርቪስ ባለቤት አቶ ፀጋዬ ገ/ወልድ
- የተክለሃይማኖት ከፍተኛ ክሊኒክ ባለቤት ዶክተር ሞላ ብርሃኑ
- የናትራን ኩባንያ የፐላስቲክ ውጤቶችና የእልፍኝ የቤት ክዳን ቆርቆሮ ማምረቻ ባለቤት አቶ ባሕሩ አብርሃም፣
- የሶጻት ቢዝነስ ግሩፕ ባለቤት አቶ ሽምሱ ሐሰን
- የዱራታና ሙን ሲቲ ባትሪድንጋዮች አስመጪና አከፋፋይ እንዲሁም በጠቅላላ የሽቱጣ ሽቀጥ ንግድ የተሰማራው የአምደሁ ጀነራል ትሬዲንግ ባለቤት
  አቶ ናስር ጀማል
- ሮቶ ፒ.ኤል.ሲ
- የብራዘርስ ዱቄትና ብስኩት እንዲሁም የወንድማማቾች ዱቄት ፋብሪካ ባለቤቶች ወንድማማቾቹ አቶ አህመድ በሽር ኢብራሒምና አቶ መሐመድ ሰይድ ኢብራሒም
- ሲቲ ልዩ የጥርስ ክሊኒክ
- እንዲሁም ይህንን መፅሐፍ ከማረም ጀምሮ ለሕትመት እንዲበቃ በማነሳሳት ከጎኔ ላልተለየው ለምወደውና ለማከብረው ለቁም ነገር መፅሔት ባለቤትና ዋና አዘጋጅ ለአቶ ታምራት ኃይሉ ልዩ ምሥጋና አቀርባለሁ። እነሱ ሃሳቤን ባይረዱልኝና ባያግዙኝ ኖሮ ይህ መጽሐፍ አይኖርም ነበር።

መግቢያ

ሰው በመሆንህ ወደፊትህ የምትጓዘው ዓላማና ግብ አስተምጠህ ነው። በዚህ መንገድ ላይ ስትራመድ ደግሞ በየደረጃው ወደዓላማህ ግብህ ለመድረስ በነፍስህ ውስጥ ሶስት ዓይነት ሚስጢሮች ትደብቃለህ። ሶስቱም ወይም አንዱ ብቻ ሊኖርህ ይችላል።

ራሺያዊው ደራሲ ፊዮዶር ዶስቶቪስኪ እንደሚያስተምጠው ከሆነ የመጀመሪያው ደረጃ ሚስጢር የልቤ ሰው ለምትለው ብቻ የምትነግረው ሲሆን የሁለተኛው ዓይነት ደግሞ ለማንም ትንፍሽ የማትለው በልብህ አንድ ጭለማ ክፍል ዘግተህ የምታስተምጠው ነው።

ሶስተኛው አይነት ግን በራስህ ውስጥም ልታኖረው የማትችለውና በቻልከው መንገድ ሁሉ እስክለተሞትህ ስትሸሸገው የምትኖረው ሚስጥር ነው። የዚህ አይነቱ ሚስጢር በስልጣን፣ በብልፅግና በሐይማኖትና በዝና መሰላል ወደላይ በወጣህ ቁጥር በነፍስህ ውስጥ በአያሌው የሚከማች ገበና ነው።

የዚህ አጭር ታሪክ ገፀ-ባህሪ «ሰውየው» ከእነዚህ ሚስጢሮቹ መካከል የመረጣቸውን ደፍሮ ለመናገር ይችል አይችል እንደሆን ለማረጋገጥ ነው ብእር ከወረቀት ያገናኘው። ምን ያህል ለራሱ ሐቀኛ እንደሆነ ለራሱም አላመነበትም። ለማንኛውም አንብባችሁ ዳኝነቱን ስጡት።

«ሲኦል ማለት» ይላል ዶስቶቪስኪ «ለማፍቀር ያለመቻል ጥልቅ ስቃይ ነው»

መልካም ንባብ!

-1-

ሀመምተኛ ነኝ። በጥላቻ የተሞላሁ ፈፅሞ ጥሩ ሰው አይደለሁም። ጉበቱ የሆነ ችግር እንዳለበት አምናለሁ። ይሁን እንጂ ስለ ችግሩ በውል የማውቀው አንዳችም ነገር የለም። ከናካቴው ጉበቱ ችግር ይኑርበት አይኑርበትም አርግጠኛ አይደለሁም። ምንም እንኳ ሕክምናና ሐኪሞች ባክብርም ልታከም ሄጄ ግን አላውቅም። በዚህ ላይ ከልክ ያለፈ የባዕድ አምልኮ ተከታይ ነኝ። (ነገሩ የተማርኩ ነኝ። ግን የባዕድ አምልኮ አስረኛ ከመሆን አልተላቀቅኩም።) እውነቱ ምንድን ነው፣ ዋንኛው ወደ ሐኪም ዘንድ የማልሄድበት ምክንያት በጥላቻ የተነሣ ነው። ምን ማለቱ እንደሆነ የሚገባችሁ አይመስለኝም። ለእኔ ግልፅ ነው። በዚህ ጥላቻዬ ማንን እየጉዳሁ ስለመሆኔ ላብራራላችሁ የምችል አይመስለኝም። ሆኖም በዚህ የሚጐዱት ዶክተሮች እንደማይሆኑ ግልፅ ነው። በዚህ ዋናው ተጐጂ እኔብቻ መሆኔን በሚገባ አገነዘባለሁ።

ወደ ሐኪም ቤት የማልሄድበት ምክንያት ከጥላቻ የተነሣ ነው። በርግጥ ጉበቴን ያመኛል። ደህና! ይመመኝ! እንደውም ብዙ ባመመኝ ቁጥር ይሻለኛል።

በዚህ ሁኔታ መኖር ከጀመርኩ ሃያ ዓመት የሞላኝ ይመስለኛል። አሁን አርባ ዓመቴ ነው። በፊት ጦር ሠራዊት ውስጥ አባል ነበርኩ። አሁን ተሰናብቻለሁ። በጥላቻ የተሞላሁ ሠራተኛ ነበርኩ። አስቸጋሪና በአስቸጋሪነቱም እደለት ነበር። ልብ አድርጉ! ጉቦ የሚባል ነገር አልቀበልም። በዚህ ማካካሻ ነው ባለጉዳዮችን የማንላላው። ! ቂላ ቂል ተልድ ቢሆንም አልሰርዘውም። መጀመሪያ ስዕፈው ጥሩ ያደረግኩ መስሎኝ ነበር። አሁን ግን ተራ የሆነ ጉራ እያንፀባረቅኩ መሆኔ ገብቶኛል። ይሁን እንጂ አልሰርዘውም!

ሰዎች በሥራ ምክንያት ወደኔ ሲመጡ ሆነ ብዬአነጫነጭባቸዋለሁ። በተለይ ላበሳጫቸው ከሆልኩ እደሰታለሁ።

ሁሌም ይሳካልኝ ነበር ማለት ይቻላል። ብዙዎቹ ዓይነአፋርና ሽቅጥቋጣ ቢጤዎች ነበሩ። ለነገሩ ወደ መንግሥት መሥሪያ ቤት ለጉዳይ

የሚመጣ ሰው ከዚህ ውጭ ምን እንዲሆን ይጠበቃል? አልፎ አልፎ ከሚመጡት ጥቂት የተከበሩ ሰዎች መካከል አንድ ትዕግስቴን ያስጨረሰኝ መኮንን ነበረ። ወደ ቢሮዬ ሲገባ ትህትና ካለማሳየቱም በላይ ጉራውን ይነካ ነበር። በዚህ የተነሳ አሥራ ስድስት ወራቶች ሙሉ ጦርነት ገጠምኩት። በመጨረሻም እኔ አሸንፍኩና ጉራ መንዛቱን አርግፍ አድርጉ ተወ። ይህ የሆነው ገና ወጣት ሳለሁ ከብዙ ዓመታት በፊት ነው። አያችሁ ውድ አንባቢዎች፣ የጥላቻዬ ዋና ምክንያት ምን እንደሆነ? ዋናው ቁም ነገር ምንድነው ማለቱ የዚህ አስጠሊታና ቀፋፊ ጉዳይ መነሻ ያለመጠን በጥልቀት መገንዘቤ ነው። አጅግ ስሜቱን የሚነካ ጉዳይ እንኳ ሲመጣ አይሰቀጭም።

የሚገርመው በጥላቻ የተሞላሁም አለመሆኔ ነው። እኔ ከመሬት ተነስተው የሚያስፈራሩና በዚህም እንደሚደሰቱ ሻርኮች ማለት ነኝ። አፈ ምራቅ አስኪደፍቅ ልቀጣ እችላለሁ። ግን የሆነ አሻንጉሊት አምጡልኝ ወይም ስኳር ያለው አንድ ብርጭቆ ሻይ ስጡኝ፣ ወዲያው ምንም እንዳልተፈጠረ ተረጋግቼ ብገኝ አይገርመኝም። እንዳውም በዚህ ድርጊት ስሜቴ ከፉኛ ከመነካቱ የተነሳ ራሴን በማማረር በሀፍረት ተጥለቅልቄ ለበርካታ ወራት አንቅልፍ በማጣት ልሠቃይ እችላለሁ። እንዲህ ዓይነት ሰው ነኝ።

ባጋጣሚ አሁን ከፉ ሠራተኛ ነበርኩ ብዬ ስል አጋንኛለሁ። አደርግ የነበረው በርግጥ በመኮንኑና በሌሎች ባለጉዳዮች ላይ ትንሽ መቀለድ ብቻ ነበር። እውነቱን ለመናገር ክፉ ሰው መሆን አይቻለኝም ነበር።

ክፉ ለመሆን የማልችልበት ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ስሜቶች ውስጤ መኖራቸውን አውቃለሁ። እነዚህ ያልኳችሁ ስሜቶች ከውስጥ ሲያጥለቀልቁኝና ልውጣ-ልውጣ ሲሉኝ ይሰማኛል። እኔ ግን እንዲወጡ አልፈቅድላቸውም። ሆነ ብዬ አፍናቸዋለሁ። እነሱም በተራቸው በራሴ እስክማርር ድረስ ያሰቃዩኛል። አልፈው ተርፈው የነርቭ መታወስ እስኪደርስብኝ ድረስ ሲጠዘጥሁኝ ሰልችቶኝ አተዋቸዋለሁ። በስመ አብ!

መጨረሻ ላይማ በጣም ነው የሚያንገሸግሹኝ.የተከበራችሁ ሰዎች፣ ስለአንድ ነገር ይቅርታ የምጠይቃችሁ አይመስልም? በአንድ ነገር ላይ ይቅር እንድትሉኝ የምጠይቅ? አዎ! ይመስላል። ለነገሩ መሰላችሁ አልመሰላችሁ ቅንጣት ታክል አልጨነቅምᢉ።

እኔ በጥላቻ የተሞላሁ ሰው አለመሆን ብቻ ሣይሆን ክፉ ወይ ደግ፣ አጭበርባሪ ወይም ሀቀኛ፣ ጀግና ወይም ነፍሳት ያልሆንኩ፣ በአጠቃላይ ምንም ሆኖ ለመገኘት የማይቻለኝ ነኝ።

አሁን እዚህ ጐሬዬ ውስጥ መኖር ከጀመርኩ አራት ዓመት ሆኖኛል። ምንም እንኳ ጥቅም የለሽ መሆኑን ባውቅም ራሴን ግን «የተማረ ሰው ከቶም ምንም መሆን አይችልም።» በማለት አፅናናለሁ። ያለበውን መሆን የሚችል ሞኝ ብቻ ነው። አዎ! የአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሰው ከሁሉም በላይ የራሱ የሆነ ባህሪ የለሽ መሆን ብቻ ሣይሆን እንዲህ እንዲሆንም ግድ ነው። እኔ እንግዲህ በአርባ ዓመቴ ይህ የፀና እምነት አለኝ። ልብ በሉ አሁን አርባ ዓመቴ ነው። አርባ ዓመት ደግሞ ሙሉ ዕድሜ ነው። አርባ የመጨረሻው የእርጅና ዕድሜ ነው። ከአርባ ዓመት በላይ መኖር ሰድነት፣ ዋልጌነትና ብልግና ነው። ከአርባ ዓመት በላይ የሚኖር ማን ነው? ይሄንን በሃቅና በቅንነት መልሱልኝ። እኔ ልንገራችሁ፣ አጭበርባሪዎችና ሞኞች ናቸው።

ይሄንን ለሸመገሉ፣ ለሸበቶ ሽማግሌዎች ፊታቸው ላይ ልነግራቸው አችላለሁ። ካስፈለገ ለመላው ዓለም ልናገር እችላለሁ። ይህንን ካላደረግኩ ሞቻለሁ። ይሄን የማለት መብት አለኝ። ምክንያቱም እኔም ራሴ ስልሣ ዓመት ድረስ እኖራለሁ። እንዳውም ሰባ! ሰማንያ! ቆይ እንዲት ደቂቃ ጠብቁኝ ትንፋሻችሁን ዋጡና.....

የተከበራችሁ ሰዎች፣ ራሴን ለማስደሰት እየሞከርኩ እንደሆነ አድርጋችሁ እንደምትቆጥሩኝ ይሰማኛል። ተሳስታችኋል። እናንተ እንደምታስቡት ዓይነት አይደለሁም። ሆኖም በዚህ ተራ የሥራፈት ወሬዬ ብበሳጭታችሁ ከሆን (የተበሳጫችሁ ይመስለኛል) ማን እንደሆንኩ ልታውቁ ትፈልጋላችሁ። እኔም እመልሣለሁ። አነስተኛ ማዕረግ ያለኝ የሲቪል

ሠራተኛ ነኝ፣ ሥራ የገባሁት መብላት ስለነበረብኝ ነው። (መብላት ብቻ) ባለፈው ዓመት አንድ የሩቅ ዘመዴ ስድስት ሺህ ሩብልስ አውርሶኝ ሲሞት ሥራ ለቅቄ አንድ ጥግ ቦታ ፈልጌ ሰፈርኩ።

እዚች ጥግ መኖር ከጀመርኩ። ቆይቻለሁ አሁን ግን በቋሚነት እዚሁ ለመቆየት ወስኛለሁ። የኔ ክፍል ከከተማው ውጭ የምትገኝ ቁፋፊና አሳፋሪ ጉሬ ነች። ሠራተኛዬ የገበር ሴት ናቸው። ከደደብነታቸው የተነሳ ወበይ የሉላቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ ሁልጊዜ መጥፎ ጠረን አይለያቸውም። የፒተርስበርግ የአየር ፀባይ ጥሩ አለመሆኑና ባለችኝ አነስተኛ ገቢ እዛ መኖር አስቸጋሪ እንደሚሆንብኝ ተነግሮኛል። ይሄም ለኔ አልጠፋኝም። ፔተርስበርግ እየሩ አስቸጋሪና ወጪ የበዛባት ከተማ መሆኗን ከከንቲባው በላይ አውቃለሁ። ይህም ሆኖ ፔተርስበርግ ከተማ እኖራለሁ። ፔተርስበርግን ብሞት አልለቅም። በፍፁም! አህ፣ ግን ለቀትኢት አልለቀቅኢት ምንም ልዩነት አያመጣም።

በነገራችን ላይ አንድ ጨዋ ሰው በክፍተኛ ደስታ የሚያወራው ስለምንድን ነው?

መልስ፡- ስለ ራሱ። በጣም ጥሩ። እኔም ስለራሴ አወራለሁ።

III

የተከበራችሁ ሰዎች ልታጸምጡኝ ፈለጋችሁም አልፈለጋችሁም ለምን ነፍሳት ፣ንኳ ለመሆን እንዳልቻልኩ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። ነፍሳት ለመሆን ብዙ ጊዜ መመኘቴን አምልሳችኋለሁ። የሚያሳዝነው ግን፣ ያም አልሆነልኝም። የተከበራችሁ ሰዎች፣ ክፉኛ ራስን ማወቅ (መንዝዙብ) በሽታ ነው። የሚያም በሽታ! ለመደበኛ ሕይወታችን የመደበኛ ሰው ንቃተህሊና (ግንዛቤ) ብቻ በቂ ነበር። ማለቴ የደስታ ቢሉ የአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ምሁር ሊኖረው ከሚገባው ራስን የማወቅ (ግንዛቤ) ግማሹ፣ እንደውም ሩብ ያህሉ በቂ ነው። ለምሳሌ ተራ ወይም የተግባር ሰዎች የምንላቸው ያላቸውን ያህል ግንዛቤ መያዝ በቂ ነው። አርግጠኛ ነኝ ይህንን በማለቴ በተግባር

ሰዎች ላይ ጉራዬን ለመንዛት ወይም ለመቀለድ የምሞክር ሊመስላችሁ ይችላል። ልክ እንደዛ መሰለኝ! ግን የተከበራችሁ ሰዎች፣ እስቲ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። ማነው በጉዶሎነቱ ጉራውን ሊነዛ ተርቶ ማለየት እንኳ የሚፈልግ?

ግን! ምንድነው የማወራው? እም፣ ሁሉም ሰው ጉድለቱን ያሳያል፣ እኔ ምናልባት ከሁሉም በላይ አደርገው ይሆናል። ለማንኛውም በዚህ አንጨቃጨቅ፣ ነገሩ ሁሉ ግራ ነው። ይሁን ፣ንጂ አሁን ድረስ ብዙ ራስን ማወቅ (መገንዘብ) በማንኛውም መልኩና መጠን በሽታ ነው አላለሁ። በዚህ አጭሜ የፀናሁ ነኝ ለማንኛውም ይህንን ለጊዜው አንተወው።

እስቲ ይሄን መልሱልኝ፣ «የተከበረና ቅንጅ» ስለምንላቸው ነገሮች በሚሰማኝ አፍታ- ልክ በዛን ሰዓት ለምንድነው ሁልጊዜ በሀፍረትና በጥልቅ-ግንዛቤ መሸማቀቅ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ወንጀለኞች የሆንበት እጅግ አሳፋሪ ድርጊቶች የሚሰመሩኝ? ደግሞ ለምንድነው ልክ ሆን ተብሎ ይመስል-እንዲህ አይነት አሳፋሪ ድርጊቶች ሀሊናዬን የሚያሳፍሩት፣ ከቶም ላስባቸው አይገባም በምላቸው ሰዓትና አጋጣሚ የሚሆነው? ሀሊናዬ ክቡርና ቅንጅ ስለሚባሉትና ጥሩ ነገሮች ባሰበ ቁጥር ወደበለጠ ችግር እገባለሁ። ትልቁ ችግር ይሄ ሁሉ በእኔ ላይ የሚሆነው በአጋጣሚ ሳይሆን ከዛ ውጭ መሆን እንደማይችል አይነት ሆኖ ነው።

አንደ መጥፎ ችግርና በሽታ ሳይሆን፣ ለኔ ከዚህ ውጭ መሆን የማይችል መደበኛና ጤናማ የሆነ ክስተት ከመምሰሉ የተነሳ ከቶም እንደ ችግር አልቆጥረው። እንደውም መጨረሻው ምናልባት ይሄ የኔ ጤናማ ሁኔታ ነው ብዬ ወደማመን ደረጃ አደረሰኝ። ምናልባትም በውል አምኜበት ይሆናል። በመጀመሪያ ግና በመነሻው ይሄን በመታገል የደረሰብኝ ስቃይ አይነገርም! ሌሎች ሰዎች እንዲህ እንደእኔ ሆነው ያውቃሉ ብዬ ስለማላምን ከዛ በኋላ ሥቃዩን በሙሉ ሚስጥር አድርጌ ያዝኩት። እየቆየም ውሎዬን

ቋጭቼ ወደቤቴ በምመላለስበት አያንዳንዱ ቀን በዛን ዕለት እጅግ አስቀያሚ የሆነ ድርጊት መፈፀሜን በመገንዘብ አሁንም ድረስ የሚያሳፍረኝ አንድ ሚስጥራዊ ጤናማ ያልሆነ አሣፋሪ ደስታ ይሰማኝ ጀመር። በውስጤም በሚስጥር የሚሰማኝ ምሬት ወደ አሣፋሪነ ውጉዝ ጣፋጭነትና ከዛም ወደ እውነተኛ ደስታ እሰኪቀየር ድረስ ራሴን በራሴ እጨቀጭቃለሁ፣ እወነጅላለሁ፣ እጨነቃለሁ አዎ! ወደ እውነተኛ ደስታ እስኪለወጥ! ደስታ! እርግጠኛ ነኝ ስለደስታነቱ። ይህን ያልኩበት ዋናው ምክንያት ሌሎች ሰዎች ተመሣሣይ ደስታ ይሰማቸው እንደሆነ ለማወቅ ነው። በዝርዝር ላብራራላችሁ። የደስታው ስሜት የሚመጣው የደረሰብኝን ውርደት በጥልቅ ሲሰማኝ ነው። ምክንያቱም ከማልገፋው ግምብ ጋር የተፋጠጥኩ ስለሚመስለኝ፣ በርግጥ መጥፎ መሆኑን ባውቅም ምንም ላደርገው እንደማልችል በማወቅ ራሴን ወደሌላ ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል ትንሽ ሙጣጭ እምነት እንኳ ቢኖረኝ ጨርሶ ለመለወጥ እሺ እንደማልል እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው። ምክንያቱም ወደ የትም ልቀየር ብፈልግም ምንም የማደርገው አለነበረኝምና ነው። ምክንያቱም ልለውጥበት የምችልበት ሌላ ነገር የለምና። ከሁሉም በላይ ደግሞ (ይሄ ላሳምርበት የምፈልገው ሃሣብ ነው) ምንም ይሁን ምን በመደበኛና በመሠረታዊ ጥልቅ እውቀት ሕጐች መሠረትና የነዚህ ሕጐች ቀጥተኛ ውጤት በሆነው የእንቅስቃሴ ሙትነት የተነሣ ራስህን ለመለወጥ አለመቻል ብቻ ሣይሆን አንዳችም ሙከራ ማድረግ አትችልም። ከዚህ ጥልቅ እውቀት (ግንዛቤ) የተነሣ ከብረቢስ ወራዳ በመሆንህ ትከከለኛ ነህ። (ከብረቢስ ወራዳ መሆን የሚያፅናና ይመስል?) ለማንኛውም ይሄ ይብቃን።

....ያንተ ያለህ ብዙ አወራሁ አይደል? ግን ያብራራሁላችሁ ነገር አለ? እንዴት ነው ይህንን የደስታ ስሜት መግለፅ የሚቻለው? በጣም ጥሩ። አብራራለሁ። እስከመጨረሻው ነጥብ ድረስ በዝርዝር አብራራለሁ። ለዚህ ነው ብዕሬን ያነሣሁት።.....

ለምሳሌ እኔ ከንቱ ነኝ። እንደጐባጣ ወይም ድንክ ሰው በጣም ፈሪና ለሚቱ በቀላሉ የሚጐዳ ተጠራጣሪ ነኝ። እንዲህም ሆኖ ግን አንድ ሰው በጥፊ ቢያጮለኝ ደስታ ሊሰማኝ እንደሚችል ያሰብኩባቸው ጊዜያት ነበሩ። ይሄን የምለው ከምሬ ነው። በጥፊ ተመትቼ ቢሆን ኖሮ ደስታ አገኝ እንደነበር ርግጠኛ ነኝ። ያለጥርጥር የተሰፋ መቁረጥ ደስታ ነው። ተሰፋ መቁረጥም እኮ የራሱ የሆነ ደስታ፣ ያውም ጥልቅ ደስታ የሚሰጥበት ሁኔታ አለ። በተለይ ያለህበትን ሁኔታ ጭራሽ ተስፋ— ቢስነት በጥልቀት የምትረዳ ከሆንክ!! ያኔውኑ— ማለቴ— በጥፊ እንደተመታህ ከፉኛ የመዋረድና የመናቅ የሀፍረት ስሜት ያጥለቀልቅሀል። ችግሩ፣ ለድርጊቱ ምንም ሰበብ አስባብ ባመጣም በማጠቃለያው ግን ጥፋቱ የራሴ ሆኖ ነው የሚገኘው። በጣም የሚጐዳው ደግሞ ተበዳይ ብሆንም በዳይ ነኝ፣ ይህም የሚሆነው በተፈጥሮ ሕግ መሠረት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ጥፋተኛ የሚያደርገኝ በዙሪያዬ ካሉት ሰዎች ሁሉ በላይ አዋቂ መሆኔ ነው። (ራሴን ሁልጊዜ በዓለም ላይ ካሉ ሰዎች በላይ አዋቂ አድርጌ ነው የማስበው። እና አንዳንድ ጊዜ እንዲህ በማሰቤ አፍራለሁ። በሕይወቴ ሙሉ ሰውን ሙሉ በሙሉ ዓይን— ለዓይን አይቼ አላውቅም። ወይ ወደጉን አለዚያም አንገቴን እሰብራለሁ እንጂ! በመጨረሻው ትንተና ጥፋተኛው እኔው ራሴ ነኝ። ምክንያቱም በውስጤ እፍኝ የማትሞላ ቸርነት ብትኖረኝም እንኳ ልደሰትባት ከምችለው ይልቅ ከቶም እንደማልጠቀምባት ከማወቄ የተነሣ ሺ— እጥፍ እሰቃይበታለሁ። ምክንያቱም በለጋስነትና በቸርነት ስሜቴ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። በጥፊ ያጋጨኝ ሰው ያደረገውን ያደረገው በተፈጥሮ ሕጐች በመታዘዝ ሊሆን ስለሚችል ለድርጊቱ ይቅር ብለው ትርጉም አይኖረውም። እንዳልረሣው ደግሞ— ምንም እንኳን የሆነው ሁሉ በተፈጥሮ ሕጐች አስገዳጅነት ቢሆንም ጥፊው ያማል። በመጨረሻም ይቅር ማለቱንም ሆነ መተውንም ትቼ ልበቀለው ብዬ ባስብ እንዳው ማድረግ ብችል እንኳ ለማድረግ የሚያነሣሣኝ የመንፈስ ብርታት ስለሌለኝ ማንንም ሆነ ምንን መበቀል አልችልም። ለምንድ ነው የመንፈስ ጥንካሬው የሌለኝ? ደህና፣ ስለዚህ ጉዳይ ትንሽ ማብራራት እፈልጋለሁ።

IIII

አያችሁ ለራሣቸው መቆምና መበቀል የሚችሉ ሰዎች እንዴት የሚያደርጉ ይመስላችኋል? እንበል፣ በበቀል ስሜት ተሞልቷል። ይህ ስሜት በውስጣቸው እስካለ ድረስ ሌላ የሚያስቡት ነገር አይኖርም።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው እንደ ዐመፀኛ ኮርማ ቀንዱን ወደ መሬት ዝቅ አድርጐ ወደሚፈልገው ዓላማ ሊንደረደር ሊገታው የሚችል ግምብ ብቻ ነው። በአጋጣሚ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ተራ ወይም የተግባር ሰዎች ፊት ለፊታቸው ግምብ ሲደነቀርባቸው ወዲያው አንገት ይደፉሉ። ለነሱ የድንጋይ ግምብ ማለት (ለተግባር ሰዎች) ለእኛ ለምናስብ ሰዎች እንደሚመስለን ፈፈተና» አይደለም። አራት ነጥብ ማለት እንጂ። እኛ የምናስብ ሰዎች ምንም ስለማናደርግ (ስለማንሠራ) የግምቡ መገተር ዞር እንድንል አያደርገንም። ምክንያቱም የግምቡ መገተር ገለል እንድንል በቂ ማሳመኛ አይሆንንም። ምንም እንኳ ምክንያታችን የሚያሳምነን ባይሆንም እንደሰትበታለን። የተግባር ሰዎች ግን በሙሉ ቅንነት ለግምቡ እጅ ይሰጣሉ። የድንጋይ ግምብ ለእነሱ የሆነ የሚያረጋጋ ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል። የሆነ የመጨረሻና ገዳይ– እንዳውም ሚስጥራዊ የሆነ ተፅዕኖ ያደርግባቸዋል። (እንዲህ ዓይነቱን ተራ ሰው– እኔ እንደማምነው እናት ምድር እንደምትፈልገው ሆኖ የተፈጠረ ፅውንተኛና ጤናማ ሰው ነው። እንዲህ ዓይነቱን ሰው ምሬት በሞላበት ልቤ ሙሉ እቀናበታለሁ። በርግጥ ደደብ ነው፣ ይሄ አያከራክርም። ምናልባትም ጤነኛ ሰው የግድ ደደብ መሆን ይኖርበታል። ይሄን እንዴት ማወቅ ይቻላል? ለምን፣ ምናልባት ይሄግ ቆንጆ ሊሆን ይችላል። እንበል የእውነተኛው ሰው (መደበኛ) ተቃርኖ የሆነው ስሚታዊ ሰው (መቼም እሱ ከተፈጥሮ ውን ሣይሆን ከቴስት ቲዩብ ብልቃጥ የተወለደ ነው) እና ይህ ከብልቃጥ የተገኘ ስሚታዊ ሰው አንዳንድ ጊዜ የሱ ተቃርኖ በሆነው ሰው ፊት (መደበኛው ሰው) ሙሉ በሙሉ ከመብረክረኩ የተነሣ ራሱን እንደ አይጥ እንጂ እንደሰው አይቆጥርም።

እውነቴን ነው የምላችሁ በጣም የሚሰማው ከመሆኑ በስተቀር ያው አይጥ ነው ከሁሉም በላይ ደግሞ ራሱን አይጥ እንደሆነ አድርጐ ነው የሚያምነው። ይሄንን የሚያደርገው ማንም ጠይቆትና አሳስቦት ሣይሆን በራሱ አስተሣሰብ ነው። ትልቁ ቁምነገር ይሄ ነው።

ደህና፣ አሁን ይህንን አይጥ በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ እንመልከተው። እንበል፣ በሆነ ምክንያት ስሜቱ ተጐድቷል። (በነገራችን ላይ ስሜቱ ሁሌም ነው የሚጐዳው) እናም ለመበቀል ይፈልጋል። በውስጡ ከልክ ያለፈ ጥላቻ ይከማቻል። የበደለውን በበደለው መጠን ለመክፈል ስሜቱ ከማንም በላይ ይንቀለቀላል። በመጨረሻም በቀሉን ወደመፈፀሙ ተግባር ይመጣል። መከረኛው አይጥ በጥያቄና በጥርጣሬ አማካኝነት ከመጀመሪያው ብሽቀት በላይ ሌሎች ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ብሽቀቶች አከማችቷል።

ጥያቄው ጥያቄዎችን አየወለደ ቀጥታማ ስሜቱ ጥርጣሬዎቹና በመጨረሻም እንደ ዳኛ ተሰይመው የሚዳኙት የተግባር ሰዎች በሚያወርዱበት ንቀትና የፈዝ ላቅ የቦካ ሃፍረትና ቅሌት ውስጥ ተደፍቆ ራሱን ሲያገኘው ያለው አማራጭ የፊት መዳፎቹን ወደላይ አንስቶ በንቀት ዓይነት ፈገግታ (ንቀቱን ራሱም አያምንበት) ወደጉድጓዱ መመለስ ብቻ ነው። እዛ ቸታታ አፀያፊና የውስጥ ለውስጥ ጉድጓዱ ውስጥ ተወሽቆ የተበደለው፣ የተሣቀበት የተደበደበው አይጥ፣ ቀዝቃዛ መርዘኛና ከሁሉም በላይ ደግሞ ሩታ የለሽ የሆነ ቁጭት ውስጥ ይዘፈቃል። አርባ ዓመታት ሙሉ ሣይረሣ ጐዳቱንና ውርደቱን እስከመጨረሻዋ ዝርዝር ድረስ እያውጠነጠነ በሐፍረት ይጥለቀለቃል።

ከዚህም በላይ በራሱ ምናብ እያገዘፈ ውርደቱንና ቅሌቱን ያጋንነዋል። በሂደትም በራሱ ምናብ ቢያፍርም ከሆኑና ከተፈፀሙበት ሌላ እንዲህም ሊሆን ይችል ነበር እያለ ላያቋርጥ ሁሉንም ነገር ደግሞ ደጋግሞ ያስታውሣል። ከዚህ በኋላ የራሱን በቀል ሊወስድ ይችላል። ያም የሚሆነው በቁጭትና በብስጭቶች በመላሰሉ ጥቃቅን መንገዶችና በድብቅ ላይታወቅ ከምድጃው ኋላ ሆኖ ነው። ምክንያቱም ራሱን በራሱ ለመበቀልም መብት

ያለው ስለማይመስለውና በዚህም ይሣካልኛል ብሎ ስለማያምን፤ በዚህም የተነሣ እበቀላለሁ ብሎ በታጣው ቁጥር በመቶ እጥፍ መልሶ እንደሚቀጣ አስቀድሞ በማወቁ ነው። (ይህንን ሁኔታ በመጨረሻዋ የሞት ሰዓት እንኳ ያስታውሣል።)

...አሁን ያልኳችሁ ደስታ የሚመነጨው እንግዲህ በዚህ ቀዝቃዛና አፀያፊ ግማሽ ተስፋ መቁረጥና ግማሽ እምነት፤ በዚህ ራስን አስከነሕይወት በህዘን አርባ ዓመታት የመቅበር ስሜት በዚህ ተስፋቢስ በሆነና ያልረካ ፍላጐት ውስጥ ውስጡን በሚመዘመዝበት የማንገራገርና የፀፀት ትኩሳት ውስጥ ነው። ከስተቱ በጣም የረቀቀ ከመሆኑ የተነሣ ነፍሳቸው ጠንካራ የሆነ የተግባር ሰዎች ጨርሶ አይረዱትም። «ምናልባትም በሕይወት ዘመናቸው ፊታቸው በጥፊ ያልተቃጠለ ሰዎች ጨርሶ አይረዱትም።!» በማለት በምፀት ልትናገሩ ትችላላችሁ። እንዲህ በማድረግ እኔ ስለጉዳዩ በርግጠኛነት የምናገረው ጉንጩ በጥፊ የጮለ ስለሆነ እንደሆነ በአሽሙር ትነግሩኛላችሁ። እርግጠኛ ነኝ። እንደዚህ ነው የምታስቡት። ግን አንድ ነገር ላረጋግጥላችሁ። በጥፊ አንድም ቀን ተመትቼ አላውቅም።

በዚህ የተነሣም እናንተ ስለኔ ስለምታስቡት ቅንጣት ታክል አልጨነቅም። ይልቅስ የሚበታኝን ያህል የብዙ ሰው አገጭ በቦክስ ስላላነገልኩ ይቅጨኝ ይሆናል። ለማንኛውም ስለዚህ ጉዳይ እዚህ ላይ ይበቃ!

ይልቅስ ወፍራም ቆዳ ያላቸው ሰዎች አሁን ስለነገርኳችሁ ደስታ ረቂቅነት ለምን እንደማይረዱ ላብራራላችሁ። ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ከጣራ በላይ እየጮሁ እንደአንበሳ ቢያገሱም (እንዲህ ማድረጋቸው ይጠቅማቸዋል ብለን እናስብ) ቅድም እንደነገርኳችሁ ከማይቻለው ጋር ሲፋጠጡ ግን ወዲያው ኩምሽሽ ይላሉ። ለነሱ የማይቻል ነገር ልክ እንደ ድንጋይ ግርግዳ ነው የሚያዩት።

የምን የድንጋይ ግድግዳ? ይሄ ምን ያጠያይቃል፤ የተፈጥሮ ሕግ ማለትም የሣይንስና የሂሣብ ድምዳሜ ማለት ነዋ! ለምሣሌ አንተ ከዝንጀሮ

የመጣህ መሆኑ ሲነግርህ ምን መጨቃጨቅ ያስፈልጋል? ያለህ ዕድል መቀበል ብቻ ነው። ያንተ ቅንጣት ታክል የሥጋ ቁራጭ ከሌሎች በሺህ ከሚቆጠሩ ሰዎች ሥጋ በላይ ውድ መሆኑንና ሥነ ምግባርና ኃላፊነት የሚባሉ ከንቱ እሳቤዎችና ገለመሌዎች ከቶም ምንም ሩይዳ የሌላቸው መሆኑን ተጠንቶ ሲነገርህ ወደድክም ጠላህም መቀበል አለብህ። ምክንያቱም ሁለት ሲደመር ሁለት አራት ነውና! እስቲ ይሄንን ለማስተባበል ሞክርክ እንበል።

«ያንተ ያለህ!» በማለት ይጮሁብሃል። «ሁለት ሲደመር ሁለት አራት መሆኑን መቼም ልትክድ አትችልም። ተፈጥሮ ያንተን አስተያየት ፈፅሞ አትፈልግም። እሷ ስላንተ ምኞቶችና ፍላጐት ቅንጣት ታክል አትጨነቅም። ሕጐቿን ወደድክ ጠላህ ግዴም አይደል። እሷን እስከውጤቷ እንዳለች እንድትቀበል ግን ግድህ ነው። የድንጋይ ግድግዳ ዞሮ ዞሮ የድንጋይ ግድግዳ ነው። ወዘተ ግን! ለምንድን ብዬ ነው የምገደደው? በዚህም ይሁን በዛ ምክንያት ይህንን ሁለት ሲደመር ሁለት አራት የተፈጥሮ ሕግና ሂሣብ የማልፈልግ ብሆንስ? በእርግጥ የድንጋይ ግድግዳውን ለመደርመስ አልችልም። (አቅሙ እስከሌለኝ ድረስ) ነገር ግን የድንጋይ ግርግዳ ስለሆነና ልደረምሰው አቅም ስለሌለኝ ብቻ ደግሞ አልቀበለውም።

ምክንያቱም ግድግዳው «የፀዕምሮ ሰላም» ማለት አይደለም። ግድግዳው ሁለት ሲደመር ሁለት አራት ስለሆነም «አርፌ እንድቀመጥ የሚያደርገኝ አፅናኝ ቃል አድርጌ ልቀመጥ አልችልም። ያንተ ያለህ! ምን ዓይነት ተራወሬ ነው የምዘበራርቀው? ለነገሩ ሁሉንም ነገር መረዳት ሁሉንም ነገር ማወቅ፣ ስለሁሉም የማይቻሉ ነገሮችና የድንጋይ ግድግዳዎች መረዳት ጠቃሚ አይደለምን? ማለቴ የማትፈልግ እስከሆነ ድረስ ከሁሉም የማይቻሉ ነገሮችና የድንጋይ ግድግዳዎች ጋር አለመታረቅ?

ከግድግዳው ጋር ላለመታረቅ ማስተባበያ የማይገኝለት ሎጂክ «የድንጋይ ግድግዳ ካለ የኔ ስህተት ያመጣው መሆን አለበት» ብሎ ራስን መወንጀል ነው። (ምንም እንኳ አንተ የፈፀምከው ስህተት አለመኖሩን

ብታውቅም) ስለዚህ ምንም እንዳትሠራ ከፈለክ ዝምብለህ ከንፈርህን በጥርስህ እየነከስክ የንዴቴ ምክንያት የሆነ ሰው የለም የሚል የማይጨበጥ እምነትህን አቅፈህ፣ የሆነው ሁሉ ያልሆነ፣ የሆነ አዘናጊ ተራ የብልጣብልጥ ቀልድ ወይም ምንም ማን መሆኑ የማይታወቅ የሆነ አሳፋሪ ውሸጉብር ነው በማለት አለመቀበል። ወዲህ አልክም ወዲያ የራስምታቱ ግን አይቀርልህም።

IV

«ሃ! ሃ! ሃ! ይሄ ማለት በጥርስ በሽታህ ጭምር ትደሰታለህ ማለት ነው!» ብላችሁ በሳቅ ተንከተከታችሁ አይደል?

«ደህና! ግን ቢሆንስ? አዎ በጥርስ ሕመም ውስጥም ደስታ አለ!» ብላችሁስ?

ለአንድ ወር ያህል ጥርሴን አምኜ አይቼዋለሁ። የራሱ ደስታ አለው። አያችሁ የጥርስ ጥዝጣዜን በዝምታ ልትታገሱት አትችሉም። ታታስታላችሁ። ነገር ግን እነዚህ ማታስቶች ቅን አይደሉም። ከክፉት ጋር የተቀላቀሉ ማታስቶች ናቸው። ቁም ነገሩ ከፋቱ ነው። ሕመምተኛው በነዚህ ማታስቶቹ የሚገልፀው ደስታውን ነው። ደስታ ባይሰጠው ኖሮ አያታስትም ነበር። የተከበራችሁ ሰዎች፣ ይሄ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ ምሳሌ ነውና ይበልጥ አብራራላችሁዋለሁ።

በነዚህ ማታስቶች የሚገልፀው በመጀመሪያ ደረጃ ሕሊናህን በእጅጉ የሚያዋርደው ሥቃይ ዓላማቢስነት ነው። ምንም እንኳ አንተ ቁብ የማትሰጠው ዞሮ ዞሮ ግን የሚያሰቃይህ የተፈጥሮ ምት ነው። እሷ የፈለገችውን ለማድረግ ነፃ ነች። በማታስቶችህ ምንም እንኳ ተጠያቂ የምታደርገው ጠላት ባይኖርህም ሥቃዩ ግን መኖሩን የመረዳትህ ቋንቋ ነው። የዓለም ጥርስ ሐኪሞች ሁሉ ቢሰባሰቡም መፍትሔውን ሊሰጥህ የሚችለው የገዛ ጥርስህ ብቻ እንደሆነ የማወቅ ሥቃይ መግለጫ ነው። ያ አንተ የማታውቀው ኃይል ከፈለገ ብቻ ጥርስህ እንደ ሚተውህ እሱ ያልፈለገ እንደሆነ ግን ጥርሶችህ ለሚቀጥሉት ሶስት ወራት ሊጠዘጥዙህ እንደሚኖሩ

የታወቀ እልህ ነው። አሁንዋ ድረስ ይህንን አምነህ ያልተቀበልክ ከሆነ የሚተርፍህ ነገር ራስህን በራስህ መደብደብ ወይም በቡጢ ግድግዳውን የቻልከውን ያህል መደብደብ ብቻ ነው።

ከነዚህ ገዳይ ሥቃዮችና የማን እንደሆነ የማይታወቅ አረመኔአዊ ቀልድ ነው እስከ ወሲባዊ ቅንዝር ድረስ ሊደርስ የሚችል ደስታ የሚቀሰቀሰው። የተከበራችሁ ሰዎች፣ እስቲ አንድ በጥርስ በሽታ የሚሠቃይ የአሥራዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ምሁር ሕመሙ ከጀመረው ዕለት በተለየ ሁኔታ የሚያደርገውን የሁለተኛ ወይም የሶስተኛ ቀኑን ማቃሰት አዳምጡ እስቲ! የሱ ማቃሰቶች እንደማንም ገበሬ ዓይነት አይደሉም።

ማቃሰቶቹ ከቀን ወደቀን አስጠሊታና አናዳጅ እየሆኑ ነው የሚሄዱት። በዚህ ማቃሰቱ ሕመሙን ለማሻል የፈየደው ነገር እንደሌለና ይልቁንም ሌሎችንም በማበሳጨት ሁሉም በጥላቻና በንቀት እንደሚያዳምጡት አላስፈላጊ መቃተቶቹን ከፈለገ ሊያቆማቸው የሚችል መሆኑን ነገር ግን አሁን የሚያባብሰው ከጥላቻና ከክፉቱ የተነሣ ራሱን እያስደሰተ መሆኑን እንደሚያውቁበት ያውቃል። እንግዲያው ልንገራችሁ ይኸ ሁሉ ማባባሻና ማብሸቂያ የስሜታዊ ደስታ መግለጫ ናቸው።

«ያስጨነቅኩዋችሁ መሰለኝ አይደል?» የሚል ይመስላል «ሁላችሁንም ረበሽኳችሁ፣ ቤቱን እንቅልፍ አሳጣሁት አይደል? በጣም ጥሩ፣ ለኔ ብላችሁ ዘላለማችሁን አትተኙ ብትፈልጉ፣ ደግሞ ሁልሽም ጥርሴ እንዴት እንደሚጠዘጥዘኝ እያንዳንዷን ደቂቃ አብራችሁኝ ልትሰቃዩ እፈልጋለሁ። ከእንግዲህ ድሮ እኔ ለእናንተ መስዩ መቅረብ እፈልግ እንደነበረው የተከበርኩ ሰው ሣይሆን ተራ በጥባጭ ነኝ። አይደል? ከሆነም – ይሁና! እንዳውም እውነተኛ ማንነቴን ስላወቃችሁ ደስ ነው የሚለኝ። አናዳጅ ማቃሰቶቼን መስማት አትፈልጉም አይደል? ደህና እንደፈለጋችሁ መሆን ትችላላችሁ። ቁጥዬ ግን እንዴት ባለማላዘን እንደማቃስት ስሙ። ከበፊቱ የበለጠ አብሻቂ እንደሚሆን አረጋግጥላችኋለሁ። እመኑኝ!... «እስካሁን አልገባችሁም፣ የተከበራችሁ ሰዎች፣ እንደዛ ከሆነ ይህን

ቅንዝራዊ ደስታ ለመረዳት ሕሊናችንን ይበልጥ ማሾል አለብን ማለት ነው። እየሳቅኩ ነው! በጣም ነው ደስ የሚለኝ። ነገር ግን ክቡራን! ቀልዶቼ ለዛቢስና የተቀጣጠበሩ፣ በራስ መተማመን የተሞላባቸው እንደሆነ ይሰማኛል። ይህ የሆነው ለምን መሰላችሁ? ለራሴ ክብር ስለሌለኝ ነው። ለነገሩስ ክፉኛ ስሜታዊ የሆነ ሰው መጀሪመያውኑስ ቢሆን ራሱን ሊያከብር ይችላል?

V

እንነጋገር ከተባለ፣ በራሱ ውርደት 'ንኳ ለመደሰት የሚጥር ሰው ቅንጣት ታክል ክብር ለራሱ ሊኖረው ይገባል ልትሉ ትችላላችሁ? ይህንን የምላችሁ ተፀፅቼ አይደለም። ለነገሩ እኔ «አባቴ—ይፍቱኝ፣ ዳግም ሐጢያት አልሠራም!» ብዬ ንሰሀ ለመግባት የምችል ሰው አይደለሁም። ማለቱ ከብዶኝ ሣይሆን እንዳውም ከሚገባው በላይ በቀላሉ ልል ስለምችል እንጂ! በእንዲህ ዓይነት አጋጣሚ— ያለሐጢያቴ ስሰቃይ ነው የምገኘው። በሚሆነው ማንኛውም ነገር ሁሉ ስሜቴ በጥልቀት ይነካል። ደጋግሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ። እንባዬ እንደጉርፍ ይወርዳል። ይህንን የማደርገው ለማስመሰል ባይሆንም እራሴን ማታለሌን ግን አውቃለሁ። የዚህ ሁሉ ጭምልቅልቅ ተጠያቂ ልቤ ነው። ምንም እንኳ ዕድሜዬን ሙሉ ያሰቃየኝና የሚያሰቃየኝ የተፈጥሮ ሕግ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ግን ተፈጥሮ ተጠያቂ አይደለችም። ብቻ ይሄን ሁሉ ማስታወሱ አፀያፊ ነገር ነው። ምክንያቱም ከዚህ ሁሉ አንድ ወይም ሁለት ደቂቃ በኋላ ያደረግኩት ንስሐ ያፈሰስኩት እንባ ሁሉ የውሸትና ተራ ግብገበት መሆኑን እገነዘባለሁ። ታዲያ ለምንድን ነው እንዲህ የማደርገው ብትሉኝ፣ መልሴ የምሠራው አጥቼ በድብርት ላለመሞት ብዬ ነው የሚል ይሆናል። ምንም ውሸት የሌለው እውነት ነው የምነግራችሁ።

የተከበራችሁ ሰዎች! ብትፈልጉ ራሳችሁን ብትመረምሩ ያልኳችሁ ሁሉ እውነት መሆኑን ታረጋግጣላችሁ። በበኩሌ መኖር እችል ዘንድ የራሴን ትንንሽ ጀብዱዎች በመፍጠር የራሴን ሕይወት አዘጋጅ ነበር። ለምሣሌ፦

አዘውትራ በሆነ ባልሆነ ሰበብ እከፋ የነበረው ሆነ ብዬ ነው። እንደ እውነቱ ግን ምንም ምክንያት የለም። በኋላ ግን መከፋቴን ራሴ በራሴ እያባባስኩ መጨረ ላይ የእውነት ይከፋኛል። ሕይወቴን በሙሉ ለእንዲህ ዓይነት ተንኩሎች ተገዥ ስለነበርኩ በመጨረሻ ላይ በራሴ ላይ ቁጥጥር አጣሁ። አንድ ጊዜ የውነት ፍቅር እንዲይዘኝ ሞከርኩ። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲገጥመኝ ሁለተኛ ጊዜዬ ነው። እውነቴን ነው የምላችሁ ከፉኛ ተሰቃየሁበት። በልቤ ውስጥ ልብ ግን የእውነት እየተሰቃየሁ መሆኔን አላምንም ነበር። እንዳውም በሆነ መንገድ በራሴ ላይ አስቅ ነበር።

ይሁን 'ንጂ– ዕውነትም በፍቅር የወደቅኩ ይመስል ማንም ሊያየውና ሊረዳው በሚችለው ሁኔታ ተሰቃየሁ። ይህን ሁሉ ያደረግኩት ግን የተከበራችሁ ሰዎች– ከመሰላቸት የተነሣ ነበር። በቃ! ድብርቴን ለማራገፍ ስል ምንም የምሠራው ስላልነበረ ደንዝዠ ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ያለሥራ መንጠራወዜ ነው። የንቃተ ህሊና ግንዛቤ ጥልቅ መሆኑ ደግሞ ውጤቱ ማንኛውንም ዓይነት እንቅስቃሴ መግታት ነው። ቀደም ሲል ተናግሬያለሁ የተከበራችሁ ሰዎች! ተራና የተግባር ሰዎች ንቁ ሠራተኛ የሚሆኑት ደነዞችና በአእምሮዋቸው ያልበሰሉ ስለሆነ ነው።

ይሄ እንዴት ነው የሚብራራው? በጣም ጥሩ። እንደዚህ እንመልከተው፤ በአእምሮዋቸው ቀርፋፋነትና ጥሬነት የተነሣ በቅርባቸው ያለውንና ሁለተኛ ደረጃ ምክንያቶችን (ዓላማዎችን) እንደ መሠረታዊ ምክንያት ይወስዱታል። በዚህም የተነሣ ማንኛውንም ዓይነት ተግባር (ሥራ) ለመሥራት ጠንካራ መሠረታዊ ምክንያት (ዓላማ) እንዳገኙ ሆነው በሙሉ ልብ ይንቀሳቀሳሉ። ዋናው ቁም ነገር ይሄ ነው። አንድ ሰው በንቃት (በግንዛቤ) መንቀሳቀስ የሚችለው በድርጊቱ አእምሮው ሙሉ በሙሉ ሲያምንበት ነው። ለምሳሌ :- እኔ እንዴት አድርጌ ነው ሙሉ በሙሉ አምኜ ልንቀሳቀስ የምችለው? ለድርጊቴ መነሻ ምክንያቶች የሚሆነውን መሠረታዊ ዓላማ የት ነው የማገኘው?

መሠረታዊ ዓላማ የሚገኘው ከየት ነው? የማሰብ ኃይሌን ያለገደብ ስለምጠቀም በመጀመሪያ መሠረታዊ ያልኩት ዓላማ ሌላ «መሠረታዊ» ምክንያት እየወለደ፣ ሌላውም ሌላ እያስከተለ ያለማቋረጥ ያቅጥላል። ይግተለተላል! ይሄ የማንኛውም ንቃተ ሕሊና (ግንዛቤ) ጥልቀትና ትንተና ውጤት ነው። ስለዚህም የተፈጥሮ ሕግ ማለት ነው። ውጤቱስ? ያው አንድ ዓይነት ነዋ! ስለብቀላ እያወራሁ እንደነበር አትርሱ።

(ይሄንን ጉዳይ በደንብ የተረዳችሁልኝ አይመስለኝም) ላስረዳ እንደሞከርኩት ሰው በቀል መውሰድ የሚችለው በድርጊቱ ፍትሐዊነት ሲያምን ነው። ይሄ ደግሞ ለእርምጃው መሠረታዊ የሚሆነው ምክንያት ማለትም ፍትህ አግኝቶበታል። ስለዚህ በሚሠራው ድርጊት ትክክለኛነት ስላመነ ድርጊቱን ተረጋግቶ በስኬታማ መንገድ ያከናውናል።

እኔ ግን በብቀላ ውስጥ ፍትህ ስለማይታየኝ ድርጊቱን ልፈፅም ብችል ከፍትህ ፍለጋ ሣይሆን ከጥላቻ ነው። ግን ጥላቻውስ ባይኖረኝ? ደግሞም የምሬት ስሜቴ በራሱ በነዛ በተረገሙ ራስን በጥልቅ የመገንዘብ ሕጐች መሠረት እየቆየ እንደጉም የሚበተን ነው። አንድ ጊዜ ቀናስል ዓላማው ድራሹ ጠፍቷል። ምክንያታዊነቴ ተኗል። ልበቀለው የምችለው ሰውም የለም። ደረሰብኝ ያልኩት «በደል» ወደ «ዕጣ ፈንታ» ተቀይሯል። ማለትም፣ ልክ እንደጥርስ በሽታው ሕመም። ስለዚህ ያለህ ዕድል ሕመምን ብቻ መታመም ነው። ሌላው አማራጭ ግን በንዴት ከግድግዳው ጋር መላተም። ስለዚህ ለበቀልህ ሰበብ በማጣትህ ሁሉንም ነገር ትተወዋለህ። እንበል:- ህሊናህን ለተወሰኑ ቀናት ዘንግተህ በጭፍን ስሜት ብቻ ተሞልተህ ራስህን በመገፋፋት እርምጃህን ወሰድክና ጠላህ ወይም ወደድክ እንበል፣ ከአንድ ሁለት ቀናት በኋላ ግን በድርጊትህ እጅግ ከማፈርህ የተነሣ ራስህን ትንቃለህ። ስለሆነም እንደላሙና አረፋ ትኩረፈረፋልህ እንጂ ምንም የምትሠራው ነገር አይኖርም። እያችሁ ውድ አንባቢዎች፣ እኔ ራሴን አዋቂ ብዬ የምጠራበት ዋናው ምክንያት የጀመርኩትን መጨረስ ስለማልችል ነው። ለማንኛውም እኔም ጉዳት የሌለኝ አሰልቺ ወሬኛ ነኝ። ደግሞስ

ማንኛውም ሙሁር ሰው ብቸኛ የመኖር ዓላማ ማውራት፣ ማለትም ጊዜውን ሆን ብሎ በከንቱ ማጥፋት ቢሆንስ?

ከቶም ምን ነገር የማልሠራው ከስንፍና የተነሣ በሆነና እንዴት በተደሰትኩ ነበር! አምላኬ! ራሴን እንዴት አድርጌ ባከበርኩ ነበር።

አዎ! ቢያንስ ሰነፍ ለመሆን ችያለሁ ማለት ነው። እንደ አንድ በጐ ተግባር ሊወሰድ የሚቻል ችሎታ ባለቤት ነኝ ብዬ ላምን እችል ነበር። ጥያቄዬ ማነው እሱ? መልስ ዘዋሪ! እንዲህ ተብዬ የምታወቅበት መለያ ማግኘቱ በራሱ እውነተኛ ደስታ ያጐናፀፈኝ ነበር። ምክንያቱም እኔን ሊገልፅ የሚችል «በጐ» መለያ ስለተገኘልኝ ሌሎች ስለኔ አንድ ነገር እንዲሉ ያስችላቸው ነበር። «የማይሠራ ዘዋሪ!» አያችሁ! ይሄ ራሱን የቻለ የሕይወት ትርጉም ያለው ተልዕኮ ነው! እውነተኛ ሥራ! ቀልድ እንዳይመስላችሁ። በትክክል የዕድሜ ልክ ሥራ ነው። እንደዛ ቢሆንልኝ ነበር ከኔ ጋር የሚስማማ የአንድ ልዩ ቡድን አባል በመሆን ራሴን ሳከብር እኖር ነበር። ሕይወቱን ሙሉ በመጠጥ ቀማሽነት ያሳለፈ ሰው አውቃለሁ። ሥራውን እንደጠቃሚ ሥራ ቆጥሮ ስለነበር አንድ ቀን 'ንኳ ጥርጣሬ አድሮበት አያውቅም። የሞተውም በሥራው የሚኮራ ሕሊና ይዞ ነው። ፍፁም ትክክለኛ ግለሰብ ነበር። እና «የማይሠራ ዘዋሪ» ለመሆን ብችል ኖሮ የሕይወት ሥራዬ አድርጌው በመዞርና በመብላት አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በሁሉም ነገር ውስጥ «ክቡርና ቆንጆ» የሆነውን ሁሉ አደንቃለሁ። እንዴት አገኛችሁት ይሄንን ሃሣብ? እኔ በበኩሌ ለረጅም ጊዜ ሳልመው የኖርኩት ነው። «ክቡርና ቆንጆ» ላለፉት አርባ ዓመታት ሲያስጨንቀኝ ቆይቷል። ግን አንድ ቀን፣ አዎ አንድቀን ሁሉም ነገር የተለየ ይሆን ነበር። ለምሣሌ «ክቡርና ቆንጆ » ለሆኑ ነገሮች ጤንነት መጠጣትን ሥራዬ አድርጌ እይዘው ነበር።

በአገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ ዕንባዬን በብርጭቆ ውስጥ በማፍሰስ «ለክቡርና ቆንጆ» ነገሮች ክብር በአንድ ትንሹ ጭልጥ አደርገዋለሁ። እንዲህ በማድረግም በዓለም ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ወደ «ክቡርና ቆንጆ»

እለውጥ ነበር። ከቆሻሻው ክምርና ጥንባት ውስጥ ሁሉ «ክቡርና ቆንጆ» ነገሮች አገኝ ነበር።

እንባዬን እንደእስፖንጅ ጭምቅ ባደረግኩ ነበር። ሰዓሊው ጂ ለምሳሌ ሥዕል ይስላል። «ክቡርና ቆንጆ» የሆነውን ሁሉ ስለማፈቅር ለሥራው የጤንነት ዋንጫዬን አነሣለሁ። ደራሲው «ሁሉንም» ለማስደሰት ይፅፋል፤ እኔም «ክቡርና ቆንጆ» የሆነውን ሁሉ ስለማፈቅር «ለሁሉም» ጤንነት እጠጣለሁ።

እንዲህ በማድረጌም ሁሉም እንዲያከብረኝ እፈልጋለሁ። አክብሮት የሚነሳኝንም እክሳለሁ።

በዚህች ዓለም ላይ ሰላሜን አግኝቼ በጥሩ ሥነምግባር እቅፍ ውስጥ እሞታለሁ። ታዲያስ? ይሄ ታላቅ ደስታ አይደለም 'ንዴ! በመንገድ ላይ ያየኝ ሁሉ «ትክክለኛ ጥሩ ሰው ሚለት እኝህ ናቸው፤ እውነተኛና በጐሰው!» እንዲለኝም ቦርጫምና የተንጠለጠለ አገጭ እንዲኖረኝ አደርጋለሁ። የተከበራችሁ ሰዎች! እናንተ ያሻችሁን በሉ፤ ለኔ ግን በዚህ ተቃራኒ (ኔጌቲቭ) ዓለም እንዲህ ዓይነት ምሥጋናዎችን ማግኘት ያስደስተኛል።

እነዚህ የማይጨበጡ ወረቃማ ሕልሞች ናቸው። እስቲ ንገሩኝ ማነው እሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው ወራዳ ፀባይ የሚያሳይበት ብቸኛው ምክንያት ፍላጐቶቹን ካለማወቅ ነው። ቢያውቅ ኖሮ እውነተኛ ጥቅሞችን ስለሚያውቅ ወራዳ ባህሪውን ትቶ ጥሩና የተከበረ ሰው ይሆን ነበር። ምክንያቱም ለሱ የሚጠቅመውን ስላወቀና ስለተረዳ ጥቅሙንም የሚያገኘው ጥሩ በመሥራት እንደሆነ ስለሚገነዘብ እናም ማንም ሰው ደግሞ እያወቀ የራሱን ጥቅም የሚጐረር ተግባር የማይፈፅም ስለሆነ ሰውዬው ጥሩ መሥራት ይጀምራል፤ ያለው ማነው? ያለውን ሰው ንገሩኝ! እንዴት ያለ ሕፃንነት ነው! እንዳው ከመጀመሪያው ሰው በነዚህ የሺህ ዓመታት ታሪኩ ያደረገውን ሁሉ ያደረገው በፍላጐቶቹ መሠረት ነውን? ሰው ሆነ ብሎ ምንም እንኳ እውነተኛ ፍላጐቶቹን ቢያውቅም፣ ነገር ግን እንዳላወቀ ሆኖ አደጋን

ለመቅመስና ዕድሉን ለመሞከር በማንምና በምንም ሳይገደድ ከተሰመረለት የዕጣ መሥመር ውጭ አፈንግጦ ወደማያውቀው ጐዳና በመግባት የእውር ድንብሩን ኳትኗል። ከዚህ በፊት ያልነበሩ፤ አዲስ መንገዶችን ስለመክፈቱ የሚያረጋግጡልንን በሚልዮን የሚቆጠሩ እውነቶችን፤ መረጃዎችን ምን ልናደርጋቸው ነው? ለሰው እምቢተኛነቱና አልከኛነቱ ከማንኛውም ዓይነት ጥቅም በላይ ያስደሰተዋል።... ጥቅም! ምንድነው ጥቅም? እንዳው ለመሆኑ የሰው ልጅ ጥቅም ምን እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ ልትገልፁ ትችላላችሁ? ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጅ የመጨረሻ ፍላጐት በአጋጣሚ ብቻ ሣይሆን መሆን ስላለበት ሥምር ከሚጠቅመው ይልቅ ወዲያውኑ የሚጐዳውንና ጥቅም የማይሰጠውን ነገር መመኘትስ ቢሆን? እንደዛ ከሆነ ደግሞ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከተከሰተ ስለሰው ልጅ ጥቅም ያወራናቸው ነገሮች በሙሉ ዋጋቢስ ይሆናሉ ማለት ነው። ምን ይምስላችኋል? እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች የሉምን? እየሣቃችሁብኝ ነው አይደል? ግዴለም ሣቁ። ግን እስቲ ይሄንን ንገሩኝ የሰው ልጅ ፍላጐቶች ፍፁም በሆነ ትክክለኛነት ተሰልተው ያውቃሉን? በዚህ የሰው ልጅ ጠቃሚ ፍላጐቶች ዝርዝር ውስጥ በትክክል ሊገጥሙና ከቶም ሊገጥሙ የማይችሉ የሉምን? እናንተ የተከበራችሁ ሰዎች! እኔ አንደሚገባኝ እስታትስቲካዊ አሃዞችን፤ ሣይንሣዊና ኢኮኖሚያዊ ቀመር ተከትላችሁ የሰው ልጅን በጐ እሴቶች ዝርዝር ሰንጠረዥ የያዛችሁ ይመስለኛል። ምንድን ናቸው እሴቶቹ? ሰላም፤ ነፃነት፤ ብልፅግና፤ ሃብትና ወዘተርፈ። በዚህ መሠረት እንግዲህ እነዚህን ነገሮች በግልፅ እያወቀ ሆነ ብሎ ተፃራሪውን የሚያደርግ ግለሰብ በናንተ አመለካከት ለነገሩ በኔም አመለካከት ሥምር ሚስጥራዊ ወይም እብድ ሰው ነው አይደለም 'ንዴ? ይልቅስ አሰገራሚው ነገር ይሄ ነው፤ ለምንድን ነው እነዚህ እስታትስቲሺያኖች ብልህ ሰዎችና የሰው ልጅን አፍቃሪዎች ሁልጊዜ የሰውን እሴቶች ሲያስሉ አንድ እሴት ችላ የሚሉት? ሌላው ቀርቶ ሊያጤኑት በሚገባ መንገድ እንኳ አያጤኑትም።

ይህን እሴት የነሱ ዝርዝር ውስጥ ቢያስገቡት ምንድነው ጉዳቱ? አያችሁ ተልፏ ችግር ይህ ልዩ ጥቅም በነሱ ሰንጠረዥ የትኛውም ምድብ

ውስጥ ስለማይካተት ነው። ለምሳሌ እኔ አንድ ጓደኛ አለኝ። ለነገሩ እሱ ጓደኛ ያልሆነው ሰው አለ 'ንዴ? እና ይሄ ጓደኛችን አንድ ሥራ ሲሠራ በቅድሚያ ሥራውን በሀቅና በምክንያት ሕጐች መሠረት ለማከናወን እንዳቀደ በከፍተኛ ድምፅና ግልፅ ቋንቋ ያብራራላችኋል። ይህም ብቻ አይደለም ለሰው ልጆች እውነተኛና ጤናማ ፍላጐቶች በስሜትና በኃይል ያወራላችሁዋል። የራሣቸውን ጥቅሞችና የሥነ ምግባርን እውነተኛ ትርጉም ያልተገነዘቡ ጠባብና ምኞችን ደግሞ በንቀት ይተቻቸዋል። ወዲያው ግን ልክ ከሩብ ሰዓት በኋላ ያለምንም ድንገታዊም ሆነ ውጫዊ ምክንያት ነገር ግን ከራሱ ፍላጐቶች በላይ ጠንካራ በሆነ ውስጣዊ ግፊት የተነሣ እስካሁን እራሱ ሲናገረው ከነበረው ፍፁም ተቃራኒ የሆነ ተግባር ሲፈፅም ታገኙታላችሁ። ድርጊቱ የምክንያታዊነትና የራሱን ፍላጐት ሕጐች በአጠቃላይ ሁሉንም ነገር የሚጥስ ነው። ...ላሳሰባችሁ የምፈልገው ይሄ የኔ ጓደኛ ግለሰብ ሣይሆን የወል ማንነት ያለው ስለሆነ ብቻውን ለመወንጀል ትንሽ አስቸጋሪ ነው። የተከበራችሁ ሰዎች! ትልቁ ነጥብ ለያንዳንዱ ሰው በጣም ጥሩ ነገር ብሎ ከሚያስበው ጥቅሙ በላይ ውድ የሚሆንበት ነገር አለ። ወይም በሌላ አነጋገር ሁልቀን ችላ የምንለው ልክ አሁን እንዳወራሁላችሁ ዓይነት ከማንኛውም ጥቅሞቹ በላይ የሆነ አስፈላጊም ከሆነ ስለዚህ ጥቅም ሲል ሁሉንም ሕጐች ማለት ምክንያት፣ ክብር፣ ሰላም፣ ብልፅግና በአጭሩ እጅግ ምርጥና አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ሁሉ በላይ ውድ የሚሆንበትን ያንን ፍላጐት ይከተላል።

«ደህና! ይህም ኮ ዞሮ ዞሮ እሴት ነው! አይደለም 'ንዴ ?» ትሉ ይሆናል።

በጣም ጥሩ። ይሄ የሚያጨቃጭቅ ነገር ስላልሆነ እየተግባባን እንደምንመጣ አምናለሁ። ይህ ያልኳችሁ ጥሩ ነገር (እሴት) በጣም የተለየ የሚያደርገው ለሰው ልጅ አሳቢዎች፣ ለሰው ዘር ደስታ ሲሉ ያወጡዋቸውን ዝርዝሮችና ምድቦች ዶግአመድ ስለሚያደርግ ነው። ይህ ጥሩ ነገር ምን እንደሆነ ከምነግራችሁ በፊት የራሴን የግል እምነት ልንገራችሁ። እነዚህ

ሁሉ ሥነ ሥርዓቶች፣ የሰው ልጆች ፍላጐቶች ለማብራራት የሚሰጡ ፅንሰ ሃሳቦችና እነዚህንም ለማግኘት ሰው ጥሩና የተከበረ ሊሆን ይገባዋል፣ የሚለውን ፍልስፍና በኔ አስተያየት ተራ የተጠየቀ (ሎጅክ) ልምምድ የሆነ ባዶ ነው። አዎ! ተራ የተጠየቀ ልምምድ ነው። የሰው ልጅን በጥቅሞቹ ሥርዓት አማካኝነት መንፈሱን እንደገና ማንሠራራት ይቻላል የሚለውን ፅንሰ ሃሣብ በኔ አስተያየት ባክል ሥልጣኔ የሰው ልጅን ይበልጥ ሰብአዊ ስለሚያደርገው ጦረኝነቱንና ደም አፍሣሽነቱን ይቀንሰዋል ካለው አባባል ጋር የሚመሳሰል ነው። የባክል ክርክር በተጠየቅ ሕግ በጥሩ ሁኔታ የተቀመጠ መሆኑን አምንበታለሁ። ነገር ግን ሰው በሥርዓቶችና በረቂቅ ድምዳሜዎች ስለተቀረደደ እውነቱን ሆነ ብሎ ለማዛባት ዝግጁ ነው። ተጠየቁን እስካረጋገጠለት ጊዜ ድረስ በስሜት ሕዋሣቶቹ የተገነዘበውን መረጃ ለመካድ ዝግጁ ነው። ለዚህ ነው ይህን ምሣሌ ያነሣሁት። እስኪ ዙሪያችሁን ቃኙ፣ የሰው ልጆች የደም ጐርፍ ልክ እንደ ሻምፓኝ እየፈሰሰ ነው። ባክል የኖረበትን አሥራ ዘጠነኛውን ክፍለ ዘመን ለምሣሌ ተመልከቱት። ናፖሊዮን ቀዳሚውና ሁለተኛውን አስተውሉ። ዘላለማዊውን አንድነት፣ ሰሚን አሜሪካንን ተመልከቱት። የቱላይነው የሰውን ልጅ ሥልጣኔ ያለዘበው? ማንኛውም ሥልጣኔ የሰውን ልጅ ባለብዙ ዘርፍ ስሜታዊነቶች ከማጐልበት ውጭ ከቶ ምንም ሌላ ነገር አልሠራም። ሰው ደግሞ በዚህ ባለብዙ ዘርፍ ስሜታዊነቱ መዳበር የተነሣ በእልቂት ውስጥ ደስታ የሚያገኝበት ደረጃ ላይ ይደርሣል። ይህንን አውንም ደርሶበት እያየነው ነው። ዋንኞቹ ደም አፍሣሾች እጅግ የሰለጠኑ ሰዎች መሆናቸውን አስተውላችኋል? ከነዚህ ሰዎች አንዳር እነ አቲላስና እነአስቴክ አሪዞንስ ጨቅላ ሕፃናት ማለት ናቸው። እንደ አቲላ ወይም እንደ አስቴክ አሪዞን ገናና ያልሆኑት ግን ምናልባት በኛ መሀል ስለሚኖሩና ሁሌ ስለምናገኛቸው ሊሆን ይችላል። በማንኛውም መልኩ ሲለካ ሥልጣኔ የሰውን ልጅ ይበልጥ ደም ፈላጊ አደረገው ባይባልም አስከፊና ቀፋፊ ደም ጠም ግን አድርጐታል። ምክንያቱም በፊት በፊት ደም ማፍሰስን ፍትሐዊና አላስፈላጊ ያላቸውን የሚያስወግድበት ትክክለኛ መንገድ አድርጐ

ይቆጥርው ነበር። አሁን ግን ደም ማፍሰስን እንደአረመኔአዊነት እየተቆጠረ ነው። ነገር ግን ከመቼውም ጊዜ በላይ እያዘወተረ ነው። የቱ ነው የሚብሰው? ይሄን ለየራሳችሁ ወስኑ። ያልሰለጠኑት ደም ማፍሰስን እንደፍትህ ማግኛ በመቁጠር በድርጊታቸው ኮርተው በንፁህ ሕሊና ሲሞቱ የሰለጠንነው ደግሞ ደም ማፍሰስን እያወገዝን ግን ደግሞ ይበልጥ ደም እያፈሰሰን በሕሊናችንም ተሰቃይተን እንሞታለን። የትኛው ነው የባሰው? ለየራሳችሁ አስቡ። ለምሳሌ ከሮማ ታሪክ ብንወስድ ኪሊዮፓትራ በሴት ባሮቿ ጡቶች ላይ ከወርቅ የተሠራ አስፒሎችን መጠቅጠቅና በሥቃይ ሲጨነቁና ሲሸማቀቁ ማየት በጣም ያስደስታት ነበር ይባላል። ይሄ የሆነው በአረመኔአዊው ጊዜ ውስጥ ነው። ዛሬም ሰው ላይ አስፒል መሰካት የሚወዱ ሞልተዋል። የአሁን ዘመን ሰው ከአረመኔያዊው ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ነገሮችን በጥራት መማር ብንችልም በሕሊናና በሣይንስ አስተውሎትና አስተምህሮት ከመገዛት ግን በጣም የራቅን ነን። የሰው ልጅ መጥፎ ልማዶቹ ሙሉ በሙሉ እንደተወገዱለት ሚዛናዊነትና ሣይንስ ተፈጥሮውን እንደገና ሙሉ በሙሉ አስተምረው ወደጤነኛ ባህሪ እንደመሩት ባስተውሎትና በሣይንስ መመራት ይጀምራል ብላችሁ እንደምታምኑ ደፍሬ መናገር እችላለሁ። እዚህ ደረጃ ላይ ሊደርስ ሰው ሆነ በሉ ስህተት መሥራትና እልከኛነቱን በመተው ከጤናማ ፍላጐቶቹ ውጭ መሥራት እንደሚያቆም እርግጠኛ ናችሁ። ይሄ ብቻም አይደለም፤ ሣይንስ በራሱ የሰውን ልጅ በውስጡ ፍላጐትም ሆነ ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ አምሮቶች እንደሌሉትና ፈልጐም እንዳላገኛቸው በማስተማር ሰው ማለት እንደ ፒያኖ ቁለፍ ማለት እንደሆነ (ከፒያኖ ቁልፍ የተለየ እንዳልሆነ) ያስተምረዋል። ያለው ሰው ሣይሆን የተፈጥሮ ሕጐች ናቸው፤ እናም ሰው ያደረገውን ቢያደርግ በራሱ ፍላጐት ሣይሆን ልክ እንደፒያኖ ቁለፍ በተፈጥሮ ሕጐች ውስጥ የተመደበለትን ዜማ ማውጣት ብቻ ነው። እነዚህ የተፈጥሮ ሕግጋት እንደታወቁ የሰው ልጅ ለድርጊቶቹ በኃላፊነት መጠየቁ ስለሚቀርለት ሕይወት ከምንጊዜውም በላይ ትቀለዋለች። ከዚያ በኋላ ያለ ጥርጥር የሰው ልጅ ድርጊቶች በሙሉ እንደ ሎጋሪዝም ሰንጠረዥ እስከ መቶ ስምንት ሺህ በሚሣብ ተሰልተው

በሰንጠረዥ ይሰፍራሉ። ወይም በተሻለ ሁኔታ በጥሩ ቃላት የተዓሩ፡ ሁሉም ነገር በስሌት ተሠርቶና በፍፁምነት ተለይቶ ከሱ ውጭ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ወይ ጀብዱዎች በዓለም ውስጥ ሊኖሩ እንደማይችሉ የተገለፀበት ኢንሳይክሎፒዲያ ሊታተም ይችላል።

ከዚህ በኋላ (አሁን እናንተ ናችሁ የምትናገሩት) ሁሉም ነገር በሂሣባዊው ፍፁምነት ተሰልቶ የተቀመጠ ስለሆነ ለሁሉም ችግሮች የተዘጋጅ መልሶች ስላሉዋቸው ችግርነታቸውም ወዲያውኑ ስለሚጠፉ አዲስ ዓይነት የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ይመሠረታሉ። ከዚህ በኋላ የክሪስታል ቤተመንግሥት ይታነፃል። በዚህም የወርቃማው ዘመን ንጋት ይበሰራል። በወርቃማው ዘመን ውስጥም ግን የሰው ልጅ እንባ እስኪተናነቀው ድረስ እንደማይሰለቸው መናገር አይቻልም። (ይህን የምናገረው እኔ ነኝ) ምንም 'ንኳ ሁሉም ነገር በትክክል የተቀመጠ ቢሆንም ሁሉም ነገር ተዳምሮ ተቀንሶ በሂሣብ የተቀመጠ ከሆነ ሰው ምን ሊሠራ ይችላል ታዲያ? የምትሠሩት ጠፍቶ ስትሰላቹ የማታስቡት ጉድ አይኖርም። የወርቅ እስፒሎች ሰው ላይ የሚሰኩትም ከመሰላቸት የተነሣ ነው። ይሄ 'ንኳ ምንም ማለት አይደለም። መጥፎው ነገር (ይሄንንም የምናገረው እኔው ነኝ) እኔ እንደምፈራው በወርቅ እስፒሎቹም መወጋትም ሊያስደስቱን ይችሉ ይሆናል። ምክንያቱም ሰው ደደብ ነው። አሰገራሚ ደደብ ነው። ማለቴ የእውነት ደደብ ባይሆንም በሌላ በኩል ግን ጭራሽ ምሥጋና ቢስ ስለሆነ በመላው ዓለም ቢፈለግ እንደሱ አይገኝም። ለምሳሌ ድንገት ሣይታሰብ አንድ ወራዳ ቀልባሽ የሆነ ሰው ፊቱን የሀዘን ገፅታ አልብሶ በወደፊቱ ዓላማችን የሁለንተናዊ ሚዛሃዊነት ዘመን መሀል ድንገት ብድግ ብሎ ወገቡን በሁለት እጆቹ ይዞ «ወንድሞቼ! ይህንን ሎጋሪዝምና ምክንያታዊነት የሚባል ገለመሌ በእርግጫ ብለን ለምን እንደራሳችን ቂላ ቂል ፍላጐቶች መሠረት አንኖርም?» ብሎ ቢጠይቅ ወይም ቢያነሣሣ አይገርመኝም። ይህን ማለቱም ምንም አልነበረም። የሚያሳዝነው ግን ያለአንዳች ጥርጣሬ ተከታይ ማግኘቱ ነው። ሰው ሊፈጥረው እንደዛ ነውና! ልብ አድርጐ ሰው ይህን የሚያደርግበት

ምክንያት ምንድነው ተብሎ ቢባል 'ንኳ የሚያሳፍር ነው። እሱም ምንድነው ሰው ማንም ይሁን ሁሌም በየትም ሥፍራ በህሊናው ወይም ጥቅሙ በሚያስገድደው መሠረት ከሚሠራው ይልቅ የልቡን ምርጫ ይከተላል። ስለዚህም የራሱን ጥቅም የሚጐዳ ነገር ሊመርጥ ይችላል። እንዳውም አንዳንድ ጊዜ እንዲህ የማድረግ ግዴታ አለበትም እላለሁ። (ይህ የኔ ሀሣብ ነው) የአንድ ሰው የራሱ የሆነ ነፃና ያልተገደበ ምርጫ፣ አምሮቶች ምንም ያህል ሕገወጥ ቢሆኑም 'ንኳ፤ የአንድ ሰው ምርታና ምንም እንኳ እንደ እብድ ቢያስቆጥረውም፤ ለሱ እጅግ አስፈላጊ ነው። ሁላችንም ችላ የምንለውና በሣይንሣዊ ሠንጠረዦችን ውስጥ ቦታ የማንሰጠው ግን ደግሞ ሣይንሣዊ ንድፈ ሀሣቦችንና ሥርዓቶቻችንን በተከታታይ ዶጋ አመድ የሚያደርገው እሴት እሱ ነው። እንዳው ለመሆኑ ለምንድነው እነዚህ ብልህ ሰዎች ሰው ሊጣጣርለት የሚገባው ጤናማና መደበኛ ጉላጐቶቹን ብቻ ነው የሚሉት? ሁሉም ሰው የሚፈልገው ፍፁም የሆነ ነፃ ምርጫ ነው። በዚህ የተነሣ የትም ገደል ይግባ፤ ቁም ስቅል ይደርስበት 'ንጂ የሱ ምርጫ ነፃነቱ ነው። ስለዚህ ሁሉም ነገር የምርጫ ጉዳይ ከሆነ ደግሞ የዓለማችንን ዕጣ ፈንታ ሰይጣን ይወቀው።...

«ሃ! ሃ! ሃ! አንተ የፈለግከውን ብትልም ምርጫ የሚባል ነገር የለም። ዛሬ ሣይንስ የሰውን ልጅ አብጠርጥሮ ከመረዳቱ የተነሣ አምሮትና ነፃ ምርጫ ማለት ምን ማለት አንዳልሆነና ግን» ግን ለምን ትሰቃላችሁ?

አንድ አፍታ (የተከበራችሁ ሰዎች፣ አሁን ያላችሁትን እኔም ራሴ ልለው ነበር። ምርጫ ብሎ ነገር ምን ማለት እንደሆነ ሰይጣን ይወቅ ብዬ ልናገር ሰል ድንገት ሣይንስን ስላስታወስኩ ቃሉ ከንፈሬ ላይ ሞተ። እናንተም ይሄንን አጋጣሚ በመጠቀም መናገር ጀመራችሁ። በእርግጥ እነዚህ ሣይንቲስቶች የፍላጐታችንና የአምሮቶቻችን ምክንያት ምን እንደሆነ ከደረሱበት የሚገዙበትን ሕግ እና እነሱንም እንዴት በስፋት ማስተማር እንደሚቻል በዚህኛውና በዚያኛው ፍላጐታቸው ላይ የሚለያዩበት ዓላማ ምን እንደሆነ ወዘተ...ሂሣባዊ ፎርሙላ ካወጡለት ሰው

ምናልባት የአምሮት ስሜቱን ሊያቆም እንደሚችል በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ስለምን ቢባል በተቀመጠለት የሂሣባዊ ስሌት ፎርሙላ መሠረት ማን ነው ከቶ ምኞት ሊኖረው የሚችለው? ይህም ብቻ አይደለም። በዚህ ስሌት (ቀመር) መሠረት ከተሄደ ሰው ከሰውነት ወደፒያኖ ቁልፍነት ወይም መሰል ነገር ይቀየራል። ሰው ያለፍላጐት፤ ሰው ያለነፃ ምርጫና የመምረጥ መብት ሲኑት የሚጮህ የፒያኖ ቁለፍነት ውጭ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ምን ይመሰላችኋል? እስኪ ሊሆን የሚችለውን ነገር እናስብ፤ ሊሆን ይችላል ወይስ ሊሆን አይችልም?

«ደህና!» ትላላችሁ እናንተ «ብዙዎቻችን ስንመለከተው ፍላጐቶቻችን ለኛ ይጠቅማሉ ብለን ካሰብናቸው የተሳሳቱ ሃሣቦች የሚፈልቁ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ በደደብነታችን የተነሣ ምንም ትርጉም ከሌለው ነገር ውስጥ ለኛ ጠቃሚ እየመሰለን ፍሙም ትርጉም የለሽ የሆነ ነገር እንፈልጋለን።» በጣም ጥሩ ይሄ ሁሉ ተብራርቶ ወረቀት ላይ ሊሰፍር (የለው ልጅ ፍላጐቶችን ከሀ አስከ ፐ በወረቀት ላይ ማስፈር ይቻላል። ምክንያቱም የለው ልጅ ሌሎች የተፈጥሮ ሕጐችን እየቆየ ሊደርስባቸው አይችልም ብሎ ማሰብ ስድነትና ምክንያት አልባነት ስለሚሆን) ፍላጐቶች የምንላቸው ነገሮች አይኖሩም። ከዕለታት አንድ ቀን ፍላጐቶቻችን ከምክንያታዊነት ጋር ሙሉ በሙሉ ሊዛመዱ መመኘት ትተን ማመዛዘን እንጀምራለን። ምክንያቱም ህሊናችንን ሳንስት ጥቅም የለሽ ነገር ልንመኝ አንችልምና። በዚህም የተነሣ እያወቅን ራሣችንን ለመጉዳት በሕሊናችን ላይ አንነሳም። እናም አንድ ቀን ፍላጐቶችና ምክንያቶች ተሰልተው ልክ እንደ ሂሣባዊ ሰንጠረዥ የአንድ የሆነ ፍላጐት መነሻ ምክንያቱ ምን ሊሆን እንደሚችል በተዛምዶ በሂሣብ ሠንጠረዡ ላይ ይቀርብልናል። እናም በዚህ ሂሣብ ስሌትና ማሰተማመኛ መሠረት ለምሣሌ አንድ ሰውን እያየሁ አፍንጫዩን በአውራ ጣቴ ብነካ የዚህ ምክንያት በሰውየው ላይ አፍንጫዩን መንካቴን ማቆም ስለማልችል በአውራ ጣቴ አፍንጫዩን መንካቴ ግድ መሆኑ ይነግረኛል። ታዲያ እንዲህ ከሆነ በተለይ ምሁር ከሆንኩና የዩኒቨርሰቲ ዲግሪ የወሰድኩ ከሆነ ምን ነፃነት ቀረኝ ማለት ነው? እንዲህ

ከሆነግ በእርግጥ በሚቀጥሉት ሰላሣ ዓመታት የሚኖረኝን ሕይወት በሂሣብ ሰንጠረዥ እየተረዳሁ ከወዲሁ አስላዋለሁ። በአጭሩ ይህ እውን መሆን ከቻለ የምንሠራው ነገር አይኖርም። ፈለግነው አልፈለግነው ሁሉንም ነገር አስቀድመን እንረዳለን። መነሻውንም ውጤቱንም። ይህም ግለት በአጠቃላይ አነጋገር ሁላችንም ተፈጥሮ በአንድ ወቅትና ሁኔታ ላይ የሆነ ነገር እንድናደርግለት ፍቃዳችንን ልትጠየቅ የምትችልበት ምክንያት እንደማይኖር ሳናቋርጥ ማሰብ አለብን። በሌላ አነጋገር ተፈጥሮን እኛ እንደምናስባት ሣይሆን ራሷ ሆና እንዳለችው መቀበል ይኖርብናል። ደግሞም እምነታችንን ወደ ሂሣብ ሠንጠረዣችንና የአውራ ጣት ደንቦችና ወይ የብልጭጥ ልጆችን ጨምሮ ካደረግን ያለውን ሁሉ ከመቀበል ውጭ ሌላ ምንም ልናደርግ አንችልም። አለበለዚያ የብልጭጥ ሙከራውን እኛ ተቀብለነው አልተቀበልነው ራሱ በራሱ ይመጣል።...

ይሄ ትክክል ነበር። ነገር ግን አንድ ችግር አለ። ከቡራንና ከቡራት! ስለፍልስፍናዬ ይቅርታ አድርጉልኝ። ደግሞም አርባ ዓመታት ሙሉ ጨለማ ውስጥ መኖራን አትርሱ። ስለዚህ የምርታናዬን እንደልቤ እንድናገር ፍቀዱልኝ። አያችሁ ከቡራን :- ህሊና እጅግ በጣም ጥሩ ነው። እዚህ ላይ ጥርጥር የለውም። ይሁን 'ንጂ ሕሊና ደግሞ የሚያረካው የሰውን የማሰብ ችሎታ ብቻ ነው።

ሰው ያሰኘውን የመፈፀም ችሎታው ከአእምሮ አስተውሎቱ ጋር ተዳምሮ የሙሉ ሕይወት ነፀብራቅ ነው። ምንም 'ንኳ ሕይወታችን እንደዚህ ቢገለፅም ብዙ ጊዜ ግን ስናየው አሳዛኝ መልክ አለው። ሕይወት ሕይወት ንጂ የቁጥር ስሌት ውጤት አይደለም።

በበኩሌ መኖር የምፈልገው ሁሉንም የሰውነት ክፍሎቼንና ስሜቶቼን አርክቼ ነው። ማለቴ የጠቅላላው እኔነቴ አንድ ሃያኛ የሆነውን ሕሊና ብቻ መከተል የለብኝም። ሕሊና ምን ያውቃል? ሕሊና የሚያውቀው ሊያውቅ የቻለውን ብቻ ነው። (ህሊና ሊደርስባቸው የማይችሉ ነገሮች መኖራቸው ግልፅ ነው። ለምን በግልፅ አናምንም?) የሰው ተፈጥሮ በውስጡ ያለውን

ሁሉ እየተጠቀመ ታውቆትና ሳይታወቀው ይቀጥላል። (ምንም 'ንኳ እግረ መንገዱን ብዙ አሳፋሪ ነገሮች ቢሠራም።) የተከበራችሁ ሰዎች! በሀዘን እንደምትመለከቱኝ ይሰማኛል። ጭንቅላቱ የዳበረው የወደፊቱ ሰው በምንም አይነት ለሱ «እውነተኛ ጥቅም» የሌለው ነገር ሆነ ብሎ ሊመኝ አይችልም እያላችሁ ደጋግማችሁ እየተከራከራችሁኝ ነው። ምክንያቱም ሂሣብ ነውና አላችሁ።

እኔም እስማማለሁ። እንዳላችሁትም ሂሣብ ነው። ነገር ግን ለመቶኛ ጊዜ ደግሜ ልናገረው የምፈልገው አንድ ጉዳይ አለ። ሰው የራሱን ምርጫ የመወሰን መብቱን ለመጠቀምና ለሌሎች እንዲመኝ ሊያስገድዱት ከሚፈልጉት ውጪ ለመመኘት ሲል ብቻ ጭኺ፣ ደደብና በጣም አሳፋሪ የሆነ ነገር ሊፈልግ ይችላል። ለሰው ትልቁ ቁም ነገር የራሱ ስብዕናና ግላዊነት ነው። እነዚህን ለማግኘት ደግሞ የተረጋገጠላቸውንና የታመነባቸውን ጠንካራ ምክንያቶች ገደል ግቡ ይላል። ፍላጐት ከፈለገ አንዳንድ ጊዜ ከሕሊናዊ ምክንያታዊነት ጋር ሊጣጣም ይችላል። ይሄ ሊሆን የሚችለው በተለይ ሰዎች በሚዛናዊነት እስከተመኙ ድረስ ነው። እንዲህ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በጣም ያስመሰግናል። ይሁን 'ንጂ ዘወትር በተደጋጋሚ ፍላጐት አብዛኛውን ጊዜ ከህሊና ጋር ይጋጫል። አይጣጣምም።

የተከበራችሁ ሰዎች! እስኪ ሰውን ደደብ እንዳልሆነ አድርገን እናስብ። (ሰው ከሱ ሌላ ብልህ የሆነ ማን አለ? የሚል ጥያቄ የምናነሣ ከሆነ ሰው ደደብ ላይባል ይቻላል።) ጥሩ፤ ሰው ደደብ ካልሆነ እንግዲያውስ ጋጠወጥ፤ ውለታቢስ እንዳውም እኔ ሰውን በትክክል የሚገልፀው ፍቺ እንደዚህ ይምስለኛል። «ሰው በሁለት እግሩ የሚሄድ ውለታቢስ ፍጡር ነው።» የሱ ድክመት ይሄ ብቻ አይደለም። ትልቁ ችግር ያላቋረጠ የሞራል ስሜት ማጣቱ ነው። የሞራል ስሜት ስለሌለው ደግሞ የጥሩ ነገር ስሜትም የለውም። ምክንያቱም የጥሩ ስሜት መጥፋት ከሞራል ስሜት መጥፋት ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ድሮ ጀምሮ የታወቀ ነው። እስኪ የዓለምን ታሪክ አገላብጡ ምን ተመለከታችሁ? ገናናነት? አዎ፤ ምናልባትመ ገናናነት።

በዚህ አረገድ ኮላሰሰ አፍ ሮድስ በምሣሌነት ሊጠቀስ አይችልም 'ንዴ አንዳንድ ሰዎች በሰው የተሠራ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ተፈጥሮ ራሷ የሠራችው ነው ይላሉ። ግርማ ምገስ? አዎ! እሱም ሊሆን ይችላል። ወታደራዊና የሲቪል ዩኒፎርሞችን ማስተዋል ይበቃል። ሁላችንም በላያችን ላይ ልብስ ስንደርብ በሚኖረን ግርማ እንደነቃለን። ማንም ታሪክ ፀሐፊ ይህንን አይስተውም። መሰላቸት? አዎ! ሰልቹነት ይምስለኛል። ሰዎች ሲዋጉ ነው የኖሩት አሁንም ይዋጋሉ። በፊትም ተዋግተዋል። ወደፊትም ይዋጋሉ። ይሄንን የሚያደርጉት ከመሰላቸት የተነሣ ነው። በአጭሩ ስለዓለም ታሪክ ጭንቅላታችሁ ላይ የመጣውን ሁሉ መናገር ትችላላችሁ። አንድ ነገር ብቻ ልትመለከሩ አትችሉም። ይኸውም የሆነው ሁሉ ትርጉም ያለው ነው ብላችሁ!! እንዲህ ብትሉ የመጀመሪያው ቃል ያንቃችኋል። ደግሞም እንዲህ ዓይነቱ አስግራሚ ነገር በየደቂቃው ያጋጥመናል። በሕይወት ዘመናችን ዋንኛ ዓላማቸው ሕይወታቸውን ትርጉምና ምራል ባለው ሁኔታ በመምራት ለጐረቤቶቻቸው የፀሐይ ብርሃን ሆነው ለመኖር የሚፈልጉ ብልሆችና የሰውን ልጅ አፍቃሪዎች ብቅ ብቅ ይላሉ። ዋንኛ ዓላማቸው ሰው ምራልና ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ በዚህች ዓለም ላይ መኖር እንደሚችል ለማረጋገጥ ነው። ውጤቱስ? እንደምናየው እነዚህ የእውነት ሰዎች ይፍጠን ወይም ይዘግይ እንኪ ወደሕይወት ፍፃሜያቸው ገደማ ጥቂት አሳፋሪ ድርጊቶችን (አንዳንድ ጊዜማ በባህሪያቸው እጅግ ወራዳ ተግባሮች ሊሆኑ ይችላሉ) ፈፅመው ስለሚገኙ ለራሣቸውም አይታመኑም። አሁን ይህን ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ ሰው በእንደዚህ ዓይነት አስገራሚ ባህሪ የተሞላ መሆኑን እያያችሁ ከቶ ምን ልትጠብቁበት ትችላላችሁ? ለምን? ብትፈልጉ ለሰው ማንኛውንም ምድራዊ በረከት ስጡት፤ በደስታ ባህር አጥለቅልቁት። ካፍ እስከገደፉ። ያለአንዳች ሥራ ተኝቶ እንዲበላ የሚያስችለው የኢኮኖሚ ብልፅግና አጐናፅፉት። ብቸኛ ሥራው ኪኩን እየገመጠ የዓለም ታሪክ እንዲቀጥል ብቻ ይኖር ዘንድ አመቻቹለት።

ሰው እንደዚህም ሆኖለት ከተፈጥሮው ውለታቢስነቱ የተነሣ ብቻ እናንተን በግል ለመጉደት ካለው ፍላጐት በመነሣት ከጀርባችሁ ተንኰል

ይሠራበችኋል።ይህን ለማድረግ ተገኩል ለመፈፀም ሲል ብቻ ኪኩንም ጠላውንም ቢያጣ ግድ አይሰጠውም። ዋናው ፍላጐቱ ባለው መልካም ሁኔታ ውስጥ የሱን አጥፊ የቅብጠት ፍላጐት ለመደባለቅ ነው። ይህ የሱ ቅብጠት ሕልም ዋና ተልኮ እሱ ማለት የተፈጥሮ ሕጐች የፈለጉትን ዚማ የሚያጫውቱበት የፒያኖ ቁልፍ እንዳልሆንና እሱ ማለት የራሱን ዕጣ ፈንታ ራሱ መወሰን የሚችል ሰው መሆኑን ለማረጋገጥ ሲል ነው። ይሄም ብቻ አይደለም ሌላው ቀርቶ እሱ ማለት የፒያኖ ቁልፍ 'ንጂ ሌላ ምንም ማለት ሊሆን እንደማይችል በተፈጥሮ ሣይንስና በሂሣብ ሰሌት ሊረጋገጥ ቢችል 'ንኳ አምኖ ከመቀበል ይልቅ ሆነ ብሎ ያለምክንያት ውለታ ቢስ ተፈጥሮውን ለማርካት ሲል ሁሉንም ሕጐች ይፃረራል። ሌላ መፍትሔ ካላገኘ ውድመትና ብጥብጥን ያቅዳል። ሁሉንም ዓይነት ሥቃዬች ይፈጥራል። በዚህም ዓላማውን ያሳካል። መላ ዓለምን እርግማን ያመጣበታል። ሰው እንጂ የፒያኖ ቁልፍ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ሲል ምድርን ሥቃይ ያላብሳታል። በእርግጥ ይሄም ባህሪ ሊሆን እንደሚችል አስቀድሞ ሊታወቅና በሂሣብ ሰንጠረዡ ውስጥም ብጥብጥ፣ ጭለምተኝነት፣ እርግማን ወዘተ ሁሉ እንዴት ሊመጡ እንደሚችሉ አውቆ ሕሊና የበላይ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል እያላችሁ ነው። ደህና እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ሰው የራሱን ቅሌታም ፍላጐት ለማርካት ሲል ብቻ ከገዛ ሕሊናው ለመገላገል ያብዳል። እኔ እንደሚመስለኝ ይሄ ነው የሚሆነው። እመኑኝ፣ ለኔ እንደሚመስለኝ የሰው ልጅ ሕይወት አጠቃላይ ትርጉም ሲታይ የመኖሩ ዋንኛ ዓላማ እሱ ማለት ሰው እንጂ የፒያኖ ቁልፍ አለመሆኑን በየደቂቃው ማረጋገጥ ነው። ይህ አቋሙ አካላዊ ሥቃይ ቢያመጣበት ወይም ደግሞ ጭራሽ በሥልጣኔ ላይ መነሣት ሆኖ ቢታይበት እንኳ አይበገርም። ደግነቱ አሁን ያለንበት ጊዜ የፍላጐቶቻችን ምንጭ ገና በሎጋሪዝም ሰንጠረቹ ያልሰፈረ፣ ለሰይጣን የተተወ በመሆኑ ደስታችን ገደብ የለውም።

ሰውየው ምንነካው? ማንም ያንተን ነፃ ፍላጐት ሰመንጠቅ ፍላጐት የለውም። ዋናው የተፈለገው ነገር ምኞትህ ከመደበኛ ፍላጐቶችህ ማለትም ከተፈጥሮ ሕጐችና ከሂሣብ ስሌት ጋር ይዛመድ ነው የተባልከው እያላችሁ በቁጣ ተናግራችሁኝ አይደል? ግን ምን ነካችሁ ልበል፣ ሁሉንም ነገር በሂሣብ ሰንጠረዥ ላይ ሰፍሮ ትልቁ ነጥብ ሁለትና ሁለት አራት መሆኑ ብቻ ከሆነ ምን ዓይነት ነፃ ፍላጐት ሊኖር ነው? ሁለትና ሁለት እኔ ወደድኩም አልወደድኩም እራት መሆኑ አይቀርም። እርግጠኛ ነኝ ነፃ ፍላጐት ማለት ደግሞ ይሄ አይደለም።

ክቡራንና ክቡራት ምንም ነገኣ ቀልዶቹ ደስ ባይሉም እየቀለድኩ ነው። ደግሞም ሁሉንም ነገር ቀልድ አድርጋችሁ አትውሰዱት የምቀልደው በሀዘን እንደሆነስ በምን ታውቃላችሁ? ወንድሞቼ እኔ በሁሉም ዓይነት ጥያቄዎች ተጨንቂያለሁ። እባካችሁ ለኔ ስትሉ መልሱልኝ። ለምሳሌ የሰው ልጅ ከጥንት ልማዶቹ እንዲገላገልና ራሱን ከሣይንስና ዘመናዊነት ጋር እንዲያራምድ ትፈልጋላችሁ። ግን ሰው እንደዛ ሆኖ ለመታደስ መቻል ብቻ ሣይሆን የግድ መታደስ እንዳለበት በምን አወቃችሁ? የሰው ልጅ ፍላጐት ሊስተካከል ይገባል የሚል ድምዳሜ ላይ ያደረሣችሁስ ምንድን ነው? ባጭሩ እንዲህ ዓይነቱ ተሃድሶ ለሰው ልጅ የሚጠቅም ስለመሆኑ እንዴት ልታውቁ ትችላላችሁ? ደግሞስ ሰው በሕሊና አስተውሎትና በሂሣብ ስሌት ድምዳሜዎች የተቀመጡለትን እውነተኛ ጥቅሞች ሣይፃረር መጓዝ እንደሚጠቅመውና ይሄም ሁለንተናዊ ሕግ ሆኖ እንዲሠራ ለሰው ልጅ ተገቢ ስለመሆኑ እንዴት እርግጠኛ ልትሆኑ ቻላችሁ? ለጊዜው ይሄ የናንተ ተግባር ላይ ያልዋለ ገና አስተሳሰብ ነው። እንበል ይሄ የተጠየቀ ሕግ ነው። ግን ይህ የሰው ልጅ ሕግም ሊሆን እንደሚችል እንዴት ታውቃላችሁ? መቼም እብድ ነህ እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ራሴን ግልፅ ላድርግላችሁ፣ ሰው እድሜ ልኩን ወደ አንድ ግብ እንዲጣጣርና ሁልጊዜም ሳያቋርጥ የትም ይውሰደው የትም መንገዶችን የማጥራት ኃላፊነት የወደቀበት ፈጣሪ እንስሳ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ሰው የማፈንገጥ ፍላጐቱ የሚፈታተነው መንገዱን እንዲያፀዳ የተፈረደበት መሆኑን ስለሚያውቅ ቢሆን አይገርመኝም። ምናልባትም ምንም እንኳ የተግባር ሰው ደደብ ቢሆንም አፈጣጠሩ፤ እሱም ግን መንገዱ ወዴትም እንደማያወጣ ቢገለፅለትም ቁም ነገሩ ወዴት እንደሚያወጣ ሣይሆን ብቻ ወደሆነ አቅጣጫ መውሰዱ ላይ ነው በማለት ይቀጥላል። ሰው መፍጠርና መንገዶችን ማፅዳት እንደሚያስደስተው የማይታበል ሃቅ ነው። ለምንድነው ውድመትን በስሜት ሊያፈቅር የቻለው? ይሄን ንገሩኝ። የማትቃወሙኝ ከሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ ራሴ የምለውን ትንሽ ነጥብ አለኝ። ሰው ውድመትንና ሁከትን የሚያፈቅረው (አንዳንድ ጊዜማ ያለቅጥ ነው የሚያፈቅረው ይህ የማይታበል ሃቅ ነው።) በደመነፍሱ ውስጥ ወደሚሄድበት ግብ መድረሱንና እየገነባ ያለውን ሕንፃ ማጠናቀቁ እያስፈራው አይደለምን? ምን አልባትም ሕንፃውን የሚወደው ከርቀት እንጂ በምንም ዓይነት በቅርብ እንዳልሆነ በምን ታውቃላችሁ? ምናልባትም እሱን የሚያስደስተው ሕንፃውን መገንባት እንጂ በውስጡ አለመኖር ቢሆንስ? ሠርቶ ከመኖር ይልቅ ለቤት እንስሳቶቹ ለጉንዳኖች፣ ለበጐች ወዘተ መተውን ይመርጣል። የጉንዳኖች እንኳ ለየት ያለ ነው። እነሱ እንደዚህ ዓይነት ለዘለዓለም የማይፈርስ ሕንፃ አላቸው፤ ኩይሣ!

ጐበዞቹ ጉንዳኖች ሕንፃውን (ኩይሣውን) መገንባት ጀምረው ከኩይሣው ፍፃሜ ጋር አብረው ይጠናቀቃሉ። ይሄም ለነሱ ቻይነትና ፅናት ትልቅ ማሳያ ነው። ሰው ግን እዚህ ግባ የማይባል ቀላል ፍጡር በመሆኑ ልክ እንደጸጋ ተጫዋች ዋንኛ የሚያስደስተው ነገር የማሸነፍ ዓላማውን ሂደት መጫወት 'ንጂ ራሱ ዓላማውን አይደለም። ደግሞስ ማን ያውቃል (ማንም ሰው በፍፁም እርግጠኛነት ሊናገር አይችልም) ምናልባት መላው የሰው ልጅ በዚህች ምድር ለማግኘት የሚጥረው ዋንኛ ዓላማ ያላቋረጠ የማግኘት ሂደት መፈፀም (በሌላ አነጋገር ራሷ ሕይወት ናት) እንጂ ሊቀዳጀው የሚፈልገው ግብ አይደለም። ግብ ማለት ምንም ማብራሪያ ሳያስፈልገው ሁለት ሲደመር ሁለት አራት ማለትም ፎርሙላ ነው ግን

ደግሞ ሁለትና ሁለት አራት ሕይወት አይደለም። የተከበራችሁ ሰዎች እሱ የሞት መጀመሪያ ነው። የሰው ልጅ ሁለት ሲደመር ሁለት አራትን ሁልጊዜ እንደፈራ ነው። እኔም እራሴ አሁን ፈርቼዋለሁ። እንበል ሰው ሁለት ሲደመር ሁለት አራትን ለማግኘት ከመፈለግ ውጭ ምንም አይሠራም ለዚህም ሲል ውቅያኖሶችን ተሻግሮ ሕይወቱን መሰዋዕት አድርጉ ይነሣል። ነገር ግን በዚህ ፍለጋው የሚፈልገውን ለማግኘት ወይም እንዲሳካለት ይፈራል። አዎ! የምሩን የሚፈራ ይመስላል። ምክንያቱም የፈለገውን ሙሉ በሙሉ ካገኘ ሌላ የሚፈልገው ነገር ላይኖር ነው። የቀን ሠራተኞች ሥራቸውን ሲጨርሱ ቢያንስ የቀን ምንዳቸውን ተቀብለው ወደ መጠጥ ቤት በመሄድ በበነጋታው ራሳቸውን እሥር ቤት ሊያገኙት ይችላሉ። ይሄ ደግሞ የሣምንት ሥራ ማለት ነው። ሰው ግን ወዴት ይሄዳል? በሁሉም አጋጣሚዎች ሰው ከእንደዚህ ዓይነት ዓላማዎቹ አንዱን ሲቀዳጅ የሆነ መደነጋገር ይታይበታል። ከመቀዳጀቱ ይልቅ የመቀዳጀት ሂደቱን ያፈቅረዋል። ይህ ደግሞ እናንተም እንደምትስማሙበት እርግጠኛ ነኝ፤ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው። በአንድ ቃል ሰው ኮሚክ ፍጡር ነው። የሆነ ቀልድ ውስጡ የተደበቀ ይመስለኛል። ሁለት ሲደመር ሁለት አራት ምንም ሊያደርጉት የማይቻል ጉዳይ ነው። በኔ ደካማ አመለካከት ሁለት ሲደመር ሁለት አራት ከስድነት በስተቀር ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም። ሁለት ሲደመር ሁለት አራት ማለት መንገድህ ላይ ወገቡን በእጆቹ ይዞ መንገድህ ዘግቶ የሚተፋብህ ቀልደኛ ማለት ነው። ልብ አድርጉ፣ ሁለት ሲደመር ሁለት ይሆናል አራት እጅግ በጣም ጥሩ ነገር እንደሆነ እኔም እስማማለሁ። ግን ለሁሉም ነገር ተገቢውን ትኩረት ከሰጠን ሁለት ሲደመር ሁለት ይሆናል አምስትም አንዳንድ ጊዜ በጣም ደስ የሚል ጥሩ ነገር ይመስለኛል።

ለሰው ልጅ ጥቅሙ መደበኛና በጉ የሆነ ባጭሩ ብልፅግና ነው ብላችሁ በቁርጠኛነትና በሙሉ ልብ ልታምኑ የቻላችሁት ለምንድን ነው? ሰው ከብልፅግና ሌላ ሊያፈቅር አይችልም? ምናልባት የብልፅግናን ያክል ሥቃይ ያስደሰተው እንደሆነስ? ደግሞም አንዳንድ ጊዜ ሥቃይን በጣም ያፈቅራል። በስሜት ነው የሚያፈቅረው። ይህ የሚታበል ሃቅ አይደለም።

ይሄን ለግረጋገጥ ደግሞ የዓለምን ታሪክ ማገላበጥ አያስፈልግም። አንተ ሰው ከሆንክና እንደሰው የኖርክ ከሆንክ ራስህን ልትጠይቅ ትችላለህ። በኔ የግል አመለካከት ግን እንዳውም ብልፅግናን ማፍቀር በመጠኑ ብልግና ይምስለኛል። ደግም ይሁን መጥፎ አንዳንድ ጊዜ እታዎችን መሰባበርም በጣም አስደሳች ነው። ስለስታይ ወይም ስለደስታ መነሻ ምክንያቶችን ላብራራላችሁ አይደለም። የምለምናችሁ እኔም አምሮቶቹ እንዲፈቀዱልኝና የፈለግኩዋቸውም ጊዜ እንዳገኛቸው ዋስትና እንዲሰጠኝ ነው። በቀላል ቀልዶች ውስጥ ለምሳሌ ሥቃይ አይፈቀድም። ሥቃይ ጥርጣሬ ነው። ሥቃይ ተቃርኖ ነው። በክርስቲያል ቤተመንግሥት ውስጥ ደግሞ ይህ ከቶም የሚታሰብ አይደለም። ከተጠራጠሩትማ ምኑን ክርስቲያል ቤተመንግሥት ሆነው? እንዲህም ሆኖ ታዲያ ሰው ከቶም ቢሆን ሥቃይን ማለትም ውድመትንና ሁከትን ያወግዛል ብዬ አላምንም። አ! ሥቃይ! የጥልቅ ንቃተ ሕሊና ግንዛቤ ብቸኛ ምክንያት። መጀመሪያ ላይ በጥልቀት መገንዘብ (ማወቅ) የሰው ልጅ ታላቅ አለመታደል ነው በማለት መከራከሬን አልረሣውም። ይሁን 'ንጂ ሰው ማወቁን፤ መገንዘቡን ያለመጠን ከማፍቀሩ የተነሣ በምንምና በማንም ዓይነት እርካታ ሊተካው አይፈልግም። ንቃተ ሕሊና ለምሳሌ ከሁለትና ሁለት ያለመጠን የራቀ ነው። ከሁለትና ሁለት በኋላ ምንም የሚቀርህ የምትማረው ነገር አይኖርም። ያለህ አማራጭ አምስቱን የሰሜት ሕዋሳቶችህን ዘግተህ በማሰላሰል መቦዘዝ ብቻ ነው።

ዘላለማዊ በሆነው መቼም በማይፈርሰው በምንም መንገድ ምላሳችሁን ልታወጡበት በማትችሉት ክርስቲያል ፓላስ ታምናላችሁ። እኔ ኦናልባትም ይህ ቤተመንግሥት በክርስቲያል በመሠራቱና ለዘለዓለም የማይፈርስ በመሆኑ እንዲሁም በድብቅ እንኳ ምላሴን ላወጣበት ስለማልችል እፈራዋለሁ። አያችሁ ቤተመንግሥት ከመሆን ፈንታ የዶሮ ቤት ቢሆን ኖሮና ቢዘንብ በዝናብ እንዳልርስ በእምብርክክ ተንፏቅቄ ገብቼ ልጠለልበት እችላለሁ። ከዝናብ ስላስጠለለኝ ብቻ ግን ከውለታው የተነሣ የዶሮ ቤቱን ቤተመንግሥት እንደሆነ አድርጌ ልቀበል አልችልም። በፍፁም አላደርገውም። እናንተ ግን እየሣቃችሁ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታው የዶሮ

ቤትም ቤተመንግሥት ነው ትሉኛላችሁ። የመኖር ብቸኛ ዓላማ በገነባ አለመበስበስ ከሆነ በእርግጥ አዎ እላችኋለሁ። ግን የሕይወት ዓላማ ይህ ብቻ አይደለም። አንድ ሰው መኖር ካለበት ቤተመንግሥት ውስጥ ነው መኖር አለበት የሚል ዓላማ ጭንቅላቴ ውስጥ ቢገባስ ምን ይደረጋል? ይህ የኔ ምርጫ ነው፤ የኔ ፍላጐት፤ ይሄንን ልታስለውጡኝ የምትችሉት ፍላጐቴን መለወጥ ስትችሉ ብቻ ነው። አድርጉታ እንግዲህ!? በጣም የተሻለ ነገር አሳዩኝ፣ ሌላ ሐሣብ ሰጡኝ። ይህን እስክትሰጡኝ ድረስ ግን የዶሮ ቤትን በቤተመንግሥት ምትክ አልቀበልም። የከርስቲያል ቤተመንግሥት ምናልባት የሥራ ፈት ሕልም ሊሆን ይችላል። የተፈጥሮን ሕጐች ሁሉ የሚፃረርም ሊሆን ይችላል። አንዲህ ዓይነቱ ሐሣብ መጀመሪያውኑ የመጣብኝ በደደብነት የተነሣ ሊሆን ይችላል። ከኔ ትውልድ የወረስኩት የሆነ ያረጀና ያፈጀ ቀበጥ ልማድ መሆን ይችላል።

ነገር ግን እስከፈለኩት ድረስ የተፈጥሮ ሕጐችን ተፃረረ አልተፃረረ እኔ ምን ጨነቀኝ? ቤተ መንግሥቱ በኔ ፍላጐቶች ውስጥ እሰካለና እስከቆየ ድረስ ምንም ግድ አይሰጠኝም። መቼም እየላቃችሁብኝ አይደለም? ሣቃችሁ?! እንደፈለጋችሁ ተንከትክቱ። ማንኛውንም ፈዛችሁን ልቋቋም ዝግጁ ነኝ። እስከመጨረሻው ድረስ ግን እየራበኝ ጠግቤአለሁ አልላችሁም። እኔ እራሴን እስከማውቀው ድረስ በመቻቻል አልረካም። በተፈጥሮ ሕጐች ውስጥና በእውን ስለሚኖር ብቻ ዘላለማዊና ተደጋጋሚ ለሆነ ዜሮ አልደራደርም። ፍላጐቶቼን፣ አምሮቴን ለማካካስ በቤተመንግሥቱ ምትክ ሌላ ህንፃ ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ዓመታት እንድኖርበት ቢሰጠኝና ለክፉም ለደጉም የጥርስ ሐኪሙ ዶክተር ማሊፎ አጠገቤ እንዲሆኑ ቢደረግ እንኳ አልቀበልም። እናንተን ልከተል የምችለው ፍላጐቴን ስታጠፉ፣ ሀሣቤን ስታስለውጡኝና የተሻለ ነገር ስታሣዩኝ ብቻ ነው። ምናልባት ካንተ ጋር ይህን ያህል መነጋገር አስፈላጊ አይደለም ልትሉ እንደምትችሉ ይሰማኛል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ እኔም እንደናንተ ልል እችላለሁ። ልብ አድርጉ፣ ይሄን ከምሬ ነው የምወያየው። ለኔ ትርጉም መስጠት ከከበዳችሁ ያለናንተ አደርገዋል።

በሕይወት እስካለሁና ፍላጐቱም አብሮ እስካለ ድረስ እናንተ የወሰናችሁልኝን ሞዴል ሕንፃ ለመሥራት አንዲት ትንሽ ጡብ ከማመጣ ይልቅ ቀኝ እጁ ተቀንጥሶ ቢወድቅ ይሻለኛል። ትንሽ ቀደም ብዬ ምላሴን ላወጣበት ስለማይፈቀድልኝ ብቻ የክርስቲያል ቤተመንግሥቱን እንደማልቀበል ተናግሬ ነበር። ያንን ያልኩት ምላሴን ማውጣት ስለሚያስደስተኝ አይደለም። ምናልባት እኔ የተቃወምኩት ካሉን ሕንፃዎች መካከል ምላሳችንን ልናወጣ የማንችልባቸው ኖረው ስለማያውቁ ነው። እንዳውም በተቃራኒው ምላሴን እንዳወጣባቸው የሚያስመኙኝ ነገሮች ሣይታይባቸው በትክክል ከተሠሩ ለዚህ ምሥጋና ስል ምላሴን ቆርጬ ብጥለው ደስ ይለኛል። ነገሮች በዚህ መልክ ተሠሩ አልተሠሩ አንድ ሰው በሞዴል ሕንፃዎች ረካ አልረካ የኔ ኃላፊነት አይደለም። እንዲህ ከሆነ ታዲያ ለምን እንዲህ ዓይነት ፍላጐት ሊኖረኝ ቻለ?

በእርግጥ የኔ አፈጣጠር ለማታለል ስለሆነ ብቻ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ እንድደርስ አይደለም። የኔ ዓላማ ይሄ ብቻ ነው እንዴ? አላምንበትም።

ግን! ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ተደብቀው የሚኖሩ ሰዎች ምን ጊዜም ሊታገዱ ይገባል። አርባ ዓመት ሙሉ ጉድጓዳቸው ውስጥ ሲኖሩ አንዲት ቃል ላይተነፍሱ ይችላሉ። ነገር ግን የቀን ብርሃን እንዳዩ ወዲያውኑ መለፍለፍ ይጀምራሉ። ማውራት፣ ማውራት፣ ማውራት...

XII

እና የተከበራችሁ ሰዎች፣ በመጨረሻም አንድም ነገር አለመሥራት ጥሩ ነው አላለሁ። ዝም ብሎ ማወቅ ይሻላል። ስለዚህ ሶስት ጭብጨባ ለጨለማው ጐሬ! ጤነኛውን ሰው እንባዬ እስኪመጣ ድረስ እንደምቀናበት ብናገርም አሁን ባለሁበት ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ግን እሱን ብሆን ባይሆን ግድ የለኝም። (ምንጊዜም ግን በሱ መቅናቴን አላቆምም። አይደለም አይደለም። የጨለማ ጐሬዬ በማንኛውም መልኩ ለኔ ይበልጥ ጠቃሚ ነው!) በጨለማ ጐሬ ውስጥ አንድ ሰው ቢያንስ...ይቅርታ እያጋነንኩ ነው መሰለኝ። ምክንያቱም የሚሻለው የጨለማ ጐሬዬ ሣይሆን ከሱ የተሻለ ሌላ ሙሉ

በሙሉ የተለየ አንድ የምፈልገው ግን ላገኘው የማልችል ነገር ስላለ ነው። ጨለማ ጉሬዬ ገደል ይግባ!

የተሻለው አማራጭ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እስካሁን በማፍኩት ራሴ የማምንበት ቢሆን እንኳ እንዴት ጥሩ ነበር። ከቡራንና ከቡራት እምልላችኋለሁ። እስካሁን ካልኩት ውስጥ የማምንበት አንድም ቃል የለም! ምን ለማለት ፈልጌ ነው ምናልባት አምን ይሆናል። ነገር ግን ደግሞ በአንድ ባልታወቀ ምክንያት ያለገደብ እየዋሸሁ መሆኔ ይሰማኛል።

«ታዲያ ይህን ሁሉ ለምን ፃፍክ? ትሉኛላችሁ»

«ደህና እንበል እናንተን አርባ ዓመታት ሙሉ ያለምንም ሥራ ጨለማ ጉሬ ውስጥ አስቀምጬ ከአርባ ዓመታት በኋላ ምን እንደሆናችሁ ላይ መጣሁ እንበል። እና አንድ ሰው አርባ ዓመት ሙሉ ምንም ሣይሠራ መቀመጥ ይችላል?»

በንቀት ጭንቅላታችሁን እየወዛወዛችሁ እንዲህ ትሉ ይሆናል።...

«አታፍርም!? ውርደት አይሰማህም? ሕይወትን ትናፍቃለህ፣ እንደገና ደግሞ የሕይወትን ችግሮች በተጠየቅ ትብትብ ልትፈታ ትሞክራለህ! እንዴት ዓይነት አሰልቺ፣ እንዴት ዓይነት ባለጌና ተንኮለኛ ነህ! የዛኑ ያህል ደግሞ ትፈራለህ። ፋይዳ ቢስ ነገሮችን ነው የምትለፈልፈው። በነሱም ትረካለህ ብዙ ሰድ ነገሮችን እየተናገርከን የኛን ጥሩ አመለካከት ለማግኘትም ትሞክራለህ የምታወራው ጥርስህን ነክሰህ እንደሆነ እየነገርከን እንደገና ደግሞ እኛን ለማሣቅ ትቀልዳልህ። ቀለዶችህ እንደማያስቁ ብታውቅም በሥነ ፅሁፋዊ ውበታቸው በጣም የምትደሰት ይመስላል። ምናልባት የምርህን ተሰቃይተህ ይሆናል። ለገዛ ሥቃይህ ግን ቅንጣት ታክል አክብሮት ያለህ አትመስልም። በእርግጥ የሆነ እውነት ይኖርሃል። ትህትና ግን የለህም። ከተራ ከንቱነትህ የተነሣ እውነትህን ለሕዝብ ዕይታ አደባባይ አውጥተህ ዋጋ ታሳጣዋለህ። በእርግጥ የሆነ ነገር ለመናገር ነው አነሳስህ። ነገር ግን ዓይን ያወጣ ብልግና እንጂ የሞራል ጥንካሬ

ስለሌለህ ከፍርሃትህ የተነሣ የመጨረሻ ታልህን ደበቅከ። ስለስሜታዊነትህ ትፎክራለህ። ግን ደግሞ የራስህን አእምሮ አታውቅም። ምንም እንኳ አእምሮህ ንቱ ቢሆንም ልብህ በክፉት የጠቆረ በመሆኑ ሙሉ ወይም እውነተኛ ስሜት የለህም። ያለንፁህ ልብ እውነተኛ ስሜት አይኖርም። እንዴት አሰልቺ ነህ! እንዴት ያለህ እኔን ብቻ ሰሙኝ ባይነህ! ደሞ ጉራህ! ውሸት– ውሸት– ውሸት!»

ይሄንን ንግግራችሁን እኔ ነኝ የፃፍኩላችሁ እሱም የመጣው ያው ከጨለማው ጐሬ ውስጥ ነው። ላለፉት አርባ ዓመታት በግርግዳው ንታታት አማካኝነት የምትሉትን ሳዳምጥ ቆይቻለሁ። እናም ራሴ ነኝ ፈጥሬ የፃፍኩት በሕይወቴ የፈጠርኩት ነገር ይሄ ብቻ ነው።

እንዳው ለነገሩስ ሁሉንም ፅፌ እንድታነቡት በማድረግ ከርከር ውስጥ የምገባ ይመስላችኋልን? ደግሞ አንድ ልፈታው የምፈልገው እንቆቅልሽ አለ። እናንተ እውነተኛ የኔ አንባቢዎች የሆናችሁ ይመስል «ለምንድን ነው የተከበራችሁ ሰዎች» ስላችሁ የነበረው? ምክንያቱም እኔ አሁን ላደረግ የተዘጋጀሁት ዓይነት ኑዛዜ አይታተምም። ለማንም ቢሆን ደግሞ አንብበው ተብሎ አይሰጥም። ለዚህ የሚያበቃ ድፍረት የለኝም። አስፈላጊም ነው ብዬ አላሰብም አያችሁ ግን! የሆነ አስገራሚ ሃሣብ ጭንቅላቴ ውስጥ መጣብኝና የፈለገው ይምጣ ብዬ ልፅፈው አሰብኩ። እንዲህ ነው ነገሩ።

የሰው ልጅ ባላሰፈው ሕይወት ውስጥ ምናልባት ለቅርብ ጓደኞቹ እንኚ ለሌላ ለማንም የማይገልፀው ሚስጢር ይኖረዋል። እንደገና ደግሞ ምናልባት ለራሱ 'ንኚ ለቀርብ ጓደኞቹ እንኳ የማይነገራቸው ነገሮች አሉ። በመጨረሻም ለራሱ እንኳ ሊገልፀው የማይደፍረው ሚስጢር ይኖረዋል። ግንኛውም ጨዋ ሰው አእምሮው በእንደዚህ ዓይነት ሚስጥሮች የታጨቀ ነው። እንዳውም እንዲህ ሊቀርብ ይችላል።... ሰውየው በጣም ጨዋና የተከበረ በሆነ መጠን የእንዲህ ዓይነት ሚስጥሮች ከምችት ይጨምራል። እኔም ከእንዲህ ዓይነት ሚስጥሮቼ ጥቂቶቹን ለማስታወስ የፈቀድኩት በቅርቡ ነው። እስካሁን ድረስ ግን ስሸሻቸው ቆይቻለሁ። አሁን ፈርቻለሁ።

አሁን ማስታወስ ብቻ ሣይሆን ልዕሩቸውም ጭምር በመወሰኔ ሁሉንም እውነት ሳለፈራ ከራሴ ጋር ፍፁም ሃቀኛ መሆን እችል ወይም አልችል እንደሆን ለመሞከር ፈልጌያለሁ። በነገራችን ላይ ሒይን ሲናገር እውነተኛ የራስ ሕይወት ታሪኮችን መፃፍ ከሞላ ጐደል የማይቻል ነው። እንዳውም ሰው ስለራሱ ብዙ ውሽቶችን መፃፉ እርግጥ ነው ማለቱን አክዩ ልነግራችሁ። እርግጠኛ ነኝ ይሄ ትክክል ነው። ሰው ተራ ውዳሴ ለማግኘት ሲል ስለራሱ የማይናገረው ውሸት አይኖርም። አልፎ ተርፎ ከንቱ ውዳሴ ያገኝ ዘንድ የማይናዘዘው ወንጀል የለም። ነገር ግን ሄን እንዲህ ሲል መሠረት ያደረገው እኔ እንዲህ ነኝ ብሎ ለሕዝብ መናዘዝ ስለፈለገ ሰው ነው ። እኔ ግን የምፅፈው ለራሴ ነው። በፅሁፌም የማነጋግረው አንባቢን ቢሆንም ለአፃፃፍ ባህሪ ቀና ሆኖ ስላገኘሁት 'ንጂ እናንተ ስለኔ እንድታውቁልኝ በመፈለግ አይደለም። የፎርም ጉዳይ ነው። የዓይነት። ባዶ ትዕይንት። ምክንያቱም አንባቢ እንደማላገኝ አውቃለሁ። እስካሁንም ብዙ አናድጃችኋለሁ።

ማስታወሻዎቼን ስፅፍ የቱን ልፃፍ አልፃፍ በሚል የማረም ሥራ ጨልጪነቅም። ሥርዓትም ሆነ ዘይቤ አያሳስበኝም። ያስታወስኩትን እንደመጣልኝ እፅፈዋለሁ። በእርግጥ አሁን ልጠየቅ እችላለሁ። እሺ ይህንን የምትፅፈው ምንም ዓይነት አንባቢ ለማግኘት አስበህ ካልሆነ ለምን ታዲያ ሥርዓት ፣ ዘይቤ፣ የማስታውሰውን ወዘተ...ወዘተ ማብራራት አስፈለገ? ምንድነው ይሄ ሁሉ ይቅርታ?

አሁን ጠየቃችሁ! አሁን እውነትም ጠየቃችሁ! በአጋጣሚ ሁሉም ነገር የሥነ ልቦና ጉዳይ ነው። ምናልባትም ፈሪ ስለሆንኩ ሊሆን ይችላል። ምናልባት ደግሞ ስፅፍ ቅድሚያ ልሰጣቸው የሚገቡ ነጥቦችን ለማስታወስ የምናብ አናባቢ ሆን ብዬ እያሰብኩ ሊሆን ይችላል። በሺ የሚቆጠሩ ምክንያቶች ያለጥርጥር ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ሌላው እንቆቅልሽ ደግሞ ይኸውላችሁ፤ ለምንድነው የምፅፈው? ምንድነው ዓላማው? የምፅፈው ለአንባቢ ሕዝብ ካልሆነ ለምን ወረቀት ላይ ሳላሰፍር ለራሴ በህሊናዬ ውስጥ ብቻ አላሰታውሰውም?

ደህና! እንደዚህ ማድረግ እንኳ የምችል ይመስለኛል። ነገር ግን ወረቀት ላይ ሲሰፍር የበለጠ ይከበራል። ሲነፍ የሆነ ግርማ አለው ራሴን ለፍርድ የማቅረብ ስሜቴንም ያጠናክረዋል። የሚሻለውም መንገድ ይሄ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ስፅፈው ቀለል ይለኛል።

ለምሳሌ :- እንዳው በቅርቡ ከረዥም ጊዜ በፊት የደረሰብኝ አንድ አጋጣሚ ጭንቅላቴን ውጥር አድርጐ ይዞታል። ልከ ከጭንቅላት አልወጣም የሚል አሳዛኝ ዜማ ይመስል ሊለቅቀኝ አልቻለም። ወደድኩም ጠላሁትም ግን ልገላገለው ይገባል። በመቶ የሚቆጠሩ እንዲህ ዓይነት ትዝታዎች ቢኖሩኝም አልፎ አልፎ ግን ከመሀል አንዱ ብቻ ገኖ ይወጣና ይጫጫነኛል። ታዲያ ለምን መፃፉን አልምከረውም?

በመጨረሻም ደግሞ በሚያስከፉ ሁኔታ ደብሮኛል። አንድም የምሠራው ነገር የለም። ነገሮችን በፅሁፍ ማስፈር ደግሞ በሆነ መልኩ ሥራ ነው። ሥራ ሰውን ያሻሽላል። ሃቀኛ ያደርጋል ይባላል። ይሄ እንግዲህ ለኔም ጥሩ ዕድል ነው ማለት ነው።

ዛሬ ቢጫ፤ ቆሻሻ በረዶ እየዘነበ ነው። ትላንትም ከትላንት ወዲያም ሲዘንብ ነበር። አሁን ፋታ ያላጣኝን አጋጣሚ ያስታወሰኝም ይሄ ቆሻሻ በረዶ ነው። ስለዚህ ከቆሻሻው በረዶ ጋር አብሮ ይሁን።

ክፍል 2

I

በዚያን ጊዜ ዕድሜዬ ገና ሃያ አራት ነበር። ያኔም ቢሆን ታዲያ ሕይወቴ ቀፋፊ፤ መልከ የለሽና ወደ አውሬነት የተጠጋ ብቸኝነት ያጠቃኝ ነበር። ጓደኞችም ሆነ እውቂያ ስላልነበረኝ ከሰዎች ጋር መነጋገርን ሆነ ብዬ አስወግጀ እያደር ራሴን ጉሬዬ ውስጥ ቀበርኩ። የሥራ ባልደረቦቼ እንደ

አንድ ልዩ ፍጡር መመልከት ብቻ ሣይሆን ሊያዩኝ ሁሉ ይጠየፉኝ ስለነበር የማንንም ፊት ቀና ብዬ ለማየት አልሞክርም ነበር። ከኔ በስተቀር ሌሎች ሰዎች ሰው ተፀይፎ እንደሚመለከታቸው ለምን እንደማያስቡ ይገርመኛል። ከቢሮዋችን ፀሐፊዎች አንዱ ደንበኛ የአረመኔ የሚያስመስል አስቀያሚና ቡግር የተጫወተበት ፊት አለው። እኔ እሱን ብሆን ይህን ፊት ይገፎ ማንንም ሰው ቀና ብዬ ለማየት አልደፍርም ነበር። ሌላው ደግሞ የሚለብሰው ዩኒፎርም እጅግ ያረጀና የቆረፈደ ከመሆኑ የተነሣ የተጠጋው ሁሉ በሽታ ይረብሻል። ይሁን ’ንጂ እነዚህ ሰዎች በመልካቸውም ሆነ በፊታቸው በሰው ላይም በሚፈጥሩት ስሜት ቅንጣት ታክል የሚረበሹ አይመስሉም። ሰው ይፀየፈናል ብለውም አስበው አያውቁም። ቢያስቡም ኖሮ እንኳ አለቆቻቸው እስካልተጠየፉቸው ድረስ ለሌላው ደንታ የላቸውም። እኔ ቅጥ በሌለው ከንቱነቴና ክፉኛ የሚጐዳ ስሜት ስላለኝ ራሴን የምመለከተው ወደጥላቻ ባደላ ብስጭት መሆኑ ግልፅ ነው። ለምሣሌ የገዛ መልኬ እጅግ አስቀያሚ ሆኖ ከማግኘቴ የተነሣ እንዳውም የፊቴ ገፅታ ንፁግነትን የሚያንፀባርቅ አድርጌ ስለምጠረጥረው ቢሮ ስገባ በተቻለኝ መጠን ባልደረቦቼ በንፁግነት እንዳይጠረጥሩኝና ለራሴም የጨዋ ሰው ገፅታ ለመስጠት በማደርገው ጥረት እጅግ በጣም እሰቃይ ነበር። ፊቴን ጠላሁት «ምን ቸገረኝ» እል ነበር። «ፊቴ ጨዋ፣ ገላጭና ከሁሉም በላይ ደግሞ በጣም የተማረ መሆኔን ካሣየ ቆንጆ ቢሆን—ባይሆን ምን ጨነቀኝ» ነገር ግን ፊቴ እነዚህን ያልኳቸውን ሁኔታዎች ሊገልፅ እንደማይችል በደንብ አድርጌ አውቀዋለሁ። አስከሬ ጐኑ እንዳውም ፊቴ ፍፁም ደደብ ነው የሚያስመስለኝ ብዬ አስባለሁ። ሙሁር ቢያስመስለኝ ኖሮ ሙሉ በሙሉ በረካሁ ነበር። በርግጥ ፊቴ የሙሁር ገፅታ ያለው መሆኑን ሁሉም የሚቀበሉኝ ቢሆን ኖሮ ንፁግ መምሰሉ ሣያስጨንቀኝ ከፊቴ ገፅታ ጋር በታረቅኩኝ ነበር። የሥራ ባለደረቦቼን በሙሉ እያንደንዱንም ሆነ ሁሉንም እንደምጠላቸውና እንደምንቃቸው መልሼም እንዳምፈራቸው መናገር አያስፈልገኝም። አንዳንድ ጊዜ ከኔ በታች አድርጌ አያቸዋለሁ። ድንገት የሚመጣብኝ ስሜት ነው። አሁን እንቃቸዋለሁ። ቀጥሎ ከኔ በላይ አድርጌ

እቆጥራቸዋለሁ። ጨዋ የተማረ ሰው አራሱን ሳያሰታይና አልፎ አልፎ ራሱን እስኪጠላ ድረስ ሳይንቅ ግብዝነቱን ማርካት አይችልም።

ናቅኳቸውም አክበርኳቸውም ፊት ለፊት ስንገናኝ ግን ሁልጊዜ አይኔን ወደመሬት እሰብራለሁ። አንዳንድ ጊዜ እንዳውም ከባልደረቦቹ አንዱን ወይም ሌላውን አይኔን ሳልሰብር ፊት ለፊት ላይው ሙከራዎች አደርግ ነበር። ሁሌም ግን ቀድሜ አይኔን የምሰብረው እኔው ነኝ። ይህም እስከ እብደት ደረጃ ያበሽቀኝ ነበር። በለዎች ፊት ጅላጅል መስሎ መታየት የሞት ያክል ስለሚያስፈራኝ ሁሉንም ማህበራዊ ደንቦች እንደባሪያ ማክበር ብቻ ሣይሆን አንዳችም የተለየ ባህሪ ላለማሣየት የሞት ያህል እፈራ ነበር። ግን ለመቀጠል እንዴት ይቻለኛል? የዘመናችን ሰው ሊሆን እንደሚገባው በአእምሮ በጣም የዳበርኩ ነበርኩ። እነሱ ግን በሌላው በኩል ሁሉም ደነዞችና ልክ እንደበግ መንጋ አንድ ነበሩ። በኛ ቢሮ እራሱን ፈሪና ባሪያ አድርጉ የሚያስብ እኔ ብቻ ነበርኩ። እንደዚህም የማስብበት ምክንያቱ የኔ አእምሮ በጣም የዳበረ ስለሆነ ይመስለኝ ነበር። እውነቱ ግን እኔ ስላሰብኩት ብቻ ሣይሆን በውልም የተረጋገጠ ስለነበረ ነው። በትክክል ፈሪና ባሪያ ነበርኩ።ይህንን የምናገረው ያላንዳች ሀፍረት ነው። የዘመናች ግንኛውም ጨዋ ሰው ፈሪና ባሪያ መሆን ብቻ ሣይሆን እንዲሆንም ግድ ነው። ይህም ጤነኛ ሁኔታ ነው። በዚህ ፍፁም አምንበታለሁ። የተፈጠረውም ለዚህ ዓላማ ነው። ለአሁን ወይም በተወሰኑ ጥሩ ሁኔታዎች ብቻ ሣይሆን ጨዋ ሰው ሁልጊዜ በአጠቃላይ ፈሪና ባርያ መሆን አለበት። ለምድራችን ጨዋ ሰዎች ይህ የተፈጥሮ ሕግ ነው። አልፎ አልፎ ስለአንድ ነገር ወይም ሌላ ድፍረት ናሮት ቢንቀሳቀስ 'ንኳ ይዋል ይደር 'ንጂ ከድርጊቱ ደስታም ሆነ ምቾት አያገኝበትም። በሌላ ጉዳይ ላይ ራሱን እንደሚያጃጅል እርግጠኛ ነኝ። ይህ ደግሞ የማይቀርና ዘላለማዊ እሱ እሱነቱን የመሆኑ ውጤት ነው። ፍርሃት ያደረባቸው ላለመምሰል የሚሞክሩ ቢኖሩ አህዮችና በቅሎዎች ናቸው። ይህንንም የሚያደርጉት እስከተወሰነ ደረጃ ብቻ ነው።

በዛን ወቅት በጣም ያስጭንቀኝ የነበረ አንድ ምንም ማስተባበሪ የማላገኝበት ሃቅ ደግሞ እኔ ካንዳቸውም ጋር እንደማልመሳሰልና ከነሱም ውስጥ እኔን የሚመስል አለመኖሩ ነበር። «እኔ አንድ ነኝ፣ እነሱ ግን ሁሉም።» ብዬ አሰብና በሀዘን እቆዝማለሁ። ከዚህ ሁሉ ተንስተን ገና ወጣት መሆኔን መገንዘብ ይቻላል። አንዳንድ ጊዜ ግን ተቃራኒው ይፈፀማል። ወደቢሮ የመሄድ ሃሣቡንም በጣም ከመጠየፌ የተነሣ ብዙ ጊዜ ወደቤቴ ታምሜ እመለሣለሁ። ድንገት ደግሞ ያለምንም መንስኤ የጥርጣሬ መንፈስ ያድርብኝና (እኔን በተመለከተ ሁሉም ነገር የሚመራው በስሜት ነው) በራሴ ትግሥት አልባነትና ስስ ገላነት በመሣቅ ሮማንቲክ ተፈጥሮዬን እወቅሣለሁ። አንዳንድ ጊዜ ከማንም ጋር ማውራት ያስጠላኛል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ከነሱ ጋር ማውራት ብቻ ሣይሆን ሥራዬ ብዬ ልወዳቸው አስባለሁ። ፈዛዛነቴ ሁሉ ያለምንም ቀዳሚ ምክንያት ድንገት ይጠፋል። ማን ያውቃል! ምናልባት መጀመሪያውኑ ፈዛዛ አልነበርኩ ይሆናል። ለዚህ ጥያቄ መልስ አሁን ድረስ ፈልጌለት አላውቅም አንዴ ከነሱ ጋር ተግባባሁና ወዳጅነት መሥርቼ በየቤታቸው መሄድ፣ ካርታ መጫወት፣ ቮድካ መጠጣትና ስለማዕረግ እድገት ማውራት ጀመርኩ።...

(ሩሲያ ውስጥ ምንም ዓይነት ነገር የማይለውጣቸው ኮከቡ ዓይን ጀርመንና ፈርንሣዊ ሮማንቲኮች ዓይነት ኖረውን አያውቁም። እነዚህ አሮማንቲኮች የረገጡት መሬት ቢከዳቸው ወይም ፈረንሣይ እንዳለ ብትወድም መሰሎ ለመታየት ያህል እንኳ ቅንጣት ታክል ሳይለወጡ ሞኖች የሆኑ ይምሰል እስከመጨረሻዋ ትንፋሻቸው ድረስ ሮማንቲክ መዝሙሮቻቸውን እያንጐራጐሩ ወደ መቃብር ይወርዳሉ። ሩሲያ ውስጥ ሞኖች እንደሞሉ የታወቀ ሀቅ ነው። ይሄም ነው ከሌሎች ሀገሮች የተለየ የሚያደርገን።

ስለዚህ ባለኮከቡ አይን ተፈጥሮ ያላቸው ንፁህና ቅን ሮማንቲኮች የሉንም። የኛ ሮማንቲኮች ባህሪያት ከባለኮከብ አይኑ አውሮፓዊ ዓይነት ሜራሽ የተለየና ተቃራኒ ከመሆኑ የተነሣ አንድም የአውሮፓ መለኪያ እኛ

ዘንድ አይሠራም። (መቼም «ሮማንቲክ» የሚለውን ቃል መጠቀሚ ቅር እያሰኛችሁም ቃሉ ጥንታዊ፤ የተከበረና ሁሉም የሚያውቀው በመሆኑ ነው።) የኛ ሮማንቲኮች ባህሪያት ሁሉንም መረዳት፤ ሁሉንም ነገር መመርመርና በግልፅ አብጠርጥሮ ማወቅ ምንም ነገር ሳይመረምሩ አለመቀበል፤ ምንም ነገር ንቆ አለ፟ማተው፤ በሁሉም ነገር ዙሪያ ማንጎበብ፤ ማንበብና ጠቃሚ የሆነ ነገር ሲገኝበት ፖሊሲን ገለል አድርጉ መጋጥ ናቸው።)

...ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር የጀመርኩት ጓደኝነት አልዘለቀም። በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደቀድሞው ፍጥጫዬ ተመለስኩ። በወጣትነት ልምድ አልባነቴ የተነሣ ሰላምታ መለዋወጥም በማቆም ጭራሽ ተቆራረጥኩ። ይሄ እንግዲህ ላንድ ጊዜ የሆነ ነገር ብቻ ነው። ከዛ በተረፈ ሁሌም ብቻዬን ነኝ። ብዙውን ጊዜ ጊዜዬን የማሳልፈው እቤቴ መፅሐፍ በማንበብ ነው። ውስጣዊ ያልተረጋጋ ስሜቴን በተገኘው ውጫዊ ግርግር አማካኝነት ላረጋጋው ምከሬያለሁ። ዋንኛ የጊዜ ማሳለፊያዬ በቀላሉ የማገኘው ንባብ ነበር። ማንበቡ ብዙ ረድቶኛል ያስደስተኝ ያስቃየኝም ነበር። አንዳንድ ጊዜ ግን ክፉኛ ይሰለቸኝ ነበር። እቤቴ መቀመጡ ክፉኛ ሲሰለቸኝ ወደ ሆነ ቦታ ሄድ ውጣ ያሰኘኛል። ያን ጊዜ ውስጥ ለውስጥ ቀፋፊ፤ ደባሪ የሆነ ሚስጥራዊ ክፉ ስሜት ውስጥ እዘፈቃለሁ። ከሚሰማኝ ያላቋረጠ በድናዊ ብሽቀት የተነሣ ቀፋፊ አምሮቶቼ በጣም ኃይለኛና አንገብጋቢ ነበሩ። ስሜቴን ላወጣ እንዘፈዘፋለሁ። ሁሌም በእንባና በሲቃ የታጀበ ነበርና ከንባብ ውጭ የምሠራው ነገር የለም። በዙሪያዬ ላከብረው የምችል ወይም ሊማርከኝ የሚበቃ ምንም ነገር የለም። በተጨማሪም ልቤ ክፉኛ ጨልሞ ልለነበር ግጭቶችና የስሜት መረበሾች ክፉኛ እመኝ ነበር። በዚህም የተነሣ የመብላትና የመጠጣት ሕይወት ውስጥ ተዘፈቅኩ። ልብ አድርጉ :- ይህንን የተናገርኩት የራሴን ትክክለኛነት ለማሣየት በመፈለግ አይደለም። እንዲህ ስል ውሸቴን ነው። በርግጥም ፍላጐቴ የራሴን ትክክለኛነት ለማሳየት ነው።

ይቺን ትንሽ ማስታወሻም የምፅፈው ለራሴ ጥቅም ስል ነው። መዋሸት አልፈልግም። ላለመዋሸት ቃል ገብቼ የለ የተከበራችሁ ሰዎች!

ብቻዬን ሆኜ ምሽቱን በሚስጥር እየፈራሁ፣ እየቀፈፍኩ እስኪያ ጥወለውለኝ ድረስ ባለቀቀኝ የሃፍረት ስሜት ተውጪ ነውረኛ እርካታዎቼን በገዛ የራስ ቅሌ ላይ መርገምት እንዲዋድቅበት እስከመኝ ድረስ ቀጠልኩበት። አሁንም 'ንኳ ጨለማ ሕይወቴን በነፍሴ ውስጥ ይገፍው እዞራለሁ። መታየት፣ ከማውቀው ሰው ጋር መገናኘት እናም መታወቅ በፅኑ እፈራ ነበር። ሁሉንም ዓይነት ድብቅ ነውረኛ እርካታዎችን አዘወትርኩ።

አንድ ምሽት በአንድ ቡና ቤት አጠገብ ሣልፍ የሆኑ ጥቂት ሰዎች በቢልያርድ መጫወቻ ዱላዎች ሲጣሉና እንደኛው በመስኮት ተወርውሮ ሲጣል አየሁ። ሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ ድርጊቱን በጣም አጠየፈው ነበር። አሁን በነበርኩበት ሁኔታ ግን በመስኮት በተወረወረው ሰው በጣም ቅናት ያዘኝ። እጅግ በጣም ከመቅናቴ የተነሣ ምናልባት እኔም ከሰዎቹ ጋር ተጣልቼ በመስኮቱ ይወረውሩኛል ብዬ ተስፋ በማድረግ ቡና ቤቱ ውስጥ በመግባት በቀጥታ ወደቢሊያርድ መጫወቻው ክፍል አመራሁ።

አልሰከርኩም። እና ምን ላድርግ? አያችሁ! ድብርቴ እንዲህ ላለ እብድ እምነት አጋልጦኛል። የሚያሳዝነው ነገር ግን ምንም ነገር አለመፈጠሩ ነበር። ሌላው ቀርቶ በመስኮት 'ንኳ ለመዝለል እንደማልችል ዓይነት ነበር የሆነው። ያለምንም ጠብ ወደቤቴ ሄድኩ። ገና ከጅምሩ በቡና ቤት ውስጥ የነበረ አንድ ወታደራዊ መኮንን ቦታዬ አስቀመጠኝ።

ካለማወቄ የተነሣ ቆሜ የነበረው መንገዱን ዘግቼ ከቢልያርዱ ጠረጴዛ አጠገብ ነበር። መኰንኑ ማለፍ ስለነበረበት ያለምንም ማስጠንቀቂያም ሆነ ማብራሪያ ቃል ትከሻዬን አንጠልጥሎ በመያዝ ጭራሽ ማንና ምን እንደሆንኩ ሳያስተውል ወደሌላ ቦታ አስቀመጠኝ በጥፊ አጋጭቶኝ ቢሆን ኖሮ ይቅር ባልኩት ነበር። ነገር ግን የቡና ረከቦት የሆንኩ ይመስል ካንዱ ቦታ ወደሌላው ስለለዋወጠኝ አልማርኩትም በዛን ሰዓት እንዲህ ከሚያደርገኝ እውነተኛ የሚጠበቅ የጨዋ መግለጫ የሆነ፣ ማለቴ የቃል ፀብ

(ስድድብ) ቢገጥመኝ ኖሮ በምን እድሉ ነበር። ነገር ግን እንደዝንብ ነው የቆጠረኝ። ወታደራዊ መኩንኑ ቀውላላ እኔ ደግሞ አሞርና ቀጫጫ ፍጥረት ነኝ። ፀቡ ግን በኔ እጅ ውስጥ ነበር። ምክንያቱም እንደረከቦት ካንዱ ቦታ ወደሌላው ሲያቀያይረኝ የተታውሞ ታል አሰምቼ ቢሆን ኖሮ ያለምንም ጥርጥር በመስኩቱ አሾልኮ ይወረውረኝ ነበር። እኔ ግን ሃሣቤን ቀይሬ በንዴት ራሴን መደበቁን መረጥኩ። ከቡና ቤቱ አብድ ሆኜ ወጣሁና ወደቤቴ ሄድኩ በሚቀጥለው ቀን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ፈራ ተባ እያልኩ እምባ በአይኖቼ ግጥም እያሉ የተለመደ ወራዳ ድብቅ እርካታዬን ቀጠልኩ። እንዲህ ስላችሁ ታዲያ ወታደራዊ መኩንኑን የፈራሁት ፈሪ ስለነበርኩ እንዳይመስላችሁ። ልቤ ከቶም ፈሪ አይደለም። ምንም 'ንኳ እርምጃ ለመውሰድ ሁሌም የምፈራ ብሆንም። ለመሣቅ አትቸኩሉ። ለሁሉም በቂ ማብራሪያ ስላለኝ አትጨነቁ።

አቤት! ይሔ ወታደራዊ መኩንን ፍልሚያ እንደሚቀበሉ ዓይነት ቢሆኑ ኖሮ! ግን አይደለም እሱ (ወይኔ! ከጠራ ቆይተዋል) በቢልያርድ ዱላ የሚደባደቡትን ወይም እንደጎጎል ሙቶ አለቃ ቢሮጉቮ ለባለሥልጣኖች ክስ ማቅረብ የሚመረጥ ዓይነት ነው። በፍፁም ፍልሚያ አይወድም። እንደ እኔ ካለ ኮሳሳ የሲቪ ሠራተኛ ጋር ደግሞ የሚደረግ ፍልሚያን ከቁም ነገር አይቆጥሩትም። ራሱ ፍልሚያን በተመለከተ ያላቸው አመለካከት ግን ጠቅላላ ድርጊቱ የነፃ ሃሣባዊያን ወይም ፈረንሣውያን የሚያዘወትሩት ከንቱነት አድርገው ነው። ይሄ ግን በዛ ግዙፍ ቁመናቸው የሰው እግር አሳምመው ከመርገጥ አላገዳቸውም። ፍራቻዬ ከፈርሃት የመነጨ አልነበረም። ጨርሶ። በገደብ የለሽ ከንቱነቱ የተነሣ 'ንጂ! ከሁለት ሚትር በላይ የሆነ ቁመቱም አያስፈራኝም። ከራፍ መደብደቡም ሆነ በመስኮት መወርወሩ ስጋቴም አልነበር። ይሄንን ለመቋቋም በቂ የሆነ አካላዊ ጥንካሬ ነበረኝ። ያጣሁት የሞራል ጥንካሬ ነው። የፈራሁት ቢሊያርድ መጫወቻ ከፍሉ ውስጥ የተሰበሰበው ከጋጠወጡ ነጥብ ያዥ ጀምሮ ያደፈ ሸሚዝ የለበሰውና በከፍሉ ውስጥ ለነበረው ለው በሙሉ ያሽቃብጥ የነበረው በስባሳ፡

ቡግራም የሲቪ ሥራተኛ ድረስ እኔ በመኩንኑ ድርጊት ተቆጥቼ በሥነዕውፍ ቋንቋ መናገር ስጀምር ሳይገነዘቡኝ ቀርተው ይሳለቁብኛል ብዬ ነበር የፈራሁት። አሁንም ድረስ ለክብር ያህል 'ንኳ (ልብ አድርጉ ስለክብር አላልኩም) ስለክብር እንኳ መነጋገር አንችልም በሥነ ዕውፍ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር። በመደበኛ ቋንቋ ውስጥ ክብር ብሎ ነገር የለም። እንዳሰብኩት ባግረ የሥነ ዕውፍ ቋንቋ ስለክብር መነካት ቱናግሬ ቢሆን ኖሮ በከፍሉ የነበሩት በሙሉ ልባቸው እስኪፈርስ መሣቅ ብቻ ሣይሆን መኩንኑም ቂም በሌለው ሁኔታ ,ጉቨም እያደረገ በቢሊያርድ ጠረጴዛው ዙሪያ በጉልበቱ እየገፋ ከአዟዟረኝ በኋላ ምናልባት ያን ጊዜ አሳገኘው በመስኮት አዘልሉ ይወረውረኛል። እንዲህ ዓይነቱን የተረገመ አጋጣሚ ደግሞ በእኔ ዘንድ ቡና ቤት ውስጥ የሚያበታ አይደለም። ከዛ በኋላ መኩንኑን መንገድ ላይ ብዙ ጊዜ ስለማገኘው በጥንቃቄ አስተዋልኩት። እርግጠኛ ያልሆንኩበት ነገር ቢኖር እሱ ይወቀኝ አይወቀኝ ነው። እንዳላወቀኝ በተለያዩ ምልክቶች ተረድቻለሁ። እኔ ግን ባየሁት ቁጥር በጥላቻና በክፉት አይኔ እስኪፈርጥ ሣፈጥበት ዓመታት አለፉ። በመጀመሪያ ስለመኩንኑ ማወቅ የምፈልገውን ያህል ለማወቅ ምርመራ ጀመርኩኝ። ማንም የማውቀው ሰው ስላልነበረኝ ሥራው አስቸጋሪ ነበር። ነገር ግን በአንድ አጋጣሚ ከሱ ሁዋላ በገመድ የታሠርኩ ይመስል ፈንጠር ብዬ ከኋላ ኋላው ስከተል አንድ ሰው በስሙ ሲጠራው ሰማሁ። ሌላ ጊዜ ደግሞ እቤቱ ድረስ ተከትየው ሄጀ ለቤት ጠባቂው አሥር ሣንቲም በመስጠት የት እንደሚኖር የትኛው ፎቅ፣ ብቻውን ይኑር ወይም ከሰው ጋር ወዘተ ካንድ የቤት ጠባቂ ሊገኝ የሚችለውን መረጃ ሁሉ ሰበሰብኩ። ምንም 'ንኳ በሥነዕውፍ ሥራ አዘውትሬ ባላውቅም አንድ ጧት ግን መኩንኑን ለማጋለጥ በለበጣ የተሞላ ዕውፍ ለአንድ ጋዜጣ ልዕፍ አሰብኩ። ሣጋልጠው ቅዕሎችን ከመስጠት 'ንኳ አላንገራገርኩም የሰጠሁት ስም በጣም ሊያሣውቀው የሚችል ሆኖ ሣለ በእርጋታ ካሰብኩ በኋላ ሀሣቤን ተውኩት። የተፃፈውን ታሪክም «ለኦብላንድ ኖትስ» ጋዜጣ ላኩት። በጊዜው ማጋለጥ ሩሽን ስላልነበረ ዕሁፉ ሳይታተም ቀረ። በጣም ቆሰልኩ።

አንዳንድ ጊዜ ቅያሜዬ የማልቋቋመው ይሆናል። በመጨረሻም ልፋለመው ቆረጥኩ። ይቅርታ እንዲለምነኝ እምቢ አሚለኝ ከሆነ ደግሞ ወደፍልሚያ እንደማመራ የሚጠቁም ውብና አስደሳች ደብዳቤ ፃፍኩ። ደብዳቤውም በግሩም ሁኔታ ከመፃፉ የተነሣ መኩንኑ «ክቡርና ቆንጆ» ስለሆኑ ነገሮች ትንሽ 'ንኳ ሃሣብ ቢኖረው ወደኔ እየሮጠ መጥቶ እንግቴን አቅፎ ጓደኛሞች እንድንሆን ይማፀን ነበር። እንደዛ ቢሆን ኖሮ በምን እድሌ! እንዴት ያለን ጓደኛሞች ይወጣን ነበር። እሱ በወታደራዊ ማዕረጉ ሲጠብቀኝ እኔ ደግሞ በከፍተኛ ትምህርቴ ማለትም በሀኣበፎ ጭንቅላቱን አሰፋው ስለነበር ብዙ ነገር ይፈጠር ነበር። እስኪ አሰቡት ይሄ ሁሉ እንግዲህ መኩንኑ ካስቀየመኝ ሁለት ዓመት በሁዋላ ነው። ምንም እንኳ ደብዳቤዬ በመካከሉ ያለፈውን ጊዜ እንዲደብቅ ተደርጉ የተጻፈና የተዋጣለት ቢሆንም ዞሮ ዞሮ የፍልሚያ ጥያቄዬን ጊዜ ያለፈበት መሆኑን ሊደብቅ አልቻለም። እግዚአብሔር ይመስገን 'ንጂ (አሁንም ድረስ ሃያሉ እግዚአብሔርን ሳመሰግን እንባዬ ግጥም ይላል) ደብደቤውን አልላኩትም። ልኪው ብሆን ኖሮ እያልኩ ሊከተል የሚችለውን ቅሌት ላስብ በጀርባዬ ላብ ይንሸርቀሸቃል። ድንገት እጅግ ቀላልና ልዩ በሆነ መንገድ በቀሌን ተወጣሁ። በጣም ድንቅ የሆነ ሃሣብ ድንገት መጣልኝ።

አንዳንድ ጊዜ በበዓላት ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ አሥር ሰዓት ገደማ በኔቪስኪ ጐዳና ፀሐይ ባለችበት ጐን ሽርሽር የማድረግ ልማድ ነበረኝ። እውነት እንነጋገር ከተባለ ሽርሽር አይባልም። ማብቂያ የሌላቸው ሥቃዮች ውርደቶችና ሃሞት የሚያስተፉ ቅሌቶችን የምቀበልበት ነው። ለነገሩ የምፈልገውም እሱን ነው። ልክ እንደ ሸለምጥማጥ በሚያሳፍር መልኩ ከፊት ለፊቴ ሣያቋርጡ ለሚመጡት ጀኔራሎች፣ መኩንኖችና ወይዛዝርት መንገድ ለመልቀቅ ወዲያና ወዲህ ስበረግግ ነው የምውለው። የሁለመናዬ ኮሳሳነትም እዚህ ግባ በማትባል ሰውነቴ ወዲያ ወዲህ መንቦጀቦጅ የተነሣ ልቤን ቀስፎ የሚይዝ የሰላ ሥቃይና መላ ጀርባዬን ደግሞ ትኩሳት ይወረኛል። አጠቃላይ ሰሚቱ የማያባራ የማይቻል በሕብረተሰቡ አባላት

መካከል እንደዝንብ እንደቀፋፊ ዝንብ የመቆጠር እጅግ የሚቆጠቁጥ ሥቃይ ነው። በጣም ጭንቅላት ያለው፣ በጣም ባስተሳሰብ የዳበረ ከማንም በላይ ቅዱስ የሆነ (በዚህ ምንም ጥርጥር የለኝም) ነገር ግን ለያንዳንዱ ሰው መንገድ መልቀቅ ያለበት ዝንብ! በሁሉም የተሰደበና የተዋረደ ዝንብ፣ ለምን ይሄን ስቃይ እንደምሰቃይ፣ ለምን በኒቪስኪ ጉዳይ ልንሸራሸር ብዬ እንደምወጣ አላውቅም። በተገኘው አጋጣሚ ግን ወደዛ ነው የምሳበው። ከዛ ወታደራዊ መኰንን ጋር ከተጋጨን በኋላ ወደሽርሽሩ በይበልጥ ተሳብኩኝ እሱንም ብዙ ጊዜ የማገኘው በኔቪስኪ አውራ ጐዳና ላይ ነበር። እሱን ለማየትም ያለቅጥ እደሰታለሁ እሱም እንደኔ በበዓላት ቀን ሽርሽር ያዘወትራል። እሱም እንደኔ ለጀኔራሎችና ለሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች መንገድ ለመልቀቅ እንደሸለምጥማጥ ቢደነብርም እንደኔ ያሉት ግን ወይም ከኔ ትንሽ ከፍ ያሉትን ፊት ለፊት ሲያገኟቸው ልክ በቦታው እንደሌሉ ቆጥሮ በላያቸው ላይ ነው የሚሄደው። ቢሞት መንገድ አይለቅላቸውም። እሱን ባየሁ ቁጥር በጥላቻ እሞላለሁ። ፊት ለፊቱ ሲመጣ ግን ሳልወድ በግዴ መንገድ አለቅለታለሁ። በመንገድ ላይ 'ንኳ ከሱ እኩል ለመሆን ባለመቻሌ አቃጠላለሁ። አንዳንድ ጊዜ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ባንኜ እስክነቃ ድረስ በብሽቀት እየተቃጠልኩ ራሴን በራሴ «ለምንድነው አንተ ብቻ ሁሌ መንገድ የምትለቀው» እያልኩ ደጋግሜ እጠይቃለሁ። «ለምን ሁልጊዜ አንተ 'ንጂ እሱ አይደለም መንገድ የሚለቀው? እንዲህ እንዲሆን ሕግ የለም። አለ 'ንዴ? ስለዚህ ጉዳይ የተፃፈ ነገር የለም አለ 'ንዴ? ለምን ሁለት በሥነ ሥርዓት ያደጉ ጨዋ ሰዎች እንደሚያደርጉት አንተም ለሱ እሱም ላንተ በከፊል መንገድ እንድትለቁ አታደርግም? አንተ ከመንገድህ ግማሹን እሱም እንዲሁ ግማሹን ለቆ በጋራ መከባበር ለምን አትተላለፉም? «እንዲህ ሆኖ ግን በፍፁም አያውቅም። ሁሌ መንገድ የምለቀው እኔ ስለሆንኩ እሱ ደግሞ መንገድ እንደለቀቅኩለትም አያስተውልም።

በዚህን ጊዜ ነው ታዲያ ያ ድንቅ ሃሣብ የመጣልኝ። «ምን ይመጣል!» አልኩ ለራሴ። «ፊት ለፊት ባገኘውና ገለል ባልልለት ምን

ይመጣል? መጋጨት ቢገባኝ 'ንኳ ልጋጭ ብዬ በታ መንገዱን አለመልቀቅ። ምን ሊፈጠር ይችላል?» ይሄ እብድ ሃሣብ ሙሉ ህሊናዬን ስለተቆጣጠረው እረፍት አጣሁ። ይሄን ለማድረግ በምወስንበት ቀን እንዴት ላደርገው እንደምችል ለማረጋገጥ ሰል ወደኒቪስኪ ጐዳና ለሽርሽር መጓዜን ቀጠልኩበት። ከነፍኩ። ይህ እቅድ እያደር ተግባራዊና ተሰፋ ሰጪ ሆነልኝ። ሃሣቡ ከፈጠረብኝ ደስታ የተነሣ ለሱ 'ንኳ ሃዘን እየተሰማኝ «መተሻሸት 'ንጂ ብዙ አልገፋውም» እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ። ብሞት መንገድ አልለቅለትም። እንዳልጐዳው ተጠንቅቄ ትከሻ ለትከሻ አጋጨዋለሁ። ልገጨው የምችለው በገጨኝ መጠን ነው።

በመጨረሻ ውሣኔዬ ፀናልኝ። ዝግጅቱ ግን ብዙ ጊዜ ወሰደብኝ። ቅድሚያ የሰጠሁት ነገር እቅዴን ተግባራዊ ሳደርግ ሊኖረኝ ስለሚገባው አለባበስ ነው። ስለዚህ ስለልብሶቼ መጠንቀቅ አለብኝ። ድርጊቱን በምፈፅምበት ጊዜ ግርግር ሊፈጠር ይችላል። (ተመልካቾች መኖራቸው አይቀርም እንዴት የተከበረች ሴት ስትሄድ፣ ልዑል ዲ ኑሱ ሲቀበሉ፣ መላው የሥነ ፅሁፍ ዓለም ሊንሸራሸር) ስለዚህ አንድ ሰው በጨዋ ደንብ መልበስ አለበት። ጥሩ ልብሶች ሰውን ስለሚማርኩ እኛንም ለማህበረሰቡ ዓይን አኩል ደረጃ ላይ ያስቀምጠናል። በዚህም መሠረት ደሞዜን በቅድሚያ ወስጀ ከተርኪ መደብር ጥንድ የእጅ ጓንቶችና ምርጥ ቆብ ገዛሁ። ጥቁር ጓንቶች በጣም ማራኪና ቆንጆ ይመስሉኛል። ደማቅ ቀለም ከሆነ ግን ሰውየው ጉራውን ለመንዛት የፈለገ ያስመስለዋል። ስለዚህም ነው ከባለደማቅ ቀለሞች ይልቅ ጥቁሩን የመረጥኩት። ከአጥንት የተሠራ የቁልፍ ጌጥ ያለው ምርጥ ሸሚዝ ቀደም ብዬ አዘጋጅቼ ነበር። የምደርበው ካፖርት ብቻ እቅዴን ከመፈፀም ለረዥም ጊዜ አዘገየኝ። ካፖርቴ መጥፎ አልነበረም። ቆንጆ ነው ይሞቃል። ነገር ግን በጨርቅ የተጣጠፈና ኮሌታውም ከራሱን ፀጉር የተሠራ ስለነበረ ዘበኛ ያስመስላል። ኮሌታው የግድ ወታደራዊ መኮንኖች እንደሚያደርጉት ዓይነት በቢቨር ፀጉር የግድ መለወጥ አለበት። እንዲህ ዓይነቱን ኮሌታ ለማግኘት ብዙ ካፈላለግኩ በኋላ

አንድ የጀርመን ርካሽ ቢቨር ኮሌታ ለመግዛት ወሰንኩ። እነዚህ የጀርመን ቢቨሮች ገላ ላይ ሲቆዩ ወዲያው የሚያከትምላቸው እላቂ ቢመስሉም በአዲስነታቸው ግን ይማርካሉ። እኔም የፈለግኩት ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው። ዋጋውን ስጠይቅ በጣም ተወደደብኝ። ብዙ ካሰብኩ በኋላ ገንዘቡን ለማሟላት ራሱን ኮሌታዬን ለመሸጥና ቀሪውን ደግሞ (በጣም ብዙ ነው) ከኛ መምሪያ ኃላፊ ከአንቶን አንቶኖቪችሴቶችኪን ለመበደር ወሰንኩ። አንቶን አንቶኖቪችሴቶችኪን ገንዘቡን ለማንም የማያበድር፤ ነገር ግን እኔን ሥራ ያስቀጠረኝ ባለከፍተኛ ማዕረግ፤ ከቸገረኝ እንዳነጋግረው የጠቆመኝ፤ ሞምት ግን ቁም ነገረኛና የሚመኩበት ሰው ነው። ብድሩን ለመጠየቅ የሊአል ያህል ተሰቃይቻለሁ። አንቶንአንቶኖቪችን ብድር መጠየቅ እንደሞራቅ አስፈራኝ፤ ሁለትና ሶስት ሌሊቶች!! በአጠቃላይ በዛን ሰሞን በጣም ትኩሳት ይሰማኝ ስለነበር እንቅልፍ የሚባል ነገር ባይኔ አልዞረም። ልቤ ወይ ይርገበገባል፤ አለዚያም ድንገት ድምድድም የሚል ይመስለኛል።...አንቶን አንቶኖቪች ጥያቄውን ሳቀርብለት መጀመሪያ የተገረመ መሰለ ከዛ ተኮሳተረ። ከዛም አሰበ። በመጨረሻም ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ የተበደርኩትን ብር ከደሞዜ ላይ እንዲቆርጥ ሥልጣን የሚሰጠውን ማስታወሻ ካስፈረመኝ በኋላ አበደረኝ። በዚህ መንገድ ሁሉም ነገር ተሟላ በአሰቀያሚው ራሱን ኮሌታ ቦታ የሚያምረው የጀርመን ቢቨር ኮሌታ ተተካ። ቀስ በቀስም የእቅዴን የመጨረሻ እርምጃዎች ለመውሰድ ተዘጋጀሁ። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ያለጠንቃቃ ዝግጅትና ያለጥልቅ ሃሣብ ሊሳካ አይችልም። በብልሃትና ያለችኩላ መደረግ አለበት። እዚህ ላይ ልደብቅ የማልችለው እቅዴን ለመተግበር ብዙ ሙከራ ካደረግኩ በኋላ ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩ። የሞከርኩትን ብሞክርም ልንጋጭ ግን አልቻልንም። ላደርግ የምችለው ነገርም አልነበረም። ሁሉንም ነገር አላዘጋጀሁም ነበርን? እቅዴን ለመፈፀም ቆርጬ አልነበረምን? እና ካሁን በኋላ በማንኛውም ደቂቃ እርስ በርስ የምንጋጭበት ጊዜ አልነበረምን?

ይሁን 'ንጂ ወሣኙ ሰዓት ሲመጣ እንደበፊቱ እኔ መንገድ ስለቅለት እሱም ልብ ሳይለኝ ያልፋል። እንዳውም እየተጠጋሁት ስሄድ እግዚአብሔር አምላክ ያሰብኩትን እፈፅም ዘንድ አስፈላጊውን ቆራጥነት እንዲሰጠኝ መፀለይ ጀመርኩ። አንድ ጊዜ ከልቤ ወስኜ እቅዱን ልፈፅም ጥቂት እርምጃዎች ብቻ ሲቀሩ ልቤ ስለከዳኝ ጅምሩ በኔ እግር ተጠላልፎ ፊት ለፊቱ በመዘረር አበቃ። እሱ ግን እርጋታ በሰፈነበት ሁኔታ ወደፊት ጉዞውን ስለቀጠለ እኔ ራሴን ለማዳን እንደኳስ ወደ አንድ ጐን ተንከባለልኩ። የዛን ዕለት ምሽት በትኩሳት ተውጬ ስባትት አደርኩ። ድንገት ግን ሁሉም ነገር በአጥጋቢ ሁኔታ ተፈፀመ። ምሽቱን ይህን ዕድለቢስ እቅዴን ላለመፈፀምና ሁሉንም ነገር ለመርሣት ወሰንኩና በኔቪስኪ ጐዳና ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ለሽርሽር ወጣሁ። የሽርሽሬ ዓላማ ሁሉንም ነገር እንዴት ለመርሳት እንደምችል ለማየት ነበር። ድንገት ከጠላቴ ፊት ለፊት ለመገጣጠም ሶስት እርምጃዎች ሲቀረኝ ጭራሽ ባልጠበቅኩትሁኔታ ወሰንኩና አይኔን ጨፍኜ ፊት ለፊት ተንደረደርኩና ትከሻ ለትከሻ ተላተምኩ። አንዲት ኢንች ወደኋላ ሳልል ፍፁም በሆነ የእኩይነት ስሜት አለፍኩት! እሱ ግን ጭራሽም ዞር አለማለት ብቻ ሣይሆን ምንም ያስተዋለ ሳይመስል ጉዞውን ቀጠለ። እርግጠኛ ነኝ ሊያስመስል ነውንጂ ተሰምቶታል። አዎ! በዚህ አሁንም ድረስ እርግጠኛ ነኝ። በርግጥ እሱ ጠንካራ ስለሆነ የከፋ ጉዳት ያገኘኝ እኔን ነው። ቁም ነገሩ ግን ይሄ አይደለም። ዋናው ነገር ያሰብኩትን መፈፀሜ ነው። ክብሬን አስጠብቄያለሁ። አንዲት ኢንች ፈቀቅ አላልኩለትም። በማህበራዊ ህይወት ደረጃም እኔ ከሱ እንደማላንስ በይፋ አስመስክሬያለሁ። ወደቤት ስመለስ ለሁሉም ውርደቴ በሚገባ እንደተበቀልኩ በደስታ ተጥለቅልቄ ነበር። ደስታዬን አልቻልኩትም። ነፍሴ ገነት ገብታ የጣልያን አርያስ ዘመርኩ። ይሄ በሆነ ከሶስት ቀን በኋላ ምን እንደደረሰብኝ ግን ልገልፅላችሁ አልችልም። የማስታወሻዬን የመጀመሪያ ምዕራፍ አንብባችሁ ከሆነ የደረሰብኝን መገመት ትችላላችሁ። መኩንኑ ከዚያ በኋላ ወደሌላ ቦታ ተዛወረ። ከዚያ በኋላ እስካሁን ድረስ ለአሥራ አራት ወራት አላየሁትም።

ውድ ጓደኛዬ አሁን እንዴት እንደሚኖር ላስበው ይገርመኛል። ማንን ይሆን የሚያሰቃየው?

የእንዲህ ዓይነቱ የሥቃይ እርካታዬ ካለፈ በኋላ ወዲያው አስፈሪ ባዶነትና የሥቃይ ስሜት ይሰማኛል። እንዳላስበው ግን የተቻለኝን አደርጋለሁ። ቀስ በቀስ ግን አሁንም እየለመድኩት መጣሁ። ሁሉንም ነገር እለምደዋለሁ። ወይም ደግሞ መለማመድ ሳይሆን ዝም ብዬ በሳቅ ላልፈውና ልሸከመው እወስናለሁ። ለሁሉም ነገር አንድ መፍትሔ አለኝ ይኸውም ክቡርና ቆንጆ በሆኑ ነገሮች ውስጥ በሕልም ዓለም ሕይወት ነፃነት መፈለግ ነው። መላ ሕይወቴን ለሕልም አሳልፌ አሰጣለሁ። በጉራዬ ጥግ ተሸጉጬ ሶስት ወር ሙሉ ላላቋርጥ አልማለሁ። እመኑኝ በእንዲህ ያለ ህልም ወቅት ያ በኔቪስኪ ጐዳና ላይ የጀርመን ቢቨር የካፖርቱ ኮሌታ ላይ ያሰፋውን ጨዋ ሰው ጨርሶ አልመስልም። ድንገት ጀግና እሆናለሁ። ሌላው ቀርቶ ባለሁለት ሜትር መኮንን ሊጐበኝ አቤቴ ቢመጣ እንኳ አላስገባውም። ጨረሶ ከኔ እኩል ላስበው አልችልም። ሕልሞቼ ስለምን እንደነበሩ እንዴትም ልረካባቸው እንደቻልኩ ለመናገር ያስቸግረኛል። ይሁን 'ንጂ ያረኩኝ ነበር። አሁን 'ንኳ ላስታውሰው የሆነ እርካታ ይሰማኛል። በህልሞቼ ውስጥ ልዩ ደስታ ማግኘት የምጀምረው የውርደት እርካታዎቼ ካለፉ በኋላ ነው። ንስሐና እንባ፣ ውግዘትና እርግማን ወደ ደስታ ይወስዱኛል በእንዲህ ዓይነት አስደሳች ስካር ጥልቅ ደስታ ከማግኘቴ የተነሣ በውስጤ ቅንጣት ታክል ፈገ የማይሰማኝ ወቅት አለ። ህልሜ የሚሰጠኝ እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ነበር። በነዛ ወቅት፣ ችግሩ ምን ነበር የሆነ ተአምር በሆነ ውጫዊነት የተነሣ ይሄ ሁሉ ድንገት ተስፋፍቶ እኔን ጠቃሚና ቆንጆ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ፍፁም የተዘጋጀ ሥራ (ሥራውን ምን ዓይነት እንደሆነ አላውቅም ትልቁ ነገር ግን አስቀድሞ ተየዘጋጀ መሆኑ ነው።) ይታየኝና በነጭ ፈረስ ላይ ሆኜ እራሴ ላይ የአበባ ጉንጉን አድርጌ ድንገት ወደቀን ብርሃን እወጣለሁ። በዚህ ወቅት ከህልሜ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ግምት የምስጠው ነገር ጭራሽ ባለመኖሩ የተነሣ በራሴ ምርጫና ደስታ በውነተኛ ዓለም ውስጥ

የምይዘው ቦታ የሌለ ያክል ነው። ጀግና ወይም ቆሻሻ፣ ሌላ አማራጭ አልነበረኝም። ይሄ እምነቴም የኔ ጥፋት ምክንያት ሆኖዋል። ምክንያቱም ቆሻሻ ውስጥ እየቦካሁ ሌላ ጊዜ ጀግና ነኝ እያልኩ ራሴን አፅናናለሁ። በዚህም ከቆሻሻው በላይ ጀግናው ተደረበ። ተራው ማቲ 'ንኳ አቧራ ውስጥ ለመንከባለል ያፍራል። ጅግና ግን እጅግ የተከበረ ነውና በአቡዋራ ሊሸፈን አይታሰብም። እና በዚህ አስተሳሰቤ የተነሣ ቆሻሻ ውስጥ ያለጭንቅ እለነቁጣለሁ። እንዲህ ዓይነቱ የክቡርና የቆንጆ ነገሮች ጥቃቅኑን በጣም አስገራሚ የሚያደርጋቸው በውርደት እርካታዬ ውስጥ በተለይ ደግሞ ስሜቴ ወርዶ ምድር በነካበት ሰዓት ጭምር መምጣታቸው ነው። አመጣጣቸውን ሳይጠብቁ በተለያየ ሁኔታ ቢሆንም መምጣታቸው ግን ሥርዓት የለሽ ሕይወቴን ሊያቆመው አልቻለም። በተቃራኒው የሚያባብሱት ይሆንብኛል። ቆይታቸውም ጥራል የለሽ ስሜቴን ለማጣፈጥ የሚጨመር ስጉ ያህል ነው። ይህ ስጎ ራስን በራስ የመመራመርን ቅራኔዎችና ሥቃይ የያዘ ነው። ውጋትና ህመሙ ለአፀያፊው የውርደት ደስታዬ ጣምና ትርጉም ይጨምርለታል። በአጭሩ የስጎንት ተግባሩን ያከናውናል። ይሄ ሁሉ የሆነው ጥብቅ ትርጉም አለው። ምክንያቱም እኔ እንደ አንዳንድ የቢሮ ፀሐፊዎች በቀላሉ ለድ ቂጥተኛና አሳዛኝ የሆነ ጥራለቢስ ሕይወት ውስጥ ለመኖርና የሱ ውጤት ከሆነው ጥንባትም ጋር ታርቄ ለመኖር ስለማልችል ነው። በምሽት ወደ ጉዳና የሚሰበኝ ሌላ ነገር እንዴት ላገኝ እችላለሁ? እመኑኝ ወንድሞቼ ለሁሉም ነገር የተከበረ ማምለጫ አለኝ.... ግን ያንተ ያለህ! በነዛ ሕልሞቼ ውስጥ ምን ያህል ፍቅር እንደማጣጥም፣ በነዛ ከቡርና ቆንጆ በሆኑ ነገሮች ኦርነትና ነፃነት በማገኝ ባቸው ሰዓታት የሚሰማኝ ፍቅር ከሥጋ ለበሱ ሰው ጋር ጭራሽ የማይገናኝ፤ እጅግ አጥለቅላቂ ፍቅር ስለሆነ በተግባር እንዲያውለው ፍላጐት የለኝም። ላድርግ ብልም የይስሙላ ድርጊት ነበር የሚሆነው። ሁሉንም ነገር ታዲያ የሚጠናቀቀው መሸጋገሪያው አጥለቅላቂ ደስታ ሆኖ ወደ ሥነጥበብ ማለትም ወደ ህላዊ ውብ ቅርጾች ሁሉም አስቀድሞ የተዘጋጁ፣ ከገጣሚያንና ከደራሲዎች በኃይል ተወስዶ ለያንዳንዱ ፍላጐትና አስፈላጊነቶች

እንዲሰማማ ሆኖ የተዘጋጀ ሕይወት! ለምሳሌ :- ሁሉም ነገር ላይ እሸናፊ እሆንና ሁሉም በራሳቸው ነፃ ፍላጐት የኔን ፍፁምነት ለመቀበል በመገደድ እግሬ ሥር ይደፉና እኔም እምራቸዋለሁ። እኔም ገነኛ ገጣሚና የቤተመንግሥት አጋፋሪ እሆንና ፍቅር ይይዘኛል። ከዛ ባለብዙ ሚሊዮን ባለቤት እሆንና ሐብቴን በሙሉ ለሰው ልጅ መሻሻል አውለዋለሁ። እዛው በዛው አስከፊና አሳፋሪ ወንጀሎቼን ሕዝቡ ፊት እናዘዛለሁ። ወንጀሎቹ ያን ያህል አስከፊና አሰፈሪ እንዳልሆኑ መግለፅ አስፈላጊ አይደልም። በውስጣቸው ግን «ክቡርና ቆንጆ» የሆነ ብዙ ነገር አላቸው፤ እንደማንፍራድ ዓይነት! ሃጢያቴን ስናዘዝ ሁሉም እያለቀሱ ይሰሙኛል (እንዲህ ባያደርጉ ምን ዓይነት የተረገሙ ጅሎች ይሆኑ) እኔም ከዚህ በኋላ ባዶ ሆዴን በባዶ እግሬ እየኳተንኩ አዳዲስ ሃሣቦችን ለመስበክና በቀልባሾች ላይ ሌላ ወተርሉ ልቀዳጅ እሄዳለሁ። ያን ጊዜ የሙዚቃ ባንዱ በሰልፍ የታጀበ ሙዚቃ ይጫወታል። አጠቃላይ ምህረት ይወርዳል። የሮማው ጳጳስም ወደ ብራዚል ለመሄድ ይስማማሉ። ኮሞ ሃይቅ ለዛ ልዩ በዓል ሲባል ወደሮም ከተማ እንዲመጣ ተደርገ ለመላው ጣልያን ኮሞ ሃይቅ ዳርቻ በተሠራው ቪላ ቤርጌሰ ታላቅ ድግስ ይጣላል። ይሄም እንዳበቃ በቴዋቂዎች ውስጥ በሚደረግ ትርኢት ይተካል። ወዘተ ወዘተ ወዘተ ይሀን አናውቅም እንዳትሉኝ! ጣራ ላይ ቆመህ አንባ እየፈሰስህ ሃጢያትህን በተናገርክበት አፍህ እንዲህ ዓይነት ነገር ጮኽህ መናገርህ ወራዳና ከቁም ነገር የማይፃፍ ነው ትላላችሁ። ግን! እስኪ አሰቡት ለምን ይሄ ወራዳ ይሆናል? እርግጠኛ ነኝ በዚህ እፍረት ተሰምቶታል ብላችሁ አታስቡም፤ አይደል? መቼም ይህ አሁን የምትቀባሸረው እስካሁን በሕይወት ውስጥ ከሆነው ሁሉ የላቀ ቀላልና ጅላጅል የሆነ ነገር ነው ብላችሁ እንደማታስቡ ነው የማምነው። ወንድሞቼ! የተወሰኑ ነገሮች ይህን ያህል አስከፊ በሆነ መንገድ የሠራሁዋቸው እንደልሆኑ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋ ለሁ።.... በእርግጥ ሁሉም ነገር ኮሞ ሃይቅ ዳርቻ ብቻ አይደለም የተፈፀመው። በርግጥ በዚህ በኩል እናንተ ትክክል ናችሁ። በርግጥም ወራዳና ከቁም ነገር የማይፃፍ ነው። የበለጠው ወራዳነት ግን አሁን የእኔን ትክክለኛነት ለናንተ

ለማስረዳት መሞከሬ ነው። ይሄ እዚህ ላይ ይብቃ። አለበለዛ ከቶም ልጨርሰው አልችልም። ለማንኛውም ነገሮች በዚህ ሁኔታ ይበልጥ ከብረቢስ እየሆኑ ነው የሚሄዱት።

ቅድም እንዳልኳችሁ ሶስት ወር ሙሉ ሳላቋርጥ ባልምም እኔ ወደማህብራዊ ሕይወት ውስጥ ዘልዬ ለመግባት የሚገፋፋኝ ያላቋረጠ ስሜት አለ። ነፃ ሆኜ ግን አይደለም። በኔ ሕይወት ውስጥ ማህበራዊ ሕይወትን መቀላቀል ማለት መምሪያ ኃላፊዬን አንቶን አንቶኖቪች ሴቶችኪን መጐብኘት ማለት ነው። በሕይወቴ ያፈራሁት ብቸኛው ቋሚ ትውውቅ እሱ ብቻ ነው። ይሄም ለራሴ ጭምር ላስበው ይገርመኛል። የምጐበኘው፤ ለጉብኝት ወደሰው እንድሄድ የሚገፋፋኝ ትክክለኛ ስሜት ውስጤ ሲፈጠር ነው። ሕልሞቼ የመጨረሻው ደስታ ሜፍ ላይ ሲደርሱ ወዲያውኑ ወገኖቼንና መላው የሰው ዘርን በሙሉ እቀፍ እቀፍ የሚያሰኝኝ ፈጣንና ልቋቋመው የማልችል ስሜት ሲያጥለቀልቀኝ ነው። ይህንን ለማድረግ አንድ ሰው ግድ ከሕልም ውጭ በውነተኛው ዓለም ውስጥ የሚኖር የእውነት አንድ ሰው ሊኖረው ይገባል። እንዲህም ሆኖ ታዲያ አንቶን አንቶኖቪችን ልጎበኝ የምችለው ማክሰኞ ማክሰኞ ብቻ ነው። (ማክሰኞ እቤት የሚያርፉበት ቀን ነው።) ስለዚህ የሰው ልጅን የማቀፍ ስሜቴን ማክሰኞ ለት ብቻ እንዲመጣልኝ ራሴን በራሴ ማዘጋጀት ግዴ ነው። አንቶን አንቶኖቪች ሴቶችኪን የሚኖረው ከኔ ሕንፃ አምስት ሕንፃዎች ማዶ አራተኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው ኣንዱ ካንዱ በቅደም ተከል ጠባብ ሆኖ የተሠሩ ኮርኒሳቸው ዝቅ ያሉ አራት ክፍሎች ውስጥ ነው። አብረውት ሁለት ሴት ልጆቹና ሻይ የምትቀዳላቸው አንድ አከስት ይኖራሉ። የልጆቹ ዕድሜ አሥራ ሶስትና አሥራ አራት ሲሆን ሁለቱም አፍንጫቸው ቅልብስ ያለና ስለኔ እየተንሾካሸኩ በማውራት ስለሚስቁብኝ ክፉኛ ያስፈሩኛል። አባታቸው ሁልጊዜ የሚገኘው በጥናት ክፍሉ ውስጥ ነው። ምንጊዜም ከዴስኩ ፊት ለፊት ባለው ከቆዳ በተሠራው ሶፋ ላይ ተቀምጦ ከኛ መምሪያ ከመጣ ሸበቶ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ከሌላ መምሪያ ከመጣ ሸበቶ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ከሌላ መምሪያ ከመጣ ጉብኚ ጋር ሲወያይ ነው የሚገኘው።

ከሁለትና ከሶስት የበለጡ ጉብኚዎች አይቼ አላውቅም። ሁሌም ደግሞ የሚያጋጥሙኝ እነሱ ናቸው። የሁልጊዜ የመወያያ ርዕሳቸው ኤክሳይዝ ቀረጥ፣ በመንግሥት ምክር ቤት ውሰጥ ስለተደረጉ ጠንካራ ክርክሮች፣ ደሞዝ፣ ሹመት፣ እሱን ለማስደሰት የሚደጋገሙ ከቡርነትዎ የሚለው ቃልና ወዘተ ወዘተ ከነሱ አጠገብ ሰሰዓታት ያህል ቁጭ ብዬ ለነሱ ለማውራት ሣልደፍር ወይም የምለውንም ሣላውቅ ልክ ዲዳ የሆንኩ ይመስል በዝምታ ሰሰዓታት አጠገባቸው የመቀመጥ ትግሥት አለኝ። በዚህ ቆይታዬ መሰላቸቴ እየጨመረ ላብ በላብ እሆንና ራሴን ስቼ እስክመወድቅ ሊያደርሰኝ የሚችል አደጋ ውስጥ እወድቃለሁ። እንዲህ መሆኔ ለኔ ጥሩና ጠቃሚ ነው። ወደቤቴ ስመለስ የሰው ዘርን ለማቀፍ የነበረኝን ፍላጐት ለሌላ ጊዜ አስተላልፈዋለሁ። በነገራችን ላይ አንድ ሊሞኖቭ የሚባል የድሮ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ የሆነ ሰው አውቃለሁ። እዚህ ፒተርስበርግ ውስጥ ብዙ የት/ቤት ጓደኞች እንዳሉኝ እገምታለሁ። ነገር ግን በምንም አጋጣሚ ስለማልገናኛቸው መንገድ ላይ ሣገኛቸው ሰላምታ መለዋወጡንም አቁሜያለሁ። እንዳውም ወደሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተዘዋወርኩበት ዋና ምክንያት ከነሱ ጋር ምንም ግንኙነት እንዲኖረኝ ሰላልፈለግኩ ነው። ምክንያቱም ራሴን ከነዛ አስጠሌታ የልጅነት ዓመታት ለማራቅ ስለምፈልግ ነው። ያ የት/ቤትና እነዛ የባርነት የሥቃይ ዓመታት ገደል ይግቡ! ባጭሩ ወደ ሌላ መሥሪያ ቤት ስዛወር ከሁሉም የት/ቤት ጓደኞቼ ጋር ተለያየሁ። መንገድ ሳገኛቸውም ሰላም የምላቸው ከሁለትና ከሶስት አይበልጡም። ከነሱ አንዱ በት/ቤት በጣም ጭምት ጥሩ ተፈጥሮ ያለው፣ ምንም እንኳ ይሄ ነው የሚባል ጉብዝና ባይኖረውም የሆነ የራሱ የሆነ መለያ ባህሪና ሃቀኛነት ጭምር ያለው ሊሞኖቭ ነበር። ፈዛዛ ነው ብዬ ጨርሶ አላሰብም። ለማንኛውም ያን ያህል ፈዛዛ አይደለም። ብዙ ባይቆዩምና በዚህም ሆነ በዛ መንገዱ ደብዛቸው ትዝታቸው ቢጠፋም በጋራ ያሳለፍናቸው ብዙ ጊዜያት ነበሩ። እነዚያን ጊዜያቶች ሳስታውሰው ደስታ እንደማይሰማው ይሰማኛል። ሲያገኘኝም እነዛን ነገሮች ድጋሚ የማነሳበት እየመሰለው የሚፈራ ይመስለኛል። እንደውም እኔን ማየት እንደሚቀፈው

አጠረጥራለሁ። ነገር ግን በጥርጣሬዬ አርግጠኛ ሰላልነበርኩ ልጠይቀው ከመሄድ አላገደኝም።

አንድ ሐሙስ ቀን ከስዓት በኋላ ብቸኝነቴን ጨርሶ መቋቋም አቃተኝና የአንቶን አንቶኖቪች በር ሐሙስ ሐሙስ ዝግ መሆኑን ስለማውቅ ሲሞኖቭን ልጐብኘው አሰብኩ። የሱ ክፍሎች ወደሚገኙበት አራተኛ ፎቅ ደረጀዎች በመውጣት ላይ እያለሁ እኔን ማየት እንደሚያንገሸግሸውና እንደሚያስጠላው በግሰብ የማደርገው ጉዞ ከንቱ መሆኑ ተሰማኝ። ግን እንደዚህ ዓይነት ሃሣቦች ሁሌም ራሴን አጣብቂኝ ሁኔታ ላይ እንዳስቀምጥ ይበልጥ የሚገፉፉኝ ስለነበር ቀጠልኩ። ሲሞኖቭን ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ከዓመት በፊት ነበር።

እቤቱ ስደርስ ሌሎች ሁለት የቀድሞ የት/ቤት ጓደኞቼን አገኘሁ። በአንድ ከፍተኛ ጉዳይ ላይ የሚወያዩ ይመስላሉ። ለዓመታት ያህል ተለያይተን የመቆየታችንን ያህል እኔን ሲያዩ ቅንጣት አለመገረማቸው በጣም ግራ አጋባኝ። እንደ አንድ ተራ ዝንብ እንደቆጠሩኝ ጥርጥር የለኝም። ምንም እንኳ ሁሉም በትምህርት ቤት ሕይወታችን ክፉኛ የሚጠሉኝ መሆኑን ባውቅም እንዲህ እንዳሁኑ ያህል ግን አድርገውኝ አያውቁም። በርግጥ በተሰማራሁበት የሲቪል ሥራ መሻሻል ለማሣየት ባለመቻሌ አያደርኩ በመኩሰሴ፤ አልባሌ አለባበስ ለብሼ መታየቴ ወዘተ እንዲንቁኝ እንዳደረጋቸው ተረድቻለሁ። በነሱ ዓይን የኔ ሁኔታ ውስጣዊ ብቃት አልባነቴንና ከቁጥር የማልገባ አልባሌ መሆኔን የሚያሣይ ነው ቢሆንም እንዲህ እንዳሁኑ ያህል ይንቁኛል ብዬ አላስብኩም። ሲሞኖቭ እንኳ በመምጣቴ የተሰማውን መደናገጥ መደበቅ አልቻለም። ለነገሩ ሲሞኖቭ እኔ ልጠይቀው በሄድኩ ጊዜ ሁሉ ይገርመዋል። ይህ ሁኔታ ስላበሳጨኝ ጐንጩን ነፍቼ አጠገባቸው በመቀመጥ ውይይታቸውን ማዳመጥ ቀጠልኩ።

የሚወያዩት ዚቨርኮቭ የተባለ ወታደራዊ መኩንን ጓደኛቸው በሥራ ምክንያት ወደ ሩቅ ክፍለ ሀገር መቀየሩን ምክንያት በማድረግ በነገው ዕለት

ሊያደርጉለት ስለሚፈልጉት የመሸኛ ግብዣ ነበር። ውይይታቸው በፍቅርና በስሜት የተሞላ ነበር። ዚቨርኮቭ ለኔም የት/ቤት ጓደኛዬ ሲሆን ወደከፍተኛ ትምህርት ስንደርስ ግን እየጠላሁት መጣሁ። አንደኛ ደረጃ ግለሁ በጣም መልከ መልካም ሁሉም የሚወደው ንቁ ልጅ ነበር። እኔም መልከ መልካምና ንቁ ልጅ ስለነበረ በተለይ ዝቅተኛ ክፍል በነበርንበት ጊዜ አየተቀጣጠርን እንጫወት ነበር። በትምህርት ጐበዝ ሆኖ አያውቅም። ጊዜው እያለፈ በሄደ ቁጥር የት/ቤት ችግሩ እየጨመረ ነው የመጣው። ነገር ግን ባለሥልጣን ዘመዶች ስለነበሩት ሠርተፊኬቱን የነፈገው የለም። ትምህርቱን ሊፈፅም የመጨረሻው ዓመት ላይ አንድ ዘመዱ ከፍተኛ የርሻ መሬት ከሁለት መቶ ጭሰኞች ጋር (ጭሰኞቹ ሁሉም ድሆች ነበሩ) አወረሱት። ከዚያ በኋላ መቦሰት ጀመረ። ያለቅጥ ስድ ነው። ነገር ግን እንደዛም ጉረኛ ሆኖ ተቀባይነት ያለው ሰው ነው። ከጥቂቶቻችን በስተቀር ብዙዎቹ በዘርኮቭፊት ያጐበድዱሉ። በጣም ጉረኛ እየሆነ በሄደ ቁጥር የሱን ተቀባይነት ለማግኘት ይበልጥ ይጣጣራል። እንዲህ የሚያጐበድዱት የሆነ ጥቅም ለማግኘት ብለው ሣይሆን ልጁ በተፈጥሮው አንዳንድ ስጦታዎችን የታደለ ስለሆነ ነው።

በተጨማሪም በሆነ ምክንያት ሁላችንም እሱን እንደዘናጭና የጥሩ ሥነ ሥርዓት አርአያ አድርገን እናየው ነበር። በተለይ የመጨረሻው ነጥብ በጣም ነበር የሚያናድደኝ። ችኩልና እኔ ነኝ የሚለው የአነጋገር ዘዬው በገዛ ቀልዶቹ የሚሰደስትበት ሁኔታ (ቀልዶቹ በጣም እዚህ ግቡ የማይባሉ ተራ ናቸው) የተነሣ በጣም እጠላው ነበር። በአነጋገሩ ሁሌም ደፋር ቢሆንም ቆንጆ ግን ደግሞ ፈዛዛ ፊቱን አልወድም ነበር። (በነገራችን ላይ ስለፊት ከተነሣ የሚቻል ቢሆን የኔን ንቁ ፊት በሱ ለመለወጥ ወደኋላ አልልም) ሌላው የምጠላበት በ1840ዎቹ እንደ ፋሽን ይታይ የነበረው ነፃና ቀበጥ ወታደራዊ ባህሪያቱ ነበሩ። የወደፊት የሕይወት ድሎቹን የሚያወራበትን ሁኔታም በጣም ነበር የምጠላው። በጊዜው የመኰንንነት ማዕረጉን ከማግኘቱ በፊት ከሴት ጋር ግንኙነት ለመጀመር ድፍረት አልነበረውም። በዚህ የተነሣ የመኮንንነት ማዕረጉን በጉጉት ነበር የጠበቀው! ሌላው የምጠላበት ነገር

ደግሞ መኩንንነቱን ከጨበጠ በኋላ በየደቂቃው ስለሚጋጠማቸው ፍልሚያዎች የሚያወራው ነበር። እኔ ሁልጊዜም ቱጥብና ጭምት ብሆንም አንድ ጊዜ ግን ዚቨርኮቭ ከጀሌዎቹ ጋር በዕረፍት ሰዓት ሲያወሩ እየተፍለቀለቀና እየተንከተከተ በውርስ ባገኘው የእርሻ መሬት ላይ የምትኖር አንድም ድንግል የገበሬ ልጅ እንደማትቀረውና በዚህም ጭሰኞቹ ለመቃወም ከደፈሩ ጀርባቸውን እንደሚያስገሸልጠው፤ ቀረጡንም በእጥፍ እንደሚያስጨምርባቸው በሚናገርበት ወቅት ኃይለኛ ከርከር እንደገጠመኩት አስታውሣለሁ። ጀሌዎቹ በአድናቆት ተቀብሉት፤ እኔ ግን በነገር ነክሼ ያዝኩት። ልጃገረዶቹ ወይም ቤተሰቦቻቸው አሳዝነውኝ ሣይሆን ይህንን የመሰለ ነፍሣት በማድነቃቸው በሽቄ ነው። በከርከሬ የበላይነት የያዝኩ ቢመስለኝም ዚቨርኮቭ ታላቅ ጅል ቢሆንም ቅሉ አፈቀላጤና ጀሊ ስለነበር እኔ ባነሣሁት ጉዳይ ላይ ምንም እንዳልተሰማው ሆኖ ሳቀበት። ሳቁም በግሩም ሁኔታ የተደረገ ስለነበር በመጨረሻም እኔ ሣልሆን አቨናሬው እሱ ሆነ። ምክንያቱም የሳቀው በኔ ላይ ነበር። ከዛም በኋላ በተደጋጋሚ አፈን አስይዞኛል። ዘዴውም እኔ በምለው የተናደደ ላይመስል እንደፈዝ እንደዋዛ መሳለቅ ነው። እኔ ለዚህ መልስ ሣልሰጥ በጥላቻና በንቀት በዝምታ አኮርፋለሁ።

ትምህርት እንደጨረስን ከኔ ጋር ጓደኛ ለመሆን ከፍተኛ ፍላጐት አላየ። እኔም ክፉኛ መቆላመጥ ስለተሰማኝ አልተቃወምኩም። ነገር ግን ብዙ አልቆየም ሊሆን አንደሚገባ ቀስ እያልን ተለያየን። ከዛ በኋላ በወታደር ቤት ውስጥ በሙቶ አልቅና ማዕረግ እየተሳካለት መምጣቱንና ደስተኛ ሕይወት እንደሚመራ ሰማሁ። በጦር ኃይሉ ውስጥ እድገት እያሣየ መምጣቱን የሚያረጋግጡ ሌሎች ጭምጭምታዎች ሰማሁ። እኔን ከመሰሉ እዚህ ግባ ከማይባል ሰው ጋር መታየቱን ስለፈራ ይመስለኛል መንገድ ላይ ሲያገኘኝ አይቶ እንዳላየ ዘግቶኝ ያልፋል። አንድ ጊዜ ቲያትር ቤት ውስጥ ማዕረጉን ገጥግጦ የሆኑ ሰዎች መካከል አየሁት። ለአንድ ጡረተኛ ጀኔራል ሴት ልጆች አክብሮቱን ለመግለፅ ሊልመጠመጥ ነበር። ቲያትር ቤት ውስጥ ሳየው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። መልኩ

እንደድሮው ቆንጆና ቀልጣፋ ቢሆንም የወጣትነት ገፅታው ግን ተቀይሯል። ከብደት በመጨመሩ ቦርጫም ይመስላል። ከዚህ በመነሣት ሰላሣ ዓመቱን ሲደፍን ሙሉ በሙሉ ድቡልቡልና ቦርጫም እንደሚሆን ይታያል። ለዚህ ለዚቨርኮቭ መሸኛ ነው እንግዲህ ጓደኞቹ የእራት ግብዣ ለማዘጋጀት የሚወያዩት። ምንም እንኳ በልባቸው የሱ አኩሪች እንዳልሆኑ ቢያውቁም በአደባባይ ግን የቅርብ ጓደኞቹ ናቸው። ከሲሞኖቭ ሁለት ጓደኞች መካከል አንዱ ፊርፊቸኪን ይባላል። የጀርመን ደም ያለበት ቀጫጫ ዝንጀሮ ፊት ሩስያዊ ነው። ከት/ቤት ሕይወቱ ጀምሮ ቆሽቴን ያደብኑት ከነበሩ ጠላቶቼ መካከል አንዱ ነው። ሁልጊዜ አክብሩኝ የሚል ስለከብር ግንዛቤ ያለው ለመምሰል ጉራ የሚነዛ በተፈጥሮው ግን አፀያፊ፣ ጋጠወጥ፣ ጉረኛና ልቡ ያበሰበሰ ፈሪ ነው። እሱ ማለት ለጥቃቅን ጥቅሞች ፍለጋ ሲሉ ለዚቨርኮቭ ከሚሰግዱ አጉብዳጆች መካከል አንዲ ነው። ሁልጊዜ ብር ይበደረዋል። ሌላው የሲሞኖቭ ጓደኛ ቱሩዶሊዩቦቭ የሚባል ሲሆን ረኸም፣ ፊቱ የማይፈታ ሃቀኛ ሊባል የሚችል ነገር ግን ስኪት ለተባለ ማንኛውንም ነገር ታላቅ አድናቂና ከዕደገትና ሹመት በስተቀር ሌላ ነገሮች ላይ ማውራት የማይችል ወታደራዊ መኩንን ነው። የዚቨርኮቭ የሩቅ ዘመድ ነው። ይህም ቁም ነገር ሆኖ በመካከላችን ተጨማሪ ክብር አስገኝቶለታል። እኔን የሚመለከተኝ እዚህ ግባ እንደማይባል ሰው አድርገው ቢሆንም ትሁት ነው ብዙም አያስከፋኝም።

ደህና! አለ ቱሩዶሊዮቦቭ «እያንደንዳችን ሰባት ሩብል ካዋጣን አንድ ላይ ሃያ አንድ ሩብል ስለሚሆን ቆንጆ እራት ለማዘጋጀት እንችላለን። ዚቨርኮቭን ለራሱ መሸኛ ልናስከፍለው አንችልም።»

«ይሄማ ሊታሰብም አይችልም።» አለሲሞኖቭ በመስማማት። «ጋባ ጉቹ እኛ እስከሆንን ድረስ እሱ እንግዳችን ነው። እንዳው ለነገሩስ እንከፈል ብንል ዚቨርኮቭ እሺ ይላል ብላችሁ ታስባላችሁ? የራቱንም እንድንከፍል ቢፈቅድልን እኛን ለማክበር በሉ ነውንጂ እርግጠኛ ነኝ ግማሽ ደርዘን ሻመፓኝ ለእራት ግብዣ ያወርዳል።» አለ ፊርፊችኪን አንድ እግረኛ

ወታደር ስለ አዛዡ ጀኔራል ሜዳልያና ማዕረግ እያደነቀ እንደሚያወራው ዓይነት።

«ለእራታችን ግማሽ ደርዘን ይበዛብናል። አይደለም 'ንዴ?» አለትርዶሊዮቦቭ ስለግማሽ ደርዘኑ ሻመፖኝ ብቻ ትኩረት በመስጠት። የእራት ግብግቡን ዝግጅት የሚያስተባብረው ሲሞኖቭ በመጨረሻ «እሺ! እንግዲህ ሶስታቸን ከዚቨርኮቭ ጋር አራታችንን በሃያ አንድ ሩብል! ራት ነገ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ በሆቴል ዲ ፓሪስ እንገናኝ!» ሲል ደመደመ።

በዚህን ጊዜ የተከፋው በመምሰል «በወቀጣ ስሜት ምን ማለታችሁ ነው ሃያ አንድ ስትሉ? እኔንም ከቆጠራችሁ ጠቅላላ ሃያ ስምንት ሩብልስ እንጂ ሃያ አንድ አይደለም» አልኩ።

እንደዚህ ድንገትና ሳልጠበቅ ለእራት ግብግቡ አስተዋፅኦ ለማድረግ በመነሣቴ በእኔ በኩል የተደረገ ጥሩ ስነ ስርዓት እነሱም ሃሣቤን በጥልቅ ስሜት ተቀበለው በአክብሮት የሚመለከቱኝ መስሎኝ ነበር።

ሲሞኖቭ ግን መከፋቱን ላይደብቅ ቀናም ብሎ ላያየኝ «ማዋጣት የምትፈልግ አይመስለኝም፤ ትፈልጋለህ?» በማለት አስተያየት ሰጠ።

እንደመፅሐፍ ነው የሚያነበኝ። እንዲህ እንደመፀሐፉ ሊያነበኝ በመቻሉ በንዴት በገንኩ።

«ለምን አላዋጣም? እኔ የድሮ የት/ቤት ጓደኛህ አይደለሁም እንዴ ? እና አንዲህ በቀላሉ መታለፌ እንዳስቆጣኝ ሣልገልፅ አላልፍም አልኩ።

ፈርፊችኪን በማንጓጠጥ ዓይነት ጣልቃ ገብቶ «ታዲያ የት ብለህ እንድናገኝህ ታስብ ነበር?» አለ። «ከዚቨርኮቭ ጋር ጥሩ ግንኙነት ኖሮዋችሁ አያውቅም። ይሄንን ታውቃለህ» አለ ትሩደሊዩቦቭ ፊቱን እያኮሳተረ።

እኔ ግን አንዲ ሃሣቡ ጭንቅላቴ ውስጥ ስለገባ በቀላሉ አልተውም ምን እንደነካኝ አላውቅም ድምጼ እየተንቀጠቀጠ እንዲህ አልኩ «ማንም ሰው በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየት የመስጠት መብት አለው ብዬ አላስብም።

እንደውም ከሱ ጋር ከዚህ በፊት ጥሩ ግንኙነት ስላልነበረኝ ሊሆን ይችላል አሁን ልንገናኝ የፈለግኩበት»

«በጣም ጥሩ» አለ ሲሞኖቭ መጨረሻ ላይ በመወሰን «እሺ ስምህን እንመዘግባለን ነገ በአሥራ አንድ ሰዓት ሆቴል ዲ ፖሪስ እንገናኝ እንዳትረሳ

«ገንዘቡስ?» አለ ፈርፊችኪን በማጉረምረም ዓይነት ወደኔ በማመልከት ለሲሞኖቭ። ነገር ግን በዚህ ጥያቄው ሲሞኖቭ ጭምር ስላፈረበት ማይጨርሰው ተወው።

«ግንኮ! ምን ጣጣ ነው። ይሄኮ የጥቂት ጓደኛሞች የአራት ግብግ ማለት 'ንጂ ሕዝባዊ ስብሰባ አይደለም። አብረንህ ልንሆን አንፈልግ እንደሆነስ በምን ታውቃለህ?» አለኝ ፈርፈችኪን ለመሄድ ቆቡን አያነሣ።

በዚህ ሁኔታ ሄዱ። ሲወጡ ፈርፈችኪን ደህና ዋል ሊለኝ አንኳ አልተቸገረም። ትርዶሊዩቦቭ ደግሞ ወደኔ ማይዞር ትከሻውን ነቅነቅ በማድረግ ብቻ ተሰናብቶኝ ሄደ። ሲሞኖቭ በአጠቃላይ ሁኔታው ግራ ከመጋባቱ የተነሣ በመገረም ተመለከተኝ። እሱም አልተቀመጠም እኔንም እንድቀመጥ አልጋበዘኝም።

«እምምም– አዎ! አዎ! ጥሩ እንግዲህ ገንዘቡን አሁን ልትሰጠኝ ትችላለህ? ማለቴ ለማወቅ የምፈልገው» አለ ሲሞኖቭ።

ጉንጩ ቀላ ። ልክ ይሄንን ሲለኝ ከዓመታት በፊት ያበደረኝንና እስካሁን ያልከፈልኩትን አሥራ አምስት ሩብልስ አስታወስኩና አፈርኩ።

«ግንኮ! ይሽውልህ ሲሞኖቭ ፣ አየህ ወዳንተ ስመጣ ስለዕራት ግብግቡ የማውቀው ነገር አልነበረም። ማለቴ ፣ ይቅርታ አድርግልኝ እረሣሁ።»

ደህና! ደህና! ደህና! ምንም ልዩነት አያመጣም። ገንዘቡን ነገ እራት ላይ ልትከፍለኝ ትችላለህ። የጠየቅኩህ ለማወቅ ያህል ነው። ስለዚህ እባክህ....» አለ ሲሞኖቭ።

ወሬውን በአጨሩ ቋጭቶ ከመቼውም በላይ መናደዱ እየታወቀበት ከፍሉ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ይንጐራደድ ጀመር።

እኔም ከሁለት ደቂቃ ፀጥታ በኋላ «የምትሄድበት ቦታ አለ 'ንዴ?» በማለት ጠየቅኩት።

ድንገት ደንገጥ በማለት «አይ..ይ የለም ማለቴ... በርግጥ አዎ። አየህ ካንድ ሰው ጋር እዚህ ቅርብ ቦታ ቀጠሮ አለኝ።» አለ በማፈርና በይቅርታ ጥያቄ ድምፅ።

«ያንተ ያለህ! ለምን አልነገርከኝም?» አልኩና ኮፍያዬን አነሣሁ።

ሲሞናቨ እበሩ ድረስ ከሸኘኝ በኋላ በመቻኮል «የቀጠሮዬ ቦታ ሩቅ አይደለም። እዚሁ አካባቢ ነው። ስለዚህ ነገ አሥራ አንድ ሰዓት! እንዳትረሣ» በማለት እኔ ደረጃውን በመውረድ ላይ እያለሁ ከኋላዬ ጮሆ ነገረኝ።

ወጥቼለት ስሄድ ደስታውን አልቻለውም። እኔ ግን በንዴት አበድኩ።

ዋናውን ሥንገድ ይገፎ ስሄድ ጥርሴን እያንቀጫቀጭኩ ምን ነካኝና ነው እመጣለሁ ያልኩት? ያውም ለዚህ ዓሳማ ዚቨርኮቭ ?! ለነገሩ አልሄድም። ሁሉም ነገር ገደል ይግባ! ምን በወጣኝ! ግድ የለብኝ። ውሣኔዬን ነገ ለሲሞናቨ አሣውቀዋለሁ። በደብዳቤ ማሳወቅ ነው። እያልኩ አጉረመረምኩ።

እውነተኛው የተናደድኩበት ምክንያት ግን መሄዴ እንደማይቀር በሚገባ ስላወቅኩ ነው። የምሄደው ሆን ብዩ ነው። አካሄዴ ያልተፈለገና ከብር ያልተሰጠው መሆኑ በተሰማኝ ቁጥር መሄዴ ይበልጥ እርግጠኛ ሆነ።

ላለመሄድ በቂ ምክንያት ነበረኝ። በመጀመሪያ ደረጃ ገንዘቡ የለኝም። በአጠቃላይ ያለኝ ዘጠኝ ሩብል ሲሆን ከዚህ ውስጥ ሰባቱ ሩብል ለአሽከሬ አፖሎ በነገው ዕለት የምከፍለው ወር ሃዊ ደሞዙ ነው። የሱን ገንዘብ አለመክፈል ማለት የማይታሰብ ነው። አፖሎ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ

አውቀዋለሁ። ስለዚህ እርሱ የኔ ሥቃይ ምንጭ የሆነ ግለሰብ ሌላ ጊዜ እነግራችኋለሁ።

ለማንኛውም ለሱ ገንዘቡን በነገው ዕለት እንደማልከፍለውና ወደጠላሁት የመቸኛ ራት ግብገር በእርግጠኝነት እንደምሄድ ታውቆኛል።

የዛን ዕለት ሌሊቱን በጣም አስከፊ በሆኑ ሕልሞች ስሰቃይ ማደሬ አያስገርምም። ምሽቱን በሙሉ የት/ቤቴ አስከፊ ጊዜያት በአእምሮዬ ሲመላለሱ ስለነበር በቀላሉ ልገላገላቸው አልቻልኩም። ወደ ት/ቤት የላኩኝ አስጠግተውኝ የነበሩ የሩቅ ዘመዶቼ ሲሆኑ ከት/ቤት በኋላ እስካሁን ድረስ ይሙቱ ይኑሩ የሰማሁት ነገር የለም። እኔ በነሱ ትችት ሞራሌ የተሰበረ ለሰዓታት ቁጭ ብዬ መተከዝ የለመደብኝ ሁሌም ዝምተኛና በዙሪያዬ ያሉትን ነገሮች በሙሉ በቅሬታ የምመለከት ወላጅ አልባ ልጅ እንደመሆኔ ት/ቤት ከተው ከተገላገሉኝ በኋላ አረሱኝ። የት/ቤት ጓደኛቼም እኔ እንደነሱ ስላልሆንኩ ብቻ ጥላቻ በተሞላና እርህራሄ በሌለው ተረብ አሰቃዩኝ። ተረብ ደግሞ በሕይወቴ ልቋቋመው የማልችል ብቸኛ ነገር ነበር። ሌሎች እንደሚያደርጉት በቀላሉ ጓደኝነት መመሥረት ለኔ የሚቻል አልነበረም ወዲያውኑ በሁሉም ላይ ከፍተኛ ጥላቻ አሳድሬ ወደራሴ የተዋረደ፣ የተሸማቀቀና የበዛ ኩራት ውስጥ ተከተትኩ። ጭካኔያቸው አስደነገጠኝ። በቁመናዬ ፣ በፊቴ ላይ ሁሉ በንቀት ይስቁብኛል። የነሱን ፊት ማን በነገራቸው! በኛ ት/ቤት የተማሪዎቹ ፊት እያደር አስገራሚ ለውጥ እያሳየና በተለይ በጣም ደደብ እየመሰለ ይሄዳል። መጀመሪያ ሲገቡ በጣም የሚያማምሩ ሕፃናት የነበሩት፣ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ግን የነሱ ፊት ሳያቅለሸልሸው የሚያያቸው አይኖርም። በአሥራ ስድስት ዓመቴ 'ንኳ በቅሬታ ነበር የማያቸው። በዛን ጊዜ 'ንኳ በሀሣባቸው አልባሌነት በሚጫወቱት ጨዋታና በሚያደርጉት ውይይት ጅላጅልነት በጣም እገረም ነበር። እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን 'ንኳ አይገነዘቡም ነበር። ከመደበኛ ነገር ውጭ የሆኑ ነገሮች 'ንኳ በጭራሽ አያስደስቱዋቸውም። ሃሣብ ሊያጭሩ በሚችሉ ነገሮች ሁሉ አይደሰቱም። በዚህ የተነሣ የበታቾቼ አድርጌ

እንዳስባቸው ተገደድኩ። እንዲህ እንድመለከታቸው ያደረገኝ የኔ የተጐዳ ሞራል እንዳይመስላችሁ። እና ደግሞ ባካችሁ፤ አንተ ማለት ዝም ብለህ ሕልመኛ ስትሆን እነሱ ግን በዛን ጊዜ እንኳን የሕይወትን እውነተኛ ትርጉም የተረዱ ነበሩ የሚል ዓይነት አቅለሸላሽ ተቃውሞ ይዛችሁ እንዳትመጡብኝ። የእውነቴን ነው የምላችሁ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ስለ እውነተኛ ሕይወት ቅንጣት ታሪክ ግንዛቤ አልነበራቸውም። እንዳውም ከአጠቃላይ ተፈጥሮዋቸው እጅግ ልታገሰው የማልችለው ይሄን ድክመታቸውን ነበር። በተቃራኒው ግን እጅግ ቁላልና እጅግ ተራ ለሆኑ ጉዳዮች በጣም የሚገርም አመለካከት ነበራቸው። ገና በዛ ዕድሜያቸው ስኪትን ብቻ የማድነቅ ልማድ ነበራቸው። ትክክል የሆኑ ነገር ግን በሌሎች የተናቁና የተጨቆኑ ማንኛውም ነገሮች ላይ ያለሀፍረትና እርህራሄ ይሣለቃሉ። ለነሱ አዋቂነት ማለት ማዕረግ ነበር። ገና በአሥራ ስድስት ዓመታቸው 'ንኳ በስሜት የሚወያዩበት ነገር ጥሩ ደሞዝ የሚያስገኙ ሥራዎችን ነው። ብዙ ባህሪያቸው በደደብነታቸው፤ በልጅነታቸውና በጉርምስናቸው ወቅት በዙሪያቸው የሚያጋጥማቸው መጥፎ ምሣሌዎች የፈጠሩባቸው ነው። ደግሞም ከፉኛ ጨካኞች ናቸው። ግን ደግሞ ከፉታቸው ውስጥ 'ንኳ የለጋነትና የጉርምስና ብልጭታ ይታያል። ግን ይህ ጉርምስና ምንም ውበት የለውም። እንደውም ብልግና ይመስልባቸዋል። እኔ ራሴ ከነሱ የከፉሁ እንደሆንኩ ባስብም አምርሬ ነበር የምጠላቸው። እነሱም በሰፈርኩት ቁና ሰፈሩኝ። ለኔ ያላቸውን ጥላቻ አይደብቁም። እኔ ደግሞ እነሱ እንዲወዱኝ ከቶም ፍላጐት አልነበረኝም። በተቃራኒው ሁሌም ላዋርዳቸው የምችልበትን ሁኔታ መናፈቅ ጀመርኩ። የነሱ መጣቂያ ላለመሆን ትምህርቴን ሆን ብዬ በትጋት መከታተል ጀመርኩና ወዲያውኑ ከከፍሉ ጐበዝ ተማሪዎች አንዱ ሆንኩ። ይሄ ደግሞ በነሱ ዘንድ ጥሩ ግምት አሳድሯል። ከዚህም በላይ ሁሉም ቀስ በቀስ እነሱ ሊያነቧቸው የማይችሉ መፅሐፍትን እኔ ቀድሜ ማንበብ የጀመርኩ መሆኔንና እነሱ ከዚህ በፊት ሰምተዋቸው ስለማያውቁ ነገሮች (በት/ቤት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የማይጠቃለሉ ነገሮችን) እኔ እንደምገነዘብ ተረዱ። ይሄንን ሁሉ በኩርፊያና

በቅሬታ ቢመለከቱትም መምህራኖቹ ግን ከጉብዝናዬ የተነሣ የተለያየ ትኩረት እንደሚሰጡኝ ሲመለከቱ በነሱ ላይ ያለኝን የሞራል የበላይነት ማመን ነበረባቸው። በዚህ የተነሣ ስላቃቸው ቢቆምም ጥላቻቸው ግን አልተቀየረም።

እናም ግንኙነቶቻችን ጣዕም አልባና ቀዝቃዛ ሆነ። በመጨረሻ ግን ልቋቋመው አልቻልኩም። እድሜዬ እየጨመረ በመጣ ቁጥር ማህበረሰቡን የመቅረብና ጓደኛ የማፍራት ፍላጐቴ እየጨመረ መጣ። ከተወለኑት ጋር ጓደኛ ለመሆን ሞከርኩ። ነገር ግን ከነሱም ጋር የምፈጥረው ጓደኝነት ሁልጊዜም እንግዳ ይመስል ነበረና ራሱ በራሱ ተቀጨ። በእርግጥ አንዴ የሆነ ጓደኛ ነገር ይገዙ ነበር። በዛን ጊዜ ግን ልቤ አምባገነን ሆኖ ነበር። በሱ ላይ ሙሉ ሥልጣኔን ለመጫን ፈለግኩ። በልቡ ውስጥ ለአካባቢው ንቀት እንዲያድርበት ለማድረግ ፈለግኩ። እነዚህ አካባቢዎቹንም ንቆ እርም ብሎ እንዲተዋቸው አስገደድኩት። ስሜት በተሞላው ጓደኝነቱ አሰጨነቅኩት። አስለቀስኩት፤ ግራ አጋባሁት። ልጅ ንፁህና ታማኝ ነፍስ ያለው ነበር። ሙሉ በሙሉ በኔ ቁጥጥር ሥር እንዳዋልኩት ሳውቅ እየጠላሁት መጣሁ። ፍላጐቴ ሁሉ በሱ ላይ ሙሉ ቁጥጥር ኖሮኝ ሙሉ በሙሉ በኔ ሥር ሆኖ ለማየት የፈለግኩ ይመስል ብቻ ከዛ በኋላ ካጠገቤ አባረርኩት። ይህ ጓደኛዬ በእርግጥ እንደሌሎቹ ዓይነት አልነበረም። ሁሌ ሣይሆን አልፎ አልፎ የሚገኝ ዓይነት ሰው ነበር። ት/ቤት እንደጨረስኩ መጀመሪያ ያደረግኩት ነገር ካለፈው ሕይወቴ ጋር የሚያገናኘኝን ማንኛውንም ነገሮች ለማስወገድ ስል የሰለጠንኩበትን ሥራ መተው ነበር። ከዚህ ሁሉ በኋላ እንግዲህ ይህንን ሲሞኖቭ ለመጠየቅ ምን ቅብጥ አርጐኝ ልጠይቅ እንደሄድኩ ከቶም አይገባኝም!.....

በበነጋታው ጠዋት ሁሉም ነገር እዛውና አሁን የሚደረግ ይመስል በከፍተኛ ስሜት ካልጋዬ ዘልዬ ወረድኩ። እስካሁን ከኖርኩት ሕይወት ጋር ሥር ነቀል በሆነ መንገድ የሚያቆራርጠኝ ነገር እንደሚከሰትና ይህም የሚሆነው በዚህ ዕለት እንደሚሆን አምኜ ነበር። የለውጥ ልምድ ስለሌለኝ

ይሆን ወይም በሌላ ምክንያት አላውቅም ብቻ መላ ሕይወቴን ሙሉ ትንሽም ነገር እንኳ ሲያጋጥመኝ ወዲያውኑ ሕይወቴን ሙሉ ለሙሉ የሚቀይረው መስሎ ይሰማኛል። ይሁን 'ንጂ እንደተለመደው ወደቢሮዬ ብሄድም ለግብጥው ለመዘጋጀት ስል ከሥራ መውጫ ሁለት ሰዓታት ያህል ቀደም ብዬ ሾልኬ ወደቤት መጣሁ። ዋና ቁም ነገር የሆነብኝ ግብጥው ላይ በተለይ ቀድሜ አለመገኘት ነበር። ምክንያቱም ከነሱ ጋር ለመሆን የጓጓሁ እንዳያስመስለኝ ነበር። ብቻ እንዲህ ዓይነት በሺ የሚቆጠሩ ሀሣቦች ስለነበሩኝ መጨረሻ ላይ አካላዊ ድካም እስኪሰማኝ ድረስ ሰቀዙኝ።

ጫማዬን ለሁለተኛ ጊዜ ቀለም ቀባሁ። እንደወትሮው አፖሉን እንዲያፀዳልኝ አላዘዝኩትም። እሱ ይሞታታል 'ንጂ አንድ ጫማን በቀን ሁለት ጊዜ አይወለውልም። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በሱ ግምት እጅግ ከሰው የማይጠበቅ ሥርዓት አልባነት ነው። ከዛ በኋላ የምለብሰውን ለመምረጥ ልብሶቼን በጥንቃቄ መመልከት ስጀምር ሁሉም ያረጁ፣ የነተቡና ምናምን የተንጠባጠበባቸው ሆነው አገኘሁዋቸው። እያደር ሰው ፊት ስለሚኖረኝ ገፅታ ግድየለሽ እየሆንኩ መምጣቴ እርግጥ ነው። ከልብሶቼ ሁሉ የሥራ ልብሴ ይሻል ነበር። ይሁን 'ንጂ እሱንም ለብሼ እራት ግብዣ ልሄድ አልችልም። ይቻላል 'ንዴ? በጣም አሳፋሪው ነገር ደግሞ ሱሪዬ ጉልበቱ ላይ የሆነ ትልቅ ቢጫ ነጥብ አለበት። ይሄ ነጠብጣብ ብቻውን እንኳ ካለኝ የራስ አክብሮት ላይ ዘጠኝ አሥረኛውን እንደሚነጥቀኝ ተሰማኝ። ይሄም ጨርሶ ልጨነቅበት የማይገባ ጉዳይ እንደሆነ አውቃለሁ። ስሜቱ በወደቀ ልቤ «ይሄ የማሰቢያ ጊዜ አይደለም። አሁን ከእውነት ጋር መፋጠጥ አለብኝ።» ብዬ አሰብኩ። በዚህን ሰዓት ነገሮችን ያለመጠን እያጋነንኩ ጭራቅ አድርጌ ማቅረቤን በሚገባ አውቃለሁ። ግን ምን ማድረግ እችላለሁ? ስሜቶቼን ለመቆጣጠር የማልችልበት ሁኔታ ላይ ደርሻለሁ። በትኩሳትም እየተንቀጠቀጥኩ ነው። ያ! በስባሳ ዚቨርኮቭ የሚባል ጉድ እንዴት ባለ የበላይነትና ቀዝቃዛ ስሜት እንደሚመለከተኝ በተስፋ መቁረጥ አሰብኩ። ያ! ድንጋይ አራስ ቱርዶሊዮቦቭ እንዴት ባለ ቀዝቃዛ ንቀት

እንደሚመለከተኝ መጣብኝ። ያ! ተባይ ፊርፊችኪን በዛ ባለጌ ተፈጥሮው በዚቨርኮቭ ለመወደስ ሲል ብቻ እንዴት አድርጐ አሳፈን እንደሚያበላኝ ታሰበኝ። ሲሞኖቭም ይሄንን ሁሉ ነገር ተገንዝቦ የእኔን የማንነቴን ተራነትና መንፈስ አልባነቴን ከሁሉም በላይ ደግሞ የሁሉንም ነገር ተራነት በመገንዘብ እንዴት አድርጐ እንደሚንቀኝ ታሰበኝ። በእርግጥ ማድረግ ያለብኝ ትክክለኛ ነገር ጭራሽ አለመሄድ ነው። ይሄ ግን ጨርሶ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። አንዴ ወደ አንድ ነገር ከተሳብኩ ግንባሬን አስቀድሜ ነው ድርግም የምለው። እንደዛ ባላደርግ ቀሪ ሕይወቴን በሙሉ በራሴ ላይ እንዳፌዝኩ ነው የምኖረው። «ይኸው አየንልህ፤ ሕይወት አስፈራችህ አይደል? ሕይወትን ፈራህ! ፈሪ!» እያልኩ። በተቃራኒው እኔ ራሴ እንደማስበው ፈሪ እንዳልሆንኩ ለማሳየት ከፉኛ ጓጓሁኝ። ይሄም ብቻ አልነበረም በተቀሰቀሰብኝ ድንገተኛ የፍርሃት ትኩሳት በነሱ ላይ ተራቅቄ የበላይነት በመጨበጥ የኔን ድንቅ ሃሳቦችና የማያከራክር የአእምሮ ስልነት አድናቆት ሊያድርባቸው ግለም ጀመርኩ። ዚቨርኮቭ በኔ የበላይነት ሙሉ በሙሉ ተዳሽቆ ጓደኞቹ ጀርባቸውን ለጥተውት አንዲት ጥግ ቦታ ላይ አንገቱን ደፍቶ ተቀምጦ ታሰበኝ። ከዛ እኔም ዜቨርኮቭን አባብለውና ለዘላቂዊ ጓደኝነታችን ዋንጫችንን እናነሣለን። ነገር ግን እጅግ ቆሸቴን የሚያደብነው ነገር ምንድነው፤ ይሄን ላልም 'ንጂ ውስጤ ግን ከህልሜ ውስጥ አንዱንም እንደማይፈልገው፡ እነሱን የመብለጥ፤ የማኮሰስና እንደኔ የማድረግ ፍላጐት እንደሌለኝ ያለ ቅንጣት ጥርጥር መገንዘቤ ነው። ያ ቀን አልፎ አይቹ! በማለት እንዴት ፀለይኩ መሰላችሁ። ስሜቴ ብዙ ስለተጐሳቆለ ወደ መስኮቱ ደጋግሜ በመመላለስ የሚዘንበው በረዶ በፈጠረው አድማስ ላይ አፈጠጥኩ።...

መጨረሻ ላይ ሰዓቴ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ጮኸ። የወር ደሞዙን ከጠዋት ጀምሮ ሲጠብቅ የነበረውና ነገር ግን በሞኝነቱ የተነሣ ቀድሞ ሊነግረኝ የፈራውን አፖሎ እንዳላየሁት ሆኜ ቆቤን አንስቼ በአጠገቡ በማለፍ ያለችኝን አሥራ አምስት ኮፒክ በመክፈል ጋሪ ተከናትራ ወደ ሆቴል ዴ-ፓሪስ አመራሁ።

መጀመሪያ የምደርሰው እኔ እንደምሆን ስሜቱ ነበረኝ። አሁን ግን ጥያቄው ቀድሞ የመድረስ ወይም ያለመድረስ አልሆነም። እነሱን እዛ አለማግኘት ብቻ ሣይሆን ለእራት ግብግቡ የተዘጋጀውንም ክፍል ማግኘት አቃተኝ፤ የተዘጋጀም ጠረጴዛ አልነበረም። ምን ማለት ነው? ከብዙ መጠይቅ በኋላ መጨረሻ ላይ አስተናጋጆቹ ሲነግሩኝ እራቱ እንዲዘጋጅ የተጠየቀው ለአሥራ ሁለት ሰዓት ገኚ ለአሥራ አንድ ሰዓት አልነበረም። የሆቴሉ ቡና ቤት ይህንን አረጋገጠልኝ። እነዚህን ጥያቄዎች ደጋግሞ መጠየቅ አሳፈረኝ። ሰዓቱ ገና አሰራ አንድ ከሃያ አምስት ነበር። የራት ሰዓቱን ከቀየሩ ቢያንስ ሊያሣውቁኝ ይገባ ነበር። የፖስታ ጥቅሙ ምንድን ነው? እንዲህ በማድረግ በራሴ ዓይን (አርግጠኛ ነኝ ባስተናጋጆቹ ዓይን ሊሆን አይችልም) ለእንዲህ ያለ ውርደት ላያጋልጡኝ ይችሉ ነበር። አንድ አስተናጋጅ ጠረጴዛዎችን ማዘጋጀት ጀመረ። እሱን ላይ ደግሞ ይበልጥ አፈርኩ። ወደ አሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ከፋኖሶቹ በተጨማሪ ሻማም መለኮስ ጀመሩ። ይህንን ሥራ አስተናጋጁ እኔ በደረስኩበት ሰዓት ለመጀመር ሃሣቡም አልነበረውም። የሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ሁለት ያኮረፉ ሰዎች የተለያየ ጠረጴዛ ላይ እራታቸውን ይበላሉ። ሊያዩዋቸው የተናደዱ ይመስላሉ። አይነጋገሩም። ሌሎች ሰዎች ደግሞ ሌሎች ክፍሎች ውስጥ አምባጓሮ ፈጥረው ከጣራ በላይ ይጮሃሉ። ሣቃቸው ከጣራ በላይ ይሰማል። በጣልቃው አንዳንድ የፊረንሣይኛ ቃላቶች የሚሰሙባቸው ጆሮ የሚቀዱ ካካታዎችም ይሰማል። ሴቶች ያሉበት የራት ግብግቡ ነው። በአጭሩ ሁሉም ነገር ከዚህ የበለጠ አስከፊ ሊሆን አይችልም።

ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት መጥፎ ነገር ያጋጠመኝን ቀን አላስታውስም። ልክ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ሁሉም ተያይዘው መጡ። ላያቸው መጀመሪያ የተሰማኝ ሰሜት እነሱ ልክ የኔ ነፃ አውጭ የሆኑ ይመስል ደስታ ነበር። መቀየሜን ግላየት እነደነበረብኝ ጨርሶ ረሣሁ። እንደ ቡድን መሪነቱ ቀድሞ የገባው ዚቨርኮቭ ነበር። ይሣሣቃሉ። ዚቨርኮቭ እኔን እንዳየኝ ሰብሰብ አለና ወደኔ በገሣታ በመራመድ ምን ዓይነት ጨዋ ሰው

መሆኑን ለማሳየት ይመስል ከወገቡ ትንሽ ጐንበስ አለ። ብዙም ሣይሆን ጥንቃቄ በተሞላበት ትህትና ልክ ጄኔራል የሆነ ይመስል እኔን ከሆነ ነገር የሚጠብቀኝና የሚያድነኝ በሚመስል እኳኋን ጨበጠኝ።

እኔ ግን አስቤው የነበረው ከመጣ ድሮ እንደማውቀው ልማዱ ከትከት ብሎ በማሾካካት ያን የተለመደ ቂላቂል ቀልዶቹንና የአነጋገር ዘይቤውን በማስቀደም የምንጨባበጥ ነበር ለዚህ ዓይነት አቀባብሎ የምስጠውን አፀፌታው ምላሽ ነበር ከትላንት ምሽት ጀምሮ ስዘጋጅበት የቆየሁት። እንዲህ ዓይነት የባለሥልጣን ዓይነት አቀራረብ አልጠበቅኩም ነበር። በሁሉም ረገድ የበላይ እንደሆነ አድርጐ ራሱ አስቧል ማለት ነው አይደል? በዚህ በሚያሣየው የበላይነት መንፈስ እኔን ሊሰድበኝ አስቦ ከሆነ ምንም አይደል አልኩኝ ለራሴ። ነገር ግን እኔን ለማስቀየም ብሎ ሣይሆን በሞኝነቱ የተነሣ ያለቅጥ ከኔ በላይ የሆነና እንደኔ ዓይነቱን ሰው በሀዘንና በርህራሄ ሊመለከት እንደሚገባ አምኖስ ቢሆን? ሃሣቡ በራሱ በጥላቻ ተናነቀኝ።

ከዚህቀደም አድርጐት በማያውቀው ሁኔታ አፉን እያጣጣመና ከንፈሩን እየመጠጠ «ከኛ ጋር ለመሆን መፈለግህን ስሰማ በጣም ገረመኝ። በቅርቡ ብዙም ተያይተን አናውቅም። እኛን የምትሸሽ ይመስላል። ያሳዝናል። አንተ እንደምታስበው ያህል ከሱ አይደለንም። ለማንኛውም እንደገና ለ–መ–ቀ..ጠል ደስተኛ ነኝ።» አለ። ንግግሩን እየተናገረ ኮፍያውን መስኮቱ መስቀያ ላይ ሊያስቀምጥ ዞር አለ።

«ብዙ ጠበቅከን 'ንዴ?» አለትሩዶሊዩቦቭ። እኔም ብስጭቴን በሚያሣይ ሰሚት ከፍ ባለ ድምፅ «ትላንት በነገራችሁኝ መሠረት እዚህ የደረስኩት አናቱ ላይ አሥራ አንድ ሰዓት ነው» አልኩ።

ትሩዶሊዩቦቭ ወደ ሊሞናቭ በመዞር «የሰዓቱን መቀየር አልነገርከውም 'ንዴ?» ሲል ጠየቀ።

ሲሞኖቭ ያለምንም ፀፀትና የይቅርታ ቃል «አ! የነገርኩት አይመስለኝም፤ ሁሉንም ነገር ረሣሁት» በማለት በመጀመሪያው ዙር የሚቀርበውን የምግብ ዓይነት ለማዘዝ ሄደ።

ዚቭርኮቭም ይሄ በሱ ግምት አስቂኝ ነገር ስለነበር በምፀት «ምስኪን! እና ድፍን አንድ ሰዓት ጠበቅከን ማለት ነው?» አለ ፎሆ።

ያ ተባይ ፊርፊችኪን ግን እንደሚያዛጋ ቡችላ እያሽካካ ተንከተከተብኝ።

አጠቃላይ ሁኔታዬ በጣም አስቂኝና በቃላት የማይገለፅ አሳፋሪ ሆነብኝ። እኔም ይበልጥ በመናደድ ፊርፊችኪን ላይ «ይሄ ምንም የሚያስቅ ነገር የለውም። ይሄ የኔ ሣይሆን የናንተ ስህተት ነው። ለማንኛውም የሰዓቱ መለወጥ ሊነገረኝ የሚገባው ሆኜ እንዳላገኛችሁኝ ነው የሚሰማኝ። ይሄ ደሞ በቀላሉ ደደብነት ነው!» ስል ፎህኩበት።

ትሩዶሊዩቦቭ በቀልድ ስሜት ለኔ በመወገን «ይሄ ደደብነት ብቻ ሣይሆን ሌላም ነገር ነው። አንተ ይልቅ አለሳለስከው። ይሄ ስድብም ነው። ሆነ ተብሎ የተደረገ ባይሆንም! እንዴት ግን ሲሞኖቭ ደህና!» አለ።

ፊርፊችኪንም «እንዲህ ዓይነት ቀልድ የተፈፀመው በኔ ላይ ቢሆን ኖሮ እ__» ሲል ዚቭርኮቭ አቋረጠውና «የሆነ ነገር ታገዝ ነበር። ወይም እኛን ሳትጠብቅ ራትህን ትበላ ነበር።» አለ።

እኔም በቁጣ «ይህንን ያለናንተ ፈቃድ ማድረግ እችል እንደነበር ልታምኑ ይገባል። የጠበቅኳችሁ እኩ____»

«ገበገዝ እንቀመጥ» አለ ሲሞኖቭ ወደኛ በመምጣት። «ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል። ስለሻምፓኝም ቢሆን በኩራት መናገር እችላለሁ። እጅግ በሚያስደስት ሁኔታ ቀዝቅዟል።» ድንገት ወደኔ በከፊል ዞር ብሎ ግን እኔን ባለማየት «ይቅርታ! አድራሻህን አላወቅኩትምና ላገኝህ አልቻልኩም። እችል ነበር?» አለኝ።

ሲሞኖቭ ትላንት ምሽት ካገኘሁት በኋላ የተቀየመበት ነገር አለ ማለት ነው። ሁሉም ሲቀመጡ እኔም ተቀመጥኩ። ጠረጴዛው ክብ ነው። ትሩዶሊዩቦቭ ከኔ በስተግራ ሲሞኖቭ ከኔ በስተቀኝ ተቀመጡ። ፊት ለፊቴ ደግሞ ዚቨርኮቭና ፊርፊችኪንን ተቀምጠዋል።

ዚቨርኮቭ ለኔ ትኩረት በመስጠት « እ...እስኪ አ–ባ...ክህ እ...አሁንም በሲቪል መሥሪያ ቤት ውስጥ ነው ያለኸው? እስኪ ንገረኝ»

እንዴት አንዳፈርኩ በማየት በህዘኔታ የተነሣ እኔን እኩልነት እንዲሰማኝ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ያህል ነው የተመለከተኝ።

«ይሄ ሰውዬ ጭንቅላቱን በጠርሙስ እንድለው ይፈልጋል 'ንዴ» አልኩ በሃሣቤ። ለእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ልምድ ስላልነበረኝ ቶሎ ቆጣ ቆጣ አልኩ።

አይኖቼን ከሰሀኑ ላይ ሳልነቅል «አ! አዎ» አልኩ።

«ያንተ ያለህ! የ– ተሻ– ለ ሆኖ አገኘ – ኸው ማለት ነው? የቀድሞ ሥራህን እንድትተው ምን እ– ን – ዳነ– ሳሳ – ህ እስኪ እባ.. ክህ ንገረኝ?» አለ በመቀጠል።

ከንዴቴ የተነሣ ራሴን መቆጣጠር አቅቶኝ ቃላቶቹን ከሱ ሶስት እጥፍ ያህል በመለጠጥ «የቀድሞ ሥራዬን እንድተው ያነ... ሳ... ሳኝ በቃ መሰልቸቴ ነው።» አልኩት።

ፊርፊችኪን አንቋረረ። ሲሞኖቭ በምፀት ገረመመኝ። ትሩዶሊዩቦቭ መብላቱን አቁሞ በትኩረት አስተዋለኝ። ዚቨርኮቭ ግን ምንም እንዳልተሰማው ሆነና «ደ– ህ – ና! መንቀላቀሻህ ስንት ነው?»

«የምን መንቀላቀሻ?»

« ማ– ለቴ፣ ደ..ምዝህ?»

መቼም መስቀለኛ ጥያቄ እያቀረበልኝ እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ።

ይሁን 'ንጂ ደሞዜን ነገርኩት። ከፉኛ አፈርኩ።

ዚቨርኮቭ በመኩራራት «ብዙ አይደለም» አለ።

«በጭራሽ!» አለ ፊርፊችኪን በንቀት። «በአንድ ሬስቶራንት ለእራት 'ንኳ የማትበቃ ናት» አለ።

ትሩዶሊዮቦቭ «በአጠቃላይ የልሞና ሥራ ያህል ነው።» አለ የምሩን

ዚቨርኮቭ በንቀት እርህራሄ ልብሶቹን ከቃኘ በኋላ «ደግም ከሳህ! እ... ከነዚያ ጊዜያት ጀምሮ እንዴት ነው የተለወጥከው?»

«ምስኪኑን አታሳፍሩት እባካችሁ!» አለ ፊችፊችኪን እየሣቀ።

መጨረሻ ላይ አልቻልኩም። «ተሳስተሃል የኔ ጌታ!» አልኩ። «ቅንጣት ታክል አላፈርኩም። ትሰማለህ እኔ ከ እዚህ ሬስቶራንት የምበላው በራሴ ገንዘብ 'ንጂ በሌሎች ወጪ አይደለም። ይህንን ብታስተውል ጥሩ ነው ፊርፊችኪን!....»

ፊርፊችኪን በቁጣ ፍም መስሎ ወደኔ በመጠጋት «ምን ለማለት ፈልገህ ነው? ማነው እዚህ በሌሎች ወጪ ራቱን እየበላ ያለ? ለማለት ያሰብክ የሚመስለው»

አላስጨረስኩትም። ትንሽ ቀበጥ ማለቴ እየተሰማኝ «ያልኩት ለማለት የፈለግኩትን ነው። ነገር ግን ሌላ የተሻለ ኢንተልጀንት የሆነ ነገር ብናወራ ይሻላል።» አልኩ።

«መቼም ያለህን እውቀት ልታሳየን የፈለግክ አይመስለኝም። ነው 'ንዴ?»

«እኔ አንተን ብሆን ይሄ ሊያስጨንቀኝ አይገባም። ምክንያቱም አስፈላጊ ጉዳይ አይደለምና» አልኩ።

«ጌታው! ምንድነው ባክህ የምታወራው? መቼም እዛ መሥሪያ ቤትህ ያበድክ አይመስለኝም። ነው 'ንዴ?»

ዚቨርኮቭ በአለቃ ድምፅ «በቃ! በቃ! ወዳጆቼ።» አለ

«እንዴት ያለጅላጅል ነው!» አለ ሲሞኖቭ በማጕረምረም።

ትሩዶሊዮቦቭ ወደኔ በመዞር «ጅላጅል እንኺ! እኛ እዚህ ጥቂት ጓደኛሞች ተሰብስበን ለአንድ ጓደኛችን መልካም ምኞታችንን ለመግለፅ ነው የመጣነው። አንተ ግን እዚህ የድሮ ቂምህን ለመወጣት እየፈለግክ ነው። ራስህነህ ትላንት ከናንተ ጋር ልሁን ብለህ ራስህን የጋበዝክ» ለምንድ ነው ታዲያ የግብግቦውን የወንድማማችነት ስሜት የምትረብሸው?» አለኝ።

« በቃ! በቃ!» አለ ዚቨርኮቭ በድጋሚ «ይህንን ነገር ተውት ወዳጆቼ! ቦታውም ሆነ ጊዚው ለአምባጓሮ አያመችም። ይልቅስ ባለፈው ጊዜ ካንዲ ጋር እንዴት ልጋባ አፋፍ ላይ ደርሼ እንደነበር ልንገራችሁ» አለ።

ከዛ በኋላ ከጥቂት ቀናት በፊት ካንዲት ሴት ጋር እንደቀልድ ተግባብቶ ምን ያህል ለጋብቻ አፋፍ ላይ ደርሰው እንደነበር መተረኩን ቀጠለ። በነገራችን ላይ ስለጋብቻ ያወራው ነገር የለም። ታሪኩ በአጠቃላይ ስለ ጂኔራሎች ስለ ኮሎኔሎችና አልፎ ተርፎም ስለ ቤተመንግሥት አጋፋሪዎች ጭምር ነው። ወሬውን የሁሉም የደስታ ማቅ አጀበው። የፊርፊችኪን ቀጭን ሳቅ ከፍሉን አናወጠው።

ይሄ ሁሉ ሲሆን እኔን ያስታወሰኝ አልነበረም። ውርደቴን ለብቼ ተቀምጫለሁ።

ያንተ ያለህ! ይሄ ነው ጓደኝነት ማለት ስል አሰብኩ።

«ምን ዓይነቱ አህያ ነኝ ራሴን በነሱ ፊት ይሄንን ያህል ያዋረድኩ? ፊርፊችኪን ሲሰድበኝ ዝም ብዬዋለሁ፤ እነዚህ ደደቦች እነሱ ጋር ገበታ እንድቀመጥ ስለፈቀዱልኝ ክብር የሰጡኝ ይመስላቸዋል። ክብር የሰጠሁዋቸው እኔ እንኺ እነሱ እንዳልሆኑ ከቶም የሚገነዘቡ አይደሉም። «በጣም ከሳህ! ልብሶችህ» ይላል ይሄ ዚቨርኮቭ ደግሞ፤ ምናባቱ! ይሄ ሱሪ አዋራጅ! እርግጠኛ ነኝ ጉልበቱ ላይ ያለውን ነጠብጣብ ገና ሲገባ ነው

ያየው... ግን አሁን እኔ እዚህ ምንይሁን ብዬ ነው የተቀመጥኩት? አሁኑኑ ተነስቼ ቆቤን ብድግ አድርጌ ያለምንም ከፉና ደግ ውልቅ ብል ይሻላል።.... ንቀቴን ላሳያቸው ይገባል። ከብራችን ተነክቷል። ነገ እንሩለም ቢሉኝ ግድ የለኝም። ቆሻሻ በስባሶች! ሰባት ሩብልስ ይሆን ያህል የሚያሳስበኝ መሰላቸው በእርግጥ ሊመስላቸውን ይችል ይሆናል።....ገደል ይግባ ብሩ! እንዳውም አሁኑኑ እሄዳለሁ» ግን አልሄድኩም።

በተስፋ መቁረጥ ሰሚት ከመጠጡ ደጋገምኩ። የመጠጥ ልምድ ስላልነበረኝ ወዲያውኑ ሰከርኩ። ምቅ ባለኝ ቁጥር ጥላቻዬ እየተጋጋመ መጣ። ድንገት ተነስተህ ሙልጭ አርገህ ሰድበሃቸው ሄድ የሚል ሃሣብ መጣብኝ። ትክክለኛውን አጋጣሚ ጠብቄ ምን ዓይነት ሰው እንደሆንኩ አሳይቻቸውና ምንም እንኳ ከሰው የተለየሁ ብሆንም ጉበዝ መሆኔን እንዲያምኑ አስገድጀ—.... ኤጭ ገደል ይግቡ!

በመጠጥ በነወዘ አይን በንቀት አፈጠጥኩባቸው። እነሱ ግን ሙሉ በሙሉ እረስተውናል። በደስታ ያውካካሉ። ዚቨርኮቭ ነበር የሚያወራው። ማዳመጥ ጀመርኩ። የሚያወራው እሱን ከማፍቀር የተነሣ እኔ እኮ እወድሃለሁ እስክትለው ድረስ በፍቅሩ ስለተቆጣጠራት አንዲት ቆንጆ ልጅ ታሪክ ነው። (ሊዋሽ እንደጠጣ ነው) በዚህም የፍቅር ድሉ ሶስት ሺህ ሞሰኞች ያሉት የመሳፍንት ደም ያለው ኮልያ የተባለ መኳንን የቅርብ ጓደኛው በጣም እንደረዳው ይተርካል።

በዚህ ጊዜ ጣልቃ ገባሁና «ግን ይሄ ሶስት ሺ ሞሰኞች ያሉት ጓደኛህ እዚህ መሸኛህ ላይ የለም። አለ እንዴ? ማለቴ ሊሸኝህ አልመጣም» አልኩ።

ለአንድ ደቂቃ ያክል ሁሉም ነገር ፀጥ አለ።

«በጣም የሰከርክ መሰለኝ።» አለ ትሩዶሊዮቦቭ በመጨረሻ ደረጃ መጠየፍ እያየኝ።

ዚቨርኮቨ የሆነ ትል በቅርበት የሚመረምር ይመስል በዝምታ አፍጥጦ ተመለከተ። ሊሞኖቭ ወዲያውኑ ሻምፓኝ መቅዳት ጀመረ። ትሩዶሊዮበቭ ብርጭቆውን ሲያነሣ ከኔ በስተቀር ሁሉም አነሱ።

«ለጤናህና ለአስደሳች ጉዞህ!» አሉ ከፍ ባለ ድምፅ ለዚቨርኮቭ።

«ለትላንት ትዝታችን ወዳጆቼ! ለነገው ሕይወታችን ቸርስ!» ብርጭቆዋቸውን ጭልጥ አደረጉና እርስ በእርስ ተቃቀፉ፤ የሞላ ብርጭቆዬን ፊቴ አስቀምጬ ካለሁበት ሁኔታ ነቅነቅ አላልኩም።

«አትጠጣም 'ንዴ አንተ ሰው?» ትራዲሊዮበቭ ትግሥቱ አልቆ በዛቻ ጮኸብኝ።

«ሚስተር ትሩዶሌዩቦቭ በመጀመሪያ አንድ ንግግር.. ልዩ ንግግር ካደረግኩ በኋላ ነው የምጠጣው።» አልኩ።

«ሥርዓት የለሽ አረመኔ!» ሊሞኖቭ አልጮመገመመ። ከወንበሬ ላይ ተነሣሁና ብርጭቆዬን በሚንቀጠቀጡ እጆቼ ይዤ የመጨረሻ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ ለመገመት ባለመቻል ለንግግር ተዘጋጀሁ።

«ፀጥታ!» አለ ፊርፊችኪን በፈዝ «ታላቅ ንግግር ልንሰማ ነው!»

ዚቨርኮቨ መጪውን በመገመት ፊቱን አቀጭም ተቀመጠ።

«ሌፍተናንት ዚቨርኮቨ!» በማለት ጀመርኩ። «ባዶ ሀረጐችን፤ ተራ የቃላት ወጀቦችንና ወገኖችን እንደምጠላ ልታውቅልኝ እፈልጋለሁ።...የመጀመሪያው ቁም ነገሬ ይኼ ነው። ሁለተኛው ይከተላል።» አልኩ።

ሁሉም ተቁነጠነጡ።

«ሁለተኛው ነጥብ፤ ስድ ወሬዎችን አልወድም። በተለይም፤ የሚያወሩትን በጣም እጠላለሁ። ሶስተኛ ነጥቤ፤ ዕውነትን፤ ግልፅነትንና ሐቀኛነትን እንደማፈቅር እንድታውቅልኝ ነው» በማለት መላ ሰውነቴ በገዛ ድፍረቴ ፈርቶ እየተንቀጠቀጠ የግብር ይውጣ ቀጠልኩ።

«አቶ ዚቨርኮቨ እኔ ከሁሉም በላይ ሐሣብ አፈቅራለሁ። ሁሉም በእኩልነት የሚተያዩበት ጓደኛነት አፈቅራለሁ። እንጂ – እን– አዎ። እኔም አፈቅራለሁ። – ለምን አላፈቅርም? ለአንተም ጤንነት ዋንጫዬን ማንሣት እችላለሁ– አቶ ዚቨርኮቨ የካውካዝያንን ልጃገረዶች ተደሰትባቸው፣ የሀገራችንን ጠላቶች ግደል እና– ለጤንነትህ አቶ ዚቨርኮቨ!»

ዚቨርኮቨ ከመቀመጫው ተነስቶ ጮንበስ ካለልኝ በኋላ «በጣም ታዛኝ ነኝ ጌታዬ!» አለ።

ከራኛ ከመቀየሙ የተነሣ ፊቱ ገረጣ። ትሩዶሊዮቦቨ ጠረጴዛውን በቡጢ በመነረት «ምንድነው እሱ!» በማለት እልህ ተናነቀው። «እንዴት! አፍንጫውን በቦክስ ማለት ነበር?» አለ ፊርፊችኪን በቁጣ።

«ለምን እየደበደብን አናስወጣውም!» አለ ሲሞኖቭ በማጉረምረም።

«በቃ፣ ምንም ድምፅ አያስፈልግም፣ ወዳጆቼ» በማለት ዚቨርኮቨ አጠቃላይ ቁጣውን አቀዘቀዘው።

«ሁላችሁንም አመሰግናለሁ። እሱ ለተናገረው ግን ምንም ያህል ዋጋ እንደማልሠጠው እኔ አሳየዋለሁ» አለ።

እኔም ፊቴን ወደ ፊርፊችኪን በማዞር ድምጼን ከፍ አድርጌ «አቶ ፊርፊችኪን አሁን ለተናገርከው ቃል ነገ ሙሉ ማብራሪያ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ» አልኩ።

«አሃ! ፍልሚያ እንግጠም ማለትዎ ነው ጌታው? በደስታ እቀበላለሁ!» አለ ፊርፊችኪን። ከኩሩ ተፈጥሮዬ የተነሣ ያቀረብኩት የፍልሚያ ሐሣብ አጠቃላይ ሁኔታውን አስቂኝ ስላደረገው ሁሉም በሳቅ ፈነዱ።

«እባካችሁ ተውት ትንሽ ጣጥ ብሏል» አለ ትሩዶሊዮቦቨ በመፀየፍ።

«በግብጥው ላይ እንዲገኝ በማድረጌ ምን ጊዜም የተረገምኩ ልሁን» አለ ሲሞኖቭ በብስጭት።

«አሁን ነው በጠርሙስ መፈንከት!» ብዬ አሰብኩ። «ወዳጆቼ፣ አሁን ተነስቼላችሁ ብሄድ ደስታውን አትችሉትም አይደል? ግን ንቅንቅ አልልም። እንዳው ሺ ተአምር ቢፈጠር 'ንኳ እዚሁ ሆን ብዬ ተቀምጪ– ምን ያህል ስለናንተ ግድ እንደማይሰጠኝ ለማሳየት– እስከመጪረሻው እጠጣለሁ። ይሄ ቦታ ማለት ምንም ማለት ያልሆነ ዝቅተኛ ደረጃ መጠጥ ቤት መሆኑን ለማሳየት ከተቀመጥኩበት ንቅንቅ ሳልል እጠጣለሁ። ደግሞም ለሁሉም ነገር ከፍዬበታለሁ። እያንዳንድሽ ተራ– ዚጋ፣ ማንም አያውቅሽ መናጢ መሆንሽን ስለማውቅ እዚችው ቁጭ ብዬ እጠጣለሁ። እጠጣለሁ፣ ብፈልግም እዘፍናለሁ፣ አዎ፣ እዘፍናለሁ! ማነው የሚከለክለኝ፣ የመዝፈን መብት አለኝ! አዎ!» አልኩና በሐሳቤ ብርጭቆዬን ሞላሁ።

ግን አልዘፈንኩም። እንዳውም ወደ እነሱ ላለማየት ተጠንቅቄ እነሱ መጀመሪያ እንዲያናግሩኝ በመጠበቅ ሰብሰብ አልኩ።

የሚያሳዝነው ግን ዘጉኝ። በዛች አፍታ እንዲታረቁኝ ምን ያህል እንደጓጓሁ እግዚአብሔር ይወቀው! ሰዓቱ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሩጥሎ ሶስት ሰዓት አለ። ከጠረጴዛው ተነስተው ወደ ሶፋው ሄዱ። ዚቨርኮቨ ሶፋው ላይ ተመቻችቶ አግሩን ፊት ለፊቱ ያለው ትንሽ ጠረጴዛ ላይ ዘርግቶ ተቀመጠ። ወይኑን ወደነሱ ወሰዱት። ዚቨርኮቨ 3 ጠርሙስ ሻምፓኝ አውርዶላቸዋል። እኔን ግን አልጋበዘኝም። ሁሉም በሶፋው ዙሪያ ከበው ከከንፈሩ ማር ጠብ የሚል እስኪመስል ድረስ አሰፍስፈው ያዳምጡታል። « ግን ለምን? ለምን?» እያልኩ ራሴን ጠየኩ። በየደቂቃው በስካር እርካታ እርስ በእርስ ይተቃቀፉሉ። ስለካውካሰስ ስለእውነተኛ ስሜት፣ ስለካርታ፣ ስለምርጥ ሥራዎች፣ ስለ ሆላር መኩንኑ ፓድካርሻቦብስኪ ገቢ (በነገራችን ላይ አንዳቸውም በእካል አያውቁትም) ይሄንን ያህል ገቢ ስላለው ደስታቸው ገለፀለት።

ስለልዕለት ዲ– አስገራሚ ውበትና ዝርጋዳነት! አንድ ቀን እንኳ በአይናቸው አይተዋት አያውቁም! በመጪረሻም ስለ ሼክስፒር አንስተው ሕያው ሰው ነው በሚል ደመደሙ።

እኔ በክፍሉ ወዲያኛው ፊት ለፊት የንቀትፈገግታ እያሣየሁ ከጠረጴዛው እስከ ምድጃው እንጐራደድ ነበር። ያለነሱ በራሴ ልደሰት የምችል መሆኔን ሳሳያቸው በማሰብ ተረከዜን ወደላይ ከፍ በማድረግ እየነጠርኩ ነበር የምመላለሰው። ምን ያደርጋል ሁሉም ጥረቴ ከንቱ ሆነ። ጨርሶም አልተመለከቱኝም። እኔ ግን ከምሽቱ 2 ሰዓት ያነሣሁ እስከ 5 ሰዓት ድረስ እዛው ከጠረጴዛው እስከ ምድጃው ድረስ የመመላለስ ትዕግሥት ነበረኝ። «ይኸው እዚህ እንደፈለግኩ እመላለሳለሁ፤ ወንድ የሆነ እስቲ ያቁመኝ!» እላለሁ በሐሣቤ።

ወደ ክፍሉ ደጋግሞ መመላለስ የነበረበት አስተናጋጅ ገርሞት ቆሞ ለጥቂት ደቂቃ ተመለከተኝ። ብዙ ከመላላሴ የተነሣ ያዞረኝ ስለጀመረ እንደመባተት ሁሉ ያደርገኝ ጀምሯል። ሳሳድርጥ ላይ ታች ባልኩበት 3 ጊዜ ያህል በላብ ተነክሬ 3 ጊዜ ያህል መልሶ ደርቆልኛል። በመሐሉም እነዚህን አስከፊና አሰቃቂ ውርደቶቼን ከ20 እና ከ40 ዓመታት በኋላ እንኳ እንደማልረሳቸው በሐሣቤ ብልጭ ይልብኝና ልቤን በኃይል ይወጋኛል። አንድ ሰው ራሱን በራሱ እንዲህ ማዋረድና ሆን ብሎ ማቃለል እንደማይቻለው ባውቅም ከጠረጴዛው እስከ ምድጃው መንጎራደድን መግታት አልቻልኩም።

ሐሣቤንና ስሜቴን ብታውቁ ኖሮ ምን ያህል አዋቂ እንደሆንኩ ባውቃችሁ ነበር! በማለት ሶፉ ላይ ስለተቀመጡትጠላቶቼ ከራሴ ጋር አወራለሁ። ጠላቶቼ ግን እኔ የሚባልሰው ከፍሉ ውስጥ ስለመኖሩ ሙሉ በሙሉ ረስተዋል። አንድ ጊዜ ዞር ብለው የተመለከቱኝ ዚቨርኮቭ ስለሺክስፒር ሲያወራና እኔም በንቀት መሳቅ የጀመርኩ ጊዜ ብቻ ነው። ከጠረጴዛው ወደ ምድጃው እየተመላለስኩ እነሱን ከቁም ነገር እንደማልቆጥራቸው ያመለክታቸዋል ብዬ በማሰብ የንቀት ሳቄን ስለቀው– ለአንድ ለሁለት ደቂቃ ያህል ያለምንም ቃል በእርጋታ ካጤኑኝ በኋላ– ረሱኝ። 5 ሰዓት ሆነ።

«ወዳጆቼ!» አለ ዚቨርኮቭ ከሶፋው በመነሣት «አሁን ወደ እዛ እንሄድ!» አለ።

«አዎ፣ አዎ!» አሉ በአንድነት።

የሥቃይ ምልልሴን ድንገት አቋርጬ ወደዚቨርኮቭ ዞርኩ። እጅግ ከመድከሜና ሙትት ከማለቴ የተነሣ ሰታዩን ለመቀነስ የራሴን ጉሮሮ ብቆርጠው ደስ ባለኝ ነበር። ትኩሳት ያንቀጠቀጠኛል። ፀጉሬ በላብ ረጥቦ ግምባሬ ላይ ተላጥቋል።

«ዚቨርኮቭ» አልኩ በቁርጠኛነት «ይቅርታ ፊርፊችኪን፣ ሁላችሁም ሁላችሁንም ይቅርታ ልበላችሁ አሰቀይሚአችኋለሁ» አልኩ።

«አረ! ፍልሚያውን ፈራህ ማለት ነው?» አለ ፊርፊችኪን በለበጣ ላቅ

ልቤን በጩቤ የወጋው ያህል አመመኝ። «በፍፁም ፊርፊችኪን፣ ፍልሚያውን አልፈራም። ከፈለክ በነገው ዕለት ልንፋለም እንችላለን። መጀመሪያ ግን እንታረቅ። እምቢ እንደማትለኝ ተስፋ አይርጋለሁ። ፍልሚያ እንደማልፈራ ግን ላሣይህ እችላለሁ። አንተ መጀመሪያ ትተኩስና ቀጥዬ እኔ ወደ ሰማይ እተኩሳለሁ።»

«በራሱ የረካ ሰው ነው» አለ ሲምኖቭ «ጉራውን ይነዛል።» አለ ትሩዶሊዮቦቭ።

«ዞር በል እንጂ ከፊቴ?» አለኝ በንቀት። «ምን ፈለግህ ነው መንገዴን የምትዘጋው?»

የሁሉም ፊት ደም መስሏል ከዓይኖቻቸው እሣት ይጫራል። በጣም ሲጠጡ ነበር።

«ዚቨርኮቭ፣ ይቅር በለኝ አሰቀይሚህለሁ? ግን—...»

«አሰቀየምኩህ?! አንተ እኔን? አንተ እኔን በምንም ሁኔታ ልታሰቀይመኝ እንደማትችል አታውቅምን ጌታው?»

« አ! በቃን ባንተ ተንገሽግሸናል። ውጣ ከመንገዳችን እንሂድ!» አለ ትሩዶሊዮቦቭ ለግርግሩ እልባት በመስጠት።

«አሊምፒያ! በኔ ነው ወዳጆቼ! ተስማማን?» አለ ዚቨርኮቭ « አዎ፣ አዎ» አሉ ቀሪዎቹ። በሐፍረት ደንዝዤ ቀረሁ። ክፍሉን ለቀው በሳቅ በጨዋታ ወጡ። ትሩዶሊዮቦቭ የሆነ ደደብ ዘፈን መገፈን ጀመረ። ሲሞኖቭ ለአስተናጋጁ ቲፕ ለመስጠት ወደኋላ ቀረ። ድንገት ወደእሱ ሄድኩ። በተሰሩ– መቁረጥና በእልህ «ሲሞኖቭ፣ አባክህ ስድስት ሩብል ስጠኝ!» አልኩት።

በመገረምና በንቀት ተመለከተኝ። እሱም ሰከሯል።

«ከኛ ጋር ልትመጣ ነው እንዴ? መቼም አታደርገውም!»

«አዎ! እመጣለሁ!» አልኩ።

ፍፁም በሆነ የንቀት ፈገግታ አቋረጠኝና– «ቤሳቤስቲ የለኝም!» አለ።

ተከትዬ ኮቱን ያገኩት ድርጊቴ ሁሉ ቅዥት መሰለኝ

«ሲሞኖቭ ገንዘብ እንዳለህ አውቃለሁ። ለምን እምቢ ትለኛለህ? ለምን እንደፈለኩት ብታውቅ እምቢ አትለኝም። የወደፊት ሕይወቴ፣ ዕቅዶቼ ሁሉ አሁን በጠየኩህ ብር ላይ የተመረኮዘ ነው።...»

ሲሞኖቭ ገንዘቡን አወጥቶ ወደ መሬት ወረወረው።

«ሀፍረት ከሌለህ አንስተህ ውሰድ!» ብሎ እነሱ ጋ ለመድረስ እየሮጠ ወጣ።

ለጥቂት ደቂቃ ብቻዬን ቀረሁ። የከፍሉ የተምሳቀለ ሁኔታ፣ የራቱ ትርፍራፊ፣ ወለሉ ላይ የተሰባበረው የወይን ብርጭቆዎችና የሲጋራ ቁርጥራጮችን የወይኑ ፍሣሽ ሽታና የኔ መታወክ፣ ልቤን የሚሰማው ስቃይ እና በመጪረሻም ሁሉንም ነገር ያየውና የሰማው፣ አሁን በመገረም የሚያጤነኝ አስተናጋጅ...

«እዛ ነው የምሄደው!» አልኩ ጮክ ብዬ «ወይ ተንበርከከው የኔን ወዳጅነት ይለምናሉ– አለዚያም የዚቨርኮቭን ፊት በጥፊ አጮለዋለሁ!»

«ይሄው ነው። መጨረሻው ይኸው ነው። ከዕውነተኛው ሕይወት ጋር ግንባር ለገንባር ግጭት!» ደረጃዎቹን እየወረዱኩ አጕረመረምኩ። «ይሄ ጳጳሱ ከሮም ወደብራዚል ይሔዱ ከሚለው ሃሣቤ በጣም የተለየ ነው! ይሄ! ኮሞ ሀይቅ ላይ የጠራኸው ዳንስ አይደለም! በዚህ ብትስቅ አሳማ ነህ!» የሚል ሀሣብ ጭንቅላቴ ውስጥ ብልጭ አለ።

«ግደለኝም» አልኩ እራሴ ለራሴ። ካሁን ወዲያ ምን ያደርጋል ሁሉም ነገር አምልጧል።

በመንገድ ላይ ደብዛቸው የለም። የት እንደሚሄዱ ስለማውቅ አላስጨነቀኝም። የሆቴሉ በር መውጫ ላይ አንድ የምሽት ጋሪ ቆሟል። ሹፈሩ የተጨማደደች የገበሬ ኮት ለብሷል። ሰውነቱ በበረዶ ተሸፍኗል። በረዶው አሁንም ላያቋርጥ እየወረደ ነው። ጕፍጓሉ ፈረሱም እንደዚሁ በበረዶ ተሸፍኖ እየሣለ ነበር። ሁሉንም አስታውሣለሁ። ወደጋሪው እየሮጥኩ ሄጄ ለመሣፈር አንድ እግሬን ብድግ እንዳደረግኩ ሲሞኖቭ ስድስቱን ሩብል በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሰጠኝ ትዝ ሲለኝ በሀፍረት ክውታ እንደጀንያ እህል ጋሪው ውስጥ ዘፍ አልኩ።

«ክብሬን ለመመለስ ብዙ ማድረግ ይጠበቅብኛል» አልኩ ለራሴ። በዛሬ ምሽት ወይ አደርገዋለሁ፣ ወይም እሞታለሁ። ሹፈር ወደፊት ቀጥል!»

ጉዞ ጀመርን ሃሣቦቼ እንደአውሎ ንፋስ ጭንቅላቴ ውስጥ ይሽከረከራሉ።

«ጓደኞቸው እንድሆን በጉልበታቸው ተንበርከከው አይለምኑኝም፣ እንዲህ ያደርጋሉ ብዬ ማሰቤ ቅዠት፣ ተራ ሮማንቲክ የማይጨበጥ አስቀያሚ ቅዠት ነው። ሌላ ዳንስ ኮሞ ሀይቅ ዳርቻ ላይ እንደማሰብ ማለት ነው። ለዚህም ነው ዚቨርኮቭን በጥፊ ማለት ያለብኝ፣ ይሄን የግድ ማድረግ

አለብኝ! በቃ ይህንን ነው የማደርግው አሁን የምከንፈው ዚቨርኮቭን በጥፊ ለማጮል ነው ሾፈር ፍጠን!»

ባለጋሪው ልጓሙን ለቀቀው።

«እንደደረስኩ በጥፊ አጮለዋለሁ ግን ምናልባት በጥፊ ከመማታቴ በፊት ለመግቢያ ያህል ጥቂት ነገር መናገር ይኖርብኝ ይሆን? በጭራሽ! እገባና በጥፊ መምታት ነው። ሁሉም ሰፊ ክፍል ውስጥ ነው የሚቀመጡት እሱ ደግሞ ከአሎሞፒያ ጋር ሶፋ ላይ ነው የሚቀመጠው። ያቺ ሆዳም አሎሞፒያ! አንድ ጊዜ በመልኪ ላይ ተልዳለች። መቀለድ ብቻ ሳይሆን ጠይቂያትም እምቢ ብላለች። እሷን ፀጉሯን ይገር ዚቨርኮቭን ደግሞ ጆሮውን ይገር መሬት ላይ እጐትታቸዋለሁ። አይደለም! አይደለም! በአንድ ጆሮው ብቻ መጐተት ይሻላል። አንድ ጆሮውን ይገር በከፍሉ ዙሪያ እጐትተዋለሁ። እንደማይምሩኝ አውቃለሁ። በጋራ ይደበድቡኛል። ይረግጡኛል። ይሄ የማይቀር ነው። ግን ምንም አይደለም። ዋናው ቁም ነገር ቀድሜ እሱን በጥፊ መምታት ነው። የመጀመሪያው መሆን! በክብር ጉዳይ ደግሞ ወሣኙ የመጀመሪያ አድራጊ ሆኖ ፅገኘት ነው። ቀሪ ዕድሜውን በጥፊ የጮለ ተብሎ ይዋረዳል። ከፍልሚያ በስተቀር በማንኛውም ዓይነት ቡጢ ፍልሚያውን ሊሰርዝ አይችልም። መፋለም ይኖርብናል። ለአሁኑ ግን ይደብድቡኝ! ግዴለም! ይደብድቡኝ እነዚህ ውለታቢስ አሳማዎች! አብዛኛውን ቡጢ የሚያላርፍብኝ ቱርድሊዮዶቭ እንደሚሆን ነው። እሱ በጣም ጠንካራ ነው። ፈርፊችኪን በጐን በኩል ነው የሚንጠለጠለው። በእርግጠኛነት ፀጉሬ ላይ ነው የሚንጠለጠለው። አዎ ፀጉሬ ላይ። ይንጠልጠል። ይንጠልጠል። የምሄድላቸውም ለዚህ ነው። እነዚህ ቂሎች በጓላ ላይ አንድ አስቃቂ ነገር እንደሚኖር ይገባቸዋል። እየጐተቱ ወደበሩ ሲወስዱኝ እናንተን የትንሽ ጣቴን ታክል እንኳ አልቆጥራችሁም በማለት ልካቸውን እነግራቸዋለሁ። ሾፈር ፍጠን! ቸ! እያልኩ ባለጋሪውን አዋከብኩት።

በጣም ስለጮህኩበት ባለጋሪው ደንግጦ ፈረሱን ባለንጋው ሾጥ ሾጥ አደረገው።

«ነገ ማለዳ መፋለማችን የማይቀር ነው። ሥራ ብሎ ነገር አከተመ። ግን ደግሞ ሽጉጥ ማነው የሚሰጠኝ? ይሄ አያስጨንቀኝም ከደሞዜ አድቫንስ (ብድር) ጠይቄ እገዛለሁ ጥይቶችስ? ይሄ የኔ ችግር አይደለም። በኔ በኩል የሚመጣው ዳኛ ይጨነቅበት። ግን ይሄንን ሁሉ በነገው ጧት ላሟላ እችላለሁ? ደግሞስ ከየት ነው ለኔ የሚቆም ዳኛ የሚመጣው። ጓደኞች የሉኝም....ይሄም አያሳስብም።» በስሜት በጣም ተውጬ በጣም ጮኪ ተናገርኩ።

«አያሳስብም። ግነም ሰው ውሃ ውስጥ የሰመጠን ሰው ጉትቶ ማውጣት እንዳለበት ሁሉ መንገድ ላይ መጀመሪያ ያገኘሁት ሰው በኔ በኩል የቀረበ ዳኛ የመሆን ግዴታ ይኖርበታል። ደግሞስ የመምሪያ ኃላፊያችንን ለነገ ጠዋት በኔ በኩል ዳኛዬ እንዲሆን ብጠይቀው ደካሞችን ለመደገፍ ባለው ስሜት የተነሣ ይቆምልኛል።——»

የሚያሳዝነው ግን ይህንን ባሰብኩ ቁጥር የጠቅላላ ሀሣቤና እቅዴ እብድነት ይበልጥ እየገባኝ መጣ። እውነቱን የተረዳሁ ግን...

«ፍጥነት ሹፌር! ፍጠን አንተ ወሮበላ! ፍጠን!»

«እሪ የእግዚአብሔር ያለህ» አለ ባለጋሪው።

ቀዝቃዛ ላብ በጀርባዬ ሲፈስ ተሰማኝ።

«ግን! በቀጥታ ወደቤት መሄድ አይሻልም!? መቶ እጥፍ አይሻልምን?! አምላኬ ምን ልሁን ብዬ ነው ራሴን ለዚህ ራት የጋበዝኩት? ከጠረጴዛው እስከ ምድጃውስ ለሶስት ሰዓታት ያህል ሣላቋርጥ መወዛወዜስ ምንድን ነው? በጭራሽ! እግሬ እስኪቀጥን ለተመላለስኩበት ዋጋቸውን አሰጣቸዋለሁ። ያንን ውርደት በነሱ ላይ ነው የማጥበው! ንዳ!»

«... ግን! ሰፖሲስ አሳልፈው ቢሰጡኝስ ይህንን ፣ንኳ ደፍረው አያደርጉትም። ምክንያቱም የሚያስከትለውን አሉባልታ ይፈራሉ። ደግሞ ዚቨርክቨ በንቀት ከኔ ጋር ፍልሚያ ለመግጠም አሻፈረኝ ቢልስ? ይሄ ሊሆን ይችላል። ግን እኔም ለዚህ ዘዴ አትጀለታለሁ። በነገው ዕለት ወደ ከፍለ አገር ለመሄድ የሚሰፈርበት ጣቢያ ድረስ ሄጂ ልክ ጋሪ ውስጥ መግባት እንደጀመረ እግሩን አንት አድርጌ በመያዝ ኮቱን ከላዩ ላይ አገፈዋለሁ። ከዚያ በኋላ እጆቹን በጥርሴ ነክሼ እንጠለጠልበታለሁ። ንክስ አደርገዋለሁ።

«ተመልከቱ አንድ ተስፋ የቆረጠ ሰው እስከምን ድረስ ሊሄድ እንደሚችል?» ቢፈልግ እሱ ጭንቅል ጭንቅላቴን ጓደኞቹ ደግሞ በኋላ በቡጢ ይነርቱኝ። እኔ ግን «ሰምች ሆይ ተመልከቱ! ፊቱ ላይ የለደፍኩበትን ምራቅ ተሸክሞ የካውካሰስ ልጃገረዶችን ለማሸነርመም የሚሄደው ቡችላ ይሸውላችሁ» አላለሁ።

«በቃ! የሥራ ነገር ያበቃለታል። እታሰራለሁ። ፍርድ ቤት አቀርባለሁ። ከሥራ ተባርሬ ከሳይቤሪያ አሥር ቤቶች ወደ አንዱ እጣላለሁ። ምንም አይደለም። ከአሥራ አምስት ዓመታት በኋላ ማለትም ከአሥር ቤት ስወጣ ቡትቶዬን ለብሼ ለማኝ እንደመሰልኩ በየቦታው አፈልገዋለሁ። በመጨረሻም የሆነ የአውራጃ ከተማ ውስጥ አገኘዋለሁ። አግብቶና ወልዶ ደስተኛ ቤተሰብ መስርቶ ይሆናል። ያኔ የደረሰች ሴት ልጅም ልትኖረው ትችላለች። እኔም «ስማ! አንተ ጭራቅ፣ ተመልከት የሰረጉዱ ንንጮቼንና ቡትቶዬን! ሁሉንም ነገር አጥቻለሁ። ሥራዬን፣ ደስታዬን፣ ሥነ ጥበብን፣ ሳይንስን፣ ያፈቀርኳትን ሴት እና ሁሉንም ባንተ ምክንያት አጥቻለሁ። ሽጉጡቼ እነዚሁልህ የመጣሁት ጥይቶቹን ላራግፍና ይቅር ልልህ ነው። ከዚያ በኋላ ወደሰማይ ተኩሼ ደብዛዬን አጠፋለሁ። ከዚህ በኋላ ስለኔ አይሰማም።...»

በራሴ ንግግር እንባዬ ፈሰሰ። ድንገት ከፍተኛ ሀፍረት ተሰማኝ። ሀፍረቱ በጣም ጥልት ከመሆኑ የተነሳ ጋሪውን አስቁሜ ወረድኩና አሰፋልቱ

መሀል በበረዶ እየተደበደብኩ ቆምኩ። ባለጋሪው ተነፈሰና በመገረም ዝም ብሎ ያየኛል።

«ምን ላድርግ፣ እዚያ መሄድ አልችልም። ሁሉም ነገር የማይሆን ነው። ግን ደግሞ ነገሮችን እንደዛው እንዳሉ ልተዋቸው አልችልም። ምክንያቱም እንደዛ ባደርግ ያንተ ያለህ! እንዴት አድርጌ እንዲሁ ልተወው እችላለሁ? እንዲህ ከተሳደብኩ በኋላ? በፍፁም!» አልኩና ወደጋሪው በሩጫ ሄድኩ። «የተወሰነ የተቆረጠ ነው! አጣ ፈንታ ነው! ንዳ! ወደዚያ ንዳ!»

ከመጣደፌ የተነሣ የሹፌሩን ጀርባ ደለቅኩት።

«ምን ነካዎት ጌታዬ? ለምንድነው የሚመቱኝ?» አለ ሚስኪኑ ሹፌር። ነገር ግን ጥድፊያዬ ሰለገባው፣ ፈረሷን ደጋግሞ ስለገረለጣት ክራኗ ትጋልብ ጀመር።

ትልልቅ በረዶ ይወርድ ጀመር። በረዶው አላስጨነቀኝም። የኮቶቼን ቁልፎች ፈታሁ። ዚቨርኮቭን ለመምታት ስለወሰንኩ ሁሉንም ነገር ረሣሁ። አሁን ያልኩትን ከመፈፀም የሚያግደኝ እንደሌለና ድርጊቱንም በእርግጠኛነት እንደምፈፅመው ተሰማኝ። በረዶው የፈጠረውን ጭጋግ እንደመቃብር ሻማ ጭል ጭል የሚሉት የመንገድ ላይ መብራቶች በመጠኑ አብርተውታል። በረዶው ካፖርቴ ላይ፣ ኮቴ ውስጥና፣ ኮሌታዬ ውስጥ እየገባ ይቀልጣል። የካፖረቴን ቁልፍ አልቆለፍኩም። ሁሉም ነገር አምልጦኛል። እና ምን አስጨነቀኝ።

በመጨረሻ ደረስኩ። ከጋሪው ወርጄ የማደርገውን ሳላውቅ ወደቤቱ ደረጃዎች በመሮጥ በሩን በሁለት እጄና በእግሮቼ ማንኳኳት ጀመርኩ። እግሮቼ በተለይ ጉልበቴ ላይ ተንቀጠቀጡ። የኔን መምጣት ያወቁ ይመስል በሩ እኔ ከጠበቅኩት በላይ በፍጥነት ተከፈተ። (ሊሞኖቭ እርግጠኛ ነኝ የሆነ ሰው እንደሚመጣ አስቀድሞ ነግሮዋቸውዋል። እዚህ ቤት ደግሞ ለጥንቃቄ ሲባል አስቀድሞ ማስታወቅ አስፈላጊ ነው። ነገሩ ፖሊስ ከከረቸማቸው

ፋሽን ሱቆች አንዱ ነው። ቀን ቀን ሱቅ ነበር ሲመሽ ግን ሚስጥሩን የሚያውቁ እየመጡ ይዝናናሉ) ጨለማ በዋጠው ሱቅ ውስጥ አልፌ የአንዲት ሻማ በርሃን ብቻ ሞል ሞል ወደምትልበት ሰፊ ክፍል አልፌ ቡና አዘዝ ቆምኩ። ማንም የለም።

«የትሄዱ?» ብዬ አንዱን ጠየቅኩት ሁሉም ተለያይተው ወደየቢታቸው ሒደው ነው የደረስኩት።

ፊት ለፊቴ አንድ ፈገግ ያለች ሴት ተገትራለች። የቡና ቤቱ ባለቤት ራሷ ነች። መጠነኛ ዕውቂያ አለን። ወዲያው በሩ ተከፈተና አንድ ሌላ ሰው ገባ።

ማንኛቸውንም ጉዳይ ሳልል ከወዲህ ወዲያ መንጎራደድ ጀመርኩ። ብቻዬንም የማወራ ይመስለኛል። ከሞት የተረፍኩ ያህል ነው የተሰማኝ። ቢኖሩ ኖሮ ያለጥርጥር ፊቱን በጥፊ አጮለው ነበር። ነገር ግን እነሱም የሉም፤ ሁሉም ነገርም በዚህ የተነሣ ተለውጧል። ዙሪያዬን ተመለከትኩ። አሁንም በጥራት ለማሰብ አልችልም ነበር። አሁን ወደገባችው ልጅ ተመለከትኩ። ወጣት፤ ትኩስ፤ በመጠኑ የገረጣ፤ ቀጥ ያሉ ጥቁር ቅንድቦችና ቦግ ያሉ ዓይኖች አየሁ። ወደድኳት። ፈገግ ብላ ቢሆን ኖሮ እጠላት ነበር። በትኩረት አያት ጀመርኩ። ሐሣቤን ግን ልሰበስብ አልቻልኩም። መልኳ ርህራሄና ጥሩ ስሜት አለው። ሌላም ኩስትር ያለ ሁኔታ ይታይባታል። ይሄ ለሷ አጠቃላይ ገፅታ ጥሩ አልነበረም። ግን ማንም ልብ አይለውም። ረጅም፤ ጠንካራና ጥሩ አቋም ያላት ብትሆንም ብዙ ቆንጆ የምትባል ዓይነት አይደለችም። አለባበሷ ቀለል ያለ ነበር። ሳያት የሆነ መጥፎ መንፈስ መጣብኝ። ወደሷ ሄድኩ።

ወደሷ ስሄድ በአጋጣሚ ራሴን በመስታወት ውስጥ ተመለከትኩት። የገፃ ፊቴ አቅለሸለሸኝ። የገረጣ፤ ክፉ፤ ወራዳና የተንጨባረረ ፀጉር፤ «ይሁን እንጂውም ደስ ይለኛል።» አሰብኩ። «እንጂውም ይበልጥ አስቀያሚ መስዬ ስለምታየት ደስ ይለኛል።...»

ከፍላችንን ከሚወስነው ግርግዳ ኋላ የሆነ ቦታ ላይ የግድግዳ ሰዓት እላዩ ላይ ከባድ ሞነት የተጫነበት ይመስል በማታሰት ያንቋርራል። ቆየት ብሎ ከዚህ የተለየ ያልተለመደ ማንቋረር (በኋላ ድንገት የጐተተውን ጊዜ ለማጣጣት የፈለገ ይመስል፤) ቀጭን ጆሮን የሚረብሽና ፈጣን ቲክ–ታክ–ቲክ–ታክ ቀጠለ።

ሰዓቱ ሁለት ሰዓት አለ። እንቅልፍ ግይሆን በጥልቅ የሰመመን ስሜት ውስጥ እንደቆየሁ ባውቅም ነቃሁ።

ትንሽ፤ ጠባቡና ኮርኒሱ ዝቅ ያለው ከፍል በአንድ ግዙፍ የልብስ ቁም ሣጥንና ግሀኖች ልብሶችና ቡትቶዎች የተሞላ ነበር። ከሞላ ጐደልም ጭለማ ውጥታል። በክፍሉ የወዲያኛው ጫፍ በኩል ጠረጴዛው ላይ ቢልቢል የሚለው ያለቀ የሻማ ብርሃን ሊጠፋ ትንሽ ቀርቶታል። ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ክፍሉ በጨለማ መዋጡ የግይቀር ነው።

ራሴን ለማወቅ ብዙ አልፈጀብኝም። ሁሉም ነገር የኔን መንቃት ይጠብቅ ይምስል ያለምንም ድካም በአእምሮዬ ብልጭ አለ። ወዲያውኑ እንቅልፍ ወስዶኝ 'ንኳ ከትውስታዬ በማይጠፉ በሚያንጉላጅ ህልሚ ዙሪያ መሀል የሚሽከረከር የሆነ ነገር አለ። አስገራሚው ነገር ግን በትላነትናው ዕለት የደረሰብኝና አሁን ስነቃ ይቅር ብዬ የተውኩት ድሮ በጣም ድሮ የተፈጠረ ነገር መስሎ ተሰማኝ።

ጭንቅላቴን ከብዶኛል። የሆነ ነገር በላዬ ላይ እያንጐበበ የሚተናኮለኝ፤ የሚቀሰቅሰኝና የሚያስጨንቀኝ ይመስላል። ብሽቀትና ጥቁር ተስፋ መቁረጥ ከውስጤ እየፈለቁ ልውጣ ልውጣ ይሉኛል። ድንገት አጠገቤ በትኩረትና በመገረም የሚያስተውሉኝ ሁለት በሰፊው የተከፈቱ ዓይኖች አየሁ። በነዛ ዓይኖች ውስጥ የማየው እይታ ደንታ ቢስና ባዶ ነበር።

ልክ ቀዝቃዛ የጥንስስ ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ ሲገባ የሚሰማውን ዓይነት የመቅፈፍ ስሜት ጭንቅላቴ ውስጥ ተቀሰቀሰ። ስሜቱም በመላ አካላቴ ውስጥ ተሠራጨ። እነዛ ሁለት ዓይኖች ሲመረምሩኝ ነው የቆዩት።

ትዝ ሲለኝ ለዚህች ፍጡር ባለፉት ሁለት ሰዓታት ውስጥ አንዲት ቃል አልተነፈስኩም። አስፈላጊም ነው ብዬ አላሰብኩም። ይሄም በሆነ ምክንያት ስሜቴን ነካው። ድንገት ያለ እውነተኛ ፍቅር ወደ አልጋ ተያይዞ የመሄዱ እርኩስ ስሜት እንደሸረሪት ቀፎ ታየኝ። በዚህ ሁኔታ እርስ በርስ ተፋጠን ለብዙ ደቂቃዎች ቆየን። ይሄ ሁሉ ሲሆን ዓይኗን ከኔ ቀድማ አልሰበረችም። ፊቷ ላይ ያለውን ስሜትም አልቀየረችም። ሰቀጠጠኝ።

ይሄንን የማይቋቋሙት ሁኔታ ለመለወጥ ስል ስምሽ ማነው? ስል ጠየቅኳት። ምንም ዓይነት የወዳጅነት ስሜት የመፍጠር ፍላጐት በማያሳይ ሁኔታ ዓይኖቿን ከኔ ላይ አንስታ ወደሌላ በመዞር እንደሹክሹክታ ባለ ድምፅ «ሊዛ እባላለሁ» አለች።

ለቀጣዩቹ ጥቂት ደቂቃዎች ምንም ቃል አልተነፈስኩም። እጆቼን ከጭንቅላቴ ሥር በማዋልና ኮርኒሱ ላይ በማፍጠጥ ለራሴ የማወራ ይመስል «ትላንት አየሩ በጣም ቀሩፈ በረዶውም አስፈሪ ነበር» አልኩ።

መልስ አልሰጠችኝም። ሁሉም ነገር ይቀፍ ነበር። በንዴት ፊቴን በከፊል ወደሷ በማዞር ከደቂቃ ፀጥታ በኋላ «እዚህ ነው የተወለድሽው?» አልኳት።

«አይደለም»

«ከየት መጣሽ ታዲያ?»

«ሪጋ» አለች በማንገራገር።

«ጀርመን?»

«አይ! ራሽያዊት ነኝ»።

«ምን ያህል ጊዜ ሆነሽ?»

«የት?»

«እዚህ ቤት»

«አሥራ አምስት ቀን»

ስትናገር ቁርጥ ቁርጥ እያደረገች ነው። ሻማው ጠፋ፤ ፊቷንም ማየት አቃተኝ።

«ወላጆችሽ አሉ?»

«አይ! – አዎ– አሉ»

«የት ናቸው?»

«እዛው ናቸው፤ ሪጋ!»

«ምንድን ናቸው?»

«አፋ!»

«አፋ? ምን ማለትሽ ነው? ንገሪኝ እነማን ናቸው? ምንድን ናቸው?»

«ባለሱቆች»

«ብዙውን ሕይወትሽን ከነሱ ጋር ነው የኖርሽው?»

«አዎ»

«ስንት ዓመትሽ ነው?»

«ሃያ»

«ለምን ከነሱ ተለየሽ?»

«አፋ!»

ይህ «አፋ» ማለት ተወኝ ለለችኝ ማለት ነው። ዝም አልን።

ለምን ትቻት እንደልሄድኩ እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው። ይበልጥ መከፋት ተሰማኝ። ትላንት የሆነው ሁሉ እየተቆራረጠ በህሊናዬ መጣብኝ። ድንገት የዛን ዕለት ጠዋት ወደ ቢሮዬ ስጣደፍ መንገድ ላይ ያጋጠመኝ ትዝ አለኝ።

ወሬ ለመጀመር ምንም ፍላጐት ሣይኖረኝ ሳላስበው ጮክ ባለ ድምፅ «ትላንትና የሬሣ ሣጥን ተሸክመው ሲሄዱ አየሁ። መሬት ፈጥፍጠውት ነበር።»

«የሬሣ ሣጥን?»

«አዎ፣ ገበያ ውስጥ ከሆነ የጥንስስ ማስቀመጫ ቤት ውስጥ ነው ያወጡት።»

« በርግጥ ከጥንስስ ማስቀመጫ ቤት ውስጥ አይደለም ከሆነ ቤት ምድር ቤት ውስጥ ነው። ሁሉም ቦታ ጥንባት ነበር። የወዳደቀ የተቀራረፉ ነገሮችና የሆነ የሚሰነፍጥ ሽታ አው! እንዴት ያስጠላል።»

ፀጥታ።

«ቀፋፊ የቀብር ቀን ነበር።» በማለት ጀመርኩ፤ ዝም ማለት ስላልፈለግኩ ብቻ።

«ምንድነው ቀፋፊው ነገር?»

«እምልሽ በረዶው –ጤዛ–» አዛጋሁ።

ላፍታ ያህል በፀጥታ ከተዋጠች በኋላ ድንገት «ምን ልዩነት ያመጣል?» አለች።

«ምን ማለትሽ ነው? በጣም ቀፋፊ እኮ ነው» አዛጋሁ።

«መቼም መቃብር ቆፋሪዎቹ በበረዶ ነመደብደባቸውና በመራሳቸው ሣይሰድቧት አይቀሩም። የመቃብሩ ጉርጓድ ውስጥም ውሃ ሳይገባበት ሉይቀርም።» ስል ቀጠልኩ።

በሚገርም ዓይነት ጉጉት ነገር ግን ቁርጥ ቁርጥ በሚልና ቁርጠኛ አነጋገር «ጉድጓድ ውስጥ እንዴት ውሃ ሊገባ ይችላል?» ስትል ጠየቀች።

ወሬውን እንድገፋበት ከውስጤ የሚቀሰቅሰኝ ነገር ተሰማኝ። «አው! በርግጥ ውሃማ ይኖረዋል። ከሥሩ ቢያንስ ቁርጭምጭሚት ድረስ የሚደርስ

ውሃ ይኖራል። እ! በቮልኮ መካነ የመቃብር ውስጥ ደረቅ መቃብር መሬት ማግኘት አይቻልም።»

«ለምን አይቻልም?»

«ምን ማለትሽ ነው? ጠቅላላ ቦታው እረግረግ አይደል 'ንዴ? ሁሉም ቦታ ረግረግ መሬት ነው። እኔ ራሴ ባይኔ አይቸዋለሁ።»

(የመቃብር ቦታውን አይቼው አላውቅም። ቮልኮ የሚባል መካነ መቃብር ድርሽ ብዬ አላውቅም። ስለሱ የማውቀው ነገር ቢኖር ከሰዎች የሰማሁት ወሬ ብቻ ነው።)

«መሞት አያሳስብሽም አይደል?»

እራሷን እንደመከላከል ዓይነት ሆና «ለምንድነው የምሞተው?» ስትል መለሰች።

«መቼም ግልፅ ነው። አንድ ቀን ትሞቻለሽ። አሟሟትሽ ትላነት ሬሣ ሣጥኗን ካየሁዋት ልጅ ብዙ ይለያል ብዬ አላሰብም። እሷም እንዳንቺ ዓይነት ልጅ ነበረች። የሞተችው በሳምባ በሽታ ነው።»

«ሆስፒታል ውስጥ ልትሞት ትችል ነበር» አለችና «ሽርሙጣዋ ሆስፒታልም መሞት ትችል ነበር።» በማለት ደግማ ተናገረች።

(«ሁሉንም ነገር ታውቀዋለች» አልኩ ለራሴ ምክንያቱም ‹ልጅቷ› ከማለት ይልቅ ‹ሽርሙጣዋ› ነው ያለችው።)

ውይይቱ ይበልጥ እየቀሰቀሰኝ ስለመጣ እንዲህ ስል ቀጠልኩ። «ለቀጠሮት ሴት ብዙ ያልከፈለቻቸው ዕዳ ነበረባት። ምንም 'ንኳ በሣንባ በሽታ ብትሰቃይም እስከ ዕለተ ሞቷ ድረስ ለቀጣሪዋ ሳትሰስት አገልግሎቷን ሰጥታለች። ታክሲ ነጂዎች መንገድ ላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር ይህንን ሲያወሩ ሰምቻለሁ። እየተሳሳቁ ነበር የሚያወሩት። እንደውም ማታ እዛው ቤት ተገናኝተው እሷን በማስታወስ ለመጠጣት ተቀጣጥረዋል።»

(የምናገረው ሁሉ በአብዛኛው የውሸት ፈጠራ ነው።)

ዝምታ ፡ ጥልቅ ዝምታ! ንቅንቅ እንኳ አላለችም።

«መቼም ሆስፒታል መሞት ይሻላል እንደማትል ተስፋ አደርጋለሁ። ምንድነው የሚያመጣው ልዩነት? ደግሞስ ለምን መሞት አለብን?» አለች በመቆርቆር ዓይነት።

«ዛሬ ባይሆንም በኋላ»

«በኋላ? እና ምን?»

«ብዙም ስለራስሽ እርግጠኛ አትሁኚ። በርግጥ አሁን ወጣት መልከ መልካምና ትኩስ ነሽ ለዚህም ነው ብዙ ዋጋ የሚሰጡሽ። ነገር ግን በእንዲህ ዓይነቱ ሕይወት ካሁን በኋላ እንደ አሁኑ አትሆኚም ውበትሽ ይጠፋል።»

«ከአንድ ዓመት በኋላ ?»

«እ...! ደህና! ካንድ ዓመት በኋላ ለማንኛውም ዋጋሽ በከፍተኛ ሁኔታ ይወርዳል።» አልኩኝ በከፉት ስሜት። ከዛ በኋላ ዝቅ ወዳለ ሌላ ቡና ቤት ለመሄድ ትገደጃለሽ። በሌላኛው ዓመት ሌላ ሶስተኛ ቤት ትዛወሪያለሽ፤ ቁልቁልዮሽ ። በሰባት ዓመት ጊዜ ውስጥ የገበያው ሥፍራ እንዳለው ጥንስስ ቤት ትወርጃለሽ። ያመጥፎ ባልሆን ነበር። ነገር ግን አየሽ ልትታመሚ ትችያለሽ። ሳል ወይም የመተንፈስ ችግር የመሰለውን! በእንዲህ ዓይነቱ ሕይወት ደግሞ በሽታን በቀላሉ መገላገል አይቻልም። አንዴ ከታመምሽ አገግሞ ለመነሣት በጣም ነው የሚያስቸግረው እና ትሞቺያለሽ።»

ገልበጥ በማለት በጣም በጥላቻ «ደህና ልሙታ! »አለች።

«አታዝኚም ማለት ነው ለሕይወትሽ?!»

ዝምታ።

«ለመጋባት ቀለበት አስረሻል አይደለም እንዴ?»

«ለምን የራስህን ጉዳይ አትከታተልም? እኔን ተወኝ።»

«አ! ይቅርታ። እኔ አንቺን በመስቀለኛ ጥያቄ ለግጣደፍ አይደለም። ደግሞስ ምን ግድ አለኝ? ለምንድነው በጣም የተናደድሽው? ሁሉም ዓይነት ችግሮች እንዳለብሽ ይለማኛል። በርግጥ ይሄ የኔ ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን አለማዘን ደግሞ አልችልም። ይሽው ነው።»

«ለማን ነው የምታዝ ነው?»

«ላንቺ»

«አስፈላጊ አይደለም» አለች እንደሹክሹክታ በሚቆጠር ድምፅ እየተገላበጠች። ከንከኝ። ያንተ ያለህ። እኔ ለሷ ትሁት ነኝ እሷ ግን ....

«ደህና እስቲ ምኑንነው የምታስቢው አንቺ? ትክክለኛ መንገድ ላይ ነኝ ብለሽ ነው የምታስቢው አይደል?»

«ምንም አላስብም»

«አዎ! ያንቺ ስህተት እሱ ላይ ነው። አታስቢም። ይልቅ አሁን ጊዜው እያለሽ ብታስቢበት ይሻላል። ገና ወጣት መልከመልካም ስለሆንሽ ፍቅር ይዞሽ ልታገቢና ደስተኛ ልትሆኚ...»

በቅድሙ ሻካራ፣ ፈጣንና ቁርጥ ያለ አነጋገሯን አቋርጣ «ያገቡ ሴቶች ሁሉ ግን ደስተኞች ናቸው ማለት አይቻልም። ይቻላል?»

«እንደሱማ አይደለም። በእርግጥ ሁሉም ደስተኞች ናቸው ማለት አይቻልም። ከዚህ ሕይወት ግን በጣም መቶ እጥፍ የተሻለ ነው። ካፈቀርሽ ያለደስታ ’ንኳ መኖር ትችያለሽ። ሕይወትኮ በሀዘንም ውስጥ ጣፋጭ ነች። ሕይወት ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆንም ’ንኳ መኖርኮ ደግ ነው! እዚህ ግን ያለሽ ምንድነው አንቺ? ርካሽነት !»

በመጠየፍ ፊቴን አዞርኩ። በቀዝቃዛ ስሚት ማስተዋሌን አቆምኩ። በራሴ ቃላትና ሰበካ ተነክቼ ታወኩ። በጐሬዬ ውስጥ ሁኜ ያከማቸሁትን ትናንሽ ሀሣቦች ለመተንተን ጓጓሁ። ድንገት የሆነ ነገር ውስጤ ተቀጣጠለ። ያልነበረ ዓላማ ተከሰተልኝ።

«ስለኔ ግድ አይስጥሽ» አልኳት። «እኔ ከቶም ምሣሌ ልሆንሽ የምችል ሰው አልሆንም። ምናልባት ካንቺም የባሰኩ ነኝ። ትላንት ወደዚህ ስመጣ ሰከሬ ነበር። ደግሞም ወንድ ለሴት ምሣሌ ሊሆን አይችልም። ምንም ’ንኳ ራሴን ባቆሽሽና ባዋርድም የማንም ባሪያ ግን አይደለሁም። አሁን እዚህ ነኝ። ትንሽ ቆይቼ እሄዳለሁ፤ ድጋሚም አታይኝም። የሆነውን ሁሉ ረስቼ ሌላ ሰው እሆናለሁ። አንቺ ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ ባሪያ ነሽ። አዎ ባሪያ! ያለሽን በሙሉ ነው የምትሰጭው። ነፃነትሽን በሙሉ። አንድ ቀንኳ ይህንን የባርነት ሰንሰለት ልሰበር ብትይ አትችይም የበለጠ ትተበተቢበታለሽ ’ንጂ። በእንዲህ ዓይነት የተረገመ ሰንሰለት ነው የተቀፈደድሽው። አውቀዋለሁ። ይገባሻል ብዬ ስለማላስብና ስለማላምን ሌሎች ነገሮችን አልጠቅስልሽም። ግን እስኪ አንድ ነገር ንገሪኝ፤ ለቀጠረችሽ ሴት ያልከፈልሽው እዳ አለብሽ? አለብሽ! አይደለም ’ንዴ ይሽው!» ምንም ’ንኳ መልስ ባትሰጥም በመላ ነፍሷ ትሰማኝ ነበረ። «አየሽ ሰንሰለቱ እሱ ነው። በምንም ተአምር እዳሽን ልትከፍይ አትችይም። ምክንያቱም ከእዳ ነፃ እንዳትሆኚ ሆነ ብለው የሚያደርጉት ነው። አንደው ባጭሩ ነፍስሽን ለሰይጣን የመሸጥ ያህል ነው። አሁን ለምሣሌ እኔ እንዳንቺ የተረገምኩ ሆነ ብዬ በጥንብ ውስጥ የምዳክር ሰው ነኝ። ምክንያቱም እኔም ልቤ በሽተኛ ነው። ሰዎች የሚጠጡት ደስተኛ ስላልሆኑ ነው አይደለም? እኔም እዚህ ያለሁት ደስተኛ ስላልሆንኩ ነው። እስቲ አሁን ንገሪኝ ምንድነው የዚህ ጥሩ ነገሩ? እኔና አንቺ ከጥቂት ሰዓታት በፊት እዚህ ወሲብ ስንፈፅም ነበር በዛን ጊዜ ሁሉ ግን አንዲትም ቃል አልተለዋወጥንም። ከዚያ በኋላ ነው ልክ እንደ አውሬ አይንሽን አፍጥጠሽ ያየሽኝ። እኔም እንደዛው አፈጠጥኩብሽ። እንዲህ ነው ’ንዴ ሰዎች እርስ በእርስ ሲፋቀሩ? እንደዛ ነው ’ንዴ አንድ ሰው ከሌላው ጋር ፍቅር መሥራት ያለበት? ባጭሩ ልንገርሽ፤ ሁሉም ነገር ቀሩፌ ነው።»

ወዲያው በፍጥነት «አዎ!» ስትል ተስማማች።

«አዎ!» ያለችበት ፍጥነት አስገረመኝ። «ለካስ እንዲያ አፍጣ ስትመለከተኝ የነበረው እንደኔ አይነት ሃሳብ መጥቶባት ነው ማለት ነው። ይሄ

የሚገርም ነው። ለክስ እሷም እንደኔ ማሰብ ትችላለች። ይሄ ማለት እርስ በእርስ እንመሳሰላለን ማለት ነው» አልኩ በሀሣቤ በደስታ።

ፊቷን ወደኔ አዙራ ተጠጋች! ጨለማ ስለሆነ የሚመስለኝን ነው የምነግራችሁ! ጭንቅላቷን በእጇ መዳፍ ደግፋዋለች። ምናልባት እየመረመረችኝ ነው። ላያት ባለመቻሌ አዝናለሁ። በረዥሙ ስትተነፍስ ሰማሁዋት። በተረጋጋ ድምፅ «ግን ለምን ወደዚህ ሕይወት መጣሽ?» በማለት ጀመርኩ።

«አፍ!»

«ባባትሽ ቤት ብትኖሪ ግን በጣም ቆንጆ ይመስለኛል አይደለም 'ንዴ? ሞቃት፣ ነፃ፣ የራስሽ ቤት።»

«ግን ከዚህ የባሰስ ቢሆን?» ትከከለኛውን ታና ማግኘት አለብኝ የሚል ሃሣብ በአይምሮዬ ብልጭ አለብኝ። «ከሷ ጋር እንዲህ ስሜታዊ በሆነ መንገድ ልቀጥል አልችልም»

ያልቆየ የአፍታ አሣቤ ብቻ ነው። በእርግጠኛነት የማውራት ፍላጐት ቀስቅሳብኛለች።

«ግን ከዚህ የባሰ አስከፊ ቢሆንስ?» ላለችው ጥያቄ እኔም «ላፍታ አልጠራጠረውም» በማለት ቀጠልኩ። «ሁሉም ነገር ሊሆን ይችላል። አየሽ! እርግጠኛ ነኝ የሆነ ሰው ደፍሮሻል። ይሄ ደግሞ ካንቺ ይልቅ የነሱ ጥፋት ነው። ልብ አድርጊ እኔ ስላንቺ ታሪክ የማውቀው ነገር የለም ነገር ግን እንዳንቺ ያለች ልጅ እንዲህ ያለ ቦታ በራሷ ዝንባሌ አትመጣም፣ ትመጣለች?»

«ምናይነት ልጅ ነኝ?» በማለት በማይሰማ ሹክሹክታ አጉረመረመች።

እኔ ግን ሰማሁት። ኤሞ! አቆላመጥኳት። ጥሩ አልሠራሁም። ግን ምናልባት መጥፎ ላይሆን ይችላል። ምናልባትም ትክክለኛ ይሆናል።...ዝም ፀጥ አለች።

«ይቺውልሽ ሊዛ፣ ስለራሴ እነግርሻለሁ። በልጅነቴ ቤት ያለኝ የነበረኝ ቢሆን ኖሮ አሁን የሆንኩትን አልሆንም ነበር። በቤተሰብ ውስጥ ያለሽ ሕይወት ምንም ያህል መጥፎ ቢሆን 'ንኳ ወላጆችሽ መጥፎ ሊሆኑ አይችሉም። ናቸው? ላንቺ ባዕዳን አይደሉም፣ ናቸው? በዓመት አንዲም 'ንኳ ቢሆን ፍቅራቸውን ያሳዩሻል። የፈለገ ብትከፊ ቤትሽ መሆኑን ታውቂያለሽ። እኔ ግን ያለ መኖሪያ ቤት ነው ያደግኩት። ለዚህ ይመስለኛል አሁን የሆንኩትን የሆንኩት። – ስሜት የሌለው ሰው!...»

አሁንም የሆነ ምላሽ ትሰጣለች ብዬ ጠበቅኩ።

ስለምናገረው ነገር የምትረዳው ነገር ያለ አልመሰለኝም አልኩ በሀሣቤ። ደግሞም ይህ ሁሉ ሞራላዊ ትንተና አሰቂኝ ነው አልኩ። «አባት ሆኜ የራሴ የምላት ሴት ልጅ ብትኖረኝ ኖሮ ከወንድ ልጆቹ በላይ የማፈቅራት ይመስለኛል አርግጠኛ ነኝ።»

«ግን ለምን?» አለች።

አ! እያዳመጠች ነው ለካ!።

«ለኔም በግልፅ አይገባኝም ሊዛ! አየሽ አንድ ጥብቅ ቆፍጣና የሆነ አባት አውቃለሁ። ነገር ግን፣ ሴት ልጁን ተንበርክኮ እጆቿን፣ እግሮቿን ይስማል፣ እሷን ማየት ፈፅሞ አይሰለቸውም። አዎ! አይሰለቸውም። እሷ የሆነ ፓርቲ ቦታ ሄዳ ምሽቱን ሁሉ ስትደንስ እሱ ባለበት ቦታ ንቅንቅ ሣይል ከአምስት ሰዓት ላላነሰ ጊዜ ዓይኑን ሳያነሣ በስስት ይመለከታታል። እሷን በተመለከተ እብድ ነው። ማታ ደክሟት ስትተኛ ሄዶ እተኛችበት ግንባሩ ላይ የመሰቀል ምልክት ሠርቶ ይስማታል። እሱን በተመለከተ ያደፈ አሮጌ ኮት ለብሶ ሊናር ላየውና ላስተዋለው ሁሉ ሚስኪን ነው። ለሷ ግን የሚሰስተው ነገር የለም። ለሷ ውድ የሆኑ ስጦታዎችን ይገዛና በስጦታው

ከረካች ደስታውን መቆጣጠር እስኪያቅተው ድረስ ይፈነጥዛል። አባቶች ሴት ልጆቻቸውን ከእናቶች በላይ ያፈቅራሉ። ስለዚህ ብዙ ልጃገረዶች በቤታቸው ደስተኞች ናቸው። እኔማ በተለይ ልጄ እንድታገባ ፈፅሞ አልፈቅድም።»

ፈዛዛ ፈገግታ እያሣየች «ለምን?» አለች።

«እቀናለሁ። ግለቴ እሷ ከሌላ ሰው ጋር የመሳሳሟን ሃሣብ ልቋቋመው አልችልም። ከአባቷ በላይ እንግዳ ማፍቀሯ አይዋጥልኝም። ሀሣቡ ራሱ ያሰቃየኛል። በእርግጥ የማወራው ትርጉም የለውም። ግንኛውም አባት ዞሮ ዞሮ መጪረሻ ላይ ወደ ትክክለኛ ውሣኔ ይመጣል። እኔ ግን ሲመስለኝ እንድታገባ ከመፍቀዴ በፊት እስከምት የሚያበቃ ጭንቀት የምጪነቅ ይመስለኛል። የልጄን እጅ ለትዳር የጠየቁ ወንዶች ላይ በሙሉ ያለጥርጥር ስህተት አገኛለሁ። መጪረሻ ላይ ግን እሷ ራሷ የመረጠችውንና የወደደችውን እንድታገባ የምፈቅድላት ይመስለኛል። ሁልጊዜ ልጅቷ ይሻለኛል ብላ በመረጠችው አባት ይበልጥ ይከፋበታል። በዚህ የተነሣ በቤተሰቦች ውስጥ ብዙ ችግሮች አሉ።»

«አንዳንድ ወላጆች እንኳን በከብር የመዳር እድል ቀርቶ ሴት ልጆቻቸውን መሸጥ ያስደስታቸዋል» አለች ድንገት።

አሃ! ለካ ይሄ ነው ያንቺ ችግር።

«አየሽ ሊዛ! ይሄ የሚሆነው እግዚአብሔርም ሆነ ፍቅር በሌለው ቤተሰብ ውስጥ ብቻ ነው።» አልኩ በሞቀ ስሜት በማቋረጥ። «ፍቅር የሌለበት ጨዋነትም የለ። እንዲህ ያሉ ቤተሰቦች መኖራቸው እውነት ነው። የማወራው ግን ስለነሱ አይደለም። እንደዚህ የምታወሪ ከሆነ ከቤተሰብሽ ውስጥ ምንም ዓይነት ርህራሄ ልታውቂ አትችይም። በጣም እድለቢስ መሆን አለብሽ። እንዲህ አይነቱ ነገር ደግሞ ባብዛኛው የሚፈጠረው በድህነት ምክንያት ነው።»

«በሃብታም ቤተሰቦችስ ውስጥ ምን የተለየ ነገር አለ? ሀቀኛ ሰዎች ደሀ ቢሆኑም 'ንኳ በደስታ ይኖራሉ።»

«አዎ! እኔም ይመስለኛል። ግን እንዴት መሰለሽ ሊዛ ሰው የሚያስታውሰው ችግሮችን ብቻ ነው። ጥሩ አድሎችን በፍፁም አያስታውስም። ጥሩ አድሎችንም ግምት ውስጥ የሚያስገባ ቢሆን ኖሮ የራሱ ጥሩ ድርሻ እንዳለው ያውቅ ነበር። ግን ቤተሰቡ ጋር ሁሉም ነገር ትክክል ቢሆን በእግዚአብሔር ምርታት ባልሽ ጥሩ ሰው ቢሆን፣ ቢያፈቅርሽ፣ ቢወድሽና ለአፍታ እንኳ ጨርሶ ባይተውሽስ? እንዲህ ዓይነቱ ቤተሰብ በርግጥም ደስተኛ ነው። አንዳንድ ጊዜ እንኳ ነገሮች እንደሚፈልገው ባይሳኩም አያስከፋም። ምክንያቱም ሃዘን የለማ። ካፈቀርሽው ሰው ጋር በመሰረትሽው ጋብቻ ውስጥ ያሣለፍሻቸውን የመጀመሪያ ዓመታት ውስጥ! አቤት ያለው ደስታ! አንዳንድ ጊዜማ! ምን ዓይነት ደስታ አለው መሰለሽ። መጀመሪያ ከባልሽ ጋር የምትፈፅሚው ፀብ እንኳ በደስታ ነው የሚያልቀው። አንዳንድ ሴቶች አሉ ባሎቻቸውን በጣም ባፈቀሩ ቁጥር በጣም ለመጣላት ነው የሚፈልጉት። እውነቴን ነው የምነግርሽ እኔ ራሴ እንዲህ ዓይነት ሴት አውቃለሁ። አየህ ትለው ነበር። በጣም ነው የምወድህ። በጣም ስለምወድህም ነው የማሰቃይህ። ይህንን ልትረዳው ይገባል! አንድ ሰው ስለወደደ ብቻ እንደሚያሰቃይስ ታውቂያለሽ? ባብዛኛው ሴቶች ናቸው እንደዛ የሚያደርጉት ለራሣቸው እንዲህ ይላሉ፤ በኋላ አለቅጥ እወደዋለሁ። እንከባከበዋለሁ። ስለዚህ አሁን ትንሽ ባሰቃየው ምንም አይደል። በቤት ውስጥ ያለው ሁሉ አንቺን ማየት ያስደስተዋል። ሁሉም ነገር ደስ ይላል። በጣም ደስተኛና ሃቀኛ...ሌሎች ሴቶች በርግጥ ቀናተኞች ናቸው። ባሏ ወደ አንድ ቦታ ሲሄድ (እንዲህ ዓይነት ሴት አውቃለሁ) በምሽት ወጥታ የት እንዳለ እዛ ቤት ወይም ከዛች ሴት ጋር የሆነውን ሁሉ በድብቅ ካላረጋገጠች የማትረካ አለች። ይሄ መጥፎ ነው። በጣም መጥፎ። ስህተት መሆኑንም እሷ ራሷ ታውቀዋለች። በዚህ ድርጊቷ ልቧ ይከዳታል። ትሰቃያለች። ነገር ግን አየሽ ታፈቅራለች። ይህ ሁሉ በፍቅር የተነሣ ነው።

አየሽ ከጠቡ በኋላ ጥፋተኛ መሆኗን ማመኗ እንዴት ያስደስታታል መሰለሽ፤ ያ ሁሉ ድንገት ወደደስታ ይለወጣል። በጣም ደስተኛ ከመሆናቸው የተነሣ በመጀመሪያ ጊዜ እንዴት እንደተገናኙ፤ አሁን ገና የተጋቡ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፋቀሩ ይመስላሉ። እርስ በእርስ የሚፋቀሩ ከሆነ በባልና በሚስት መካከል የሚሆነውን ሁሉ ማንም ሊያውቅ አይገባም። ምንም ያህል ቢጣሉ 'ንኳ በመካከላቸው እንዲዳኙ እናቶቻቸውን 'ንኳ መጥራት የለባቸውም። እንዲህ አረገኝ፤ እንዲህ አደረገችኝ መባባል የለባቸውም። የራሣቸው ዳኞች ራሣቸው ናቸው። ፍቅር እግዚአብሔር ብቻ የሚገነዘበው ሚስጥር ነው። ስለዚህ ምንም ተፈጠረ ምን ከሁሉም ዓይኖች መደበቅ አለበት። እንዲህ ከሆነ ፍቅሩ ይበልጥ ቅዱስና ይበልጥ ጣፋጭ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ይበልጥ ሊከባበሩ ይችላሉ። ብዙ ደስታቸው የሚመነጨው ደግሞ ከዚህ የእርስ በእርስ መከባበር ነው። አንድ ጊዜ ፍቅር ካላቸው የተጋቡት ለፍቅር ከሆነ ያ ፍቅር የሚጠፋበት ምንም ምክንያት የለም። ያለጥርጥር እስከ ዕድሚያቸው መጨረሻ ሊያቆዩት ይችላሉ። ሊያቆዩት የማይችሉበት ሁኔታ ብዙም አይከሰትም። ባልየው ጥሩና ጨዋ ሰው ከሆነ ፍቅር ለምን ያልፋል? በእርግጥ ሲጋቡ እንደነበረው እርስ በእርስ አይፋቀሩም በኋላ ላይ ግን ፍቅራቸው የበለጠ ይሆናል። ምክንያቱም በነፍስም በሥጋም ይጣመራሉ። ጉዳዮቻቸውን በጋራ ይመራሉ። በመካከላቸው ሚስጥር አይኖርም። ዋናው ነገር ማፍቀርና ፅናት ነው። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ከባድ ሥራ እንኳ ደስታ ነው። ለልጆችሽ ስትይ 'ንኳ አንዳንድ ጊዜ መራብ ራሱን የቻለ ደስታ ነው። ምክንያቱም ለዚህ ውለታሽ ነገ ልጆችሽ ያፈቅሩሻል። በሌላ አነጋገር ለወደፊትሽ ቅርስ ነው የምትይዢው ማለት ነው። ልጆችሽ እያደጉ ሲመጡ የነሱ ምሳሌ መሆንሽ ይሰማሻል። የነሱ ደጋፊ መሆንሽ ይታወቅሻል። ብትሞቺ 'ንኳ ያንቺ ሐሳቦችና ሰሚቶች እነሱ ዘንድ ይቀራሉ። ምክንያቱም እነሱ ማለት በሁሉም ነገር አንቺ ናቸውና። የሚኖሩት ካንቺ በተቀበሉት ነውና! ስለዚህ ትልቅ ኃላፊነት ነው። በእርግጥ አባትና እናት ይቤልጥ ከመቀራረብ የሚያግዳቸው ነገር የለም። ልጆች ትልቅ ችግር ናቸው ይላሉ ሰዎች። ግን

ማነው እንዲህ የሚለው? ሰዎች በምድር ላይ የሚያገኙት ታላቅ ደስታ ልጆች ናቸው። ትናንሽ ሕፃናትን ትወጂያቸዋለሽ ሊዛ? እኔ በጣም ነው የምወዳቸው። እስኪ ይታይሽ የሆነ ትንሽ ሕፃን ጡትሽን ሲጠባሽ፣ ሚስቱ ልጁን ስታጠባ አይቶ ስሜቱ የማይነካ የባል ልብ የት ይገኛል? ድብልብል ሕፃን፣ ይዘረጋጋል ወደ አንቺ ያንጋጥጣል። ትናንሽ እጆቹ ነጭና ቡፍ ያሉ ጥፍሮቹ ንፁህና ትናንሽ በጣም ትንሽ ከመሆናቸው የተነሣ ስታያቸው ሳቅሽ ነው የሚመጣው። ትናንሽ ዓይኖቹ አፍጥጠውና አተኩረው ሲያዩሽ ሁሉን ነገር የተረዳው ይመስላል። ጡትሽን ሲጠባ በነዛ ማር ትንሽ እጆች ጡትሽን ሳብ እያደረገ ይጫወታል። አባቱ ከተጠጋው ጡቱን ለቆ ወደኋላው ውጥር ይላል። አባቱን አየት ያደርግና መቼም እንዴት ደስ እንደሚል ልነግርሽ አልችልም ከትከት ብሎ ይስቃል። ወዲያው ወደተወው ጡት እንደገና ተመልሶ በስስት መጥባት ይጀምራል። ወይም ጥርሶቹ ብቅ ብቅ ማለት ሲጀምሩ ደግሞ የናቱን ጡት ንክስ ያደርግና በጨረፍታ የናቱን ዓይን ዓይን ይመለከታለ። «አየሽ! እየነከስኩሽ ነው!» አባት ሚስትና ልጅ አንድ ላይ ባሉበት ሁሉም ነገር ደስታ አይደለምን? ማንም ሰው በነዚህ ደስታዎች የተነሣ ሁሉን ነገር ይቅር ይላል። አዎ! አየሽ ሊዛ አንድ ሰው ሌሎችን ከመወንጀሉ በፊት መጀመሪያ እንዴት መኖር እንደለበት ማወቅ አለበት።

«በነዚህ ሥዕሎች ነው የምታሰቃያት» አልኩ ለራሴ። የተናገርኩት እውነተኛ ስሜት ስለነበር ድንገት አፈርኩ። «እኔ ይሄንን እየተናገርኩ ድንገት በሳቅ ብትፈነዳስ? እንዴት ዓይነት መሣቂያ ጅል እመስል ነበር» ይህ ሀሣብ አበሳጨኝ። ወደ ንግግሬ መጨረሻ ላይ ይበልጥ ተነሣሣሁ። ኩራቴ በመጠኑ ተገድቷል። ጐሽም፣ ጐንተል አድርጋት የሚል ስሜት መጣብኝ።»

«ምንድ ነው? _____» አለችና ድንገት አቆመች።

ሁሉንም ነገር ተረድቼዋለሁ። በሚንቀጠቀጥ ድምፅ ውስጥ ለየት ያለ ቃና ሰማሁ ሻካራ፣ ቀዝቃዛና አልበገር ባይነቱ አሁን የለም። ለስላሳና ስብር ባለ አዲስ ቃና ተተክቷል። ድንገት እኔ ለሷ አፈርኩ። ጥፋተኛነት ተሰማኝ።

«ምን?» አልኩ ለማወቅ በመጓጓት።

«ለምን አንተ____»

«ምን?»

«ለምን አንተ ኧ– ኧ....እምትናገረው.. ማለቴ ስትናገር ከመፅሐፍ የምታነብ ነው የምትመስለው» አለች ድንገት ምፀት በተቀላቀለበት ድምፅ።

ይህን አስተያየቷን ከፉኛ ጠላሁት። የጠበቅኩት ይህንን አል ነበረም።

በዚህ ምፀቷ የራሷን ስሜቶች ሆነ ብላ መደበቋ አልገባኝም ነበር። ንፁህና ድንግል ልብ ያላቸው ሰዎች ድንገትና ያለምንም መግቢያ በአእምሮዋቸው ጓዳ ውስጥ ገብተው የሚበረብራቸውን ሰዎች የሚያቆሙበት መንገድ አልገባኝም ነበር። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ከኩራታቸው የተነሣ እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ እጅ እንደማይሰጡ፣ ስሜታቸውን ለማንም ሰው ለማሳየት እንደሚፈሩ አልተገነዘብኩም ነበር። ምፀታዊ አስተያየቷን ለመሰጠት ካደረገቻቸው ሙከራዎች እርብትብትነትና መጨረሻ ላይ አስተያየቱን ከሰጠችበት ዓይን አፋር ሁኔታ አንፃር ልገምት ይገባ ነበር። እኔ ግን ይህንን ለመረዳት ስላልተቸገርኩ ኃይለኛ የጥላቻ ስሜት ተቆጣጠረኝ። እንግዲያው ጠብቂኝ አልኩ በሃሣቤ።

VII

«ያንተ ያለህ! ሊዛ፣ እኔ እንኳን ስላንቺ ላስብ ቀርቶ የገዛ ራሴ ያንገሸገሸኝ ሰው ከምን ዓይነት መፅሐፍ ይጠቅሳል ተብዬ ልታሰብ እችላለሁ? በርግጥ ለምንም ነገር ደንታቢስ ነው ላልባል እችላለሁ። አይደለሁምና! ልቤ ውስጥ አሁን የተገለፀልኝ ስሜት ግን በእርግጠኛነት! በእረግጠኛነት! እዚህ በመገኘትሽ ከፉኛ የተቅለሸለሽ መሆንሽን ነው። ወይስ ልምድ ግን ልምድ ይህንን ያህል ትርጉም ልንሰጠው የሚገባ ነው? እርሺው ባክሽ፣ ልምድ ሰውን አይፈጥርም! እንዳው እውነቱን እንነጋገር ከተባለ አንቺ የማታረጂ፣ ሁልጊዜ ቁንጅናሽ አብሮሽ የሚኖርና እነሱም

ለዘለዓለም እዚህ እንድትሆኚ የሚፈቅዱልሽ መስሎሽ ታምኚያለሽን? ይሄን ስልሽ እንግዲህ ይህም ኑሮሽ እንደጤነኛ ኑሮ ተቆጥሮ ነው። ግን አሁን ስለምትኖረው ኑሮ ስላንቺ ሕይወት ላስረዳሽ። ምንም 'ንኳ አሁን ወጣት፣ አግላይ ውብ፣ ስሜታምና ፍልቅልቅ ብትሆኚም እኔ ከእንቅልፌ እንደባነንኩ የተሰማኝ ስሜት ካንቺ ጋር እዚህ መገኘቴን መጠየፍ ነበር። አየሽ ሰው እንዲህ ዓይነት ቦታ የሚመጣው ሊለክር ብቻ ነው። ነገር ግን አንቺን ያገኘሁሽ ሌላ ቦታ ቢሆን አኗኗርሽ እንደጥሩ ጨዋ ሰዎች ሕይወት ቢሆን ኖሮ ካንቺ ጋር ለመሆን መቋመጥ ብቻ ሣይሆን ከእግር እስከራሴ በፍቅርሽ ልጥለቀለቅ እችል ነበር። ልታዋሪኝ ቀርቶ ዞር ብለሽ ብታይኝ 'ንኳ ደስታውን አልችለውም ነበር። ከበርሽም ባልጠፋሁ ነበር። ፊት ለፊትሽ ተንበርክኬ በተለማመጥኩ ለጋብቻ እጅሽን ብትፈቅጅልኝ መደሰት ብቻ ሣይሆን ክብር እንደሰጠሽኝም እቆጥረው ነበር። ባንቺ ላይ አንዳችም ቅሌታም ሃሣብ ለመወጠን ባልደፈርኩ ነበር። እዚህ ግን እኔ አንቺን ከፈለግኩ ያለብኝ ግሩጨት ብቻ ነው። አንቺ ወደድሽም ጠላሽም ወደእኔ መምጣት አለብሽ። እኔ ሣልሆን ያንቺን ፈቃድ የምጠይቀው አንቺ ነሽ። ወራዳ ገበሬ 'ንኳ የቀን ሠራተኛ መሆን ቢመርጥ ራሱን ግን ባሪያ አያደርግም ደግሞም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መልሶ የራሱ ጌታ እንደሚሆን እርግጠኛ ነው። አንቺ ስለራስሽ እንዲህ ማለት ግን ትችያለሽ? እስኪ እዚህ የምትከፍይውን መስዋዕትነት አስቢው! ምንድነው እንዲህ ባሪያ የሆንሽለት ዓላማ? ልብ በይ እዚህ በሥጋሽ ላይ ብቻ ሣይሆን በነፍስሽም ላይ አዛዦነት የለሽም! ፍቅርሽን ግንም ስካራም እንዲላለቅበት ነው የምትሰጪው! ፍቅር? ታዲያስ! ፍቅር ሁሉም ነገር ነው። ፍቅር የተከበረ እንቁ ነው። የሴት ልጅ ተመን ያለሽ ቅርሰ ፍቅር ነው! ፍቅር ነው! ይሄን ፍቅር ለማግኘት ወንድ ነፍሱን 'ንኳ አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ ነው። ራሱን ሞትን ፊትለፊት ለመቋቋም አይሸበረም! ያንቺ ፍቅር ግን ስንት ያወጣል? ሁለመናሽ ሊገዛ ይችላል። ሁለመናሽ!! ወንድ ደግሞ ያለፍቅር በቀላሉ ሊያገኝሽ እንደሚችል እስካወቀ ድረስ ግን ያንቺን ፍቅር ለማግኘት ይጣጣራል? ሰሴት ልጅ ደግሞ ከዚህ የበለጠ ስድብ የለም አይታይሽም ሁኔታው?

እናንተን ለማስደሰት—ሚስኪኖች! በቡና ቤት ፍቅርኞች እንዲኖራችሁ ያደርጋሉ። ያንተ ያለህ! ይሄ ሰድብ 'ንጂ ሌላ ምንድነው? ዓይን ያወጣ ግታለል 'ንጂ ሌላ ምን ይባላል? አንቺ ታምኚያቸዋለሽ እነሱ ከጀርባሽ ይንከተከቱበሻል! እንዳው ለነገሩ ይሄ አፍታሪሽ ከልቡ የሚያፈቅርሽ ይመስልሻል? እኔ አይመስለኝም። በየትኛውም ደቂቃና ሰዓት ከአጠገቡ ተጠርተሽ እንደምትሄጂ እያወቀ እንዴት ሊያፈቅርሽ ይችላል? ከሱ ጋር እያለሽ ጥለሽው ስትሄጂ እሱ ሰው ሣይሆን ትንኝ ነው ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ታዲያ ላንቺ ቅንጣት ታክል ክብር ሊኖረው ይችላልን? በሁለታችሁ መካከል ያለ የጋራ ፍላጐትስ ምን ሊሆን ይችላል? እሱ ይስቅብሻል። በዛም ፍላጐቱን ያረካል። ካንቺም የሚፈልገው ይህንን ነው። ካልደበደበሽም ዕድለኛ ነሽ። ይደበድብሽም ይሆናል። እስኪ ፍቅረኛሽ እንደመሆኑ መጠን ያገባሽ እንደሆነ ጠይቂው፤ ይሳለቅብሻል። ፊትሽ ላይ ካልተፋብሽ ወይም ካልደበደበሽ እሱ ራሱም ስሙኒ የማያወጣ ነው ማለት ነው። እና ታዲያ ለምን ብለሽ ነው ሕይወትሽን እዚህ የምታበላሺው? ለምን? ለምትጠጪው ቡና? ለምትበይው ምግብ? ደግሞስ እዚህ ለምን በደምብ እንደሚመግቡሽስ አስበሽው ታወቂያለሽ? ሌላ ሴት ጨዋ ሴት ብትሆን ኖሮ ለምን እንደሚቀልድቢት ስለምታውቅ የነሱን ምግብ ልትጐርስ አትችልም። አንቺ ግን እዚህ በዕዳ ተወጥረሻል። አመኚኝ ዕዳሽን ለመክፈል ከቶም አትችይም።

ስለዚህ እስከመጨረሻው ደንበኞችሽ በማንነትሽ እስኪያፈሡ እስኪሳለቱበሽ ድረስ እዚህ ነው የምትቆይው ይሄ ደግሞ አንቺ እንደምታስቢው የሚቆይ ሣይሆን በቅርቡ የሚደርስ ነው። በውበትሽ ልትመኪ አያስፈልግም። በዚህ ሕይወት ብዙ እንደማይቆይ ታውቂያለሽ፤ ከዛም ያስወጡሻል። ይሄብቻም በሆነ ባልከፋም ነበር፤ ከዚህ ከማባረራቸው በፊት በሆነ ባልሆነው በሰበብ ባስባቡ ጥፋት እየፈለጉ ይተቹሻል። ያረክሱሻል። ጤንነትሽን፤ ወጣትነትሽንና ነፍስሽን ካለአንዳች አጠፈታ እንዳልሰዋሽላቸው ሁሉ ይልቁንም እንዳወደምሻቸው፤ እንደዘረፍሻቸው፤

ሽክም እንደሆንሽባቸው አድርገው ያጣጥሉሻል። በዚህ ውስጥ ሌሎች ጓደኞቼ አህቶቼ ከጐኔ ይቆማሉ ብለሽ እንዳትጠብቂ፤ እነዚህ ጓደኞችሽ የቀጣሪያቸውን መልካም አስተያየት ለማግኘት ሲሉ ተደርበው ያዋርዱሻል። ምክንያቱም ሁላችሁም፤ ከረጅም ጊዜ በፊት ህሊናችሁንና ርህራሄን የሸጣችሁ ባሮች ናችሁና! እነሱ ራሣቸው በሕይወት እጅግ የዘቀጡ በመሆናቸው ከነሱ መዋረድ በላይ የከፋ ጥንባት፤ ክርፋትና ስድብ የለም። በዚህ የተነሣም እዚህ አለኝ የምትይው ንብረት ቤሳ ቤስቲን ሳይቀር ተመልሰሽ እንደማታገኚው ሆኖ ጣጥለሽ አንድት ሄጂ ትገደጃለሽ። እነዛ ንብረቶችሽ ጤናሽ፤ ውበትሽና ተስፋዎችሽ ነበሩ። መልስሽ አታገኛቸውም። ገና በሃያ ሁለት ዓመትሽ የሰላሣ አምስት ዓመት ሴት ትመስያለሽ። በሽተኛ ካልሆንሽም በጣም እድለኛ መሆን አለብሽ! ለዚህ ለእግዚአብሔር ፀልይ። በአሁኑ ሰዓት የምትኖሪው ኑሮ የሥራ ሣይሆን ደስ የሚል የደስታ ጊዜ አድርገሽ ብትቆጥሪው አይደንቀኝም! ነገር ግን ልነግርሽ የምፈልገው በዚህች ምድር አንዳንቺ ሥራ ከባድ ወይም በጣም ጨቋኝ የሆነ የለም። ኖሮም አያውቅም። እስከ አሁንም በለቅሶ አለመፈንዳትሽ የሚገርም ነው። ከበር አውጥተው ሲጥሉሽ በዳይና ጥፋተኛዋ አንቺ እንደሆንሽ ሁሉ አንገትሽን አጐንብሰሽ ሹልክ ብሎ ከመሄድ ውጭ አንዲት ቃል መተንፈስ 'ንኳ አትደፍሪም። በዚህም የተነሣ ወደሌላ ቡና ቤት ትሸጋገሪያለሽ ከዛም ወደሶስተኛ ቡና ቤት ትዛወሪያለሽ፤ እንደገና ወደሌላ ቦታ እያልሽ መጨረሻሽ መርካቶ ይሆናል። እዛ ያለጥርጥር ይደበድቡሻል። እዛ ያላቸው ወግ ትንሽ ለየት ያለ ነው። እዛ የምታገኝው ደንበኛ በቅድሚያ አንድ ሁለቴ ሣያጋጭሽ በፊት ስለፍቅር መነጋገር አይችልም። ላታምኚ ትችያለሽ ግን እዛ እጅግ አስፈሪ ነው። አንድ ቀን ሄድ ብለሽ ብትመለከችው ጥሩ ነበር።

አንድ ጊዜ የሆነ አዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ አንዲት ልጅ አየሁ እዛ። ጓደኛቿ ሰካሩ እንዲለቃት በሚል እንደቀልድ ከቤቷ አስወጥተው ወደ ውርጩ ጣሏት። በጣም አሪ እያለች እየጮኸች ስላስቸገረቻቸው በሩን ዘግተውታል። ገና በጧቱ ሶስት ሰዓት ሙትት ብላ ሰክራለች። ወጉሩ

ተንጨባሯል። ሐለመናዋ ተዝረገፈርኳል ግማሽ እራቁቷን ሆና ባረፈባት ድብደባ ገላዋ በልሏል። አይኖቿ ጠቁረዋል። ካፍ እና ከአፍንጫዋ ደም ይፈሳል። የቡና ቤቱ ደረጃዎች ላይ ተቀምጣ በእጆቿ የሆነ አሣ ይዛለች። መጥፎ እድሏን እያማረረች፣ ከጣራ በላይ እየጮኸች የያዘችውን አሣ ከደረጃው ጋር ታጋጨዋለች። የሆኑ ታክሲ ሹፌሮችና የሰከሩ ወታደሮች ከበው ይሳለቁባታል። አንችም ያው አንድ ቀን እንዲህ እንደእሷ እንደምትሆኚ ታምኚያለሽ? ለነገሩ እኔም እንዲህ ዓይነት ነገር እንዳስብብሽ አልፈልግም። ግን ይሄ እንደማይሆን እንዴት ልናውቅ እንችላለን? ምናልባት የዛሬ አሥርና ስምንት ዓመታት በፊት—ይህችው ልጅ አሣ የያዘችው ልጅ መጀመሪያ የመጣችው እዚህ አንቺ ያለሽበት ቦታ፣ ቅን ንውህ፣ ከፉት የለሽና እያንዳንዱ ባለጌ ታል የሚያሳፍራት ትኩሰ ወጣት ሆና ይሆናል። ምናልባትም እሷም አንዳንቺ ኩሩ፣ በቀላሉ የምትከፋ፣ ጭምት፣ ንግሥት የመሰለች በእርግጥም ከሷ ጋር በፍቅር የወደቀውን ሰውና የወደደችውን የዚን ዓለምን ደስታ ልትጐናፅፈው የምትችል ነበረች። ግን አይታይሽም ፍፃሜው! ያንን ደረጃ በያዘችው አሣ ትደበደብ በነበረችበት አፍታ እንደዛ ቆሽሻና የተዝረከረከችበት አፍታ፣ አባቷ ቤት ያሳለፈቻቸውን ንውህ የልጅነት ዓመታት ወደ ት/ቤት ስትሄድና ያ መንገድ ላይ የሚጠብቃት የጐረቤታቸው ልጅ በሕይወት እስካለ ድረስ እንደሚያፈቅራት ሲያረጋግጥላት፣ መላ የወደፊት ሕይወቱን ለሷ እንደሚያውለው ታል ሲገባለት፣ እርስ በርስ ተፋቅረው ሲያድጉ እንደሚጋቡ ታል ሲለዋወጡ የነበረው ሁሉ ትዝ ቢላትስ? እ! ሊዛ! ከዚህ ሁሉ አሁኑኑ ብትሞቺ በጣም እድለኛ ትሆኛለሽ። ልክ እንደዛች ሴትዬ የሆነ ጥግ ቦታ ላይ የሆነ ጥንሰስ ቤት ውስጥ በሣንባ በሽታ ብትሞቺ ግልግል ነው።

ሆስፒታልስ ለምን አይሆንም ነው ያልሽው? ሆስፒታል የሚወስድሽ ቢገኝ በጣም እድለኛ ነሽ። ምክንያቱም እንደዛም ሆነሽ ለቀጣሪሽ ታስፈልጊያለሽ ማለት ነውና! የሣንባ በሽታ ለየት ያለ በሽታ ነው። እንደትኩሳት አይነት አይደለም። የሣንባ በሽተኛ እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ በእድናለሁ ተስፋ ነው የሚኖረው። እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ

እሱ ጋር ምንም ችግር እንደሌለ፣ እንዳልታመመ በማመን ራሱን ያታልላል። በዚህ ደግሞ ቀጣሪዎችሽ በጣም ነው የሚደሰቱት። እንዲህ ነው የሚሆነው ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም። ነፍስሽን ሽጠሻል። በዚህም የገንዘብ ዕዳ አለብሽ ስለዚህም አንዲትም ቃል ለመናገር አትደፍሪም። መሞት ስትጀምሪ ግን ሁሉም ይተውሻል። ሁሉም ካንቺ ዞር ይላሉ። ምክንያቱም ከዚያ በኋላ ካንቺ ምን ጥቅም ይጠበቃል? ከዛ በኋላ የሚያደርጉት ቢኖር ሳትከፍይ ለምትይዢው አልጋና ቶሎ ባለመሞትሽ ጭቅጭቅ ይሆናል። የሚጠጣ ውሃ እንዲሰጡሽ ደግመሽ ደጋግመሽ ትለምኚና መጨረሻ ላይ ሲያመጡልሽም አፈር ጠጪ እያሉ ነው። «መቼ ነው የምትሞቺው? ምን ዓይነት ችኮ ነች እባካችሁ? ሙሉ ቀን እያቃሰትሽ እንቅልፍ ነሣሽን ደንበኞቻቸንን ማስተናገድ አቃተን» ይሉሻል። ይሄ እውነት ነው። እንዲህ ሲባል እኔ ራሴ በጆሮዬ ሰምቻለሁ። የእውነት መሞት ስትጀምሪ ወደ አንድ ሽታታ፣ እርጥብና ጨለማ ጥግ ወስደው ያስተኙሻል። በዛን አፍታ ምን ይሰማሽ ይሆን? ስትሞቺም አንቺ የምትባይ ፍጡር ማን እንደሆነሽ የማያውቁ በችኮላ፣ በትዕግሥት ማጣትና በማጉረምገም ይገንዙሻል፣ ማንም አይባርከሽም። ማንም ወየው! አይልልሽም። የሁሉም ትኩረት አንቺን አስወግዶ ሥራ እንዲቀጥል ነው፣ እርካሽ የሬሣ ሣጥን ውሰጥ ከተው እንደትላንቷ ልጅ ወደ ቀብር ቦታ ይወስዱሻል።

ግታ እዚያው ተገናኝተው ስላንቺ ያወራሉ። መቃብርሽ በውሃና በቆሻሻ ይዋጣል ይህንን ሊያስተካክል ማንም ጊዜውን አያጠፋም። «ልጆች! ልቀቋት ወደታች! እግሯ ወደላይ ወጣ እባካችሁ! ምስኪን! ከርታታ!! እባካችሁ እዛ ጋር! ገመዱን አሳጥሩት በጣም ጥሩ ነው አሁን! በጐኗ ነው እኮ ያስተኛናት! አይታያችሁም! እንዴት ነው? ምንም ቢሆንኮ ሰው ነበረች! ተው እንጂ! በታ እንግዲህ ምን ይደረግ፣ አፈር ሙሉት!» ባንቺ የተነሣ እርስ በእርስ በመጣላት ብዙ ጊዜ ማባከንም አይፈልጉም። አላይሽ ላይ እርጥቡን መሬት ቆልለው ወደ ቡና ቤታቸው ይሄዳሉ.... በዚህ ሁኔታ በምድር ላይ ጥለሽው ያለፍሽው ትዝታ ይደመደማል። ሌሎች ሴቶች መካነ መቃበራቸውን በየጊዜው የሚጐበኙ ልጆች፣ ባሎችና አባቶች

አሉዋቸው ላንቺ ግን እንባ የሚራጭ፤ ዋይ የሚልም ሆነ የሚያስታውስሽ አይኖርም። ማንም! ከቶ ማንም! አንቺን አስታውሶ የሚመጣ የለም። ከቶም ያልተፈጠርሽ ያክል ስምሽ ከምድር ገፅ ይጠፋል! ሙታን በሚነሱበት ምሽት የሬሣ ሣጥን መዝጊያውን ባለና በሌለ ሃይልሽ እየመታሽና እየጮህሽ ‹እባካችሁ ሰዎች! እንድኖር ፍቀዱልኝ! ብኖርም እውነተኛ ሕይወትን አላወቅኩም። ዕድሜዬን ያሳለፍኩት ሰዎች ጫማቸውን የሚጠርጉበት የበረንዳ ጆንያ ሆኜ ነው። ሕይወቴን መርካቶ መሃል ቡና ቤት ጠጥተውታል። እባካችሁ! ድጋሚ እንድኖር ፍቀዱልኝ! እጂን ስባችሁ አውጡኝ!› እያልሽ ብትጣሪም ከበላይሽ ቆሻሻና ጭቃ ብቻ ’ንጂ አንቺን ብሎ የሚመጣ ሰው አይኖርም።»

እራሴን በራሴ ወደከፍተኛ የሀዘን ሁኔታ ውስጥ ስለጨመርኩት እንባ ተናነቀኝ። ድንገት ንግግሬን በማቆም በሀዘን መንፈስ ብድግ አልኩና ከፉኛ የሚደውለውን ልቤን በመረበሽ አዳምጥ ጀመር። ለማፈር ጥሩ ምክንያት ነበረኝ። ልቧን በሀዘን እንዳስጨነቅኩት ይሰማኛል። ድል አድራጊነቱ በተሰማኝ ቁጥር የጀመርኩትን የመጨረስ ፍላጐቱ ተጋጋለ። እንዲህ ያደረገኝ ከድርጊቴ ውስጥ የማገኘው መዝናናት ነበር። አዎ መዝናናት! ግን ደግሞ መዝናኛነቱ ብቻ አልነበረም።

አነጋገሬም ደረቅ፤ በሌሎች ላይ ስሜት ለመፍጠርና እንደውም መፀሐፋዊ ባህሪ እንዳለው አውቃለሁ። ነገር ግን መፀሐፍ እንደሚያነብ ዓይነት ካልሆነ መናገር አልችልም። ይሄ ግን አያሳስበኝም። ምክንያቱም ሌሎች እንደሚረዱኝና ይህም መፀሐፋዊ ባህሪዬ ከማደናቀፍ ይልቅ ሊያግዘኝ እንደሚችል አውቃለሁ። አሁን ግን የምፈልገውን ስሜት ማላደር ስለቻልኩ ፈራሁ አይሆንም! በፍፁም! በፍፁም! እንዲህ ዓይነት ተስፋ መቁረጥ አድሮብኝ አያውቅም። እሷ ፊቷን ትራሱ ውስጥ ደብቃ በደረቷ ተኝታለች። እጆቿ ትራሱን ጭምቅ አድርገው ይዘዋል። ደረቷ በአተነፋፈሷ ኃይለኛነት መጠን ብድግ ቁጭ ይላል። ሰውነቷ እንደአቅለሸለሸው ሰው ኩምትር ብሏል። እንዳይፈስ የተቆጣጠረችው እንባዋ ትንፋሽ ነስቷትና

ልቧን እያስጨነቀ ቆይቶ ድንገት መቆጣጠር አቅቷት ለቀቀችው። ወዲያው ኃይለኛ ማቃሰትና ሰቅሰቅ ያለ እንባ አነባች። በዚህን ጊዜ ነው ትራሱን ይበልጥ ጭምቅ አድርጋ የያዘችው እዚህ ቦታ ላይ የቧን ሥቃዮችና እንባዎች ማንም ሰው እንዲያውቅባት አትፈልግም። ትራሱን–ከዛም– እጆቿን እስኪደማ ድረስ ነከሰችው።! ከደማች በኋላ ነው ያወቅኩት።! የተንጨበረረ ፀጉሯን በጣቶቿ እንቅ አድርጋ ያዘቻቸው። ከእንድ ሰው በማይጠበቅ ኃይል ትንፋሿን ዋጥ አድርጋና ጥርሿን ነክሳ ድርቅ አለች። የሆነ ነገር ግለትም እራሿን እንድታረጋጋ ለማድረግ ያህል እንድ ሁለት ያህል ቃላት መናገር ጀምሬ ነገር ግን ልቀጥልበት ባለመድፈሬ ወድያውኑ ወባው እንደተነሣችበት ሰው በመሸበር ስሜት እየተንዘፈዘፍኩ ለባብሼ ከቦታው ለመጥፋት ልብሶቼን መፈለግ ጀመርኩ። ጨልሞ ነበር። ልብሴን ለመለባበስ የተቻለኝን ያህል ብንደፋደፍም ወዲያውኑ መጨረስ አልቻልኩም። ድንገት እጇ አንድ የኩበሪት ቤትና ያልተለኮሰ ሻማ ላይ አረፈ።

«ሊዛ! የኔ ውድ! በጣም አዝናለሁ። ማ– ማድረግ አልነበረኝም –» በማለት እንደጀመርኩ እጇን በእጆቿ ከፉኛ ጭምቅ አድርጋ ስትይዘኝ መናገር የሌለብኝን የተናገርኩ መሆኔ ገባኝና አቆምኩ።

«ሊዛ! ይቅውልሽ አድራሻዬ። ነይና ጠይቂኝ»

«እሺ» አለች በሹክሹክታ ነገር ግን አንገቷን ቀና ለማድረግ አልደፈረችም።

«አ– አሁንም መሄዴ ነው። ይህና ሁኚ! ትመጪለሽ አይደል?»

ተነሣሁ። እሷም ተነሣች። ድንገት ፊቷ ላምባ መሰለና ተንዘፈዘፈች። ፎጣዋን ከወንበሩ አንስታ ትከሻዋ ላይ አስቀመጠችና እስከአገጯ ድረስ ተሸፋፈነችበት። ይህን ካደረገች በኋላ የሀዘን ፈገግታ ፈገግ ብላ እንደማፈር በማለት በሚገርም አኳኋን ወደኔ ተመለከተች። እጅግ በጣም አዘንኩላት። ከቦታው ድራሼን ለማጥፋት ወለሉ ተሰንጥቆ እንዲውጠኝ ተመኘሁ።

«እንዴ ቆይ!» አለች። ድንገት የቤቱ በር ላይ እንደደረስኩ የካፖርቴን ጫፍ ይዛ እያስቆመችኝ።

ወዲያውኑ ሻማውን አጥፍታ ሮጣ ወጣች። የሆነ ነገር አስታውሳለች ወይም ልታሳየኝ የፈለገችው ነገር አለ። እየሮጠች ሣለ ሁለመናዋ በሀፍረት ተሸማቀቀ። አይኖቿ ያበራሉ። ከንፈሮቿ ላይ ፈገግታ እንደ ንጋት ፀሐይ በራ። ምን ማለቷ ነው? ያለፍላጐቴ መጠበቅ ነበረብኝ። በደቂቃ ውስጥ ተመልሳ መጣችና ለሆነ ነገር ይቅርታዬን እንደምትጠይቅ ዓይነት ሆና ተመለከተችኝ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ከነበረው ጨፍጋጋ ተጠራጣሪና እልኸኛ ገፅታ ሙሉ ለሙሉ የተለየ ነበር። አሁን ግን አይኖቿ ለስላሳና ተለማማጭ በዛው መጠን አማኝ ለስላሣና ተሸኮርማሚ ነበሩ። ሕፃናት የሚወዱትንና የሆነ ውለታ እንዲያደርግላቸው የሚፈልጉትን ሰው እንደሚያዩት ዓይነት። አይኖቿ ነጣ ያሉ ቡናማ ቆንጆና ሕይወት የሚንፀባረቅባቸው ሆነው ፍቅርን መግለፅ የሚችሉትን ያህል የዝምታ ጥላቻ ይታይባቸዋል። ያለምንም ማብራሪያ ልክ ምንም ነገርን ያለምንም ገለፃ ልረዳ የሚገባኝ የተለየ ፍጡር የሆንኩ ይመስል አንድ ወረቀት ሰጠችኝ። በዛች አፍታ መላ ገፅታዋ ፈፁም በሆነ ቅንነት ሕይወት ቸፈፍብሎበት መታየት ብቻ ሣይሆን የሕፃን ዓይነት የድል ስሜት ተንፀባርቆበታል። የታጠፈውን ወረቀት ፈታታሁት። ከአንድ የሕክምና ተማሪ የተላከላት በጣም እዩኝ ባይና በቃላት ያሸበረቀ ነገር ግን ደግሞ ፍፁም አክብሮት የተሞላበት የፍቅር መግለጫ ደብዳቤ ነበረ። እያንዳንዱን ቃል ማስታወስ አልችልም። ነገር ግን በነዛ ገናና አገላለጾች ውስጥ በፍፁም ፈዝ ሊሆኑ የማይችሉ እውነተኛ ስሜቶችም አይቼበታለሁ። ደብዳቤውን አንብቤ ስጨርስ እነዛ ኃይለኛ ጉጉና እንደሕፃን ትዕግሥት አልባ የሆኑ ዓይኖች እኔ ላይ ፈጠው አገኘሁዋቸው።

አይኖቿን እንደሙጫ ፊቴ ላይ አጣብቃ የምለውን ለመስማት በጉጉት ትጠባበቀኛለች። በፍጠነት ደስተኛ በሆነ ወኔና በኩራት «በጣም በጣም አሪፍ የሆኑ ምንም ነገር የማያውቁ» ግለሰብ ቤት ከልጅ ጋር መደነስ፤

ቡና ቤት ከገባች ብዙ ጊዜ እንዳልሆናትና ለመቆየትም ሃሣቡ እንደሌላት– እንደውም እዚህ ላለመቆየት መወሰኗንና ያለባትን ዕዳ እንደጨረሰች ከዚህ እንደምትለቅ ገለፀችልኝ....ለማንኛውም እዛ ቤት ምሽቱን ሙሉ አብሯት የደነሰውን ተማሪ አግኝታዋለች። አውርተዋል፣ ሪጋ ውስጥ በልጅነቷ እንደሚያውቃት፣ አብረው እንደተጫወቱ ግን ጊዜው አረጅም እንደሆነም ነግሯታል። የቧንም ወላጆች እንደሚያውቃቸው ስለአሁኑ ሕይወቷ ግን ምንም የሚያውቀው ነገር እንደሌለ በዚህ ጉዳይ ላይ ቅንጣትም ችግር እንደሌለ አስረዳችኝ። ከዳንሱ ዕለት በበነጋታው (ከዛሬ ሶስት ቀን በፊት) ዳንስ ቤቱ አብሯት በሄደችው ጓደኛዋ አማካኝነት ይህንን ደብዳቤ ልኮላታል።

ታሪኳን ነግራኝ ስትጨርስ የሚያንፀባርቁ አይኖቿ በመጠኑ በሀፈረት ስብር አደረገቻቸው። ምስኪን፣ ደብዳቤውን እንደታላቅ ቅርሷ ስለምታየውና እኔም እሷን ከልብና ከእውነት ተፈቅራ እንደነበር ሰዎች በአክብሮት ያነጋግሩት እንደነበር ሳላውቅላት እንድሄድ ስላልፈለገች ነው ሮጣ ሄዳ ያመጣችው። እርግጠኛ ነኝ ያ ደብዳቤ የትም ባያደርሳትም ሣጥኗ ውስጥ ግን እስከሕይወቷ ፍፃሜ በክብር ይቀመጣል። ሕይወቷን ሙሉ ተመን የሌለው ቅርስ አድርጋ ትጠብቀዋለች። የኩራቷና የሷነቷ ማረጋገጫ አድርጋ ትጠብቀዋለች። ለዚህም ነው እንዲህ የኔ ቅኝት ባየለበት ወቅት እሷ ክብር ያላት እንደማንም ሙሉ ሰው መሆኗን ለመበቀል አውጥታ በማሣየት እንዳደነቃት የፈለገችው። ምንም አልተናገርኩም እጆቿን ጨብጬ ወጣሁ። መሄድ፣ መራቅ ፈለግኩ... ትላላቅ በረዶው ሳያቋርጥ መዝነቡን ቢቀጥልም ቀጥ ብዬ ወደቤቴ ሄድኩ። ስደርስ የሞት ያህል ደክሞኝ ደብሮኝና ግራ ገብቶኝ ነበር። በዚህ ግራ መጋባት ውስጥ ግን እውነቱ ይንቀለቀል ነበር። ቀፋፊው እውነት!

እውነቱን አምኜ ከመቀበሌ በፊት ብዙ ጊዜ ፈጅቦኝ። በበነጋታው ከጥቂት ለዓታት በፊት ከከባድ የሚጫጫን እንቅልፍ ከነቃሁና ባለፈው ቀን

የሆነውን ሁሉ ካስታወስኩ በኋላ የዛን ዕለት ምሽት ለሊዛ ባሣየሁት ስሜታዊነት፣ ስቃዬችና ውርደቶች ክራኝ ተገረምኩ።

«ልክ እንደጃጀች አሮጊት ሴት ያለ የነርቭ መታወክ ሣይደርስብኝ አልቀረም» አልኩ ለራሴ «አ! አምላኬ! ምንኛ ጅል ነበርኩ?! ደግሞስ ምን ልሁን ብዬ ነው አድራሻዬን የሰጠሁዋት? ብትመጣስ! ለነገሩ መጣች አልመጣች ምን የተለየ ነገር ይፈጠራል? ከፈለገች ትምጣ! አይጨንቀኝም.....»

ነገር ግን ዋናውና ወሣኙ ነገር ይህ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። ማድረግ ያለብኝ አሁን በፍጥነት በነዚቫርኮቭና ሲሞኖቭ ፊት የጠፋውን ክብሬን ማስመለስ ነው። ዋናው ነገር ይሄ ነው። በዚህ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ በመመሠጤ የተነሣ ሊዛን ሙሉ በሙሉ ረሣሁዋት።

በመጀመሪያ ደረጃ ከሲሞኖቭ የተበደርኩትን ገንዘብ መመለስ ነው። ለዚህም የመጨረሻ አማራጭ መውሰድ ነበረብኝ። ከአንቶን አንቶኖቪች አሥራ አምስት ሩብል መበደር። የዛን ዕለት ጠዋት እንደአጋጣሚ ሆኖ አንቶኖቪች እጅግ ከፍተኛ በሆነ የደስታ ስሜት ውስጥ ስለነበረ ብሩን እንደጠየቅኩት አበደረኝ። እኔም ክራኝ በደስታ በመጥለቅለቄ የተነሣ የብድር ውሉን ከተፈራረምኩ በኋላ በጣም በተዝናና ስሜት «እ! ትላንት ምሽት በሠቴል ዲ–ፓሪስ አንድ ጓደኛችንን እንደውም የልጅነት ጓደኛዩን ማለት እችላለሁ፣ ለመሸኘት ታላቅ ፓርቲ አዘጋጅተን ነበር። ጓደኛዬ በጣም የተቀማጠለና የተሞላቀቀ እምልህ ከጥሩ ቤተሰብ የፈለቀና ጥሩ ደረጃ ላይ ያለ ትልቅ ሥራ ያለው ብልህ ተጫዋችና በወይዛዝርት ዙሪያም በጣም የተወደደ ሰው ነው። በታ ምን ልበልህ በግብጣው ላይ እሱ ግማሽ ደርዘን ጨመረበትና ሁሉም ነገር በጣም ባማረ ሁኔታ ተጠናቋል» አልኩ በጣም በራስ መተማመንና በደስታ መንፈስ።

እቤቴ እንደደረስኩ ለሲሞኖቭ ፃፍኩለት። ለሲሞኖቭ የፃፍኩለትን ደብዳቤ ሳስታውሰው በአገላለጼ ጨዋነት፣ ለዛና ግልፅነት በጣም እገረማለሁ። በጣም በቅልጥፍና፣ ፍፁም በሆነ ገርጋዳነትና ከሁሉም በላይ

ደግሞ ያለምንም የታላት ጥራዝ ነጠቅነት በዕለቱ ሙሉ በሙሉ ጥሩተኛው እኔ እንደነበርኩ አመንኩ። ይቅርታዩም «ለዕለቱ ድርጊቱ ምክንያት ሊቀርብለት የሚችል ከሆነ» ምናልባት ለመጠጥ አዲስ በመሆኔና እነሱ ሳይመጡ በፊት ከአሥራ አንድ እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በሆቴሉ እነሱን ስጠብቅ በነበረበት አፍታ የጠጣሁት አስክሮኝ መሆኑን አብራራሁላቸው።! ውሸቴን ነው! እነሱን ስጠብቅ በንዴት እበግን ነበር እንጂ ጠብታ ውሃ ’ንኳ አልጠጣሁም። በቅድሚያ ይቅርታዩን ያቀረብኩት ለሲሞኖቭ ነው። በሱም በኩል ለሁሉም በተለይም ደግሞ «እንዳስቀየምኩት እንደህልም በሰመመን ለሚታወሰኝ» ዚቪርኮቭ አቀረብኩ። በተጨማሪም እንደፍላጐቴ ቢሆን ለየአንዳንዳቸው በአካል ተገኝቼ ይቅርታ ብጠይቅ ደስታዩ እንደሆነና ነገር ግን በገጠመኝ ከፍተኛ የራስ ምታት ሕመም የተነሣ እንዳልቻልኩ አስረዳሁ። (እውነቱ ግን የነሱን ፊት ለማየት ከፉኛ በማፈሬ ነው።) በጣም የተደሰትኩት በደብዳቤዩ ውስጥ በሚታየው «የሆነ ነገነትና ብዙ አለመጨነቅ።» (እንዲህ ሲል ያለ አክብሮት በግዴለሽነት ማለቴ አይደለም ነበር) ይህን የአፃፃፍ ዘይቤን ትላንት የደረሰውን ሁሉ እንደማንኛውም ተራ ክስተት የምመለከተው መሆኑንና እነሱ እንደሚያስቡት በሚያሳፍር ሁኔታ ያልተዋረድኩብት እንደሆነ እንዳውም ጠቅላላ ድርጊቱ ራሱን የሚያከብር ማንኛውም የተከበረ ሰው ሊያየው እንደሚጠበቅ ዓይነት አድርጌ እንደተረዳሁት የሚያሣይ ነበር። «ወጣት ለሚፈፅማቸው ማናቸውም የወጣትነት ስህተቶች ሊጠየቅ አይችልም» አልኩ።

ደብዳቤዩን ኢንብቤ ስጨርስ አድናቆቴ በረታ። «የተማርኩ ስለሆንኩ ነው! ሌሎች በኔ ቦታ ቢሆኑ ኖሮ እራሣቸውን ከእንዲህ ዓይነቱ ቅሌት እንዴት እንደሚያወጡ አያውቁም ነበር። እኔ ግን ሙሉ በሙሉ ነፃ ወጥቼ እንደምንጊዜውም ብሩህና ደስተኛ ነኝ። ለዚህ ምክንያቱም «የተማርኩ ዘመናዊ ምሁር ስለሆንኩኝ ነው።»

ደግሞም እኩ የዚያ ሁሉ አስቀያሚ ችግር መንስኤ የተገኘጨሁት ወይዓ ይሆናል። ምናልባትም ደግሞ በወይኑ ምክንያት አይደለም። እውነቱን ለመናገር በአሥራ አንድና በአሥራ ሁለት ሰዓት መካከል አንዲት ጠብታም አልቀመስኩም። ለሲሞኖቭ ዋሽቼዋለሁ። በጣም ሀፍረት የለሽ ውሸት ነው የነገርኩት። ቢሆንም አሁንም ድረስ እንዲህ በማድረጌ የሚሰማኝ ፀፀት የለም ምን አስጨነቀኝ? ገሀነም ይግባ! ዋናው ቁም ነገር የኔ ከችግሩ መውጣት ነው። ደብዳቤው ውስጥ ስድስት ሩብል ከትቼ አሸግኩና አፖሉን ለሲሞኖቭ እንዲያደርስልኝ ጠየቅኩት። አፖሎም ደበዳቤው ውስጥ ገንዘብ መኖሩን ሲረዳ ደብዳቤውን ለማድረስ በጣም ፈቃደኛ ሆነ። ወደ ምሽት ገደማ ለሽርሽር ወጣሁ። እራሴን ከትላንት የጀመረ ያመኛል ምሽቱ እየገፋና ጭለማው እየጠነከረ ሲመጣ የኔም ስሜትና ሃሣቤ እየተለዋወጠና እየተመሰቃቀለ ሄደ። በውስጤም በጥልቀት ልቤና ህሊናዬ ውስጥ የሆነ ነገር ይላወሳል የሆነ አልሞት ያለ ስሜት አእምሮዬን በማሰቃየት በሚፈጥረው ድብርት የሆነ ነገር አልወጣልኝ ብሎኛል። ብዙ ጊዜ ሰው በሚበዛባቸው አውራ ጐዳናዎች ያለአንዳች ዓላማ እኳትናለሁ። በአብዛኛው የማዘወትራቸው ጐዳናዎች ሚሽ ቻኖስካያ፣ ሳዶቫያና ቸሱፖሽ መናፈሻዎች ናቸው። በነዚህ ጐዳናዎች ሽርሽር ማድረግ ደስ የሚለኝ ሠራተኞችና ነጋዴዎች የቀን ሥራቸውን ጨርሰው የተጨነቀ ፊታቸውን እያሣዩ ወደቤታቸው በሚመለሱበት ፀሐይ መግቢያ አካባቢ ነው። ለኔ ደስታ የሚሰጠኝ የየሁልጊዜው የሰው ትርምስ ነው። በዚህ ምሽት ግን ይሄ ሁሉ ጥድፊያና ግፊያ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አበሳጨኝ። ስሜቴን መቆጣጠር አልቻልኩም። ማብራሪያም ላገኝለት አልቻልኩም የሆነ ነገር ውስጤ እየተንቀሳቀሰ ነበር። ጭራሽ ፀጥ የማይል ነፍሴ ውስጥ እየተገላበጠ የሚያመኝ የሆነ ስሜት ይገላበጥብኛል። ወደቤቴ ስመለስ ከፉኛ ቀፎኝ ነበር። የሚሰማኝ ስሜት ወንጀል የፈፀምኩ ያህል ነበር። ሊዛ ልትመጣ ትችላለች የሚለው ሃሣብ ፋታ ሣይሰጥ ያስጨንቀኛል። የሊዛ ጉዳይ ትላንት ከማስታውሣቸው ነገሮች ሁሉ በተለይ በጣም የሚያሰቃይ ትውስታ ይሆንብኛል። የሷ ትውስታ ከሌሎች ተነጥሎ በጣም ይለማኛል። ከሷ

በስተቀር ሌሎቹ ትውስታዎች በሙሉ የዛን ዕለት ምሽት ሙሉ በሙሉ ላስወግዳቸው ችዬ ነበር። ሁሉንም በቀላሉ ተገላግዬ ለሲሞኖቭ ለነፍኩት ደበዳቤ ሙሉ የሆነ እርካታ ይሰማኛል። ደስታዬን የነሣኝ የሷ ጉዳይ የሆነ ይመስል ሊዛን በተመለከተ ዕፎይ ልል አልቻልኩም። «ብትመጣስ?» እያልኩ አስባለሁ። «ይሁና! ታዲያ ብትመጣስ? ትምጣ! እ.... እንዴት እንደምኖር እንድታውቅብኝ ግን አልፈልግም። ትናንት ምሽት ለሷ ጀግና ነበርኩ አሁን – ግ – ን እም...!» ቤቴ ውስጥ ያለው ነገር በሙሉ አዳሩና ያረጀ ነው። ምን ብደፍር ነው በነዚህ ልብሶች ትናንት ለዕራት ግብግ የሄድኩት? ያ ስፖንጁ ቡርድስ ብሎ የወጣ ሶፋዬ! ያ ሙሉ ለሙሉ ሰውነቴን የማያዳርስ የቤት ልብስ ቡቱቶና ድሪቶ... ሁሉንም ማየቷ አይቀርም። አፖሎን ጭምር ታየዋለች። ይሄ አላማ ምናልባትም ሊሰድባት ይችላል።

እኔን ለማብሸቅ ሲል ያበሽቃታል። እኔም እንደ ልምዴ የሚገርሙ አመለካከቶች ከመግለፅ፣ ዙሪያ ሰውነቴን የማይሸፍነውን ጋውን ከመልበስ፣ ፈገግ ከማለትና ውሸት ከመናገር አልቆጠብም። አይ! እንዴት ይቀፋል! እውነተኛዋ አቅለሽላሽ ጉደይ ይሄ አይደለም። ሌላ በጣም አስፈላጊ በጣም አስፈሪና ፀያፍ ነገር አለ! አዎ፣ በጣም አፀያፊ ይሸውም ያንኑ የተለመደውን የውሸት መሸፈኛ ጭምብል መልበስ፣ እንደገና ጭምብል!»

አስካሁን በታሰበኝ በንዴት ጮኩ።

«ለምንድ ነው ሐቅ የማይሆነው? በምን መልኩ ነው ሐቀኛ ያልሆነው? ትናንት ምሽት የተናገርኩት በሙሉ በቅንነትና ከእውነቴ ነው።

በውስጤ የሆነ ዕውነተኛ ስሜት እንደነበረኝም አስታውሣለሁ። በውስጧ የክብር ስሜት ለመቀስቀስ ነበር ያደርኩት... ብታለቅስም እንኳ ጉዳይ የለውም። ዕፎይታ ነው የሚሰጣት.....

እቤት ከተመለስኩና ከምሽቱ 3 ሰዓት በኋላ እንኳ የሊዛ መምጣት ጉዳይ ከጭንቅላቴ ሊወጣ አልቻለም። ከሁሉም በላይ ደግሞ ትገ የምትለኝ

በማይለዋወጥ አንድ ሁኔታ ላይ እንዳለሁኝ ብቻ ነው። ከትናንት ምሽቱ ሁኔታ መካከል አንዷ ከስተት ብቻ ከሁሉ ተነጥላ በአእምሮዬ ጓዳ ተቀርፃለች። እሱም ሻማውን እንደለኩስኩት ያየሁት የገረጣ፣ የተኮማተረ ፊትና በዓይኖቿ ውስጥ ያየሁት ስቃይ ነበር።

በዛች አፍታ አሳዛኝና እንግዳ የሆነ የተጠመዘዘ ፈገግታ ነበር ያሳየችው ሊዛን እንዲህ እንዳለች ከ15 ዓመታት በኋላም ጥርት ባለሁኔታ አስታውሳለሁ ብዬ ከቶም አላስብኩም ነበር።

በበነጋታው ይሄን ሁሉ በምስቅልቅል የተወጠሩ ነርቮች ከሁሉም በላይ ደግሞ የማጋነን ውጤት ነው ብዬ ከጭንቅላቴ ላስወጣው ዝግጅ ሆንኩኝ። ማጋነን አልፎ አልፎ የሚያስፈራኝ ድክመቴ ነው «የኔ ችግር ሁልጊዜ አጋንናለሁ!» በማለት በየሰዓቱ ራሴን አስታውሰው ነበር። ይሁን እንጂ «ሊዛ ዞሮ ዞሮ መምጣቷ አይቀርም!» የሚለው ደግሞ ሐሣቤን የሚገታ ቋሚ ማስታወሻ ሆነብኝ።

በዚህም በጣም ከመጨነቄ የተነሣ አንዳንድ ጊዜ ከመሬት ተነስቼ በንዴት እዛድ እሆናለሁ። «ትመጣለች! ያለጥርጥር ትመጣለች!» እያልኩ በንዴት ክፍሌ ውስጥ ከግድግዳ እስከ ግድግዳ እመላለሳለሁ። «አዎ! ዛሬ ባትመጣ ነገ፣ ነገ ባትመጣ ከነገ ወዲያ፣ ብቻ መምጣቷ አይቀርም! ፈልጋ ተገኝኛለች። ምክንያቱም እነዚህ ሮማንቲክ የሆኑ ንፁህን ልቦች እንደዚያ ናቸውና! አቤት! የእነዚህ ስሜታዊ ነፍሶች ቀፋፊነት፣ ደደብነትና ለሰው ያለማሰብ ረኽተነት፣ ለእሷ እንዴትሊገባት ይችላል? ማንም ሌላ ሰው ግን ሊገነዘበው በቻለ ነበር!»

እንዲህ ሲሆን በሐፍረት እጥለቀለቅና አቆዝማለሁ፤ የሚገርም ነው። የአንድን ሰው ሙሉ ሕይወት እኔ በፈለግኩት መሠረት ለመቅረፅ ትንሽ የሆነች በእግረ መንገድ ጣል የምትደርግ አስተያየትና ጣፋጭ ገለፃ በቂ ነው ጃል?! እነዛ– የለበጣ መፅሐፍዊ– ከልብ ያልሆኑ! አያችሁ የዋህነትን! ድንግል መሬት!

አንዳንድ ጊዜ በቀጥታ ያለችበት ድረስ ሄጀ «ሁሉንም ነገር ነግሬ» ወደ እኔ እንዳትመጣ ማድረግ የለብኝምን? ብዬ አስባለሁ ወዲያው በገዛ ሐሳቤ በንዴት እጦፍና በዛ ሰዓት ሊዛን ባገኛት ቦጫጭቂ እንዳምጥላት ብልጭ ይልብኛል። አዋርዳታለሁ። ቅስም የሚሰብሩ ስድቦችን አወርድባትና እየደበደብኩ አውጥቼ እጥላታለሁ።

ለማንኛውም ምንም ሳይፈጠር አንድ ቀን አለፈ። ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ቀን መጣ። እሷ አልመጣችም አእምሮዬ እርይ ማለት ጀመረ። በጣም ደስተኛነት እየተሰማኝ በተለይ ከምሽቱ 3 ሰዓት ሲያልፍ ራሴን በራሴ በምርቃና ሕልም ውስጥ እንዲደሰት ፈቀድኩለት።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቀንም አልማለሁ። ለምሳሌ ከማልማቸው ውስጥ «ሊዛ እኔጋ ባለማቋረጥ በመምጣቷና በማውራቷ የተነሣ ከእስከፊ ሕይወት እያዳንኳት ነው። እያስተማርኩና አስተሳሰቧን እያሰፋሁትነው። በመጨረሻም በእኔ ላይ ፍቅር እንዳደረባት የምገነዘብ ይመስለኛል። ሆን ብዬ እንዳላወቀ እሆናለሁ! ግን ለምን እንደማስመስል አይገባኝም። ምናልባት ለራሱ ለማስመሰሉ ስል መሆን አለበት። በመጨረሻ በሐፍረት ተጥለቅልቃ እየተንቀጠቀጠችና እየተንዘፈዘፈች እግሬ ሥር ትደፋና ከጉድ ስላወጣሽኝ በዓለም ላይ እንዳንተ የማፈቅረው የለም! ትለኛለች። እኔ ደግሞ ግራ የተጋባሁ እመስልና «ሊዛ» እላለሁ። «ሊዛ መቼም እንዳፈቀርሽኝ አስካሁን ድረስ ያላወኩ እንዳይመስልሽ? ሁሉንም ነገር ተረድቼዋለሁ። ገምቻለሁ።

ነገር ግን አንቺ ሙሉ በሙሉ በነሱ ሥር ስለሆንሽ ቀድሚ ሐሣቤን ባቀርብልሽ ከውለታ መክበድ የተነሣ እሺ እንድትይ የማሰገደድ ያህል ይሆናል ብዬ በማሰብ ሐሣቡ ራሱ ካንቺ እንዲመጣ ፈልጌ ነው። አየሽ ሐሣቡን እኔ ባነሣው ኖሮ ምናልባት በሐሳብሽ ውስጥ ከቶም ያልነበረውን እንደነበር አድርገሽ ልትመልሺ ስለምትችይና እኔም እሱን ባደርግ የአምባገንንነት ድርጊት ስለሚሆንብኝ ነው።

አሁን ግን ሁሉ ነገር ካንቺ ስለመጣ የኔነሽ፣ የኔ ፍጥረት ነሽ፣ ንፁህና ቆንጆ ነሽ፣ አንቺ የኔ ሚስት ነሽ! እነሆ ወደቤቴ ሳትፈሪና ሳትቸሪ እመቤቴ ሆይ ዝለቂ!

ከዚህ በኋላ በደስታ መኖር እንጀምራለን። ውጪ ሁሉ ለጎብኝነት እንሄዳለን። ወዘተ... በአጭሩ በራሴ የቀቢፀ ተስፋ ትብትብ ውስጥ ተሳስሬ ሕልሜን ራሴ በራሴ ላይ ምላሴን በማውጣት እደመድማለሁ።

ደግሞም እነዛ እባቦች እንድትመጣ አይፈቀዱላትም እንጂ! እላለሁ ለራሴ። ሥራ ትተው ወጣ ወጣ እንዲሉ ብዙም የሚፈቅዱላቸው አይመስለኝም። በተለይም በምሽት አይለቋቸውም (በሆነ በማላውቀው ምክንያት ልትመጣ የምትችለው ማታና እሱም ልክ ከምሽቱ 1 ሰዓት ላይ እንደሚሆን አስባለሁ) ይሁን እንጂ እሷ ራሷ እንደነገረችኝ ኑሮዋ ሙሉ ለሙሉ የራሷ እንደሆነና እንደፈለገች የመሆን መብት አላት። ይሄ ማለት ደግሞ ኤዲያ! ትመጣለች ማለት ነው። በእርግጠኝነት ትመጣለች!

በአጋጣሚ አፖሎን በአብሻቂ ተፈጥሮው የተነሣ ለጥቂት ሰዓታትም ቢሆን ከሊዛ ሐሣብ ገላገለኝ። ትዕግሥቴን ሙሉ በሙሉ አስጨርሶኛል! እግዚአብሔር እንድቀጣበት የላከብኝ ሥቃይ እሱ ነው ዓመታት ሙሉ እንዲሁ እንደተበሻሸቅን አለን። ጠልቼዋለሁ። አቤት አምላኬ! እንዴት ፃው የጠላሁት! በተለይ አንዳንድ ጊዜያት ላይ በምድር እንደሱ የጠላሁት ነገር አይገኝም። በትርፍ ጊዜው ልብስ የሚሰፋ ጉረኛ ሽማግሌ ነው። በሆነ ባልታወቀ ምክንያት ከልክ በላይ ይንቀኛል። ለኔ ያለው ንቀት ዕብድ ያደርጋል። ለነገሩ ሁሉንም ሰው ነው የሚንቀው። ያን በለስላላው የተበጠረ ጭንቅላቱን፣ በቅባት አርሶ ግምባሩ ላይ የሚያስተኛውን ቁንጮውን በሸ ቅርፅ ጨምቆ የሚከድነውን አይን ለተመለከተ ሰውዬው በራሱ ጥርጥር የሌለው መሆኑን ይረዳል። ያለቅጥ አውቃለሁ ባይ ወግ አጥባቂ ከመሆኑ የተነሣ የታላቁን አሌክሳንደር ያህል ኩራት የተጫነው ነው። ኮቱ ላይ በተሰፋ እያንዳንዱ ቁልፍና ራስ- ቅሉ ላይ ባሉ እያንዳንዱ ፀጉር በፍቅር የሰከረ ነው። አዎ ከነሱ ጋር ጭልጥ ባለ ፍቅር ተውጧል።

ለእኔ ያለው አመለካከት የገር ነው ጨርሶም አያነጋግረኝም ማለት ይቻላል። ቁምነገር ኖሮት ሊያነጋግረኝ ግድ የሆነበት ጊዜ ደግሞ አስተያየቱ ሻካራ፣ ግርማዊና በራስ መተማመን ሞልቶ የፈሰሰበት ከመሆኑ የተነሣ ዕብድ ሊያደርገኝ ምንም አየቀረውም። የተቀጠረበትን ሥራ ሲሰራልኝ ልክ ታላቅ ውለታ እንደሚውልልኝ ዐይነት ይቆነናል። ለነገሩ ለኔ ይሠራልኛል የምለውም የለኝ፣ እሱም እኔን የሚገልገል ግዴታ ያለበት አድርጉ አያስብም። በሱ እምነት ምድራችን እንደኔ ያለ ሞኝ ሊኖራት እንደማይችልና አብሬው እንድኖር የሚታገሰው ደሞዙን በየወሩ የሚያገኘው ከኔ ስለሆነ ብቻ ነው። ለኔ በወር ሰባት ሩብልስ ሒሣብ ምንም ባይሠራልኝ ዴንታው አይደለም እርግጠኛ ነኝ። ከሱ ከሚደርስብኝ ሥቃይ የተነሣ ማንኛውም ሀጢያቱ ይሰረይልኛል። አንዳንዴማ በጣም ምርር ብዬ ከመናደዴ የተነሣ ክፍሉ ውስጥ ሲዘዋወር ሰሰማ እንደቀውስ ያደርገኛል። ምላሱ ረዥም ወይም እንደዛ ያለ መሆን አለበት። ምክንያቱም በተናገረ ቁጥር ከንፈሩን እየላሰ ታላት ያኝካል። እኔ እንደሚመስለኝ እንዲህ በማድረጉ ከብሩን የጨመረ ስለሚመስለው በጣም ይኮራበታል። ሲናገር እጆቹን ወደኋላ አድርጉና ዓይናቹን መሬት ላይ ተክሉ በዝግታና በተለካ ድምፅ ነው። በተለይ በተለይማ ከኔ ክፍል ከሚለየው መጋረጀ ጀርባ ሆኖ መዝሙር ዳዊቱን ማንበብ ሲጀምር ቁጣዮ ከቁጥጥር ውጭ ይሆናል። በዛ ንባቡ የተነሣ ብዙ ጊዜ ጦርነት ገጥሜዋለሁ። ምሽት ምሽት ጮክ ብሎ ማንበብ በጣም ይወዳል። አነባበቡ ደግሞ ለሙታን የሚደግምላቸው ይመስል በዝግታ አልፎ ተርፎ እንደ መዝሙር ባለ ድምፅ ነው። በአሁኑ ሰዓትም እያነበበ መሆኑ የሚገረም ነው። ለሙታን ዳዊት መድገም፣ አይጦችን ማጥፋትና የጫማ ቀለም ማምረት ትርፍ ሥራዎቹ ናቸው። ከእኔ ጋር የሆነ የኪሚካል ውህድ ስለፈጠረ ላባርረው አልችልም። እሱም በምንም ተአምር ለቆኝ ሊሄድ አይፈቅድም። እኔ በተሟሉ ቤቶች ውስጥ ልኖር አልችልም። የኖርኩት ባልተሟሉ ባዶ ቤቶች ውስጥ ነው። ይሄ ደግሞ እኔ ከሰው የምደበቅበት ዋሻዬ ነው። በአንድ የጋራ የሆነ ምክንያት አፖሎም

ከኔ ሕንፃ የማይገነጠል አካል በመሆኑ የተነሣ ባለፉት ሰባት ዓመታት ውስጥ ላባርረው አልቻልኩም።

ለሁለትና ለሶስት ቀን ንኳ ደሞዙን ማዘግየት ብሎ ነገር ጨርሶ የማይታሰብ ነው። ገንዘቡ ሲዘገይበት የሚፈጥረው ሁኔታ የምገባበትን ያሳጣኛል። አሁን ግን እኔ ራሴ በግልፅ በማልረዳው ምክንያት በሁሉም ሰው ላይ ጥላቻ ስላደረብኝ የአፖሎን ገንዘብ አሥራ አምስት ቀን ሙሉ በማዘግየት ልቀጣው ወስኛለሁ። እንዲህ ለማድረግ ማሰብ የጀመርኩት ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት ነበር። ዓላማዬም እሱ እኔን እንዲህ እንደትንኝ ሊንቀኝ እንደማይችልና ከፈለኩ ደሞዙን ልከለክለው እንደምችል ለማሳየት ነው። ኩራቱን እንክትክቱን ለማውጣትና እሱ ራሱ ደሞዜን ብሎ እንዲጠይቅ ለማስገደድ ስለገንዘቡ ጉዳይ ምንም ነገር ላለመናገር ወሰንኩ። ከዚያ በኋላ ገንዘቡን ከጠረጴዛ መሳቢያ ውስጥ አውጥቼ አሳየውና ገንዘቡን የያዝኩበት ሆን ብዬ መሆኑን በመግለፅ «ደሞዝህን አልሰጥም ያለምንም ምክንያት እከለክልሃለሁ። አልሰጥም! ይህን የማደርገው ደስ ስላለኝ ነው። «ምክንያቱም እኔ የቤቱ ባለቤት በመሆኔ፤ እሱ ደግሞ ተገቢውን ክብር ስላላሳየ፤ ባለጌ ስለሆነ፤ ነገር ግን በትህትና ከጠየቀኝ ሀሳቤን ቀይሬ ልሰጠው እንደምችል፤ አለበለዛ ግን አሥራ አምስት ቀን ወይም ሶስት ሣምንታቶች ወይም አንድ ወር መጠበቅ እንደሚኖርበት...

ምንም ያህል ልቆጣ 'ንጂ መጨረሻ ላይ ግን የሚያሸንፈው እሱ ነው። ደሞዙን አራት ቀን 'ንኳ ላዘገይበት አልቻልኩም። ሁልጊዜ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት (እንዲህ ለማድረግ ስምክር የመጀመሪያዩ አይደለም፤ ከዚህ በፊትም አድርጌዋለሁ። እንዲህ ሳደርግም የሚጠቀምባቸውን ቀፋፊ ታክቲኮችም አውቃቸዋለሁ።) የሚያደርገውን ጀመረ። ለአያሌ ደቂቃዎች ፍጥጥ ብሎ ማየት ጀመረ። በተለይ ይሄን የሚያደርገው ፊት ለፊት ስንገናኝ ወይም እኔ ከቤት ስወጣ ነው። ወደኋላዩ ሳልሸማቀቅና ጨርሶ እንዳላስተዋልኩ ከሆንኩበት ደግሞ አሁንም እንዴት ቃል ሣይናገር በርካታ ስቃዮችን ይፈጥርብኛል። እኔ እያነበብኩ ወይም

እንደተለመደው ከፍሌ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ስመላለስ ያለአንዳች ምክንያትና ይቅርታ በድንገት ዘው ይልና አንድ እጁን ወደኋላ አድርጉና አንድ እግሩን ወደ ውስጥ አስገብቶ ፍጥጥ ብሎ ያየኛል። በዚህን ጊዜ ደግሞ ፍጥጫው ቁጣ ብቻ ሣይሆን የሚያንቋሽሽ ንቀትም ይታይበታለ። ድንገት ምን ትፈልጋለህ ብዬ የጠየቅኩት እንደሆነ አይመልስልኝም። ለጥቂት ሰኮንዶች አይኑን ሳይሰብር ያፈጥና ልዩ በሆነ አመለካከት ከንፈሩን መጠ ቀስ ብሎ ወደኋላው ይዞርና በጣም በእርጋታ ወደ ከፍሉ ይመለሳል። ይህ በሆነ ከሁለት ሰዓት በኋላ እንደበፊቱ ሆኖ ይመጣል። አንዳንድ ጊዜ በንዴት የማያደርገውን ባለማወቅ ምን እንደሚፈልግ ሣልጠይቀው ተንጠራርቼ በእልህ እኔም መልሼ አፈጥበታለሁ። በዚህ ሁኔታ ለሁለት ደቂቃ ያህል እርስ በርስ ተፋጠን እንቆይና መጪረሻ ላይ እንደተለመደው በዝግታና በመንቀባረር ዞሮ ወደ ገዛ ክፍሉ ሄዶ ለሁለት ሰዓታት ያህል ይቆያል።

ይህ ዘዴው የኔን አመፅ አስቁሞ ገንዘቡን ካልሰጠሁት ድንገት ሊያየኝ ቁና ቁና እየተነፈሰ ማፍጠጥ ይጀምራል። በዚህ ማቃሰቱ የሚያሣየኝ የኔ የሞራል መላሸቅ እምን ደረጃ እንደደረሰ ሊያሣየኝ ነው፤ ይህ ዘዴውም ሁልጊዜ ድል ያጐናፅፈዋል። አብዳለሁ፤ እጮሀለሁ ግን እሱ የፈለገውን ያደርጋል። አሁን ይህ የቁጣ ዕይታው ገና እንደጀመረ ወዲያውኑ ትዕግሥቴ ተሟጦ በቁጣ የእውር ድንብሬን ተጠጋሁት። «ቁም! ብዬ ጮህኩበት። አንድ እጅን ወደኋላ እንዳደረገ በቀስታ ወደ ከፍሉ ሊሄድ ሲል ደርሼበት «ቁም! ተመለስ ብዬሃለሁ! ልነግርህ የምፈልገው አለ። ተመለስ!»

የጮህኩበት ከዚህ በፊት በማያውቀው ኃይለኛ ድምፅ ይምስለኛል ወደ ኋላ ዞሮ በመገረም ተመለከተኝ። ይህ ሁሉ ሲሆን አሁንም አንድም ቃል ባለመናገሩ አበድኩ።

«ከፍሌ እንዴት ላታንኳኳ ልትገባና እንዲህ ልታፈጥብኝ ደፈርክ? በልተናገር!»

ለግማሽ ደቂቃ ያህል በእርጋታ ካየኝ በኋላ ወደ ከፍሉ ለመሄድ መዘር ጀመረ።

ተንደርድሬ ወደሱ በመሄድ «ቁም!» በማለት አምባረቅኩበት። «ንቅንቅ ለማለት እንዳትቃጣ! ብትቆም ይሻልሃል! ምን ለመፈለግ ነው ወደኔ የመጣኸው? መልስልኝ»

«እንድሠራልዎ የሚፈልጉት ነገር ካለ ጌታዬ ያንን ማድረግ ሥራዬ ነው» አለ እንደለመደው ከመናገሩ ፊት ትንሽ ዘግየት ብሎ። በተለመደ አዝጋሚና የተለካ ከንፈር መጠጣውን ሳያቋርጥ ቅንድቦቹን ወደላይ አንስቶ አንዴ ወደግራ አንዴ ወደቀኝ እያደረገ።

«ይሄን አይደለም የጠየቅኩህ አንተ ከፉ» በማለት በንዴት እየተንቀጠቀጥኩ ጮህኩበት «ለምን ወደኔ እንደመጣህ ራሴ እነግርሀለሁ አንተ ከፉ። አየህ! ደሞዝህን ይገርብሃለሁ። ያለቅጥ ኩሩ በመሆንህ የተነሣ ገንዘብህን ልትጠይቅ ስለማትችል ሆነ ብለህ እኔን ለመቅጣት፡ ለማሰቃየት ከፍሌ እየመጣህ ታፈጥብኛለሁ። ድርጊትህ ሁሉ ጅላጅል ቂላቂል መሆኑን ባየህ!»

እንደገና በፀጥታ ዙሮ ለመሄድ ሲሞክር ሲል ያዝኩት።

«ተመልከት!» በማለት ጮህኩበት። «ገንዘብህ ይሽውልህ! ይታይሃል?! ከጠረጴዛው ውስጥ አወጣሁት። ሰባት ሩብሎቹን አሳየሁት! አታገኛቸውም በሥነ ሥርዓት መጥተህ ስህተቶችህን አምነህ ይቅርታ እስካልጠየከ ድረስ አ–ታ–ገ–ኛ–ቸ–ው–ም። ሰማህ!»

«ይሄማ ጨርሶ አይሆንም!» አለ። እንግዳ በሆነ የራስ መተማመን።

«ይሆናል!» ሰል ጮህኩበት።«የክብር ቃሌን እሰጥሀለሁ፡ ይሆናል!»

«ይቅርታ የምጠይቅበት ምንም ምክንያት የለኝም» አለ በመቅጠል ጩኸቶቹን ከቁብ ሣይቆጥራቸው። «ምክንያቱም እርስዎ ጌታዬ «አሰቃይ» ብለውኛል። ለዚህ ደግሞ ፖሊስ ጣቢያ ክስ መመሥረት እችላለሁ።»

«ሂድና አንካሳ ዶሮ ሣይቀድምህ አመልክት!» አጓራሁ። «ሄድ! አሁኑኑ! በዚህች ደቂቃ! በዚህች ሰኮንድ። አንተ አሰቃይ! አሰቃይ! አሰቃይ!» አልኩት።

አየት አደረገኝና ቁጣዉን እንዲቆም ንኳ ሳይጠብቅ ወደጓዋላው ዞሮ በተለመደ የተለካ እርምጃው ወደ ከፍሉ ሄደ።

ይሄ ግን ሊዛ ላይ አይደርስም! አልኩ ለራሴ ለአንድ ደቂቃ ያህል ከቆምኩ በኋላ ወደሱ ከፍል ሄጀ በእርጋታና በጨዋነት ያለምንም ችኩላ (ምንም ’ንኳ ልቤ በጣም ቢመታም) «አፖሎ! ሂድና የፖሊስ መርማሪ ይዘህ ና! አሁኑኑ!» አልኩት በእርጋታ።

እሱ ግን ጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ መነፅሩን አድርጉ ልብስ መቀምቀሙን ጀምሯል። ትዕዛዜን ሊሰማ በረጅሙ ተነፈሰ።

«ሂድ አሁኑኑ! በዚህች ደቂቃ! ሂድ ብዬሃለሁ! ወይም ካሁን ወዲያ ለሚሆነው ነገር ተጠያቂ አይደለሁም!»

«ጌታዬ! አብደዋል መሰለኝ!» አለ በተለመደ አዝጋሚ ከንፈር መጠጣና ቃላት ማኘክ አነጋገሩ ራሱን ከጠረጴዛው ቀና ሳያደርግ በመርፌው ውስጥ ክር እያስገባ። «ማነው በራሱ ላይ ሄዶ ለፖሊስ የሚያመለክት? ነገር ግን ጌታዬ ሊያስፈራሩኝ ፈልገው ከሆነ ብዙም አይጨነቁ ምክንያቱም አንድም የሚፈጠር ነገር አይኖርምና!»

«ሂድ ብዬሃለሁ!» በማለት ትከሻውን ያዝኩት። የሆነ ደቂቃ ላይ እንደምመታው ይሰማኝ ነበር።

በሩ በፀጥታ በእርጋታ ተከፍቶ አንድ ሰው ገብቶ ሁለታችንንም ቆሞ ሲመለከት አልተሰማኝም ነበር። ቀና ስል ከሀፍረቴ የተነሣ ራሴን ስቼ ልወድቅ ምንም አልቀረኝ። ሮጬ ወደ ከፍሌ ሄድኩ። ከፍሌ እንደደረስኩ ፀጉሬን በእጆቼ ይገርና ግርግዳውን ተደግፌ ቆሜ ቀረሁ።

ከሁለት ደቂቃዎች ብኋላ የአፖሎን ቀርፋፋ እርምጃዎች ሰማሁ።

«የሆነች ወጣት ልጅ ትፈልግዎታለች ጌታዬ!» አለ ከፉኛ እየተመለከተኝ።

ሊካ አንድትገባ መንገዱን ለቀቀላት። ለመሄድ የፈለገ አይመስልም። ሁለታችንንም ቆሞ በለበጣ ይመለከተናል።

«ሂድ! ሂድ!» ስል አዘዝኩት የምይዝ የምጨብጠው ጠፍቶኝ።

ልክ በዚች አፍታ የግርግዳ ሰዓቴ በከፍተኛ ማቃሰት አንድ ሰዓት አለች።

እነሆ ወደቤቴ ሳትፈሪና ሳትቸሪ

እመቤቴ ሆይ ዝለቂ!

ሙሉ በሙሉ አልቆልኝ ተዋርጀና ከፉኛ አፍሬ ፊት ለፊቷ ቆምኩ። እራሴን በተቀደደው አሮጌ ገዋኔ ለመጠቅለል እየሞከርኩ ፈገግ ያልኩ ይመስለኛል። ልክ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በተደበረው መንፈሴ ይሆናል ብዬ ገምቼው እንደ ነበረው ማለት ነው። አፖሎም ጥቂት የቂቃዎች ከተመለከተኝ በኋላ ጥሎን ሄደ። እንዲህ ማድረጉ ያቀለለው ነገር ግን አልነበረም። ከሁሉም በላይ ነገሩን ያባባሰው የሷ ድንገት ግራ መጋባት ነበር። እንዲህ ትሆናለች ብዬ ጨርሶ አላሰብኩም።

ወደጠረጴዛው መቀመጫ እየሳብኩላተ «ተቀመጭ» አልኳት። እኔ ሶፋው ላይ ተቀመጥኩ። ያለቅጥ በተበለጠጡ ዓይኖቿ እያየችኝና ከኔ የሆነ ነገር እንደምትጠብቅ በግልፅ በሚያሣይ ሁኔታ በትዛዜ መሠረት ወዲያው ቁጭ አለች። ይበልጥ ውስጤን ያነሣሣው ይህ ሁኔታዋ ነበር። ይሁን እንጂ ራሴን ተቆጣጠርኩ።

ጭንቅላት ቢኖራት ኖሮ አይታ እንዳላየች ትሆን ነበር። እሷ ግን....

ለዚህ ድርጊቷ ዋጋዋን እንደምከፍላት በድብስብሱ ተሰማኝ። «ትንሽ በሚገርም ሁኔታ ላይ እንዳለሁ ያገኘሽኝ መሰለኝ ሊዛ!» በማለት ጀመርኩ። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ መጀመር እንዳልነበረብኝ በሚገባ ይረዳኛል። ድንገት ማፈሯን አይቼ «በፍፁም ችግር አለ ብለሽ እንዳታስቢ! በድህነቱ አላፍርም። እንደውም በኩራት ነው የምመለከተው። ደሀ ከመሆኔ በስተቀር

ክብር ያለኝ ሰው ነኝ። ሰው ደግሞ ደሀም ሆኖ ክብር ያለው ሊሆን ይችላል።» በማለት ተንገታገትኩ።«ለማንኛውም ሻይ ይፈላልሻ?»

«አይ! አመሰግናለሁ » አለች።

«አንድ ደቂቃ ጠብቂኝ»

ዘልዬ ተነስቼ ወደአፖሎ ሮጥኩ። በሆነ ሰበብ ከሷ ዕይታ መራቅ ስለነበረብኝ ነው።

«አፖሎ!» አልኩት በማንሾካሾክ ድምፅ፤ በዛውም እስካሁን ድረስ የቆየሁበትን ሰባት ሩብል ጠረጴዛው ላይ እያስቀመጥኩለት።

«ደሞዝህ ይኸውልህ! አየህ ስለጥህ ለዚህ ውለታ ግን አሁን እንድታድነኝ እፈልጋለሁ። ሱቅ ሂድና አንድ ጀበና ሙሉ ሻይና በርካታ ብስኩቶች ይዘህልኝ ና! የማትሄድ ከሆነ ግን በዓለም ላይ ደስታ አልባው ሰው ታደርገኛለህ! እንዴት ያለች ጥሩ ሴት እንደሆነች አታውቅም! ልዩ ሴት ነች! በመካከላችን የሆነ ነገር ያለ ሊመስልህ ይችላል። ግን እንዴት ያለች ንፁህ ሴት መሰለችህ!»

አፖሎ መነፅሩን እንዳደረገ ሥራውን ሳያቆም በመጀመሪያ ገንዘቡን በዝምታ ተመለከተው። ከዚያ በኋላ ለኔ ምንም መልስ ባለመመለስ መስፋቱን ቀጠለ። እጆቼን አጣምሬ ፊት ለፊት ለሶስት ደቂቃዎች ያክል ተገተርኩ። ማጅራቴ በላብ ተነከሮ አቅም ሊያንሰኝ ተሰማኝ። ይሁን ንጂ እግዜር ምሥጋና ይግባውና በዚያ ሁኔታ ሊያየኝ ሃዘን ስለተሰማው መሆን አለበት ከመቀመጫው ቀስ ብሎ ተነሣ። ቀስ ብሎ ወንበሩን ወደኋላ ገፋው። ቀስ ብሎ መነፅሩን አወለቀ። በቀስታ ብሩን ቆጠረ። በመጨረሻም በመንቀባረር ማምጣት ያለበት አንድ ጀበና ሻይ መሆን አለመሆኑን ከጠየቀኝ በኋላ በቀስታ ከክፍሉ ወጥቶ ሄደ። ከዚህ ፍጻ በኋላ ወደ ሊዛ እየተመለስኩ እንዳለ ቡትቶ ገዋኔን እንደለበስኩ የትም ይሁን የት ሳልጨነቅ ብርር ብዬ ጠፍቼ ሁሉም ነገር የራሱ ጉዳይ የሚል ሃሣብ መጣብኝ።

ከፍል ገብቼ ተቀመጥኩ። በሞንቀት ተመለከተችኝ። ለጥቂት ደቂቃዎች ሁለታችንም ሳንነጋገር ቆየን።

«አገለዋለሁ!» በማለት በጠርሙስ ውስጥ ያለው የብዕር ቀለም እስኪደፋ ድረስ ጠረጴዛውን በኃይል በቡጢ በመምታት ድንገት ተናገርኩኝ።

«ወይኔ አምላኪ! ምን እያልክ ነው?» አለች ግራ ተጋብታ።

«አገለዋለሁ! አገለዋለሁ!» አልኩ በንዴት ጠረጴዛውን በቡጢ እየመታሁ። ግን ደግሞ እንዲህ እስክሆን መናደዴ ምን ያህል አሳፋሪ እንደነበር ይሰማኛል።

«ሊዛ! ምን ዓይነት ተንኰለኛ ሰው እንደሆነ ልነግርሽ አልችልም። እርኩስ ነው! አሁን ጥቂት ብስኩቶች ሊገዛ ሄዷል። እሱ—»

ድንገት እንባዬ ፈሰሰ። መንሰቅሰቅ ጀመርኩ። በለቅሶዬ መካከል ከፉኛ ሀፍረት ቢሰማኝም ለማቆም ግን አልቻልኩም።

ፈራች። ግራ በመጋባት ከበላዬ ቆማ «ምንድነው ነገሩ? ምንድ ነው ነገሩ?» እያለች ባለማቋረጥ ትጠይቃለች።

«ውሃ!...ትንሽ ውሃ ስጭኝ እባክሽ ውሃ እዛ ጋር አለልሽ!» በማለት በደከመ ድምፅ አጕረመረምኩ። ግን ደግሞ ይህን ላደርግ ውሃም ሆነ በደካማ ድምፅ ማቃሰት አስፈላጊ እንዳልነበር ውስጤን ይሰማው ነበር። ምንም 'ንኳ ስቃዩ የውነት ቢሆንም አጠቃላይ አኳሆኔ ግን ለራሴ ሰበብ ለማግኘት ድራማ የመሥራት ያህል ነበር።

ውሃውን ሰጥታኝ ፍፁም በሆነ ግራ መጋባት ዝም ብላ ታየኝ ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳል አፖሎ ሻዬን ይዞ ገባ። ይዞት የመጣው ሻይ ተራና ጣዕም የለሽ ስለነበር አፈርኩ። ሊዛ አፖሎን በድንጋጤ ተውጣ አየችው። እሱ ግን አንዳችንንም መልከት ሳያደርግ ወጥቶ ሄደ።

ስለኔ ምን እንደምታስብ ለማወቅ አተኩራ እየተመለከትኳትና እየተጣደፍኩ «ሊዛ! ትንቂኛለሽ?» አልኳት።

ግራ በመግባት ተውጣ ስለነበረ ምንም ልትመልስልኝ አልቻለችም።

«ሻይሽን ጠጪ!» አልኩ በንዴት። በራሴ ብናደድም መከራውን መቀበል ያለባት ግን እሷ ነች። በእሷ ላይ ከፍተኛ የሆነ የጥላቻ ስሜት በልቤ ውስጥ ተቀሰቀሰ። በዛ ሁኔታዬ የምገላት ይመስለኝ ነበር። ልበቀላት ስላሰብኩ ከክፍሌ እስክትወጣ ድረስ አንድ ቃል ላላናግራት ማልኩ። የሁሉም ነገር ጦስ እሷ ነች በማለት አሰብኩ።

ዝምታችን ለአምስት ደቂቃ ገደማ ያክል ቀጠለ። ሻዩ ጠረጴዛው ላይ ቢቀመጥም ንክችም አላደረገችውም። ሁኔታዋን የበለጠ አሳፋሪ ለማድረግ ሆነ ብዬ ሻዩን ከመንካት ተቆጠብኩ። በሚያሳዝን ግራ መጋባት ጥቂት ጊዜያት ቀና እያለች ተመለከተችኝ። እኔም በእልህ አስጨራሽ ዝምታዬ ገፋሁ። ከደደብነት የመነጨውን የጥላቻ ስሜቴና በቃላት የማይገለፅ ወራዳነቴ ቢገሰኝም ራሴን ለመቆጣጠር ግን አልቻልኩም። ምክንያቱም ዋንኛው ተሰቃይ እኔ ነበርኩ።

«እ–እ– እኔ ከዛ ቦታ ለአንዲና ለመጨረሻ ጊዜ ለመላቀቅ እፈልጋለሁ» በማለት ዝምታውን ለመስበር ተናገረች። በዛች አፍታ ከቶም ልታደርገውና በተለይም እንደኔ ባለ ደደብ ሰው ፊት ልትናገረው የማይገባ እምነቷን አስታወቀች። ለአነጋገሯ ገልጿጽነትና አላስፈላጊ ግልፅነት በልቤ የሀዘን ንክሻ ተሰማኝ። ነገር ግን ውስጤ ያለው የሆነ አፀያፊ ስሜት ለሷ ያለኝን ሃዘን አደበዘዘው። እንዳውም የበለጠ እንድጠላት ገፋፉኝ። በዚህ ሁኔታ አምስት ደቂቃዎች አለፉ።

«መቼም በማያስፈልግ ሰዓት እንደመጣሁ እርግጠኛ ነኝ አይደለም ንዴ?» ስትል በሹክሹክታ ድምፅ አንገቷን ደፍታ በመናገር ልትሄድ ብድግ አለች።

እኔም ይህንን የተጉዳ ክብር የመጀመሪያ ምልክት እንዳየሁ በጥላቻ ተቀጣጥዬ መዓት አወረድኩባት።

«ለምን መጣሽ እዚህ? መልሺልኝ! መልሺ!» አልኩ ትንፋሽ አጥሮኝ እያለከለኩና ለቃላት ሥርዓት ሳልጨነቅ። ስሜቴን ሁሉ በቁጣ ለማውጣት ስለፈለግኩ በምን እንደጀመርኩ ሊያስጨንቀኝ አልቻለም። «የኔ እመቤት! እዚህ ለምን እንደመጣሽ ራሴ ልነግርሽ እችላለሁ። ባለፈው ምሽት አላዛኝ ንግግር ስላደረግኩልሽ ነው። ይህን በማድረጌም መንፈስሽ ስለተረጋጋ ድጋሚ ኧንድሰብክሽ ፈልገሽ ነው። እና እውነቱን ልንገርሽና ትላንት ያን ሁሉ ስሰብክሽ በፈዝ እየሣቅኩብሽ ነበር። አውንም እየሳቅኩብሽ ነበር! ወዳንቺ ከመምጣቴ በፊት የጓደኞቼ የራት ግብዣ ላይ ተዋርጀ ነበር። ወዳንቺ ያመጣኝ ዋናው ምክንያትም ከነሱ መካከል አንዱን ወታደራዊ መኩንን ለመደብደብ ነበር።

«ይሁን 'ንጂ ዘግይቼ ስለነበር እነሱ ከሄዱ በኋላ ደረስኩ ስለዚህም የተዋረደ ክብሬን በሆነ ሰው ላይ ለመበቀልና ራሴን መልሼ ለማግኘት ስል ጥላቻዬን በአንቺ ላይ በማድረግ ተሣለቅኩብሽ። ተዋርጀ ስለነበር እኔም ሌላ ሰው ለማዋረድ ፈለግኩ። እነሱ እግራቸውን እንደጠረጉብኝ ሁሉ እኔም ኃይሌን ለማሣየት ፈለግኩ። ያንዕለት ምሽት የሆነው ባጭሩ ይሄ ነው። አንቺ ግን ወዳንቺ የመጣሁት በተለይ አንቺን ለማዳን ስል እንደሆነ አድርገሽ አስበሽ አይደል? ሃሣብሽ እንዳዛ ነው አይደለም 'ንዴ? ነው፤ አይደለም?»

አጠቃላይ ንግግሬ ግራ እንደሚያጋባትና መያዣ መጨበጫ እንደሚጠፋት ባውቅም ማዕከላዊ መልእክቱን ልትገነዘብ እንደምትችል ደግሞ አውቃለሁ። አልተሳሳትኩም። እንደወረቀት ነጭ ሆነች። የሆነ ነገር ለመናገር ሞከራ ከንፈሮቿ በሕመም ስሜት እጥፍ አሉ። አንዲት ቃል ለማውጣት ከመቻሏ በፊት በመጥረቢያ የቆረጧት ያህል ወንበሩ ላይ ተዝለፈለፈች። ከዚህ በኋላ ያዳመጠችኝ ከንፈሮቿ እንደተከፈቱና አይኖቿ እንዳፈጠጡ በከፍተኛ ፍርሀት እየተንቀጠቀጠች ነበር። የቃላቶቼ አሽሙርና ንቀት ሞራሏን እንከት አደረገው....

ከወንበሬ ዘልዬ በመነሣትና ፊት ለፊቷ ላይና ታች በመንጐራደድ «እንዳድንሽ ነበር የፈለግሽው!» በማለት ጀመርኩ። «ከምንድነው የማድንሽ? ምናልባትም እኔ ካንቺ የባሰኩኝ ነኝ። ለምንድነው ያን ሁሉ ሰበካ ሳነበንብልሽ ያልተቃወምሽኝ? ለምንስ ወደእኔ መጣሽ? አሁንም ስለሞራል ሰበካ እንዲደረግልሽ? አየሽ እኔ የፈለግኩት ኃይል ነው። የኔ ፍላጐት ኃይል ነው። መዝናናት ፈለግኩ ስለታለቅሽ ማየት አሰኘኝ። ላዋርድሽ ፈለግኩ። ተሸብረሽ ማየት አሰኘኝ። የፈለግኩት እኔ ይህንን ነው። አንቺን ማሰቃየቴን ልቀጥልበት ያልቻልኩት ራሴም ጥራጊ በመሆኔ ነው። ፍርሀት ተጠናወተኝ የት እንደምኖር ለምን እንደነገርኩሽ የማውቀው ነገር የለም። ሲፈጥረኝ ጅል ስለሆንኩ መሆን አለበት የት እንደምኖር እንድነግርሽ ያደረገኝ። የዛኑ ዕለት ምሽት ገና ቤቴ ሳልደርስ ጀምሮ ምን ሲባል አድራሻዬን እንደሰጠሁሽ በማሰብ እርግማንና የስድብ መዓት አወርድብሽ ነበር። በነገርኩሽ ውሸቶች ምክንያት ጠላሁሽ። እኔ ፈልጌ የነበረው ትንሽ እንደ ሕልምና እንደተስፋ የምትይዣት ጥሩ ንግግር ነበር። ግን ከልቤ አፈልግ የነበረው ምን እንደሆነ ልንገርሽ! ሁላችሁም ገሀነም እንድትገቡ ነው! የኔ ፍላጐት ይሄ ነው። በማንኛውም መንገድ የምፈልገው የአእምሮ ሰላም ነው። የአእምሮ ሰላሜን ለማግኘት ማንም ሊያስጨንቀኝ እንደማይችል ስል ብቻ ዓለምን በአንድ ሣንቲም መሸጥ ቢኖርብኝ ግድ አይሰጠኝም። ዓለም ትፈራርስ ወይስ እኔ አንድ ኩባያ ሻዬን ላግኝ? ደህና! በኔ በኩል እኔ ሻዬን እስካገኘሁድረስ ዓለም ልትፈነዳ ትችላለች። ይህን ታውቂያለሽ ወይስ አታውቂም? ለማንኛውም እኔ ከብረቢስ፣ ወራዳ፣ ራስ ወዳድና ሥራ ፈት ዘዋሪ መሆኔን አውቃለሁ። እዚህች ጐሬዬ ውስጥ ገና ለገና ትመጪብኝ ይሆናል ብዬ ላለፉት ሶስት ቀናት ስንዘፈዘፍ ቆይቻለሁ። በነዚህ ሶስት ቀናት ውስጥ በተለይ ያስጨንቀኝ የነበረው ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? እነግርሻለሁ! በዛ ሰበካዬ እራሴን ታላቅ ጀግና አድርጌ ከሰበኩ በኋላ እዚህ መጥተሽ ይህን ያረጀና የተቀዳደደ የቤት ልብሴን ታይቢኛለሽ ብዬ ነው። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በድህነቴ ቅንጣት ታክል እንደማላፍር ነግሬሽ ነበር። ውሸቴን ነው። እንደድህነቴ የሚያሳፍረኝ ነገር

የለም። ድህኑቴን ሌባ ከመሆን በላይ እፈራዋለሁ። አንዳንድ ጊዜ ቆዳዬ ተገፎ የተንጠለጠልኩ ያህል አየሩ ሞምር ያመኛል።

እና አሁን በእዚህ በተቀዳደደ አሮጌ የቤት ልብሴ ውስጥ ሆኜና የአፖሎን ጉሮሮ ለማነቅ እንደ መንገድ ላይ ውሻ በመከለፍለፍ ላይ ባለሁበት ሰዓት በመምጣትሽ የተነሣ እስከመቼም ድረስ ይቅር እንደማልልሽ ታውቂያለሽ? አየሽ! ይህ ያንቺ አዳኝ፣ ይህ ያንቺ የበፊት ጀግና እንደ አንድ ኮስኳሳና ልከስከስ ውሻ አሽከሩን ለመንከስ ዘሎ ሲሄድና አሽከሩም እያየው ሲስቅበት ደረሰሽ! ከአንድ ደቂቃ በፊት ሃፍረት እንደተከናነበች ቂላቂል አሮጊት ሴት እንባዬን ሳዝረከርክ ቆመሽ ለተመለከትሽኝ እስከ ዓለም ፍፃሜ ይቅር አልልሽም። አሁን በምናዘዝልሽ ነገር ሁሉ በአንቺ የተነሣ ነውና መቼም ቢሆን ይቅርታ የለኝም። አዎ! ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዋ አንቺ ነሽ! ምክንያቱም የመጣሽብኝ እኔ እዚህ ግባ የማልባል በጣም አፀያፊ በጣም አስቂኝ፣ በጣም ደደብ ከመሆኔ የተነሣ ከኔ ትንሽም በማይሻሉ ነገር ግን ምክንያቱን በማላውቀው ሁኔታ እድሜዬን በሙሉ በትናንሽ ቅማሎች ሁሉ ሰዋረድ እነሱ ግን ቅንጣት ታክል በማያፍሩ የምድር ላይ ትሎች በሙሉ በምቀናበት ሰዓት ስለመጣሽ ነው። የማወራው ገባሽ አልገባሽ ለኔ ደንታዬ አይደለም። ደግሞስ ስላንቺ እኔን ምን ያገባኛል። ያንቺ እዛ ቤት ወላልቀሽ ቀረሽ አልቀረሽ ለኔ ምንድነው? ይገባሻል፣ ይህን ሁሉ እንድነግርሽ ስላስገደድሽኝ፣ የምለውን ሁሉ እዚህ መጥተሽ ስለሰማሽኝ ጥላቻዬ በእጥፍ እንደሚያይል! አየሽ! ሰው የልቡንና የጭንቅላቱን እንዲህ የሚናገረው በሕይወቱ አንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሲገባ ነው። ከዚህ በላይ ምን ትፈልጊያለሽ? ይሄን ሁሉ እየነገርኩሽ ለምን ቆመሽ ሥቃዬን ታበዢዋለሽ? ከዚህ ቦታ አትጠፊም?»

አንድ ያልጠበቅኩት ነገር ሆነ።

አዘውትሬ ሁሉንም ነገር የማስበው መፅሐፎች ውስጥ እንደማነበውና ሁሉንም ነገሮች በህሊናዬ የምስለው ከዚህ ቀደም በሕልሞቼ እንዳየሁት አድርጌ ስለነበር ይህ አሁን የሆነውን ነገር ትርጉም በመጀመሪያ ልገነዘበው

አልቻልኩም ነበር። የሆነው እንደዚህ ነው በኔ የተዋረደችው እና የተደቆሰችው ሊዛ ሁሉንም ነገር እኔ ከማስበው በላይ ተገንዝባለች። ከዚህ ሁሉ ከተናገርኩት ውስጥ እሷ የተገነዘበችው፤ በቅንነት የሚያፈቅሩ ሴቶች ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት ሁሉ፤ ደስተኛ ሰው አለመሆኔን ነው። ፊቷ ላይ የነበረው የፍርሐትና የጥላቻ ስሜት በአሳዛኝ መገረም ተተካ። እራሴን ወራዳና ክብረቢስ እያደረግኩ ስለድብና እንባዬ ሲፈስ መላ ፊቷ በሀዘን ስሜት ተናወጠ።

መጀመሪያ ተነስታ ንግግሬን ልታቆም አስባ ነበር። ለሷ ትኩረት የሰጠችው ለምን እዚህ እንደተገናኘን ለምን ከፊቴ እንማትጠፉ በዛች ስለተናገርኩት ሣይሆን ይህን ሁሉ ለማለት የወሰድኩትን ሥቃይ ነው። በዛ ላይ በጣም በሀዘን ተሰብራለች። ምስኪን! ራሷን ከኔ በታች አድርጋ ገምታለች። ለምንድነው ንዴት ወይም መዋረድ የሚሰማት? ልትቆጣጠረው ባልቻለችው ስሜት አስገዳጅነት ከወንበሩ ተፈናጥራ ተነስታ በዓይኗ አፋርነት ስሜቷና ከቦታዋ ለመነቃነቅ ባለመድፈር የተነሣ ወደኔ ጋደል ብላ እጆቿን ዘረጋችልኝ።

....በዚህን ጊዜ ልቤ ተሰበረ። እየሮጠች መጥታ አንገቴን በጆቿ አቅፋ መንሰቅሰቅ ጀመረች። እኔም ራሴን መግታት አቅቶኝ በሕይቴ አድርጌው በማላውቀው ሁኔታ መንሰቅሰቅ ጀመርኩ።

«አ–አይ...ፈቀዱልኝም። ጥሩ ሰው እንድሆን...ጥ... ጥሩ ሰው መሆን አልችልም።» ይሄንን እንደምንም ተናገሬ ሶፋው ላይ በፊቴ ወደቅኩ። በዚህ ሁኔታ ለሩብ ሰዓት እየተንዘፈዘፍኩ አለቀስኩ። እሷም እኔን እንቅ አድርጋ አንገቴ ላይ ተጠምጥማ እንደ በረዶ የቀዘቀዝን ያክል ተቃቅፈን ቆየን።

ችግሩ ይህ ስሜቴ ዘላለማዊ ባለመሆኑ ማቆም ነበረበት። ስለዚህም (አሁን አፀያፊው እውነት ነው የምነግራችሁ) ሶፋው ላይ ተጋድሜ እንቅ አድርጌ ይዤው ፊቴ በርካሹ ሶፋ ውስጥ ተቀብሮ ቀስ በቀስ እንደሰመመን አድርጌ ይገፋው ፊቴ በርካሹ ሶፋ ውስጥ ተቀብሮ ቀስ በቀስ እንደሰመመን አንገቴን ቀና ባደርግና ሊዛን ብመለከታት እጅግ አሳፋሪ አህያ እንደምመስል

ይሰማኝ ጀመር። ምንድነው ያስፈራኝ? አላውቅም። የማውቀው ማፈሬን ነው በተጨማሪ እንዲህ ተደቋቁሼ ባለሁበት ሰዓት ቦታ መለዋወጣችን ተገለፀልኝ። እሷ እንደጀግና እኔ ደግሞ ልክ የዛሬ አራት ቀን በፊት እሷ ሞራሷ ተሰብሮና ተዋርዶ እንደነበረችበት ሁኔታ ሆኛለሁ። ይህ ሁሉ ነገር ሶፋው ላይ እንደተደፋሁ በአእምሮዬ ጓዳ ተመላለሰ።

ወይ አምላኪ! በሷም እቀና ነበር ማለት ነው?

አላውቅም። አሁንም ድረስ በሷም እቀና ወይ አልቀና እንደነበር በእርግጠኛነት መናገር አልችልም። ሙሉ በሙሉ በኔ ቁጥጥር ሥር የሆነ ሰው እንዳለ ሳይሰማኝ መኖር አልችልም። እንደልቤ የምገዛው ሰው በሥሬ መኖር አለበት። ግን ሁሉንም ነገር በምክንያታዊነት ማስረዳት ስለማይቻል በዚህም የተነሣ ምክንያታዊነት ጥቅም የለውም።

ወዲያውም ከተሸጉጥኩበት ሶፋ ራሴን ቀና አደረግኩ። ዞሮ ዞሮ አይቀርልኝም ነበርና!.... እስከ ዛሬም ድረስ በዛ ሁኔታ እሷን ቀና ብዬ ባያት በሀፈረት እንደምጥለቀለቅ በግሰቤ የተነሣ ድንገት ሌላ የመግዛትና የመቆጣጠር ስሜት በልቤ ውስጥ ተጭሮ ተቀጣጠለ። አይናቼ በስሜት ቀሉና እጆቿን አጥብቄ ያዝኳቸው። እንዴት እንደጠላሁዋትና እንዴት እንደተጠጋሁዋት በዛች አፍታ ለመግለፅ ያስቸግራል! አንደኛው ስሜት ሌላኛውን ስሜት አባባሰው። እንደብቀላ ያለ ነገር ነው....በመጀመሪያ ግራ በመጋባት እንዳውም በመፍራት ተመለከተችኝ ላፍታ ያህል፤ ወዲያው ግን በፍቅርና በስሜት እቅፍ አደረገችኝ።

ከሩብ ሰዓት በኋላ በሰይጣን ፈረስ ከፍሉ ውስጥ ከታች ወደላይ እንጉራደድ ነበር። በእያንዳንዱ ደቂቃ ወደመጋረጃው ሄጀ በጠባቡ ከፍተት ውስጥ ሊዛን እመለከታለሁ። ጭንቅላቷን የአልጋው ጫፍ ላይ አስደግፋ ወለሉ ላይ ተረከዞቿ ላይ ተቀምጣ ታለቅሳለች። እኔ እንዳዘገከኩት ግን አልሄደችም። ይሄም አበሳጨኝ። አሁን ሁሉም ነገር ገብቷታል። በመጨረሻ ሰድቢያታለሁ። እሱን መዘርዘር አያስፈልግም። የአሁኑ የስሜት ፍንዳታዬ ከበቀልና በእሷ ላይ የተቃጣ ሌላ ስድብ ከመሆን ውጭ ሌላ ምንም ነገር

ሊሆን እንደማይችል ገምታለች። ከበፊቱ አላማ የለሽ ጥላቻ አንፃር ያሁኑ ግን ግላዊና ቅናት የተሞላበት ጥላቻዬ መሆኑን አውቃለች።...ይሁን 'ንጂ ነገሮችን በዚህ መንገድ በግልፅ ስለመረዳቷ እርገጠኛ መሆን አልችልም በርግጠኛነት የተረዳችው ነገር ግን እኔ እጅግ አፀያፊና ከሁሉም ነገር በላይ ደግሞ ላፈቅራት እንደማልችል ነው።

ይህን በማለቴ ድርጊቴ ሁሉ የማይታመን እንደኔ በጥላቻ የተሞላና ደደብ መሆን እንደማይቻል ልትናገሩ ትችላላችሁ። እንዳውም እሷን ላለማፍቀር ወይም ፍቅሬን ላለመቀበል እንደምችል መናገሬ በናንተ በኩል የማይመስል ነገር ነው። ግን ለምንድ ነው የማይመስለው? በመጀመሪያ ደረጃ ማንንም ላፈቅር የምችልበት ሁኔታ የለም። ምክንያቱም እደግመዋለሁ ለኔ ፍቅር ማለት መግዛትና በሞራል የበላይ መሆን ነው። በሕይወቴ ፍቅርን ከዚህ ውጭ አስቤው አላውቅም። አሁንማ ፍቅር ማለት የምትወዳት ሴት በራሷ ነፃ ፈቃድ እንድትገዛትና እንድትቆጣጠራት መብት ሰትሰጥ ነው የሚል ደረጃ ላይ ደርሻለሁ። በሚስጥር ህልሜ ውስጥ ፍቅርን በጥላቻ ተጀምሮ በሞራል አሸናፊነት ከሚደመደም ትግል ውጭ አስቤው አላውቅም። ልጅቷን ሙሉ በሙሉ ከስሬ ካደረግኩ በኋላ ለምን እንደምፈልጋትና ምንስ ላደርጋት እንደምችል ቅንጣት ታክል የማውቀው ነገር የለም። በእርግጥ የማይመስል ነገር ቢኖር እንዲህ ዓይነት የሞራል ውድቀት ላይ ሲደርስና ከገሀዱ ዓለም ጋር ያለኝ ልዩነት ሲሰፋ አሁን ከጥቂት ሰዓታት በፊት ወደኔ የመጣችው ያንን «አላዛኝ ሰበብ» ለመስማት እንደሆነ አድርጌ ነበር ያሰብኩት። ነገር ግን የሷ አመጣጥ እነዛን ሰበካዎች ለመስማት ሣይሆን ሴት ልጅ እውነተኛ ትንሣኤ የምታገኘው ከማንኛውም አደጋ የእውነት የምትድነውና ሞራሏ የሚታደሰው በፍቅር ብቻ ስለሆነ የመጣችው ልታፈቅረኝ መሆኑን አልገመትኩም ነበር። እዚህ ላይ ነው የማይመስል ነገር ሊባል የሚችለው። በከፍሌ ውስጥ እየተንጐራደድኩ በመጋረጃ ቀደዳው ውስጥ ሣያት በነበረበት ሰዓት እንኳ ያን ያክል አልጠላሁዋትም ነበር። እዛ መገኘቷን ብቻ ነው ልቋቋመው ያልቻልኩት። እንድትሄድ ፈለግኩ። «ሰላም» ናፈቀኝ። ጐሬዬ ውስጥ ብቻዬን መሆን

ፈለግኩ። «ከእውነተኛ ሕይወት» ጋር ያልተላመድኩ ከመሆኔ የተነሣ መተንፈስ አቃተኝ።

ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ። ሕሊናዋን የሳተች ይመስል እሷ ግን አሁንም አልተነሣችም። ሁለታችንን የለየንን ግድግዳ በማንኳኳት እንድትሄድ አስታወስኳት.... ደንገጥ አለችና ዋንኛው ፍላጐቷ ከኔ አካባቢ ድራሿን ማጥፋት እንደሆነ ሁሉ በፍጥነት ብድግ ብላ መሃረቧን፣ ኮፍያዋንና ፀጉራማ ኮቷንሰበሰበች። ከሁለት ደቂቃ በኋላ ከጓዳው ወጥታ ከፉኛ አትኩራ ተመለከተችኝ። በከፉት ፈገግ አልኩ። እውነቱን ለመናገር ፈገግታዬ ጨዋ ለመምሰል ስል በግድ ያደረግኩት ነው። ወዲያው ከፊቷ ገለል አልኩኝ።

«ደህና ሁን።» አለች ወደበሩ እየሄደች።

ድንገት ወደሷ ሮጬ እጇን ያዝ አድርጌ ከፊትኩና ውስጡ አንድ ነገር አሰቀምጬ መልሼ ጭብጥ አደረግኩ። ወዲያው ፊቴን አዙሬ ቢያንስ እንዳላያት ስል ወደክፈሉ ሌላ ጥግ በፍጥነት ሮጬ ሄድኩ።

በዚህች ደቂቃ ውሸት ልናገር ነበር። እጇን ከፍቼ የሆነ ነገር ጨምሬ መልሼ የጨበጥኩት ሆነ ብዬ ሣይሆን በተፈጠረው ድርጊት በአጠቃላይ ህሊናዬን ስቼ ስለነበር የማደርገውን ሳላውቅ ያደረግኩት ነው ብዬ የውሸቴን ልፅፍ ነበር። ነገር ግን መዋሸት አልፈልግም እና ግልፁን ለመነጋገር እጇን ከፍቼ ውስጡ የሆነ ነገር ያስቀመጥኩት ከጥላቻዬ የተነሣ ነው። ሃሣቡ የመጣልኝ እሷ ጓዳ ውስጥ ሆና እኔ ሣሎን ስንጐራደድ በነበረበት ወቅት ነው። ይሄንን በሙሉ እውነተኛነት ልናገር እችላለሁ። ያንን አረመኔያዊ ድርጊት የፈፀምኩት ሆን ብዬ ነው። ያደረግኩት በልቤ ፈቃድ ሣይሆን በተረገመ ጭንቅላቴ ትዕዛዝ ነው። ይህ የኔ ጭካኔ ቅንነት የሌለው፣ በጣም የታሰበበት ሆነ ተብሎ የተፈጠረ ከመፅሐፍ የተወሰደ ስለነበረ ለእንዲት ደቂቃ 'ንኳ ልታገሰው አልቻልኩም መጀመሪያ ምንም ነገር ላለማየት ስል ወደጥግ እሮጥኩ። ወዲያውኑ በሃፍረትና ተስፋ በመቁረጥ በመጥለቅለጥ ሊዛ ላይ ለመድረስ ወጣሁ። በሩን ከፍቼ ማዳመጥ ጀመርኩ።

«ሊዛ! ሊዛ!» እያልኩ ደረጃዎቹን እየወረድኩ ተጣራሁ።

ምንም መልስ አልነበረም። ነገር ግን ታች ደረጃዎቹን ስትወርድ ኮቴዋን የሰማሁ መሰለኝ።

«ሊዛ!» በከፍተኛ ድምፅ ተጣራሁ።

መልስ የለም። ልክ በዛች አፍታ የአፓርትመንቱ ከመስታወት የተሠራ የምድር በር በከፍተኛ ድምፅ ሲከፈትና ሲዘጋ ሰማሁ። የመዝጊያው ድምፅ በደረጃዎቹ ሁሉ አስተጋባ።

ሄዳለች። ወደከፍሌ ከፉኛ በተሰበረ ስሜት ተመለስኩ።

ተቀምጣበት ከነበረውና በሀዘን ታየኝ ከነበረበት ወንበር አጠገብ ያለው ጠረጴዛ ጋር ስደርስ ቆምኩ። አንድ ደቂቃ አለፈ። ድንገት በረገጣኩ። ፊት ለፊቴ ጠረጴዛው ላይ የተጨባበጠ ባለአምስት ሩብል ኖት ተቀምጧል። ከአንድ ደቂቃ በፊት እጇን ከፍቼ መዳፏ ላይ ያስቀመጥኩት የራሴ ብር ነበር። ራሱ ነው! ቤት ውስጥ ከሱ ሌላ አምስት ብር ስላልነበረኝ ሌላ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ እኔ ወደከፍኩ ሌላ ጥግ ተጣድፌ በመሄድ ላይ እያለሁ እሷ ጠረጴዛው ላይ ለማስቀመጥ ጊዜ አግኝታ ነበር ማለት ነው።

ይሄ የጠበቅኩት ሊሆን ይችላል። ጠብቄው ሊሆን ይችላል? አያችሁ አለቅጥ እራስ ወዳድ በመሆኔ መጠበቅ ብቻ ሣይሆን በትክክል ጠረጴዛው ላይ ወርውራልኝ ልትሄድ እንደምትችል ለማሰብ የሚያስችል 'ንኳ ለሌሎች ክብር የለኝም። ልቋቋመው የማልችለው ሆነብኝ። ወዲያው ያገኘሁትን ልብስ ደራረብኩና ተከትዩ ልደርስባት በሩን በርግጀ ወጣሁ። ደረጀዎቹን ጨርሼ መንገዱን ሳቆለቁል እሷ ቢበዛ ከመቶ ሜትር በላይ ልትሄድ አትችልም ነበር።

ጭደናው ፀጥ ረጭ ብሏል። በረዶው በከፍተኛ ደረጃ ይዘንባል። የሚዘንበው በረዶ በመንገዱ መሃልና በመንገዱ ዳሮች ላይ ተከምሯል። አንድምፍጡር አይታይም። አንድም ድምፅ አይሰማም። የመንገዱ

መብራቶች በአሳዛኝ ሁኔታ ጥቅም አልባ ደብዛዛ ብርሃናቸውን ይረጫሉ። እስከመንገዱ ማቋረጫ ድረስ ለመቶ ሜትር ያህልሮጥኩና ቆምኩ።

የት ሄዳ ነው። ለምንድነው የምከተላት? ለምን? እግሮቿ ሥር ተንበርክኬ በፀፀት ላለቅስ? እግሮቿን ስሜ ይቅር እንድትለኝ ልለማመጥ! አዎ! ልቤ እንደጨርቅ እየተቀደደ ስለነበረ እንባዬን እየዘራሁ ይቅርታዬን ለመግፀን ፈለግኩ። ያንን ቅፅበት መቼም ጊዜ ቢሆን ሳስታውሰው በቸልታ ላልፈው አልችልም። ግን ለምን? ማሰቤ አልቀረም። ዛሬ እግሮቿን በመሣሜ ነገ የበለጠ አልጠላትምን? ደስተኛ ላደርጋት እችላለሁ? ምን ዓይነት እዚህ ግባ የማልባል ፍጡር መሆኔን ዛሬ ለመቶኛ ጊዜ አልተረዳሁምን? አሰቃይቼ ለሞት አልዳርጋትም ነበርን?

በበረዶው መሃል ቆሜ ደብዛዛው አድማስ ላይ አትኩሬ ይህንን አሰብኩ።

እቤቴ ስመለስ ሀሣቤን ገትቼና የልቤን ሕመም ተቆጣጥሬ ያወረድኩባትን ስድብና ውርደት እስከ መጨረሻው መሸከም የኋላ ኋላ የሚጠቅማት አይደለምን? ስድብ እራስን የማፀጃ መንገድ አይደለምን? ውርደት አስገዳጅና በሕመም የተሞላ የግንዛቤ ነው። ነገ ሕይወቷን ጭታ እቀባው ነበር። ሀሣቤን ሙሉ በሙሉ በእሷ ላይ ጥዬ በመመካት ልሷን አዳክመው ነበር። አሁን ግን ውርደት ከልሷ አይጠፋም። ፊት ለፊቷ የሚጠብቃት ቆሻሻ ሕይወት ምንም ያህል ከባድ ቢሆንም የዚህ ውርደት ትውስታ በጥላቻ ምናልባትም በይቅር ባይነት ዳግም ትንሣኤ ሰጥቶ ያፀዳታለ።

እዚህ ቁጭ ብዬ እራሴን በሥራ ፈት ጥያቄዬ እየሞገትኩት ነው። የቱ ነው የሚሻለው አርካሽ ደስታ ወይስ የክብር ሥቃይ! ደህና የቱ ይሻላል?

እና ይኸውላችሁ ያንን ምሽት ቁጭ ብዬ የልቤ ውጋት ቀስፎ እንደያዘኝ የቁም ሕልሜን ቀጠልኩ። በሕይወቴ እንዲህ ተሰቃይቼና ተፀፅቼ አላውቅም። ግን! ከፎቁ ወጥቼ እሷን ተከትዬ ስሮጥ ግማሽ መንገድ ላይ

እንደምመለስ አስቀድሜ አላውቅምን? ሊዛን ከዛ በኋላ አግኝቼያትም ሆነ ስለሷ ሰምቼ አላውቅም። ምንም እንኳ ከባዶ ተስፋ መቁረጥ ስሜት የመታመም ያህል ብደርስም «የውርደትና የጥላቻ» ጠቃሚነት በሚለው ሐረጌ ለብዙ ጊዜ ተደስትኩበት።

አሁን 'ንኳ ስንትና ስንት ዓመታት በኋላ ላስታውሰው መከፋት ይሰማኛል። አሁን ላስታውሣቸው ብዙ ነገሮች ደስታ ቢስ ያደርጉኛል። ግን ለምን ይሄን ግለታወሻዬን እዚህ ላይ አላቆምም? መጀመሪያውኑ ይህን ለመፃፍ መሞከሬ ስህተት መሆኑን አስባለሁ። ይህን ታሪክ በፃፍኩበት ጊዜ ሁሉ ሃፍረት አልለቀቀኝም ነበር። ስለዚህ ይሄ የሥነ ፅሁፍ ውጤት ሣይሆን ራስን ማረሚያ ቅጣት ነው። ለምሳሌ በጉሬዬ ውስጥ በደረሰብኝ የሞራል መፈረካከስ ግህበራዊነት በሌላቸው ልምዶቼ ከውነተኛ ሕይወት ጋር ግንኙነት በማጣት ጉድጓዴ ውስጥ ሆኜ ጥላቻዬን በማስታመሜ የተነሣ ሕይወቴ ስለመበላሸቱና ስለመላለለው ረጅም ታሪክ መፃፉ አስደሳች አይመስለኝም። አንድ ረጅም ልብወለድ አንድ የታሪኩ ጀግና ሊኖረው ይገባል። እኔ ግን ሆን ብዬ የፀረ–ጀግና ባህሪያትን ያሰባሰብኩ ይመስለኛል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ይሄ ሁሉ በሁላችንም ላይ አስከሬ ስሜት እንደሚያሳድርብን እርግጥ ነው። ምክንያቱም ሁላችንም ከውነተኛ ሕይወት ጋር ግንኙነት የለንምና። ከሞላ ጐደል እያንዳንዳችን ሁላችንም ሸመድማዶች ነን። ከውነተኛ ሕይወት ጋር ከመቆራረጣችን የተነሣ አልፎ አልፎ «እውነተኛ ሕይወትን» ለመጥላት እንገደዳለን። ለዚህም ነው ሰዎች እውነተኛ ሕይወትን ሲያስታውሱን በጣም የምንናደደው። ልክ ነው! ሁላችንም «እውነተኛ ሕይወትን» እንደሸከም አስከመቁጠር ደርሰናል። «ሕይወት» መፀሐፍ ውስጥ እንደምናነበው ዓይነት ቢሆን እንደሚሻል ሁላችንም ተስማምተናል ለምንድነው ታዲያ አንዳንድ ጊዜ አላስፈላጊ ሁከት የምንፈጥረው? ለምንድነው ራሣችንን የምናሞኘው ምንድነው የምንፈልገው? ራሣችንን አናውቅም በእርግጥ ነው የምላችሁ እግዚአብሔር ትርጉም የለሽ ፀሎቶቻችንን ቢያሰምርልን ኖሮ ካሁኑ የባሰ ሁኔታ ውስጥ አንወድቅ ነበር። እንበል ለምሳሌ ይበልጥ ነፃ ሆነን እጆቻችን ተፈቱ።

የእንቅስቃሴ አድማሳችን ሰፋ፣ ቁጥጥሩም ላላ። እመኑኝ እውነቱን ነው የምላችሁ፣ ወዲያውኑ ቁጥጥሩ መልሶ እንዲጫንበን በእንብርክክ መለመን እንጀምራለን። ይህን ስላልኩ እንደምትናደዱብኝ አውቃለሁ። በቁጣ እየጮኋችሁና መሬቱን እየተመተማችሁ አዛው ስለራስህ የጨለማ ጎራ፣ በሰቃይ ሕይወት ብቻ ተናገር። «ሁላችንም!» እያልክ ደፍረህ አፍህን እንዳትከፍት ትሳላችሁ። ያንተ ያለህ! ወንድሞቼ! ብታምኑም ባታምኑም በዚህ «ሁላችንም» አባባል አራሴን ትክክለኛ አድርጌ ለማቅረብ ፈፅሞ አየሞከርኩ አይደለም። በኔ በኩል የማውቀው እናንተ ግማሽ መንገድ ያህል ፣ንኳ ልትደፍሩ የማትችሉትን እኔ እስከመጨረሻው ጥግ መሄዴን ነው። እናንተ ፍርሃታችሁን እንደ አርቆ ማስተዋል አድርጋችሁ በስህተት አምናችሁበታል። ስህተታችሁም ተመችቶዋችሁ ራሳችሁን ታታልላላችሁ። እውነቱን እንነጋገር ከተባለማ እኔ ከናንተ ይበልጥ የእውነት ኖሬያለሁ። ብትፈልጉ ጠጋ ብላችሁ መርምሩኝ። ግልፁን እንነጋገር! በመጀመሪያ ደረጃ እውነተኛ ሕይወትን የት እንደምናገኝ ወይም ምን እንደሆነ ወይም እንደሚባል እንኳ አናውቅም። እስኪ ያለመፅሐፍትና ያለፊልም ብቻችንን ተተውን እንበል፣ ሁላችንም በአንድ ጊዜ ግራ በመጋባት በጨለማ እንዋጣለን።

የምንይዘው የምንጨብጠውን ምን እንደምናፈቅር ምን እንደምንጠላ ምን እንደምናከብርና ምን እንደምንንቅ ጨርሶ አናውቅም። እንዳውም ሰው መሆን ፣ንኳ ያስቸግረናል። ከእውነተኛ ሥጋና ደም የተሠራ የራሳችን ሥጋ መሆን ፣ንኳ ያስቸግረናል። ያሳፍረናል። ቅሌት ይመስለናል። የሆነ ፅንሰ ሃሳባዊ፣ የሆነ የቴዎሪ «አማካኝ» ሰው ለመሆን የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን። ሁላችንም ሞተን የተወለድን ነን። ለረጅም ጊዜ ስንፀንስ የቆየነው በሕይወት ባሉ አባቶች አልነበረም። እያደር የምናሳየው ሁኔታም ይህንን ነው የሚያረጋግጠው። እየጣመን ነው። ብዙ ሳይርቅ በዚህም ሆነ በዚያ መንገድ ከአጥንትና ከሥጋ በተሠራ አባት ሳይሆን ከፅንሰ ሃሳብ

የምንወለድበትን ሁኔታ አንፈጥራለን። ግን ይብቃኝ! «ከጨለማ ጐራዬ» ውስጥ መፃፍ አልፈልግም።

(በነገራችን ላይ ይሄ የዚህ የእንቆቅልሽ ግለሰብ ማስታወሻ መጨረሻ አይደለም። እሱ ስሜቱን ሊገታ ባለመቻሉ ቀጥሎበታል። ለኛ ግን እዚህ ላይ ብናበቃ ይሻላል።)

ስለመጽሐፉ ያሉትን አስተያየት በሚከተለው አድራሻ ቢልኩልኝ ከልብ አመሰግናለሁ
የፖ. ሳ.ቁጥር 1732 ወይም 2153 ኮድ 1110 አ.አ ነው።